fetena.net : Ethiopian online exams and books





አማርኛ

እንደአፍ መፍቻ ቋንቋ

የተማሪ መጽሐፍ

(ፊ) 5ኛ ክፍል

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ
በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ለከተማ ዐውድ ተስማምቶ የቀረበ

አስማምቶ አዘጋጆች

ሞላ መኮንን አበራ

ይርጋለም ኃይሉ ወልዴ

ጥራት ተቆጣጣሪ

ፍሬህይወት አሠፋ ከበደ



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የትምህርት ሚኒስቴር

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው ከአሜሪካ ህዝብ በአሜሪካ ዓለማዓቀፍ የልማት ድርጅት (United States Agency for International Development (USAID)) በኩል በተገኘው የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ፣ በትምህርት ሚኒስቴር፣ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮና በREAD - TA ፕሮጀክት ትብብር ሲሆን የማስማማቱ ስራ የተከናወነው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ሆኖ የህትመቱ ወጪ በሁለተኛው የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፕሮግራም (General Education Quality Improvement Program (GEQIP) II) ተሸፍኗል።

የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2007 ዓ.ም. የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ናቸው።

ISBN: 978-99944-2-541-9

የይዘት ማውጫ

መግቢያ (ለወላጆች ማስታወሻ) iv

ምዕራፍ 1

ጓደኝነት 1

ምዕራፍ 2

አካባቢያችን 21

ምዕራፍ 3

ልማዶች 41

ምዕራፍ 4

የትራፊክ ደህንነት 61

ምዕራፍ 5

ጽዳትና ንፅህና 81

ምዕራፍ 6

ምግብ 104

ምዕራፍ 7

የዱር እንስሳት በኢትዮጵያ 128

ምዕራፍ 8

ባህላዊ ጨዋታዎች 154

ምዕራፍ 9

ሥነቃል 180

ምዕራፍ 10

ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ፤ መድሎና መገለል፣ 202

ሙዳየቃላት 226

ዋቢዎች 230

መግቢያ (ለወላጆች ማስታወሻ)

ይህ መጽሐፍ ከ5ኛ እስከ8ኛ ክፍል ድረስ በአፍ መፍቻ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋዉ በብቃት ማንበብ፣ መጻፍ፣ ማዳመጥና መናገር እንዲችሉ ለማድረግ ተሻሽሎ የተዘጋጀው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሥርዓተትምህርት አካል ነው። የመጽሐፍ ዝግጅቱም፣ ተማሪዎች እንዴት ማንበብና መጻፍ እንደሚችሉ፣ መማር ፈጠራዊና አስደሳች እንዴት እንደሚሆን፣ የትምህርትቤት ውስጥ ተግባራት እንዴት መማርን እንደሚያግዙና እንደሚያጐለብቱ በተደረጉ ጥናቶች ላይ የተመሠረተ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም መጽሐፉ ስለነዚህ የክፍል ደረጃዎች ሥርዓተትምህርትና ስለሚሰጡ ትምህርቶች ሽፋን መረጃ ይሰጣል። በመሆኑም ተማሪዎችና ወላጆች በትምህርትቤት የተከናወኑ ተግባራትን ለማስቀጠልና ይበልጥ ለማዳበር በጋራ ለመሥራት ያስችላቸዋል።

የሥርዓተትምህርቱ መሠረታዊ መርሖች፤

1. ተማሪዎች በማኅበረሰብ ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰጉዳዮች ይማራሉ (እያንዳንዱ ምዕራፍ አንድ የምንባብ ይዘትና የተለያዩ ርዕሰጉዳዮችን ይሸፍናል።)
2. ተማሪዎች ስለነዚህ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰጉዳዮች የተጻፉ ምንባቦችን ካነበቡና ካዳመጡ በኋላ፣ በእነሱ ላይ በመመሥረት ይናገራሉ፤ ይጽፋሉም።
3. ሁሉም የቋንቋ ትምህርት ከእነዚህ የምንባብ ይዘቶች፣ ርዕሰጉዳዮችና ምንባቦች ጋር የተያያዘ ነው።
4. ተማሪዎች በርካታ የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመጻፍ ተግባራት እንዲያከናውኑ ይጠበቅባቸዋል። ስለሆነም ተግባራቱን በቀላሉ በተገቢ ሁኔታ ለማከናወንና ራሳቸውንም በትክክል ለመግለጽ አይቸገሩም።
5. ተማሪዎች በግላቸው ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው ከሚማሩ ቢጤዎቻቸውና በቡድን አብረዋቸው ከሚሠሩ ተማሪዎች ይማራሉ።
6. ተማሪዎች በምዕራፎቹ ይዘቶችና በርዕሰጉዳዮች ላይ ተመሥርተው የቀረቡ ጽሑፎችን በሚያዳምጡበት፣ በሚያነቡበትና አዳዲስ ቃላትን በሚተዋወቁበት ጊዜ የቃላቱን ፍቺዎች ይማራሉ፤ ይረዳሉ፤ ይጠቀሙባቸዋልም። እነዚህን አዳዲስ ቃላት በሚጠቀሙበት ጊዜም የበለጠ ይረዷቸዋል፤ የቋንቋ ችሎታቸውንም የበለጠ ያበለጽጋሉ።

በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር በጋራ መማር

ተማሪዎች በትምህርትቤት የሚቀስሟቸውና በቤታቸው ከወላጆቻቸው ጋር የሚሠሯቸው በርካታ ትምህርታዊ ተግባራት አሉ። ስለዚህ ወላጆች ከእነዚህ በርካታ ተግባራት ቢያንስ የተወሰኑትን ከልጆቻቸው ጋር በጋራ እንዲሠሩ ይጠበቃል።

1. ወላጆች የሳምንቱን ወይም የዕለቱን የምንባብ ይዘት ወይም ርዕሰጉዳይ ልጆቻችሁን በመጠየቅ ተረዱ።
2. በትምህርትቤት ያነበቧቸውን ምንባቦች በጋራ አንብቡ። ይህንንም ልጆች ወይም ወላጆች ለብቻ ወይም በየተራ በማንበብ ሊተገብሩት ይችላሉ።
3. ልጆቻችሁን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለምንባቡ ተወያዩ፤
   - ምንባቡ ምን ዓይነት የምንባብ ይዘት ይሸፍናል?
   - በምን ዓይነት ርዕሰጉዳይ ላይ ያተኩራል?
   - ከዚህ የምንማረው ምንድን ነው?
   - ስለርዕሰጉዳዩ በተጨማሪ ምን እናውቃለን? ስለርዕሰጉዳዩ በዜና ወይም ሌሎች ሰዎች ሲናገሩ የሰማነው ምንድን ነው? ስለርዕሰጉዳዩ በሌላ ቦታ ምን አንብበናል?
   - ስለርዕሰጉዳዩ ወይም ርዕሰጉዳዩ በምንባቡ ውስጥ በቀረበበት መንገድ ላይ በግል ያለን አስተያየት ምንድን ነው?
   - በምንባቡ ውስጥ ከተጠቀሰው ሌላ ስለርዕሰጉዳዩ ምን ማወቅ እንፈልጋለን?
   - ስለርዕሰጉዳዩ በተለየ ሁኔታ ምን ለመሥራት እንፈልጋለን?
4. በምንባቡ ውስጥ ስላጋጠሟችሁ ቃላት የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በመጠየቅ ተወያዩ፤
   - የዚህ ቃል ፍቺ ምንድን ነው?
   - ቃሉስ ምንባቡን ለመረዳት ረድቶኛል?
   - በተለያዩ መንገዶች በጥቅም ላይ ውሏል?
   - እንዴትስ በሕይወቴ ውስጥ ልጠቀምበት እችላለሁ?
5. ስለርዕሰጉዳዩ የሚያወሱ ሌሎች ጽሁፎችን ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች ወይም ከመጽሔቶች ፈልጋችሁ አንብቡ።
6. በግል ያንብቡ (ልጆች ራሳቸውን ችለው በግላቸው እንዲያነቡ አበረታቱ)፤ ከዚያም ስላነበቡት ጉዳይ ተወያዩ።
7. ከቴሌቪዥን፣ ከሬዲዮ ወይም ከድረገጽ ስለርዕሰጉዳዩ አዳምጡ ወይም ተመልከቱ።

8. ልጆች በክፍል ውስጥ ምን ምን እንደተማሩ ደብተራቸውን በጋራ ተመልከቱ፣ ስለምን እንደተማሩና ምን እንደተሰማቸው የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች በማንሳት ተወያዩ።
   - ትምህርቱ ከባድ ነው/ነበር?
   - ትምህርቱ ቀላል ነው/ነበር?
   - የቋንቋ ትምህርቱ ጠቃሚ ነው/ነበር?
   - ልጆቹ ቀጥሎ ምን መማር ይፈልጋሉ?
9. የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የተማሯቸውን ዝርዝር ክሂሎች በመረዳት ምን እንደተማሩ ለማወቅ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ልጆቹን ጠይቋቸው፣ ለምሳሌ፣ የቃላቱ ፊደላት በተገቢ ሁኔታ ተጽፈዋል/ተሰድረዋልወይ? በዓረፍተነገሮች ውስጥና/ወይም መካከል ያሉት ሥርዓተነጥቦች (አራት ነጥብ፣ ነጠላ ሰረዝ፣ ድርብ ሰረዝና የመሳሰሉት) በተገቢ ቦታቸው ገብተዋልወይ? ወዘተ.
10. ልጆች የተሰጣቸውን የቤትሥራ ሲሠሩ፣ ራስን ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላትን በቃለመጠይቅ፣ ንግግርን በመጻፍ ወይም በንግግር ልምምድ ወቅት በመሳተፍ አብሮ መሥራት ተገቢ ነው።
11. ልጆች አጫጭር ደብዳቤዎች (ለምሳሌ፣ ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞች) እንዲጽፉ ወይም በዕለቱ ወይም በሳምንቱ ስለተከሰቱ ጉዳዮች ወይም ስለአንድ ጉዳይ ያላቸውን አስተያየት ወዘተ እንዲጽፉ አበረታቷቸው።

የመጽሐፍ ይዘቶች አደረጃጀት

ትምህርቶች

በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች በምዕራፍ ተደራጅተው ቀርበዋል። እያንዳንዱ ምዕራፍ የራሱ የምንባብ ይዘት፣ እያንዳንዱም የምንባብ ይዘት ሦስት ርዕሰጉዳዮችና አራት አራት ምንባቦች አሉት። የምንባብ ይዘቶቹና ርዕሰጉዳዮቹ ተማሪዎች በቋንቋቸው እንዲናገሩ፣ እንዲያዳምጡ፣ እንዲያነቡና እንዲጽፉ እንደመነሻ ያገለግሏቸዋል።

ተማሪዎች በእያንዳንዱ ምዕራፍ የሚያዳብሯቸው ክሂሎች ከላይ የተጠቀሱት ናቸው። ወላጆች ምናልባት ስለነዚህ ክሂሎች ጥያቄዎች ካሏችሁ ልጆቻችሁን ወይም መምህሮቻቸውን ጠይቃችሁ ማብራሪያ ማግኘት ትችላላችሁ። በተጨማሪም ልጆቻችሁን እንዴት መርዳት እንደምትችሉ ከመምህራን ጋር ተወያዩ።

የቃላት ጥናት

ተማሪዎች አዳዲስ ቃላትን፣ የቃላቱን የተለያዩ የመዋቅር አካላት፣ የተለያዩ አጠቃቀሞች የሚያሳዩትን የቅርጽ ለውጦች ይማራሉ።

አንብቦ መረዳት

ተማሪዎች የሚያነቡትን ጽሑፍ እንዴት ትኩረት ሰጥተው እንደሚያነቡና እንደሚረዱ ይማራሉ። ከዚህም በተጨማሪ ባነበቡት ጽሑፍ ላይ ተመሥርተው በሚዘጋጁ የመናገርና የመጻፍ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ። እነዚህም ተግባራት የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- ምንባቡ ስለተመሠረተበት ይዘትና ርዕሰጉዳይ መነጋገር፣
- ከማንበብ በፊት መገመት፣
- አስፈላጊ ቃላትን መማርና ስለእነሱ መነጋገር፣
- የቅድመንባብ፣ የማንበብ ሂደትና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ፣
- ከሌሎች ጋር በምንባቡ ላይ በክፍል ውስጥ መወያየት፣
- ስለምንባቡ፣ ስለርዕሰጉዳዩና ስለምንባቡ ይዘት መጻፍ፣
- ስለምንባቡ እንዲናገሩ፣ የግል ሀሳባቸውንም እንዲያቀርቡ ማድረግ፣
- በምንባቦቹ ይዘቶች ወይም በርዕሰጉዳዮቹ ላይ ያተኮሩና በክፍል ውስጥ ሊከወኑ የሚችሉ ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ የተውኔት ጽሑፎችን ሰጥቶ እንዲከውኑ ማድረግ።

ቃላት

ተማሪዎች በሚያነቧቸውና በሚያዳምጧቸው ምንባቦች ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን አዳዲስ ቃላት ተምረው ይጠቀማሉ። ለምሳሌ፡-

- የቃላትን ንበት፣ ፍቺና የተለያየ አጠቃቀም ይማራሉ፤
- ተመሳሳይ ፍቺ ያላቸውን ሌሎች ቃላት ይማራሉ፤
- በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጪ (ለምሳሌ በቤት ወይም በማኅበረሰብ አካባቢ) በሚፈጸሙ የመናገርና የመጻፍ ተግባራት ላይ ቃላቱን ይጠቀማሉ።

መጻፍ

ተማሪዎች ስለሚያነቧቸው የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰጉዳዮች በግል ወይም በቡድን ይጽፋሉ። የሚጽፏቸውም ጽሑፎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- የተለያዩ የጽሑፍ ዓይነቶችን፣ ለምሳሌ ተራኪ፣ ገላጭና አወዳዳሪ ወይም አነፃፃሪ ጽሑፎችን መጻፍ፣
- ሃሳባቸውን እንዲጽፉ፣ እንዲከልሱ (እንዲያርሙ) እና ለጎትመት ዝግጁ እንዲያደርጉ ማድረግ፣
- የጽሑፍን የተለያዩ ቁምነገሮች፣ ለምሳሌ በቃላት ውስጥ ፊደላትን በአግባቡና በትክክል መጻፍ፣ ቃላትን በትክክል ማንበብ፣ አጥረው የተጻፉ ቃላትን ወዘተ መረዳት።

አቀላጥፎ ማንበብ

ተማሪዎች ጽሑፎችን ለደረጃቸው ተገቢ በሆነ ፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢ አገላለጽ ማለትም የምንባቡን መልዕክት በሚገልጽ ስሜት ደረጃ ድምፅ በማሰማት ያነባሉ።


ቃላዊ ክሂሎች፣ ማዳመጥና መናገር

ተማሪዎች በሚያነቡትና በሚያዳምጡት ጽሑፍ ላይ ትኩረት ማድረግንና መረዳትን ይማራሉ። በተጨማሪም በሚያዳምጡትም ሆነ በሚያነቡት ጽሑፍ ላይ በተመሠረቱ ተግባራት ላይ ይሳተፋሉ። የሚሠሯቸውም ተግባራት የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤

- የማዳመጡ ምንባብ ስለተመሠረተበት ይዘትና ርዕሰጉዳይ መነጋገር፣
- ከማዳመጥ በፊት መገመት፣
- ቁልፍ ቃላትን መማርና ስለእነሱ መነጋገር፣
- የቅድመማዳመጥ፣ የማዳመጥ ሂደትና የአዳምጠ መረዳት ጥያቄዎችን መጠየቅና መመለስ፣
- ከሌሎች ጋር በማዳመጥ ምንባቡ ላይ በክፍል ውስጥ መወያየት፣
- ስለማዳመጥ ምንባቡ፣ ስለርዕሰጉዳዩና ስለማዳመጥ ምንባቡ ይዘት መጻፍ፣
- ስላዳመጡት ምንባብ መናገር፣ የግል ሀሳብን ማቅረብ፣
- በማዳመጥ ምንባቦቹ ይዘቶች ወይም በርዕሰጉዳዮች ላይ ያተኮሩና በክፍል ውስጥ ሊከወኑ የሚችሉ ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ ተውኔቶችን መከወን።

ሰዋስው

ተማሪዎች የቋንቋውን የተወሰኑ መዋቅራዊ ክፍሎች ለምሳሌ፣ ነጠላና ብዙ ቁጥር ስሞችን፣ የአሁንና የኃላፊ ጊዜ ግሶችን፣ ቅጽሎችን፣ ተውሳከግሶችን፣ ነጠላና ድብልቅ ዓረፍተነገሮችንና አጠቃቀማቸውን ይማራሉ።



ጓደኝነት

ምዕራፍ 1

ሠላምታ

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ማስታወሻ

መነጠልና ማጣመር

መነጠል፡- ውስብስብ ቃላትና ሐረጋትን በመነጣጠል የምናነብበት ዘዴ ነው።

ማጣመር፡- ተነጣጥለው የቀረቡ ልዩ ልዩ የቃላትና የሐረጋት ክፍሎችን በማጣመር ማንበብ ነው።

የመነጠልም ሆነ የማጣመር ዓላማ ለማንበብ አስቸጋሪ የሆኑ ውስብስብ ቃላትና ሐረጋትን በትክክል የምናነብበት ስልት ነው።

ተግባር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	መተላለፍ-ኢ,ያ	መተላለፊ,ያ
ለ	በ-መሰንበት-ኣቸው	በመሰንበታቸው
ሐ	በ-ሃይማኖት-ኣዊ	በሃይማኖታዊ
መ	ለ-ባለ-ሥልጣን-ኣት	ለባለሥልጣናት
ሠ	በ-መቀጠል-ም	በመቀጠልም

ማንበብ

ቅድመንባብ

መገመት

ተግባር

የምንባቡን ርዕስና ሥዕሉን ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለምን እንደሚገልፅ ገምቱ።

የማንበብ ሂደት

የሚከተለውን በትረካ የቀረበ ምንባብ ግምታችሁን እያረጋገጣችሁ ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ።

ሐዋና ጓደኞቿ



ሐዋ ቀጭን፣ ረጅም፣ ጠይም ልጅ ናት። ንጽህናዋን በሚገባ ትጠብቃለች። በትምህርቷ ከክፍሉ ተማሪዎች የላቀች ናት። ይህም በክፍል ውስጥ የቡድን መሪ ለመሆን አስችሏታል። ከሌሎች ጋር የመግባባት ችሎታዋም በጓደኞቿና በአስተማሪዎቿ ዘንድ የተወደደች አድርጓታል።

ሐዋ፣ አያልነህና ጀማል የተሰጣቸውን የቤትሥራ ለመሥራት በያዙት ቀጠሮ መሠረት በቦታው ተገኝተዋል። በሰዓቱና በቦታው ያልተገኘችው ሳምራዊት ብቻ ነበረች። በሁኔታው ግራ ተጋብተው ለተወሰኑ ደቂቃዎች እየጠበቋት ሳለ በርቀት ስትመጣ አዩዋት። ሦስቱም እየሮጡ ሄደው በደስታ ተቀበሏትና ለምን እንደዘገየች ጠየቋት። ሳምራዊትም «ነጭ በትሬ ጠፍቶብኝ ስፈልግ ነው» አለቻቸው። አራቱም የክፍል ጓደኛሞች እየተጫወቱ እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደትምህርትቤቱ ግቢ ገቡ። ከዚያም ጀማል አንድ የመማሪያ ክፍል ፈልጎ ቦታ ካመቻቸ በኋላ ገቡና ውይይታቸውን ቀጠሉ።

በመጀመሪያ ሐዋ ለውይይታቸው መነሻ ይሆን ዘንድ «ሠላምታ ሰዎች ለአጭር ጊዜ ወይም ለረጅም ጊዜ ተለያይተው ሲገናኙ ናፍቆታቸውን ይገልጹበታል፤ ደህንነታቸውንና መተሳሰባቸውን ይጠያየቁበታል» ስትል፣ ሳምራዊት ቀጠል አድርጋ «ሠላምታ በንክኪ ወይም በምልክት አማካይነትም ይገለጻል» አለች። ሐዋም «ጥያቄው 'በአካባቢያችሁ የተለመዱ የሠላምታ ልውውጥ ሥርዓቶችን ዘርዝሩ' የሚል ስለሆነ እያንዳንዳችን የምናውቀውን መልስ መስጠት እንችላለን» በማለት ውይይቱ እንዲቀጥል የቡድን አባላቱን ጋበዘች።

ቀድሞ መልስ ለመስጠት የተፈቀደለት በደንብ የተዘጋጀው አያልነህ ነው፤ እንዲህም አለ፤ «ሰዎች ዉት ሲገናኙ እንዴት አደራችሁ? ረፈድ ሲል እንዴት አረፈዳችሁ? ከምሳ በኋላ እንዴት ዋላችሁ? ጀንበር ከጠለቀች በኋላ እንዴት አመሻችሁ?» ይላሉ። መላሾችም፤ «ደህና! እግዚአብሔር ይመስገን! አልሃምዱሊላህ! እናንተስ እንደምን አደራችሁ? አረፈዳችሁ? ዋላችሁ? አመሻችሁ? ይላሉ» ሲል መልስ ሰጠ።

ቀጥሎ መልስ የሰጠው ጀማል ነው። «እኛ ቀንም ሆነ ማታ ስንገናኝ አሰላም አለይኩም ስንል ምላሹ ወአለይኩም ሰላም! ይሆናል። ሌላው ደግሞ ወንድና ወንድ፣ ወይም ሴትና ሴት በሚገናኙበት ጊዜ አንዱ የሌላውን ወይም አንዷ የሌላዋን የእጅ መዳፍ የውጭ ክፍል በመሳም ሠላምታ ይለዋወጣሉ» አለ። ሐዋም «ትክክል ነው» አለች።

ሳምራዊት «እኔም የምጨምረው ሀሳብ አለኝ» ካለች በኋላ «አዎ! በዐውዳመት ጊዜ ብዙ ሰዎች 'እንኳን አደረሳችሁ' ሲባባሉ፣ 'እንኳን አብሮ አደረሰን' ሲሉ ሰምቻለሁ» አለች። ከቡድኑ አባላት ሌላ ተጨማሪ ሀሳብ ስላልቀረበ ሐዋ የቀረቡትን አስተያየቶች አጠቃለለች። መልሱንም አያልነህ አጠናቅሮ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርበው ተስማምተው ተለያዩ።

(ባየ ይማም። 1997። የግንኙነት፣ የጥያቄና የማፅናኛ መግለጫዎች ማኅበራዊ ግንኙነትና አጠቃቀም በአራት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች። አዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ ድህረምረቃ ትምህርትቤት መነሻነት የተጻፈ።)

አንብቦ መረዳት

የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በታሪኩ ውስጥ ያሉት ባለታሪኮች ማን ማን ናቸው?

ለ. ሐዋ ለቡድን መሪነት የተመረጠችበት ምክንያት ምን ነበር?

ሐ. የእነሐዋ ቡድን አባላት የተገናኙት ምን ለመሥራት ነበር?

መ. ሳምራዊት ነጭ በትር የያዘችው ለምን ነበር?

ሠ. ሳምራዊት «በቃላት ብቻ አይደለም፣ በንክኪ ወይም በምልክት አማካይነት የሚፈፀሙ የሠላምታ ዓይነቶች አሉ» ብላለች። ይህን የሠላምታ አሠጣጥ ዘዴ በተግባር አሳዩ።

ረ. የቡድኑ ጸሐፊ ማን ናት/ነው?

ተግባር 2

በአካባቢያችሁ በተለያዩ በዓላት ጊዜ ሰዎች መልካም ምኞታቸውን እንዴት እንደሚገልፁ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ በተግባር አሳዩ።

2ኛ ቀን

ቃላት

የቃላትና የሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ

ተግባር

በ«ሀ» ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ ከ«ለ» ረድፍ እየመረጣችሁ በማዛመድ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ።

ሀ	ለ
1. ተመራጭ	ሀ. ማርፈድ
2. ግራመጋባት	ለ. ዓመትበዓል
3. መዘግየት	ሐ. ተፈላጊ
4. የተለመዱ	መ. ከረመ
5. ዐውዳመት	ሠ. የተዘወተሩ
6. ሰነበተ	ረ. መደናገር

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በገላጭ ስልት የቢጋር ሠንጠረዥ ማዘጋጀት

ተግባር

«ሐዋና ጓደኞቿ» ከሚለው ምንባብ አንድ ገፀባህርይ መርጣችሁ፣ የገፀባህርይውን መልክና ቁመና፣ ባህርይውንና የትምህርትቤት ተሳትፎ በቢጋር ሠንጠረዥ ዘርዝሩ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

ተግባር 1

ቀጥሎ ሥርዓተነጥቦች ያልተሟሉለት አንቀጽ ቀርቦላችኋል። ባዶ ቦታዎቹን በተገቢዎቹ ሥርዓተነጥቦች አሟልታችሁ እንደገና ጻፉት።

ሠላምታ በተለያዩ ምክንያቶች ተለያይተው የዋሉ _____ ያደሩ _____ የሰነበቱ ወይም የከረሙ ሰዎች ናፍቆታቸውን _____ ፍቅራቸውን_____መተሳሰባቸውን _____ መልካም ምኞታቸውን ወዘተ. ለመግለፅ የሚጠቀሙበት የቃል ምልልስ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሠላምታ በንክኪ ወይም በምልክት አማካይነትም ሊገለፅ ይችላል _____

ተግባር 2

ነጠላሠረዝና አራትነጥብን በመጠቀም ሦስት ዓረፍነገሮች ጻፉ።

3ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

ሐዋና ጓደኞቿ

ቅድመንባብ

ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች «ሐዋና ጓደኞቿ» የሚለውን ምንባብ በማስታወስ መልሱ።

ሀ. በታሪኩ ውስጥ የቡድኑ ሰብሳቢ ማን ነበረ/ች?

ለ. በምንባቡ ውስጥ የተገለጹት ሠላምታ የሚገለፅባቸው ሦስቱ መንገዶች ምን ምን ናቸው?

ማንበብ

ተግባር

«ሐዋና ጓደኞቿ» የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሠጧችሁ መመሪያ መሠረት በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ በየተራ ድምፅ እያሰማችሁ አንብቡ።

ማዳመጥ

ሠላምታ መቼና እንዴት?

ቅድመማዳመጥ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

በሚከተሉት የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩና በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. ለረጅም ጊዜ ተለያይተው የቆዩ ሰዎች ሠላምታ የሚለዋወጡት እንዴት ነው?

ለ. በሠላምታ ልውውጥ ሂደት ደህንነታቸውን የተጠየቁ ሰዎች የሚሰጡት ምላሽ ምንድን ነው? ለምን ይመስላችኋል?

ሐ. ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ፣ ለረጅም ጊዜ ተለያይተው እንደቆዩ ጓደኞሞች በመሆን፣ ሠላምታ ተለዋወጡ።

የማዳመጥ ሂደት

ማስታወሻ፡-

የሚከተሉትን መመሪያዎች እያዳመጣችሁ ተግብሩ።

- ትኩረታችሁን ሙሉ በሙሉ በሚደመጠው ነገር ላይ አድርጉ፤
- ዋናዋና ነጥቦችን በማስታወሻችሁ መዝግቡ፣
- ስታዳምጡ ዋናውን ሀሳብ ከዝርዝር ሀሳቦች ለመለየት ሞክሩ፤
- የሚደመጠውን ነገር አጠቃላይ መልዕክት ለመረዳት ሞክሩ፤
- የሚደመጠውን ምንባብ አቀራረብ የሚያመላክቱ አያያዥ ቃላትን በትኩረት ተከታተሉ።

ለምሳሌ፡- የሚደመጠው ትረካ ከሆነ **በመጀመሪያ፣ ከዚያም፣ ቀጥሎ** የመሳሰሉት አያያዥ ቃላት የታሪኩን አካሄድ ይጠቁማሉ።

በማስታወሻው ላይ የቀረቡትን መመሪያዎች እየተከተላችሁ መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ በጥሞና አዳምጡ።

አዳምጠ መረዳት

ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የሠላምታ አጠቃቀሞች ከጊዜ አንፃር ምን ምን ተብለው ተዘርዝረዋል?

ለ. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱትን የሠላምታ ዓይነቶች ዘርዝሩ።

ሐ. ተለያይተው ያደሩ ሰዎች ጠዋት ሲገናኙ ምን ይባላሉ?

መ. ከቀኑ 6 ሰዓት ላይ የሚከናወን የሠላምታ ዓይነት ምን ይባላል?

ሠ. የመልካም ምኞት መግለጫ የሚባለው የሠላምታ ዓይነት የሚከናወነው መቼ መቼ ነው?

ረ. ለዓመታት ያህል ተለያይተው የተገናኙ ሰዎች ምን በመባባል ሠላምታ ይለዋወጣሉ?

ሰ. ሠላምታ መለዋወጥ ለምን ይጠቅማል ትላላችሁ?

ሸ. አንድ ሰው ሌላውን/ዋን ሰው በጧት ሲያገኘው ወይም ሲያገኛት እንዴት ዋልክ ወይም እንዴት ዋልሽ የማይለው ለምንድን ነው?

ቀ. የሠላምታ ልውውጥ ባይኖር የሰዎች ግንኙነት ምን የሚሆን ይመስላችኋል?

ሰዋስው

የተጸውዖ ስም

ተግባር 1

ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጁ። የምታውቋቸውን የሰው፣ የወንዝ፣ የሀይቅ፣ የቦታ ወይም የከተማ ስሞችን ባዘጋጃችሁት ሠንጠረዥ ውስጥ ዘርዝሩ። (ለእያንዳንዱ የስም ዓይነት ከ8 ያላነሱ ስሞችን ዘርዝሩ።)

የሰው ስም	የወንዝ ስም	የቦታ/የከተማ ስም	የሀይቅ ስም
ሐዋ	አባይ	አዲስ አበባ	ጣና

ተግባር 2

ቀጥሎ በቀረቡት ምሳሌዎች መሠረት ከዘረዘራችኋቸው ስሞች በስምንቱ ዓረፍተነገር ሥሩባቸው።

ምሳሌ፡- 1. ሐዋ ትጉህ ተማሪ ናት።

2. ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ላይ ታላቁን የህዳሴ ግድብ እየገነባች ነው።

ማንበብ

ቅድመንባብ

መገመት

በሚከተሉት የቅድመንባብ ጥያቄዎች ላይ ከመምህራችሁ ጋር ተወያዩ።

ሀ. «ለጓደኛ አለመታመን» ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. «ለጓደኛ አለመታመን» ከሚለው ርዕስና ሥዕል በመነሳት ምንባቡ ስለምን የሚያወሳ ይመስላችኋል?

የማንበብ ሂደት

«ለጓደኛ አለመታመን» የሚለውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ በግላችሁ አንብቡ።

ለጓደኛ አለመታመን



በድሮ ጊዜ ደረጀና በላይ የሚባሉ ሁለት ጓደኛሞች ነበሩ። ለብዙ ዓመታት በመተማመን ይኖሩ ነበር። አገሬው ሁሉ ጉድ እስኪል ድረስ ርስበርስ በመተሳሰብ መንፈስ ኖረዋል። በዚህም ምክንያት እስከሕይወት ፍፃሜያቸው በመተማመን ይዘልቃሉ ብሎ የማያስብ ሰው አልነበረም።

አንድ ቀን ግን ያልተጠበቀ ነገር ተከሰተ። ሁለቱ ጓደኛሞች ክረምት እንደወጣ ከመኖሪያ አካባቢያቸው ራቅ ወዳለ ቀበሌ ይሄዱ ነበር። ጥቅጥቅ ያለ ደን ውስጥ ሲደርሱ በድንገት አንበሳ አጋጠማቸው። ሁለቱም ከመቅጽበት በፍጥነት መሮጥ ጀመሩ። ደረጀ በአቅራቢያው በሚገኝ ዛፍ ላይ ወጣ። በላይ ግን ዛፍ የመውጣት ልምድ ስላልነበረው ለመውጣት ሲሞክር ተንሸራትቶ ወደቀ። ሮጦ እንደማያመልጥ ሲገነዘብ ሌላ ዘዴ አሰበ። ከዚያም አንድ ሀሳብ ብልጭ አለለት። «አንበሳ የሞተ ሰው አይበላም» ሲባል ይሰማ ነበርና እንደሞተ ሰው ሆኖ በመሬት ላይ ተኛ።

አንበሳውም እያገላበጠ አፍንጫውን፣ አፉን፣ ጆሮውን፣ ሆዱን ያሽተው ጀመር። እሱ ግን ፈጽሞ እንደሞተ ሰው ትንፋሹን ውጦ ዝም አለ። አንበሳውም የሞተ ሰው መስሎት ትቶት ሔደ። ደረጀም ከዛፉ ላይ ሆኖ ቁልቁል ይመለከት ነበር። አንበሳው ትቶት መሔዱን አረጋግጦ ከዛፉ ላይ ወረደ፤ ወደበላይም ቀረበ። ከዚያም፣

«ወንድሜ ሆይ፣ አንበሳው አፉን በጆሮህ ላይ ተክሎ አየሁት፤ በዚህ ጊዜም የበላህ መስሎኝ እጅግ ደንግጬ ነበር» አለው።

በላይም ጓደኛው እምነት የማይጣልበት መሆኑን ተረዳ። ከዚህም የተነሳ የነገሩን አቅጣጫ ለውጦ፣

«አንበሳው በጆሮዬ ምሥጢር ነገረኝ» አለው።

ደረጀም ምስጢሩን ለማወቅ ጓጉቶ፣

«ምን ምሥጢር ነገረህ?» አለው። በላይም «በመከራና በጭንቅ ቀን የሚከድ ሰው ጓደኛ አትሁን አለኝ» አለው።

ደረጀ ያደረገውን ያውቃልና ሰምቶ ዝም አለ። መልስ አይስጥ እንጂ ነገሩ ከንክኖታል። ይህ ነገር በእኔ ላይ ደርሶ ቢሆንስ ሲል አሰበ፤ ሰቀጠጠው። ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ ደግፎ አቀረቀረ። «አያድርስ ነው!» ብሎ ዓይኖቹን ጨፈነ። የዚህ ዓይነት አደጋ እንዳያጋጥመው አንጋጦ ለአምላኩ ነገረ።

(ኅሩይ ወልደሥላሴ። 2000። *ወዳጀ ልቤና ሌሎችም(በድጋሚ የታተመ)*። ከገጽ 14-15 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የቀረበ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሁለቱ ጓደኛሞች ራቅ ወዳለ ቀበሌ ሲሄዱ ምን አጋጠማቸው?

ለ. ሁለቱ ጓደኛሞች ያልተጠበቀ ክስተት ሲያጋጥማቸው ምን አደረጉ?

ሐ. በላይ ዛፉ ላይ መውጣት ያልቻለው ለምን ነበር?

መ. ከሁለቱ ጓደኛሞች አንዱ የሞተ ሰው የመሰለው ለምንድን ነው?

ሠ. አንበሳው ለበላይ ምሥጢር ነግሮታል ወይ?

ረ. በሶስተኛው አንቀጽ፣ በሁለተኛው ዓረፍተነገር «እሱ» የተባለው ማን ነው?

ሰ. ሁለቱ ጓደኛሞች የተጓዙት በየትኛው ወር ነበር?

ሸ. ከሁለቱ ጓደኛሞች እምነት የማይጣልበት የትኛው ነው? ለምን?

ቀ. ከሁለቱ ጓደኛሞች ታሪክ ምን ተማራችሁ?

በ. ሁለት ጓደኛሞች ዕድሜያቸውን በሙሉ ታማኝ ጓደኛ ሊሆኑ የሚችሉ ይመስላችኋል?


ማስታወሻ፡-

- ገፀባህርያት፡- በታሪኩ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ወይም እንስሳት ናቸው።
- መቼት፡- ታሪኩ የተፈፀመበት ጊዜና ቦታ ነው።
- ድርጊት፡- ገፀባህርያቱ የሚፈጽሙት ተግባር ነው።

ተግባር 2

ያነበባችሁትን ታሪክ መሠረት በማድረግ የሚከተለውን ስዕላዊ ቢጋር በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ መልሱን ጻፉ።

የትረካ የቢጋር ሠንጠረዥ



5ኛ ቀን

ቃላት

የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ

ተግባር 1

ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ጻፉ።

ሀ. አካባቢ	ሐ. ሰቀጠጠው	ሠ. ተረዳ
ለ. ጓጉቶ	መ. ጉድ	ረ. አንጋጠ

ተግባር 2

በምንባቡ ውስጥ ለተሠመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ተቃራኒያቸውን ጻፉ።

1. ከመቅፅበት (አንቀጽ 2)
2. ብልጭ (አንቀጽ 2)
3. መካድ (አንቀጽ 3)
4. መከራ (አንቀጽ 3)
5. አቀረቀረ (አንቀጽ 4)

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በገላጭ ስልት አንቀጽ መጻፍ

ተግባር

ባለፈው ሳምንት ያዘጋጃችሁትን የቢጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም በገላጭ ስልት የተዋቀረ አንድ አንቀጽ ጻፉ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

ተግባር

የሚከተለው አንቀጽ ሥርዓተነጥቦቹ የተጓደሉ ናቸው። ስለዚህ አስፈላጊ የሆኑትን ሥርዓተነጥቦች በባዶ ቦታዎቹ በማስገባት አሟልታችሁ እንደገና ጻፉ።

ፍራፍሬና አትክልት በሽታ ተከላካይ ምግቦች ይባላሉ ___ ከፍራፍሬ ዓይነቶች እንደብርቱካን ___ ሎሚ ___ ሙዝ ___ ፓፓየና አናናስ ያሉት በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው ___ ከአትክልት ደግሞ ጎመን ___ ቃሪያ ___ ቆስጣ ___ ሰላጣ የመሳሰሉትን ለአብነት ያህል ማንሳት ይቻላል ___

6ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

ለጓደኛ አለመታመን

ቅድመንባብ

ተግባር

የሚከተለውን ጥያቄ «ለጓደኛ አለመታመን» በሚለው ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ደረጀ በጓደኛው ላይ ክህደት እንዲፈፅም ያስገደደው ምክንያት ምንድን ነው?

ማንበብ

«ለጓደኛ አለመታመን» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተራበተራ አንብቡ።

መናገር

ተግባር

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩ

ሀ. እናንተ ደረጀን ብትሆኑ ኖሮ ምን ታደርጉ ነበር?

ለ. የደረጀና የበላይ ጓደኝነት የሚቀጥል ይመስላችኋል? ለምን?

ሰዋስው

የወል ስም

ተግባር 1

ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጁና የቤትና የዱር እንስሳትን የሚያመለክቱ የወል ስሞች ዘርዝሩ።

የቤት እንስሳ	የዱር እንስሳ
በግ	አንበሳ

ተግባር 2

ከዘረዘራችሁት መካከል 5 በቤት እንስሳት ስሞች፣ 5 በዱር እንስሳት ስሞች፣ በድምሩ 10 ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ።

ምሳሌ፡-

ሀ. <u>አንበሳ</u> አስፈሪ የዱር እንስሳ ነው።

ለ. <u>በግ</u> የቤት እንስሳ ነው።

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ተግባር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	ቁም-ነገር	ቁምነገር
ለ	እንደ-ገፋፋ-ው	እንደገፋፋው
ሐ	ዘመን-ኣዊ-ነት	ዘመናዊነት
መ	እንደ-አስ-ጀመሩ-ት	እንዳስጀመሩት
ሠ	እየ-ተደረገ-ልኝ	እየተደረገልኝ
ረ	ምላሄ-ሀብት-ኣዊ	ምላሄሀብታዊ

ማንበብ

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀት መቀስቀስና መገመት

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ወጣቶች በተለያዩ ሱሶች ውስጥ እንዲጠመዱ የሚያደርጓቸው ምክንያቶች ምን ምን ይመስሏችኋል?

ለ. ሥዕሉን አስተውላችሁ የተረዳችሁትን ተናገሩ።

የማንበብ ሂደት

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ድምጽ ሳታሰሙ በግል አንብቡ።

ሱሰኝነትና መዘዙ



ሲጋራ ማጨስና ጫት መቃም በብዙ ሰዎች ዘንድ ተወዳጅነትን ያተረፉ ተግባራት አይደሉም። ምንም ዓይነት ምጣኔሀብታዊና ማኅበራዊ ጠቀሜታም የላቸውም። ሱሰኞችም ቢሆኑ የሚናገሩት ጎጂነታቸውን ነው። «መቼ ነው ከነዚህ ሱሶች የምንላቀቀው?» በሚል ስሜት ሲማረሩ ይደመጣሉ። ማንኛውም ሱስ ፈታኝና በአንድ ጊዜ ለማቆም አስቸጋሪ በመሆኑ ብዙዎች ከገቡበት በኋላ ለመውጣት ይቸገራሉ። ሲጋራ በማጨስና ጫት በመቃም ሱሶች የተጠመዱ ብዙ ወጣቶችን አውቃለሁ። ከእነሱ መካከል አንዱ ዮሐንስ ነው። ዮሐንስ መልከመልካም፣ ታዛዥና ከሰዎች ጋር የሚግባባ የ25 ዓመት ወጣት ነው። አንድ ባህርይው ብቻ በሰዎች ዘንድ አይወደድም። ቁንጥንጥ ነው። የጀመረውን ሥራ ሳይጨርስ ይጠፋል። ደግሞ ይመለሳል። ምድጃ የመሰለው ከንፈሩ ማንነቱን ይናገራል። ለምን ወጣገባ እንደሚል መጠየቅ አያስፈልግም። ሲመለስ ከአፉ የሚወጣው ጠረን ምን ሲያደርግ እንደቆየ ይናገራል።

ዮሐንስ በጓደኞቹ ግፊት ሱሰኛ እንደሆነ ይናገራል። ዩኒቨርሲቲ በመማር ላይ እያለ ያፈራቸው ጓደኞቹ ገፋፍተው ሲጋራ ማጨስና ጫት መቃም እንዳስጀመሩት

ይገልጻል። በግቢው ውስጥ ብዙ ወጣቶች ሲያጨሱና ሲቅሙ መመልከቱ እንደገፋፋው ይተርካል። በተለይ ደግሞ «ሲጋራ ማጨስ ለዘመናዊነት፣ ጫት መቃም ለጥናት ጥሩ ነው» በሚል የሞኞች ፈሊጥና በአቻ ግፊት ወደሱስ እንደገባ አጫውቶኛል።

ሲጋራ ማጨስና ጫት መቃም ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትሉ መሆናቸውን እንደተረዳም ይገልጻል። «ሲጋራ ማጨስና ጫት መቃም የሥራ ፍቅርንና ታታሪነትን ያሳጣሉ። ሠርተን የምናገኘውን ገንዘብ ለቁምነገር እንዳናውለው ያደርጋሉ። ከሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት እንዳይኖረን ያደርጋሉ። ጤናችንን በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳሉ፣ ለሳንባ ቲቢ፣ ለካንሰር፣ ለደምግፊትና፣ ለመሳሰሉት በሽታዎች ይዳርጋሉ። እኔም ለሳንባ ቲቢ በሽታ ተዳርጌ የሕክምና ዕርዳታ እየተደረገልኝ ነው» ይላል።

«ወጣቶች ከእኔ እንዲማሩ የምፈልገው ነገር አለ። የሚቅሙና የሚያጨሱ ወጣቶች የአልጋ ቁራኛ ከመሆናቸው በፊት ሲጋራ ማጨስና ጫት መቃም ማቆም አለባቸው። ከሱሰቹ ተላቀው ራሳቸውን፣ ወገናቸውንና ሐገራቸውን የሚጠቅሙ አምራች ዜጎች መሆን ይጠበቅባቸዋል» በማለት በአፅንዖት ነግሮኛል።

(ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል። ሐምሌ 15/2014። ድምጽ አልባው ገዳይ መጣሪያ-ትምባሆ። www.waltainformation.com መነሻነት የተጻፈ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ዮሐንስ የጀመረውን ቁምነገር ሳይጨርስ የሚጠፋው ለምንድንነው?

ለ. ዮሐንስ ሲጋራ ማጨስና ጫት መቃም ለመጀመሩ ተጠያቂ ያደረገው እነማንን ነው? ለምን ይመስላችኋል?

ሐ. የዮሐንስ ከንፈር ምድጃ መምሰል የሚያመለክተው ምንን ነው?

መ. ሱሰኞች ከገቡበት ልማድ ለመውጣት የሚፈልጉት ለምንድን ነው?

ሠ. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱት የሱስ ዓይነቶች ምን ምን ናቸው? ምን ጉዳት ያመጣሉ?

ረ. ሱሰኞች ከገቡበት ሱስ ለመውጣት እየፈለጉ መውጣት የማይችሉት ለምን ይመስላችኋል?

ሰ. ለጫትና ለሲጋራ ሱሰኞች ምን ትመክራላችሁ?

ተግባር 2

ካነበባችሁት ታሪክ የወደዳችሁት፣ ያሳዘናችሁ፣ ያናደዳችሁ ወይም ያስደነገጣችሁ ነገር ምንድን ነው? ለምን? በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

8ኛ ቀን

ቃላት

የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ

ተግባር 1

ለተሠመረባቸው ቃላትና ሐረግ ተመሳሳያቸውን ጻፉ።

ሀ. ሱስን መተው <u>ፈታኝ</u> ነው።

ለ. የአቻ <u>ግፊት</u> ለጥሩም ለመጥፎም ባህርይ ይዳርጋል።

ሐ. <u>መልካም</u> ባህርይ በሰዎች ዘንድ ያስመሰግናል።

መ. <u>ታታሪ</u> ልጆች ካሰቡት ደረጃ መድረስ ይችላሉ።

ሠ. <u>የአልጋ ቁራኛ</u> የሆኑ ሰዎች ከፍተኛ ሕክምና ያስፈልጋቸዋል።

ረ. ለትምህርቱ <u>አፅንኦት</u> የሚሰጥ ተማሪ ደስ ይለኛል።

ተግባር 2

በ«ሀ» ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት በ«ለ» ረድፍ ከቀረቡት ተቃራኒያቸውን በመምረጥ አዛምዳችሁ ጻፉ።

ሀ	ለ
1. ተጎጂ	ሀ. ቀልድ
2. ማማረር	ለ. ማመስገን
3. ቁምነገር	ሐ. ጭምት
4. ቁንጥንጥ	መ. ዝቅተኛ
5. ከፍተኛ	ሠ. ተጠቃሚ

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በገላጭ ስልት የቀረበ አንቀጽን አስተካክሎ መጻፍ

ተግባር

ባለፈው ክፍለጊዜ የጻፋችሁትን አንቀጽ ደብተራችሁን በመቀያየር ተራረሙ። ጽሑፋችሁን ለማረም በሠንጠረዡ የቀረቡትን ማመሳከሪያዎች ተጠቀሙ። ከዚያም በተሠጣችሁ እርማት መሠረት አስተካክላችሁ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ።

		አዎ	አይደለም
1	ጽሑፉ በግላጭ አጻጻፍ ስልት የቀረበ ነው?		
2	ጽሑፉ በቢጋር ሠንጠረዥ ውስጥ የተዘረዘሩትን ነጥቦች አካቷል?		
3	ፊደላት ሳይገደፉ በትክክል ተጽፈዋል?		
4	አንቀጹ የሀሳብ አንድነት አለው?		

የአጻጻፍ ሥርዓት

ተግባር

«የትምህርትቤት ጓደኛዬ» በሚል ርዕስ ነጠላ ሠረዝንና አራት ነጥብን በመጠቀም አንድ አንቀጽ ጻፉ።

9ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

ሱሰኝነትና መዘዙ

ቅድመንባብ

ጫት መቃምና ሲጋራ ማጨስ ምን ምን ጥቅምና ጉዳት አላቸው? ከጥቅማቸውና ከጉዳታቸው የትኛው ያመዝናል?

ማንበብ

ተግባር

«ሱሰኝነትና መዘዙ» የሚለውን ምንባብ 2ኛ አንቀጽ ተራበተራ ድምፅ እያሰማችሁ አንብቡ። አንዳችሁ ስታነቡ ሌሎቻችሁ የፊደል ስህተት የተፈፀመባቸው ቃላትን፣ ተቆራርጠው የተነበቡ ቃላትን፣ በተገቢው ቦታ ላይ ከፊል ወይም ሙሉ እረፍት ያልተደረገባቸውን ዓረፍተነገሮች ብዛት በሠንጠረዡ ውስጥ የእዝባር (/) ምልክት እያደረጋችሁ መዝግቡ። ሁላችሁም አንብባችሁ ስትጨርሱ በየቡድናችሁ አንድ የተጠቃለለ ማስታወሻ አዘጋጅታችሁ ለመምህራችሁ አስረክቡ።

ምሳሌ፡-

ሲነበቡ የፊደል ስህተት የተፈፀመባቸው ቃላት ብዛት	ተቆራርጠው የተነበቡ ቃላት ብዛት	በሐረጎችና በነጠላ ሠረዝ ላይ ግማሽ እረፍት፣ አራት ነጥብ ላይ ደግሞ ሙሉ እረፍት ያልተደረገባቸው
///	//	////
3	2	4

መናገር

ውይይት

መምህራችሁ በሚሠጧችሁ መመሪያ መሠረት ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

ሀ. ጫት በመቃም የሚጠፋውን ጊዜ ለሥራ ብንጠቀምበት ምን ጥቅም የምናገኝ ይመስላችኋል?

ለ. ጫት የሚቅሙ ወጣቶች መቃማቸውን ቢያቆሙ ጊዜያቸውን እንዴት ሊያሳልፉ ይችላሉ?

ሰዋስው

የወልና የተጸውዖ ስሞች

ተግባር 1


ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ስሞች የተጸውዖ ወይም የወል ስም መሆናቸውን ለይታችሁ በደብተራችሁ ሠንጠረዥ አዘጋጅታችሁ መድቡ።

ዝሆን	ድሬዳዋ	ድመት	ሙስጠፋ	ዝዋይ
ልጅ	ግመል	ተማሪ	ዶሮ	ፋጡማ
ዋቢሸበሌ	ተስፋዬ	ተክዜ	ፀሐይነሽ	ቤት

የተጸውዖ ስም	የወል ስም
ዋቢሸበሌ	ድሙት

ተግባር 2

«ሱሰኝነትና መዘዙ» ከሚለው ምንባብ ውስጥ የተጸውዖና የወል ስሞችን ለይታችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።



አካባቢያችን

ምዕራፍ 2

ብክለት

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	ያቀጭጭ-ኣቸው-ኣል	ያቀጭጫቸዋል
ለ	ያደርቅ-ኣቸው-ኣል	ያደርቃቸዋል
ሐ	የአካባቢ-ኣችን-ን	የአካባቢያችንን
መ	ሥርዓት-ኣቸው-ን	ሥርዓታቸውን
ሠ	ከ-ፋብሪካ-ዎች	ከፋብሪካዎች

ማንበብ

የአየርና የውኃ ብክለት

ቅድመንባብ

አዳዲስ ቃላትንና ሐረጋትን ማስተዋወቅና መገመት

ተግባር

በሚከተሉት የቅድመንባብ ጥያቄዎች ላይ በመወያየት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. ብክለት፣ ዝቃጭ፣ ሰደድእሳት፣ መርዛማ ንጥረነገሮች፣ የአንጀት ተስቦ የሚሉትን ቃላት ወይም ሐረጋት ፍቺ ተናገሩ።


ለ. ሥዕሉን በጥልቀት ተመልከቱና የተረዳችሁትን ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

የማንበብ ሂደት

ተግባር

ቀጥሎ «የአየርና የውኃ ብክለት» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ የምክንያትና የውጤት ትስስርን በማስተዋል አንብቡ።

የአየርና የውኃ ብክለት



አካባቢ በተለያዩ ነገሮች ሊበከል ይችላል። አካባቢ ከተበከለ ደግሞ በኗሪዎች ላይ ጉዳት ያደርሳል። በተለይ ሕይወት ላላቸው ፍጡሮች እጅግ አስፈላጊ የሆኑት አየርና ውኃ ከተበከሉ ደግሞ የጉዳቱ መጠን ከፍተኛ ይሆናል።

የአየር ብክለት መንስኤዎች ብዙ ናቸው። አንደኛ ትላልቅ ፋብሪካዎችና መኪናዎች በሚፈጥሩት ብናኝ፣ አቧራና ጪስ አየር ይበክላል፤ ሁለተኛ ከጫካ በሚነሳ ሰደድ እሳትና ከመኖሪያ ቤቶች በሚወጣ ጪስ አየር ሊበክል ይችላል፤ ሦስተኛ በእንስሳት ጽዳጅና፤ በሞቱ እንስሳት ብስባሽ በሚፈጠር ጋዝ አየር ይበክላል፤ አራተኛ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከመሬት የሚነሳ አቧራም ለአየር መበከል ምክንያት ይሆናል።

ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የሚፈጠር የአየር ብክለት ሰዎችን፣ እንስሳትን፣ ነፍሳትንና ዕፅዋትን ይጎዳል። አየር ሲበከል የሰዎች የመተንፈሻ አካል ይጎዳል። በዚህም የአተነፋፈስ ሥርዓታቸው ታውኮ ለካንሰር፣ ለአስምና ለሌሎች በሽታዎች

ይጋለጣሉ። አየር ከተበከለ እንስሳትና ነፍሳት ለእልቂት ይዳረጋሉ። ዕፅዋትም ይደርቃሉ።

እንደአየር ብክለት ሁሉ የውኃ ብክለትም ከፋብሪካዎች በቆሻሻ መልክ በሚወገዱ ፈሳሽ መርዛማ ንጥረነገሮችና ዝቃጮች ምክንያት ይፈጠራል። ሰዎች ከመኖሪያ ቤታቸው ጠርገው የሚያወጧቸውን ቆሻሻዎች ሰብስበው በጉድጓድ ውስጥ ከመቅበር ይልቅ በየቦታው በመጣላቸው ምክንያት ውኃ ይበክላል። እንዲሁም ከእንስሳት የሚወገዱ ቆሻሻዎችና የሞቱ እንስሳት ወንዝ ወይም ሀይቅ ውስጥ ሲጣሉ ውኃ ይበክላል።

የውኃ ብክለት ውኃውን በሚጠቀሙ ሰዎች፣ እንስሳትና ዕፅዋት ላይ ብዙ ጉዳት ያደርሳል። ለምሳሌ ሰዎችን ለተቅማጥ፣ ለአንጀት ተስቦና ለሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ይዳርጋል። እንስሳትንም ለልዩ ልዩ በሽታዎች በማጋለጥ ለሞት ያደርሳል። ዕፅዋትንም ያቀጭጫል፤ ያደርቃል።

በአጠቃላይ በጨስ፣ በብናኝ፣ በአቧራ፣ በጋዝ፣ ወዘተ. ምክንያት የአየር ብክለት ይፈጠራል። በፍሳሽና በደረቅ ቆሻሻነት እየተወገዱ ውኃ ውስጥ የሚጨመሩ ነገሮች ውኃን ይበክላሉ። የአየርም ሆነ የውኃ ብክለት በሰዎች፣ በእንስሳት፣ በነፍሳትና በዕፅዋት እድገትና ደህንነት ላይ ጉዳት ያስከትላል። ስለዚህ ብክለትን እንከላከል። «ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ» ይሻላልና።

(ክሪስ ውድፎርድ። 2014። *የውኃ ብክለት*። (ቦታ አልተጠቀሰም) መነሻነት የተጻፈ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱት የብክለት ዓይነቶች ምንና ምን ናቸው?

ለ. የውኃ ብክለት እንዴት ይፈጠራል?

ሐ. የውኃ ብክለት ምን ምን ጉዳቶችን ያደርሳል?

መ. የአየር ብክለት በሰዎች ላይ ምን ጉዳት ያደርሳል?

ሠ. ሰዎች፣ እንስሳትና ዕፅዋት ለብክለት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ? ከሆኑስ እንዴት?

ረ. ሰዎች አየርና ውኃን የሚበክሉ ነገሮችን እንዴት ማስወገድ የሚችሉ ይመስላችኋል?

ተግባር 2

የአየርና የውኃ ብክለት መንስኤዎችንና የሚያደርሱትን ጉዳት አሳጥራችሁ በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

2ኛ ቀን

ቃላት

ለቃላትና ለሐረጋት ፍቺ መስጠት

ተግባር

በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ለተሠመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ፍቺ ስጡ።

ምሳሌ፡-

1. «ጨስ፣ ብናኝና ጋዝ መሰል ነገሮች ከአየር ጋር በሚገናኙበት ጊዜ የአየር ብክለት ይከሰታል።» በዚህ ዓረፍተነገር ብክለት የሚለው ቃል መቆሸሸን፣ ንፁህ አለመሆንን ይገልፃል።
2. «ዝናብ በመዝነቡ ምክንያት መሬቱ ጨቀየ።» በዚህ ዓረፍተነገር ጨቀየ የሚለው ቃል ራሰ፣ ረጠበ፣ ጭቃ ሆነ የሚል ፍቺ አለው።

ሀ. የውኃ ብክለት ቆሻሻዎች ከንፁህ ውኃ ጋር በሚቀላቀሉበት ጊዜ ይከሠታል።

ለ. የውኃ ብክለት እንስሳትን ለልዩ ልዩ በሽታዎች ይዳርጋል።

ሐ. የአየር ብክለት የሰዎችን የመተንፈሻ አካል ይጎዳል።

መ. የአየር ብክለት እንስሳትና ዕፅዋትን ለጉዳት ይዳርጋል።

ሠ. የአየር ብክለት የሰዎችን የአተነፋፈስ ሥርዓት ያውካል።

መጻፍ


ድርሰት መጻፍ

በምክንያትና ውጤት ስልት የቢጋር ሳጥን ማዘጋጀት

ተግባር

የግብርና ምርትን የሚቀንሱ ምክንያቶችና ውጤቶች ግንኙነት በቢጋር ሠንጠረዥ አሳዩ::

ምሳሌ፡-



የአጻጻፍ ሥርዓት

በተወሰነ አካባቢ ብቻ አገልግሎት ያላቸውን ቃላት በብዙ አካባቢዎች አገልግሎት ባላቸው ቃላት ለውጠ መጻፍ

የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሠረት እየለወጣችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡- ባኤላ = ባቄላ

ሀ. ቄጠ	መ. አሻቦ	ሰ. ዴያቦ
ለ. ቡሆ	ሠ. ጠረሾ	ሸ. ኮሞዶሮ
ሐ. ቤሳ	ረ. ዱጨት	ቀ. ወረኾት

3ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

የአየርና የውኃ ብክለት

ቅድመንባብ

ተግባር

የአየርና የውኃ ብክለት በሰዎች ላይ የሚያደርሷቸውን ጉዳቶች ዘርዝሩ።

ማንበብ

ተግባር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት «የአየርና የውኃ ብክለት» ከሚለው ምንባብ፣ የመጀመሪያውን አንቀጽ ተራበተራ ድምጽ በማሰማት አንብቡ።

ማዳመጥ

የውኃ ብክለት

ቅድመማዳመጥ

ተግባር

«የውኃ ብክለት» የሚለውን የማዳመጥ ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።

ሀ. በአካባቢያችሁ ውኃን የሚበክሉ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

ለ. የውኃ መበከል ምን ምን ችግሮችን የሚያስከትል ይመስላችኋል?

የማዳመጥ ሂደት

ተግባር

በምንባቡ የተገለፀውን ምክንያትና ውጤት እየለያችሁ አዳምጡ። መምህራችሁ የሚያቀርቡላችሁን ጥያቄ መልሱ።

አዳምጠ መረዳት

ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት በምክንያት መልሱ።

ሀ. አብዛኛው የውኃ ብክለት ችግር ከራሱ ከውኃ የሚፈጠር ነው።

ለ. ፍሳሽ ቆሻሻ የሰዎችን መኖሪያ አካባቢ በመበከል ለውኃወለድ በሽታዎች ይዳርጋል።

ሐ. ወባ ውኃወለድ በሽታ ነው።

መ. የውኃ ብክለት ችግሮችን ለመቀነስ አንደኛው ዘዴ ተጠቃሚዎችን ማስተማር ነው።

ሠ. የውኃ ብክለትን በሕግ በመደንገግ መከላከል ይቻላል።

ሰዋስው

መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮች

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን ለይታችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

1. አልማዝ ከአምስተኛ ክፍል ተማሪዎች አንደኛ ወጣች።

   <u>አምስተኛ</u> = ደረጃ አመልካች ቁጥር

   <u>አንደኛ</u> = ደረጃ አመልካች ቁጥር

2. አለ. አንድ ወንድም አለው።

   <u>አንድ</u> = መጣኝ ቁጥር

ሀ. እኛ ሦስት በጎች አሉን።

ለ. ኢትዮጵያ ዘጠኝ ክልሎች አሏት።

ሐ. እኔ ትናትና አምስት መጽሐፎች ገዛሁ።

መ. ብዙነሽ ከገበያ አምስት ኪሎ ሽንኩርት ገዛች።

ሠ. መምህራችን በሶስተኛው ክፍል ውስጥ ይገኛል።

ረ. መሐመድ ከክፍሉ ተማሪዎች በቁመት ስድስተኛ ነው።

ሰ. ትምህርትቤታችን በሩጫ ውድድር ሁለተኛ ወጣ።

ሸ. ስመኘው ባለፈው ዓመት ዘጠና ኩንታል በቆሎ አምርቷል።

ቀ. ለጥያቄና መልስ ውድድሩ ሀያ ተማሪዎች ተመርጠዋል።

ማንበብ

የቆሻሻ አፈጣጠርና የሚያስከትላቸው ችግሮች

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር 1

«የቆሻሻ አፈጣጠርና የሚያስከትላቸው ችግሮች» የሚለውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን የቅድመንባብ ተግባራት በትክክል ሥሩ።

ቀጥሎ የቀረበውን የቢጋር ሳጥን በምሳሌው መሠረት በተገቢ የምክንያትና የውጤት ሀሳቦች አሟሉ።

የቆሻሻ መፈጠሪያ ምክንያቶች	ቆሻሻ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች
ሀ. በየቦታው መፀዳዳት	ሀ. የተቅማጥ በሽታ
ለ.	ለ.
ሐ.	ሐ.
መ.	መ.

ተግባር 2

«የቆሻሻ አፈጣጠርና የሚያስከትላቸው ችግሮች» የሚለውን ምንባብና በስሩ የቀረበውን ሥዕል አዛምዳችሁ በማስተዋል ምንባቡ ስለምን እንደተጻፈ ገምቱ።

የማንበብ ሂደት

ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ የምክንያትና ውጤት ግንኙነትን በማጤን ድምጽ ሳታሰሙ አንብቡ።

የቆሻሻ አፈጣጠርና የሚያስከትላቸው ችግሮች



ቆሻሻ በተለያዩ መንገዶች ይፈጠራል። ሰዎች በየዕለቱ ቁርጥራጭ ወረቀቶችን፣ የምግብ ትራፊዎችን፣ የቤት ጥራጊዎችንና የዕቃ እጣቢዎችን በየቦታው እየደፉ ቆሻሻ እንዲፈጠር ያደርጋሉ። ከዚህም በተጨማሪ ሰዎች ከመፀዳጃ ቤት ውጪ በየቦታው በሚፀዳዱበት ጊዜ ቆሻሻ ይከሰታል። በተመሳሳይ ሁኔታ ፋብሪካዎች በሥራ ሂደት የሚፈጥሯቸውን ተረፈ ምርቶች በየቦታው በሚያስወግዱበት ጊዜ ቆሻሻ ይፈጠራል።

ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ምክንያቶች የሚፈጠር ቆሻሻ ቁጥጥር ካልተደረገበትና በአግባቡ ካልተያዘ በሰዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል። በአግባቡ ያልተወገደ ቆሻሻ ለዝንቦች፣ ለአይጦችና ለልዩ ልዩ ነፍሳት መራቢያ ይሆናል። ዝንቦች፣ አይጦችና ልዩ ልዩ ነፍሳት ደግሞ ሰዎች የሚመገቧቸውን ምግቦች ይበክላሉ። ሰዎች የተበከሉ ምግቦችን በመመገባቸው ለተቅማጥ፣ ለኮሌራ፣ ለተስቦ፣ ለሳንባ ምችና ለመሳሰሉት በሽታዎች ይዳረጋሉ።

ቆሻሻ የአካባቢ ብክለትንም ያስከትላል። በየቦታው የተከማቸ ቆሻሻ በቅዝቃዜና በሙቀት ምክንያት ይበሰብሳል። ብስባሹም በጋዝ መልክ ከአየር ጋር እየተቀላቀለ አየርን ይበክላል። የተበከለው አየር ደግሞ የሰዎችንና የእንስሳትን የአተነፋፈስ ሥርዓት በማቃወስ ለበሽታ ይዳርጋቸዋል። ለምሳሌ ሰዎች ለጉንፋን፣ ለአስምና ለካንሰር በሽታ የሚጋለጡት በተበከለ አየር ምክንያት ነው። በሌላ በኩል ወደመሬት የሚሰርግ መርዛማ ብስባሽ በዕፅዋት እድገት ላይ ችግር ይፈጥራል፤ ያቀጭጫቸዋል፤ ያደርቃቸዋል።

በየቦታው በብዛት ተከማችቶ የሚገኝ ቆሻሻ የመኖሪያ አካባቢን ሳቢና ማራኪ እንዳይሆን ያደርጋል። ይህም ኗሪዎች ሠፈራቸውን እንዲጠሉት ከማድረጉም በላይ ለሥራ የሚኖራቸውን ፍላጎት ይቀንሳል። ሲወጡና ሲገቡ ቆሻሻውን ስለሚመለከቱ አእምሯቸው ንቁ ሊሆን አይችልም።

በአጠቃላይ በተለያዩ መንገዶች የሚፈጠር ቆሻሻ ለሰዎች፣ ለእንስሳትና ለዕፅዋት ጤንነትና ደህንነት ጠንቅ ነው። በመሆኑም ቆሻሻን በየቦታው ከመጣል ይልቅ በአግባቡ ሰብስቦ በተዘጋጀላቸው ገንዳ መጨመር ወይም በቆሻሻ ማስወገጃ ጉድጓድ መቅበር ያስፈልጋል።

(ተፈጥሮ መጽሔት። የካቲት 1997። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የቀረበ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት «እውነት» ወይም «ሐሰት » በማለት በምክንያት መልሱ።

ሀ. የኢንዱስትሪ ምርቶች በሚመረቱበት ጊዜ ቆሻሻ ይፈጠራል።

ለ. በቆሻሻ ምክንያት ከሚመጡ በሽታዎች መካከል ተቅማጥን፣ ኮሌራን፣ ያንጀት ተስቦን፣ ወባንና ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

ሐ. ቆሻሻ ለዝንቦች፣ ለአይጦችና ለልዩ ልዩ ነፍሳት መራቢያ ይሆናል።

ተግባር 2

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልስ ስጡ።

ሀ. በሰዎች ምክንያት የሚፈጠሩ ቆሻሻዎችን እንዴት መቀነስ የሚቻል ይመስላችኋል?

ለ. በሁለተኛው አንቀጽ የመጀመሪያ ዓረፍተነገር «ከላይ በተጠቀሱት» የሚለው አገላለፅ ምንን ያመለክታል?

ሐ. ለአፈር ማዳበሪያነት የሚያገለግለውን ብስባሽ ከበካይ ቆሻሻ መለየት የሚቻለው እንዴት ነው?

ተግባር 3

ቆሻሻ በየቦታው በመጣሉ የሚያደርስብንን ጉዳት በተመለከተ ሥዕሉን መሠረት በማድረግ በምክንያትና ውጤት ስልት አንድ አንቀጽ ጻፉ።

5ኛ ቀን

ቃላት

ለቃላትና ለሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት

ተግባር

በ«ሀ» ረድፍ ለቀረቡት ቃላትና ሐረግ ተመሳሳይ ፍቻቸውን በ«ለ» ረድፍ ካሉት ጋር እያዛመዳችሁ ጻፉ።

ሀ	ለ
1. ጥራጊ	ሀ. ሽንትቤት
2. ማቃወስ	ለ. ፀር
3. መፀዳጃቤት	ሐ. ሳቢ
4. ማራኪ	መ. የቆሸሸ ውኃ
5. ጠንቅ	ሠ. ደረቅ ቆሻሻ
6. እጣቢ	ረ. ማዛባት
	ሰ. ማስታመም

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በምክንያትና ውጤት ስልት የድርሰት ረቂቅ መጻፍ

ተግባር

«የግብርና ምርትን የሚቀንሱ ምክንያቶች» በሚል ርዕስ ባለፈው ሳምንት ያዘጋጃችሁትን የቢጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም በምክንያትና ውጤት ስልት አንድ አንቀጽ ጻፉ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

ተግባር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በምሳሌው መሠረት አስተካክላችሁ ጻፉ።

1. እንዳስተማራችሁ ⟶ እንዳስተማራችሁ-ኣችው = እንዳስተማራችኋችው።
2. አጠብኩ ⟶ አጠብኩ-ኣችው = አጠብኳችው

ሀ. ሰጠሁ	ሐ. የሚፈጥሩ	ሠ. ያከማቹ
ለ. መገብኩ	መ. የሚያስከትሉ	ረ. ሰበሰብኩ

6ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

የቆሻሻ አፈጣጠርና የሚያስከትላቸው ችግሮች

ቅድመንባብ

ተግባር

ቆሻሻ በምን ምክንያት እንደሚፈጠር ተናገሩ።

ማንበብ

ተግባር

«የቆሻሻ አፈጣጠርና የሚያስከትላቸው ችግሮች» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ በማሰማት ተራበተራ አንብቡ።

መናገር

ተግባር

የውኃና የአየር ብክለት በሚያስከትሉ ምክንያቶችና ብክለቱ በሚያደርሰው ጉዳት ላይ በቡድን ተወያዩ። የቡድኑንም ሀሳብ አንድ/አንዲት ተማሪ ለክፍሉ ተማሪዎች ያቅርብ/ታቅርብ።

ሰዋስው

መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮች

ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ያሉትን ቁጥሮች በምሳሌው መሠረት መጣኝ ወይም ደረጃ አመልካች መሆናቸውን በመለየት ጻፉ።

ምሳሌ፡- የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ 4 ደረጃዎች አሉት።

4 ⟶ መጣኝ ቁጥር

ሀ. መደርደሪያው ላይ 11 መጽሐፎች አሉ።

ለ. ፋጡማ በሁለተኛው ወሰነትምህርት አንደኛ ለመውጣት ወስናለች።

ሐ. በክፍላችን ውስጥ 32 ተማሪዎች አሉ።

መ. ሁለተኛው የቆሻሻ አወጋገድ ደረጃ ማንኛውንም ነገር ከቆሻሻ መለየት ነው።

ሠ. በጫካው ውስጥ 320 ግመሎች አየሁ።

ተግባር 2

የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጁ። ከሠንጠረዡ በላይ ያለውንም አንቀጽ በሚገባ አንብቡ። ከዚያም በአንቀጹ ውስጥ ያሉትን ቁጥሮች በሠንጠረዡ ውስጥ አስፍሩ። በመጨረሻም ቁጥሩ መጣኝ ከሆነ መጣኝ ቁጥር በሚለው አምድ፣ ቁጥሩ ደረጃ አመልካች ከሆነ ደግሞ ደረጃ አመልካች ቁጥር በሚለው አምድ ላይ የ«✓» ምልክት አድርጉ።

ቅዳሜ የሳምንቱ ስድስተኛ ቀን ነው። አስቴርና ባለቤቷ የዕረፍት ጊዜያቸው ስለሆነ ወደገበያ ሄዱ። አትክልት ተራ በመግባት ስድስት ኪሎ ሽንኩርት፣ ሦስት ኪሎ ድንች፣ አራት ኪሎ ቲማቲምና አንድ ኪሎ ቃሪያ ገዙ። ከዚያም በገበያ አዳራሹ ሰባተኛ ፎቅ ላይ ከሚገኘው የልብስ ሱቅ ለልጆቻቸው ልዩ ልዩ ልብሶች ገዙ፡

ቁጥር		መጣኝ ቁጥር	ደረጃ አመልካች ቁጥር
ሀ.	ስድስተኛ		✓
ለ.			
ሐ.			
መ.			
ሠ.			
ረ.			

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ተግባር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

ነጣጥሎ ማንበብ		አጣምሮ ማንበብ
ሀ	በ-ዝናብ-አማ-ነቱ	በዝናባማነቱ
ለ	መሠረት-አዊ	መሠረታዊ
ሐ	እየ-ተ-ጠቀመ-በት	እየተጠቀመበት
መ	በ-መጨፍጨፍ	በመጨፍጨፍ
ሠ	በ-ባህርይ-አቸው	በባህርያቸው
ረ	የ-ምርት-አማ-ነት	የምርታማነት
ሰ	ለ-ማስተካከል-አ-ም	ለማስተካከሉም

ማንበብ


በኢትዮጵያ የደን መመናመን መንስኤዎችና የሚያስከትላቸው ችግሮች

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር

በምሳሌው መሠረት የሚከተለውን የቢጋር ሳጥን በተገቢ የምክንያትና የውጤት ሀሳቦች አሟሉ።



የማንበብ ሂደት

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

በኢትዮጵያ የደን መመናመን መንስኤዎችና የሚያስከትላቸው ችግሮች

ከብዙ አስርት ዓመታት በፊት 40 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ የቆዳ ስፋት በደን ተሸፍኖ እንደነበር ይነገራል። አሁን ግን በዝናባማነቱ፣ በለምነቱና በውኃ መሠረትነቱ የሚታወቀው የደን አካባቢ በከፍተኛ መጠን ቀንሶ ይገኛል። ይህ ለምን ሆነ?

በኢትዮጵያ ለደን ሽፋን መመናመን በርካታ ምክንያቶች አሉ። ከነዚህም የእርሻ መሬት መስፋፋት አንዱ ነው። ይህን በተመለከተ ሁለት ምክንያቶች ማንሳት ይቻላል። አንደኛው አርሶአደሮች ለእርሻ እየተጠቀሙበት ያለው መሬት ለምነቱን ያጣል። በዚህ ጊዜ አርሶአደሮች በአካባቢው የሚገኘውን ደን በመጨፍጨፍ ለእርሻነት ይጠቀሙበታል። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የሰፋፊ እርሻዎች መስፋፋት ነው። ሰፋፊ እርሻዎች በባህርያቸው ሰፊ መሬትን ይፈልጋሉ። ለሰፋፊ እርሻዎች ሲባል ደኖች ይመነጠራሉ።

ሁለተኛው ለደን ሽፋን መመናመን ምክንያት የሆነው እንጨትን ለማገዶና ለግንባታ መጠቀም ነው። ሰዎች በየዕለቱ ምግባቸውን ለማብሰልና ቤታቸውን ለመሥራት በአካባቢያቸው የሚገኘውን ማንኛውንም ዛፍ ይቆርጣሉ። ይህ ድርጊት ለብዙ ጊዜያት እየተደጋገመ መቀጠሉ የደንን ሽፋን በከፍተኛ መጠን እንዲቀንስ አድርጎታል።

ሶስተኛው ለደን ሽፋን መቀነስ ምክንያት የሆነው የእንጨት ውጤቶችን ማምረት በከፍተኛ ደረጃ መከናወኑ ነው። የሰዎች አኗኗር በመለወጡ ምክንያት በቤታቸው ውስጥ በአብዛኛው የሚገለገሉባቸው ቁሳቁሶች የእንጨት ውጤቶች ናቸው። ዛሬ ሰዎች የሚተኙበት አልጋ፣ የሚቀመጡበት ወንበር፣ ለምግብ ማዘጋጃና ማቅረቢያ የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች በሙሉ የሚሠሩት ከእንጨት ነው። እነዚህ ፍላጎቶችም የደን ሽፍጨፋን ሳያቋርጥ እንዲቀጥል አድርገውታል።

ከላይ ለደን ሽፋን መመናመን መንስዔ ሆነው የተጠቀሱት ድርጊቶች በደን ሽፋን ላይ ያስከተሏቸው አሉታዊ ተፅዕኖዎችም አሉ። በደን መመናመን ምክንያት አፈር ለነፋስና ለጎርፍ ይጋለጣል። በዚህም ምክንያት አፈር በቀላሉ ይሸረሸራል። የአፈር መሸርሸር ደግሞ የአፈርን ለምነት ስለሚያሳጣ ምርታማነትን ይቀንሳል። ምርታማነት መቀነስ ደግሞ ለረሀብ ስለሚያጋልጥ የህዝብ ፍልሰትን ያስከትላል።

በሌላ በኩል የደን መጨፍጨፍ የከርሰምድር ውኃ እንዲቀንስ ያደርጋል፤ የአየር መዛባትንም ያስከትላል። በዚህም ምክንያት በረሀማነት ይፈጠራል። በረሀማነት ድርቅንና ረሀብን ያመጣል። የደን መጨፍጨፍ እንስሳትን መጠለያ ያሳጣል። በዚህም ምክንያት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙት ብርቅየ የዱር እንስሳት ይሞታሉ፤ ወይም ወደጎረቤት አገር ይሰደዳሉ።

በአጠቃላይ ደን የአየር ጠባይን ለማስተካከልም ሆነ አካባቢን ከብክለት ለመከላከል ሚናው ከፍተኛ ነው። አፈር በንፋስና በውኃ ተጠርጎ እንዳይወሰድ በየቦታው ደን መኖር አለበት። ስለዚህ በሀገራችን የከርሰምድር ውኃ እንዳይቀንስ ደኖችን መንከባከብ አስፈላጊ ነው። ችግኞችን በመትከልና በመንከባከብ የደን ሽፋንን ለመጨመር የበኩላችንን ድርሻ ማበርከት ይጠበቅብናል።

(አይቸው ደሳለኝ። 2014። ሰንደቅ ጋዜጣ ድረገጽ። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

ቀጥሎ የቀረቡትን የምርጫ ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. ከብዙ ዓመታት በፊት ከሀገሪቱ መሬት ምን ያህሉ በደን ተሸፍኖ ነበር?
   ሀ. 3 በመቶ ለ. 4 በመቶ ሐ. 10 በመቶ መ. 40 በመቶ
2. በዝናባማነቱና በውኃ መሠረትነቱ የሚታወቀው አካባቢ የትኛው ነው?
   ሀ. የደን አካባቢ ሐ. ቆላማ አካባቢ
   ለ. በርሃማ አካባቢ መ. ደጋማ አካባቢ
3. በርሃማነትን ለመከላከል ምን ማድረግ ይኖርብናል?
   ሀ. ደኖችን መመንጠር
   ለ. የደን ውጤቶችን ለማገዶ መጠቀም
   ሐ. ችግኞችን መትከልና መንከባከብ
   መ. የደን ውጤቶችን ለግንባታ ማዋል
4. ከሚከተሉት ውስጥ የደን ጥቅም ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. የአየር ጠባይን ማስተካከል፣
   ለ. አፈር በነፋስ እንዳይጠረግ ማድረግ፣

ሐ. የከርሰምድር ውኃ እንዳይቀንስ ማድረግ፣

መ. ንጹህ አየር እንዳይኖር ማድረግ፣

5. የከርሰምድር ውኃና ደን ግንኙነታቸው እንዴት ነው?

ሀ. ደኖች ውኃውን ስለሚመጡት ውኃው ያልቃል።

ለ. ደኖች ለዝናብ መኖር ምክንያት ስለሆኑ ውኃ ይኖራል።

ሐ. የደኖች መኖር የውኃ ትነቱን ስለሚጨምር ውኃው ያልቃል።

መ. ደኖችና የከርሰምድር ውኃ ግንኙነት የላቸውም።

6. ደኖች የአየር ጠባይን የሚያስተካክሉት እንዴት ነው?

ሀ. ደኖች መሬት በንፋስና በውኃ እንዳይጠረግ ስለሚከላከሉ፣

ለ. ደኖች ለሰው ልጆች የኃይል ምንጭ ሆነው ስለሚያገለግሉ፣

ሐ. ደኖች መርዛማ አየርን መጠው ስለሚያስቀሩ፣

መ. ደኖች የፀሐይ ጮራ መሬት ላይ እንዳያርፍ ስለሚከላከሉ፣

ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን እየተወያያችሁ በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የእርሻ መሬት መስፋፋት ለምን ለደን መመናመን ምክንያት ሆነ?

ለ. በአካባቢያችሁ ደኖችን ለመጠበቅ የተሠራውን ሥራ፣ በአጭሩ በቃላችሁ ግለጹ።

ሐ. የደን ልማት ሥራ ባንሠራ ምን ሁኔታ የሚከሰት ይመስላችኋል?

ተግባር 3

ደኖች የሚመናመኑበትን ምክንያትና የሚያስከትለውን ጉዳት በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

8ኛ ቀን

ቃላት

ቃላትን በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀም

ተግባር

የሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ፍቺ ስጡና ዓረፍተነገር በመመሥረት አሳዩ።

ምሳሌ፡- ቁሳቁስ ⟶ የቤት ውስጥ መገልገያ እቃዎች

ወንበር፣ ጠረጴዛና አልጋ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ናቸው።

ሀ. መስፋፋት ሐ. መዛባት ሠ. መነጠረ

ለ. ፍልሰት መ. ብርቅዬ

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

የጻፉትን ረቂቅ አስተካክለው መጻፍ

ተግባር

መምህራችሁ የሚሠጧችሁን መመሪያ በመከተል ባለፈው ሳምንት የጻፋችሁትን ረቂቅ አስተካክላችሁ በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

የአጻጻፍ ሥርዓት

ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት በደብተራችሁ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

9ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

በኢትዮጵያ የደን መመናመን መንስኤዎችና የሚያስከትላቸው ችግሮች

ቅድመንባብ

ተግባር

የደን መመናመን የሚያደርሳቸውን ጉዳቶች አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ማንበብ

ተግባር

መምህራችሁ የሚሰጧችሁን መመሪያ በመከተል ሦስት ሦስት ሆናችሁ ተራበተራ «በኢትዮጵያ የደን መመናመን መንስኤዎችና የሚያስከትሏቸው ችግሮች» የሚለውን ምንባብ፣ አንቀጽ 2 አንብቡ። ስታነቡ በተገቢው የንባብ ፍጥነት፣ ድምፅ በማሰማት፣ ቃላትና ሐረጋትን በትክክል በመጥራትና በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን ሥርዓተነጥቦች በአግባቡ በመጠቀም አንብቡ።

መናገር

ተግባር

በኢትዮጵያ የደን ሽፋን የቀነሰበትን ምክንያትና የደን መመናመን የሚያስከትለውን ጉዳት በተመለከተ በቡድን ተወያዩ። በመጨረሻም ከቡድናችሁ አንዳንድ ተማሪዎች ተመርጠው ለክፍሉ ተማሪዎች ያቅርቡ።

ሰዋስው

መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮች

ተግባር 1

ሐረጋቱን ከትክክለኛ ፍቻቸው ጋር በቃላችሁ አዛምዱ።

ሀ	ለ
1. መጣኝ ቁጥር	ሀ. የነገሮችን እኩልነት የሚያሳይ ቁጥር
2. ደረጃ አመልካች ቁጥር	ለ. የአንድን ነገር ስንትነት የሚያሳይ ቁጥር
	ሐ. አንድ ነገር ያለበትን ቦታ ወይም ደረጃ የሚያመለክት ቁጥር

ተግባር 2

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን ለይታችሁ ተናገሩ።

ሀ. ፋጡማ የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ናት።

ለ. እረኛው 24 ፍየሎችን ይጠብቃል።

ሐ. መቅደስ ለቤተሰቦቿ ሦስተኛ ልጅ ናት።

መ. ቅርጫቱ ውስጥ 33 ብርቱካኖች አሉ።

ሠ. በ20ኛው የዓለም የእግርኳስ ዋንጫ ውድድር ብራዚል አራተኛ ወጣች።

ተግባር 3

በሚከተለው ጽሑፍ መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን በምሳሌው መሠረት ለይታችሁ ጻፉ።

ትምህርትቤታችን ለሦስተኛ ጊዜ በተካሄደው ክልላዊ የትምህርትቤቶች ስፖርታዊ ውድድር ላይ ተካፋይ ነበር። በውድድሩ ላይም በመረብኳስ 19፣ በእግርኳስ 38 እና በአትሌቲክስ 18 ተወዳዳሪዎችን ይዞ ቀርቧል። አሠልጣኙንና ሌሎች ረዳት ባለሙያዎችን ጨምሮ የስፖርት ልዑካን ቡድኑ 82 አባላት ነበሩት። በውድድሩ መጨረሻም ለውድድር ከቀረቡት 30 ትምህርትቤቶች መካከል ቡድናችን በመረብ ኳስ ሦስተኛ፣ በእግርኳስ 12ኛ፣ በአትሌቲክስ ደግሞ አምስተኛ ደረጃ ሊይዝ ችሏል። በፀባይ ደግሞ አንደኛ በመውጣቱ የዋንጫ ተሸላሚ ሆኗል።

ምሳሌ፡-

ቁጥሩ	የቁጥሩ ዓይነት	በፊደል ሲፃፍ
19	መጣኝ ቁጥር	አሥራዘጠኝ
1ኛ	ደረጃ አመልካች ቁጥር	አንደኛ



ልማዶች

ምዕራፍ 3

አካባቢያዊ ልማዶች

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	ከ-ተንተከተከ	ከተንተከተከ
ለ	የ-ዐውድ-ዓመት	የዐውዳመት
ሐ	አል-አረረ-ብኝ-ም	አላረረብኝም
መ	ከ-አ-ቀረበ-ች-ው	ካቀረበችው
ሠ	ስለ-ተካንኩ-በት	ስለተካንኩበት
ረ	የ-ተ-ወቀጠ-ው-ን	የተወቀጠውን

ማንበብ

ቡና ጠጡ

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስና መገመት

ተግባር

በሚከተሉት የቅድመንባብ ጥያቄዎች ላይ ከተወያያችሁ በኋላ በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በቤተሰባችሁ ውስጥ ቡና የሚያፈላው/የምታፈላው ማን ነው/ናት? ለምን ይመስላችኋል?

ለ. ሥዕሉን በትክክል አስተውላችሁ የተረዳችሁትን ተናገሩ።

ሐ. በአካባቢያችሁ ወይም በቤታችሁ ቡና ሲፈላ ምርቃት በማንና እንዴት ይከናወናል?

የማንበብ ሂደት

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ በየግላችሁ አንብቡ።

ቡና ጠጡ



ሕጻን እያለሁ እናቴ ቡና አፍልታ ጎረቤቶቻችንን «ቡና ጠጡ» በዪ ትለኝ ነበር። እኔም ደስ ብሎኝ ሮጨ ሄጄ «ቡና ጠጡ» ብዬ እጠራ ነበር። ጠርቼ ስመለስ እናቴ ለቡና ቁርስ ካቀረበችው ዳቦ ትልቁን ቁራሽ ትሰጠኝ ነበር። ጎረቤቶቻችንም ሲበሉ ከደረስሁ ጉንጭ ሙሉ ጉርሻ ባፌ ውስጥ ያደርጉልኝ ነበር። «የተላከ አፉን ለከከ» ይሏል እንዲህ ነው።

አሁን ደግሞ ከእኔ ቤት ቡና እየተፈላ ልጆቼ «ቡና ጠጡ» እያሉ ጎረቤቶቻችንን ይጠራሉ። ቡናውን እኔ፣ ባለቤቴና ትልልቆቹ ልጆቼ በየተራ እናፈላለን። ሁላችንም አምሮት የሚቆርጥ ቡና እናፈላለን። ትንንሾቹ ልጆቻችን የቡና ማፍያ ቁሳቁሶችና መጠጫ ስኒዎች በማቀራረብ ቡናውን በመውቀጥ ያግዙናል። ሌላውን ተግባር ግን ተረኛ ቡና አፍይ ይወጣዋል።

ዛሬ ቡና የማፍላት ተራው የኔ ነው። ቡና የማፍላት ጥበቡን ስለተካንኩት አልችገረኝም። «ቡናን ማፍላት ረጋ ብሎ እያሳመሩ ነው፤ ሥነሥርዓቱ ውበቱ ነው» የሚል እምነት አለኝ። ስለዚህ ቡና ሳፈላ አልቻኮልም። ዛሬ ደግሞ የዘመን

መለወጫ በዓል ስለሆነ ሥነሥርዓቱን የበለጠ ማሳመር ይኖርብኛል። በመሆኑም ረጋ ብዬ አፈላዋለሁ።

በዐውዳመት የክት ልብስ ይለበሳል። እኔም ዉት ተነስቼ፣ ሰውነቴን ተጣጥቤ፣ የዐውዳመት ልብሴን ለብሻለሁ። ልብሱ ደስ የሚል በሀገር ባህል የተዘጋጀ ባለጥልፍ ቀሚስ ነው። ቀኑ ዐውዳመት በመሆኑ ቡናው ከመቆላቱ በፊት ጎረቤቶቻችን ተጠርተው መጥተዋል። ሴቶችም ወንዶችም የሀገር ባህል ልብስ ለብሰው አምሮባቸዋል። በተለይ ሴቶች፣ የሚያምር የሀበሻ ቀሚሳቸውን ለብሰው በትከሻቸው ላይ ነጠላ ጣል አድርገዋል።

የቡና ዝግጅቴ ረጋ ያለና የቡና አፈላል ሥርዓትን የተከተለ ነው። በዚህ መሠረትም በሚያምር ዝግጅት ቡና ማፍላቴን ቀጠልኩ። ትርክክ ብሎ የተያያዘ ከሰል አቀረብሁ። ብረት ምጣድ ጥጄ ቡናውን ቆላሁ። አንድም ፍሬ ቡና አላረረብኝም። የቆላሁት ቡና አንድ መልክ፣ አንድ ወዝ ይዞ ወጣ። ለዐውዳመት ማድመቂያ በተከፈተው ሙዚቃ እየታጀብኩ በቆላሁት ቡና ሳሎኑን አጠንኩት። መአዛው ብቻ ሱስ ያስታግሳል። ከሰሉን እንደገና አራግቤ እሳቱ ትርክክ ሲል ታጥቦ የቀረበውን ጀበና ጣድኩ። ውኃው በደንብ ከፈላ በኋላ የተወቀጠውን ቡና ጨመርኩበት። ለተወሰነ ደቂቃ ከተንተከተከ በኋላ እንዲሰክን አውጥቼ አስቀመጥኩት። ትንሽ ቆይቼም በሚያምር ረከቦት ላይ በተቀመጡት ስድስት ስኒዎች ቡና ቀድቼ አደልኩ። እኔም አንድ ስኒ ያዝኩ።

> **የቆላሁት ቡና አንድ መልክ፣ አንድ ወዝ ይዞ ወጣ።**

በቡና አፈላል ሥርዓታችን ሂደት ቁርስ ቀምሰናል፣ ተጨዋውተናል፣ ተቀላልደናል። ወግ እያቀረብን ዘና ብለናል። በዚህ ሁኔታ አቦል፣ ቶናና በረካ ተጠጣ። ቡናው በማክተሙም እንደወጋችንና ልማዳችን ተመራረቅን። ምርቃቱም «ተባረኩ፣ ቡናው እንደፈላ ሲሳያችሁ ይፍላ፣ ያለም የሲሳይ ቤት ይሁን፤ ከዓመት ዓመት ያድርሰን፤ ቸር ዐውዳመት ያድርግልን፤ በረካ ሁኑ» የሚል ነው። እኔን ጨምሮ ታዳሚዎችም «አሜን! አሜን!» እያልን ምላሽ በመስጠት ተሰነባበትን።

(በዓሉ ግርማ። 1984። *አሮማይ*። ከገጽ 264-265፣ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ጎረቤቶቹ ቡናው ከመፈላቱ በፊት የመጡት ለምንድን ነው?

ለ. በታሪኩ ውስጥ እንደተገለጸው ሴቶቹ የለበሱት ልብስ ምን ዓይነት ነው?

ሐ. ቡናውን ያፈላው ማን ነው/ናት? እንዴት ይታወቃል?

መ. የቡና አፈላል ስንት ደረጃዎች አሉት?

ሠ. በአንቀጽ 5 በተገለጸው መሠረት ቡና የጠጡት ጎረቤቶች ስንት ናቸው? ቡና ያልጠጡ ሰዎች አሉን? ለምን ይመስላችኋል?

ረ. ወንድ ቡና ማፍላት አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

2ኛ ቀን

ቃላት

ለቃላትና ለሐረጋት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት

ተግባር 1

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በቡድን እየተወያያችሁ ከምንባቡ ውስጥ ተመሳሳያቸውን ፈልጉ።

ምሳሌ፡- የሚያረካ = (2ኛ አንቀጽ) = የሚቆርጥ

አጫጭር ታሪኮች = (6ኛ አንቀጽ) = ወግ

ሀ. ፍላጎት (2ኛ አንቀጽ)= _____

ለ. ፍም ሆነ (5ኛ አንቀጽ) = _____

ሐ. ሦስተኛ ቡና (6ኛ አንቀጽ) = _____

መ. ሁለተኛ ቡና (6ኛ አንቀጽ) = _____

ሠ. የመጀመሪያ ቡና (6ኛ አንቀጽ) = _____

ተግባር 2

በ«ሀ» ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላትና ሐረጋት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ«ለ» ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

ሀ	ለ
1. ቸር	ሀ. ማራራቅ
2. ጣደ	ለ. ቸኮለ
3. ሰከነ	ሐ. አወጣ
4. ምርቃት	መ. ንፉግ
5. ማቀራረብ	ሠ. ርግማን
6. ረጋ አለ	ረ. ደፈረሰ

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

ዋናና መዘርዝር ሀሳቦችን በቢጋር ሠንጠረዥ ማስፈር

ማስታወሻ፡-


ዋና ሀሳብ የሚባለው ጽሑፉ ውስጥ ሊገለጽ የተፈለገው ዋና ጉዳይ ነው። ዋናውን ሀሳብ የሚያብራሩት ደግሞ መዘርዝር ሀሳቦች ይባላሉ።

ዋናውን ሀሳብ ከመዘርዝር ሀሳቦች ለመለየት የሚከተሉትን ስልቶች መጠቀም ያስፈልጋል፤

- ዋናውን ርዕስና ንዑስ ርዕሶችን መመልከት፣
- ሥዕሎችን መመልከት፣
- ዝርዝር ሀሳቦችን ማንበብ።

ተግባር 1

«ቡና ጠጡ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ 5ኛውን አንቀጽ በጥንቃቄ አንብቡና በምሳሌው መሠረት ዝርዝር ሀሳቦችን በቢጋር ሳጥን አስፍሩ።



ተግባር 2

«የምግብ ዓይነቶች» በሚል መሪ ሀሳብ የቢጋር ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ ዝርዝር ሀሳቦችን አስፍሩ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

የቃላትን ቅደምተከተል እንደገና በማዋቀር ዓረፍተነገር አስተካክሎ መጻፍ።

ተግባር

በምሳሌው መሠረት የቃላትን ቅደምተከተል እንደገና በማዋቀር ዓረፍተነገሮቹን አስተካክላችሁ ጻፉ።

ምሳሌ:- ተኛ በሰፍነግ (በስፖንጅ) ፍራሽ ላይ አለባቸው።

አለባቸው በሰፍነግ (በስፖንጅ) ፍራሽ ላይ ተኛ።

ሀ. አለቀሰች በጣም ስለራባት አምርራ ሕጻኗ።

ለ. ወረደ ጣራውን ጠግኖ አናጢው።

ሐ. ትስላለች ጉንፋን ስለያዛት ጀሚላ።

መ. መምህሯ ስለመጡ ተነሱ ከወንበራቸው ተማሪዎች።

ሠ. አነጠሰ ቅዝቃዜው ስለተሰማው ሕጻኑ።

ረ. ዋኘ ከቤታቸው ጀርባ ካለው ወንዝ ውስጥ ደምሴ።

ሰ. ሄደ ወደመስጊድ መንሱር።

3ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

ቡና ጠጡ

ማስታወሻ:-

አንድ ምንባብ በሚነበብበት ጊዜ:-

- በተቻለ መጠን ፊደላትን አለመግደፍ፤
- ቃላትን አለመደጋገም፤
- ፊደላትን ሳይነጥሉ ሙሉውን ቃል ማንበብ ያስፈልጋል፤

ተግባር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አንብቡ።

የመገምገሚያ መስፈርት	በመጀመሪያ ጊዜ ንባብ	በሁለተኛ ጊዜ ንባብ
በስህተት የተነበቡ ቃላት ብዛት		
በንባብ ጊዜ የተደገሙ ቃላት ብዛት		
ተነጥለው የተነበቡ ቃላት ብዛት		
በሐረግ መነበብ ሲገባቸው፣ ቃል በቃል የተነበቡ ቃላት ብዛት		

ማዳመጥ

ልማድ

ቅድመማዳመጥ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ልማዳዊ ተግባራት በደብተራችሁ ዘርዝራችሁ ጻፉ።

ለ. ከርዕሱ በመነሳት ምንባቡ ስለምን የሚገልፅ ይመስላችኋል?

የማዳመጥ ሂደት

ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ በጥሞና አዳምጡ። በምታዳምጡበት ጊዜ ዋናዋና ሀሳቦችን በማስታወሻ መዝግቡ፤ ያልተረዳችኋቸው እንግዳ ቃላት ካጋጠሟችሁም ለይታችሁ ጻፏቸው።

አዳምጠ መረዳት

ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ልማድ ምን ምን ነገሮችን ያካትታል?

ለ. ልማድ ጎጂና ጠቃሚ የተባለው ከምን አንፃር ነው?

ሐ. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ጠቃሚና ጎጂ ልማዶች ዘርዝሩ።

መ. በጽሑፉ ውስጥ «ልማድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የማኅበረሰባዊ ሕጎች ስብስብ ነው» ይላል። እያንዳንዱ ትውልድ የየራሱን ልማድ ሊመሠርት አይችልም ማለት ነው? ለምን ይመስላችኋል?

ሠ. ልማድ ትውልድን ከትውልድ የሚያገናኘው እንዴት ባለ ሁኔታ ነው ትላላችሁ?

ሰዋስው

ኢሳቢ ግስ

ማስታወሻ፡-

ኢሳቢ ግስ የሚባለው ድርጊቱ በራሱ በባለቤቱ ላይ ያለቀ መሆኑን የሚያሳይ ወይም ድርጊቱ ወደሌላ አካል የማይሻገር የግስ ዓይነት ነው። ምሳሌ፡- መጣ፣ ሄደች፣ ቆመ፣ ተቀመጠች... የመሳሰሉት ግሶች ኢሳቢ ግሶች ናቸው።

ተግባር 1

«ሄደ» የሚለውን ግስ በመጠቀም በምሳሌው መሠረት ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፡- ሄደ

እኔ ሄድኩ።

እኛ ሄድን።

ተግባር 2

«ተኛ» የሚለውን ግስ በመጠቀም ከላይ በተሠራው መሠረት ዓረፍተነገር ሥሩ።

ማንበብ

ዕድር

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር

«ዕድር» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች «እውነት» ወይም «ሐሰት» በማለት ምክንያት እየሰጣችሁ በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ዕድር የሚመሠረተው በአንድ ሠፈር በሚኖሩ ሰዎች ብቻ ነው።

ለ. ዕድር በሀዘንም ሆነ በደስታ ጊዜ ለመደጋገፍ ይጠቅማል።

ሐ. ዕድር ድጋፍ የሚሰጠው ዘመድ ለሞተባቸው ሰዎች ብቻ ነው።

መ. ከዕድር አባላት ግዴታዎች መካከል አንዱ በሞት ጊዜ መቃብር መቆፈር ነው።

የማንበብ ሂደት

ተግባር

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ መረዳታችሁን እያረጋገጣችሁ አንብቡ።

ዕድር

ዕድር ሰዎች አብሮ በመኖር በሚፈጠር ማኅበራዊ ግንኙነት የሚመሠርቱት ማኅበር ነው። አመሠራረቱም በሁለት መንገድ ሊሆን ይችላል። አንደኛው በሠፈር ሲሆን ሁለተኛው በሥራ ቦታ ነው። በአንድ አካባቢ በሚኖሩ ሰዎች የጋራ ስምምነት የሚመሠረተው የሠፈር ዕድር ይባላል። በአንድ መስሪያቤት በሚሠሩ ሰዎች ትብብር የሚመሠረተው ደግሞ የመሥሪያቤት ዕድር ይባላል።

ሁለቱም የዕድር ዓይነቶች ማኅበራዊ የመተዳደሪያ ደንብ አላቸው። መተዳደሪያ ደንቡ አባላቱ ሰፊ ውይይት አድርገውበት የሚጸድቅ ነው። ደንቡ በዋናነት የማኅበርተኞችን መብትና ግዴታ እንዲሁም የዕድር ኮሚቴ አባላትን ኃላፊነት በዝርዝር ይይዛል። የዕድር ኮሚቴ አባላት ሥራቸውን የሚያከናውኑት በደንቡ

መሠረት ነው። የዕድሩ አባላትም ደንቡ በሚፈቅደው መሠረት የመገልገልና የማገልገል መብትና ግዴታ አላቸው።

ዕድር የራሱ የሆነ ጽሕፈትቤትና ንብረቶች ሊኖሩት የሚችል ማኅበራዊ ተቋም ነው። ድንኳን፣ አግዳሚ ወንበር፣ የአስከሬን አልጋ፣ አካፋና ዶማ ዋና ንብረቶች ናቸው። መመገቢያ፣ መጠጫና ማብሰያ እቃዎች በተጨማሪነት ይገኛሉ።

የዕድር ዓላማ በሀዘንና በደስታ ጊዜ ተባብሮና ተረዳድቶ ችግርን መፍታት ነው። በተለይ በሀዘን ጊዜ የዕድር ጥቅም ጎልቶ ይታያል። በሞትና በመርዶ ጊዜ የቀብር ሥነሥርዓት ማስፈጸምና ማስተዛዘን የዕድርተኞች ግዴታ ነው። መቃብር መቆፈር፣ ድንኳን መትከል፣ የማስተዛዘኛ ምግብ ማዘጋጀት የማይቀሩ ግዴታዎች ናቸው። በገንዘብ የሚደረገው ርዳታ ግን እንደሟች ቤተሰባዊ ግንኙነት የተለያየ ነው። ከአባላት ከሚሰበሰበው ገንዘብ ወጪ ተደርጎ ለሬሳ ሳጥን፣ ለከፈንና ለማስተዛዘኛ የሚሆን ምግብ መግዣ ይውላል። እድሩ ሬሳ ከቤት ሲወጣም ሆነ በመርዶ ጊዜ የገንዘብና የጉልበት ዕርዳታ ይሰጣል። የዕድሩ አባላትም በሀዘንተኞች ቤት በመገኘት ያስተዛዝናሉ።

መቃብር መቆፈር፣ ድንኳን መትከል፣ የማስተዛዘኛ ምግብ ማዘጋጀት የማይቀሩ ግዴታዎች ናቸው።

የዕድሩ አቅም ከፍ ያለ ከሆነ ሌሎች ተጨማሪ እርዳታዎችንም ይሰጣል። የዕድር አባላት ድንገተኛ ችግር ሲደርስባቸው ተመጣጣኝ ብር በብድር ሊሰጣቸው ይችላል። ሌሎችም እንደቃጠሎ፣ ዘረፋ፣ ሕመም፣ ወዘተ. ሲያጋጥማቸው ዕድሩ አለኝታ ይሆናቸዋል። የጋብቻ ሥነሥርዓት ለማስፈጸም የዕድር አባላት በመዋጮ ወይም በብድር ገንዘብ ያገኛሉ። ጉልበትና የዕቃ ዕርዳታ ሊደረግላቸው ይችላል።

ዕድር ዘመናዊና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ከአንዳንድ ልማዳዊ አሠራሮች መላቀቅ ይኖርበታል። በምትኩም ዘመናዊ አስተሳሰቦችን ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግ አለበት። አባላቱም በቋሚነት ሊታገዙ የሚችሉባቸውን የልማት ሥራዎች መሥራት ይኖርባቸዋል።

(ሌስላው። 2001። *የአማርኛ ንባብ*። መነሻነት የተጻፈ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሰዎች ዕድር መመሥረት ለምን አስፈለጋቸው?

ለ. በሰፈር ዕድርና በሥራ ቦታ ዕድር መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?

ሐ. የዕድር አባላት በቀብር ሥነሥርዓት ወቅት ምን ምን ተግባሮችን ያከናውናሉ?

መ. ዕድርን በኮሚቴ መምራት ለምን አስፈለገ?

ሠ. ዕድርን ማኅበራዊ ተቋም ያሰኘው ጉዳይ ምንድን ነው?

ረ. የዕድር ኮሚቴ አባላትን ኃላፊነት በመተዳደሪያ ደንብ መወሰን ለምን ያስፈልጋል?

ሰ. የዕድር አባላት መብትና ግዴታ በመተዳደሪያ ደንብ ባይደነገግ ምን ችግር የሚያስከትል ይመስላችኋል?

ተግባር 2

በ«ሀ» ረድፍ የቀረቡትን አንቀጾች በምንባቡ መሠረት በ«ለ» ረድፍ ከቀረቡት ቁልፍ ሀሳቦች በመምረጥ አዛምዱ።

ሀ	ለ
1. አንቀጽ አንድ	ሀ. የዕድር ንብረቶች
2. አንቀጽ ሁለት	ለ. ዕድር የሚሰጣቸው ተጨማሪ አገልግሎቶች
3. አንቀጽ ሦስት	ሐ. የዕድር ዓላማ
4. አንቀጽ አራት	መ. የዕድር አሠራርን ማሻሻል
5. አንቀጽ አምስት	ሠ. የዕድር ምንነትና አመሠራረት
6. አንቀጽ ስድስት	ረ. የዕድር መተዳደሪያ ደንቦች

5ኛ ቀን

ቃላት

ለቃላትና ለሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት

ተግባር 1

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ፍቺ ስጡ።

ምሳሌ፡-

1. ድንገተኛ = ያልተጠበቀ

2. አስከሬን = ሬሳ

ሀ. ማስተዛዘን	ሐ. ድንኳን	ሠ. አለኝታ
ለ. መርዶ	መ. መስሪያቤት	ረ. ከፊን

ተግባር 2

ከላይ በቀረቡት ቃላት፣ በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በዋናና መዘርዝር ሀሳብ ስልት አንቀጽ መጻፍ

ተግባር

ያዘጋጃችሁትን የቢጋር ሠንጠረዥ በመጠቀም በዋናና መዘርዝር ሀሳቦች የአጻጻፍ ስልት አንድ አንቀጽ ጻፉ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

የቃላትን ቅደምተከተል እንደገና በማዋቀር ዓረፍተነገር አስተካክሎ መጻፍ

ተግባር

ቀጥሎ የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች የቃላት ቅደምተከተላቸውን እንደገና በማዋቀር አስተካክላችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

1. አለምነሽ ሂደች ወደትምህርትቤት።

   ተስተካክሎ ሲጻፍ ⟶ አለምነሽ ወደትምህርትቤት ሂደች።

2. አብደላ ሠራ ትልቅ ቤት

   ተስተካክሎ ሲጻፍ ⟶ አብደላ ትልቅ ቤት ሠራ።

   ሀ. የብርቱካን ቀለም ነው ቢጫ።

   ለ. ወርቅነሽ ተደሰተች ሎተሪ ስለደረሳት።

   ሐ. ያሲን ደክሞታል ብዙ ሥራ ስለሠራ።

   መ. ካሳሁን ገዛ ለእህቱ ሰማያዊ ሹራብ።

   ሠ. አዳነ ግርማ ተጨዋች ነው ዝነኛ የእግርኳስ።

አቀላጥፎ ማንበብ

ዕድር

ቅድመንባብ

ተግባር

መምህራችሁ የሚሰጧችሁን ማብራሪያ አዳምጡ።

ማንበብ

ተግባር

«ዕድር» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ውስጥ 3ኛውንና 4ኛውን አንቀጽ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተራበተራ ድምፅ እያሰማችሁ አንብቡ። አንዳችሁ ስታነቡ ሌሎቻችሁ በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ ስህተቶችን መዝግቡ።

የመገምገሚያ መስፈርት		በመጀመሪያ ንባብ	በሁለተኛ ንባብ
ሀ	በስህተት የተነበቡ ፊደላት ብዛት		
ለ	ተነጥለው የተነበቡ ቃላት ብዛት		
ሐ	በንባብ ጊዜ የተደገሙ ቃላት ብዛት		
መ	ተገቢው እረፍት ያልተደረገባቸው ሥርዓተነጥቦች ብዛት		
ድምር			

መናገር

ተግባር

ቀጥሎ ከቀረቡት ርዕሰጉዳዮች አንዱን መርጣችሁ በቡድን ተከራከሩ።

ሀ. ዕድር ከጠቀሜታውና ከጉዳቱ የትኛው ያመዝናል?

ለ. የዕድር አባል መሆን ግዴታ ነው ወይስ ውዴታ? ለምን?

ሰዋስው

ኢሳቢ ግሶች

ተግባር 1

ምሳሌ

ተነሳ	እኔ	እኛ	አንቺ	አንተ	እናንተ	እሱ	እሷ	እነሱ
	ተነሳሁ	ተነሳን	ተነሳሽ	ተነሳህ	ተነሳችሁ	ተነሳ	ተነሳች	ተነሱ

«አዘነ» የሚለውን ግስ ተጠቅማችሁ በምሳሌው መሠረት ሥሩ።

ተግባር 2

ከየጥያቄዎቹ ፊት ለፊት በቅንፍ ውስጥ ከቀረቡት ኢሳቢ ግሶች መካከል ተስማሚውን በመምረጥ ዓረፍተነገሩን አሟልታችሁ ጻፉ።

ሀ. እኔ _____። (መጣ/መጣሁ)

ለ. እኛ _____። (ሳቅን/ሳቁ)

ሐ. አንቺ _____። (ወፈረች/ወፈርሽ)

መ. አንተ _____። (ቀላህ/ቀላሽ)

ሠ. እናንተ _____። (ወደቅን/ወደቃችሁ)

ረ. እሱ _____። (ነቃ/ነቁ)

ሰ. እሷ _____። (ተናገሩ/ተናገረች)

ሸ. እነሱ _____። (ተከፋሁ/ተከፉ)

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ተግባር

ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

ነጣጥሎ ማንበብ		አጣምሮ ማንበብ
ሀ	ይ-አል-አገናዘበ	ያላገናዘበ
ለ	የ-ተ-ት-ረፈረፈ	የተትረፈረፈ
ሐ	ከ-ጠቀሜታ-ቸው	ከጠቀሜታቸው
መ	የ-ኋላ-ቀር-ነት	የኋላቀርነት
ሠ	የሚ-ያስገኝ-ል-ኣቸው	የሚያስገኝላቸው

ማንበብ

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ምን ማለት ነው?

ለ. በአካባቢያችሁ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አሉ? ምን ምን ናቸው?

ሐ. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸው ጠቃሚ ልማዶችስ አሉ? ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝሩ።

የማንበብ ሂደት

«ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ፣ መረዳታችሁን እያረጋገጣችሁ አንብቡ። በምታነቡበት ጊዜ አዳዲስ ቃላት ሲያጋጥሟችሁ፡-

ሀ. በደብተራችሁ መዝግቡ፤

ለ. የቃሉን ፍቺ በአግባቡ ለመረዳት ሞክሩ።

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት

አንድ ነገር በተመሳሳይ ሁኔታ ለብዙ ጊዜያት ተደጋግሞ ሲከናወን ልማድ ይሆናል። ልማድ በጎም ክፉም ገጽታ አለው። በሰዎች ላይ አካላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነልቦናዊ ጉዳት የሚያደርስ ልማድ ጎጂ ይባላል። በተቃራኒው ሥነልቦናዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካላዊ ጠቀሜታ ያለው ልማድ ጠቃሚ ይሆናል።

በኢትዮጵያ፣ ጎጂ ከሚባሉት ልማዶች መካከል የሴት ልጅ ግርዛት፣ ያለዕድሜ ጋብቻ፣ አቅምን ያላገናዘበ ድግስ ከፊሎቹ ናቸው። በማኅበረሰቡ ውስጥ ሥር ሰደው የቆዩት እነዚህ ልማዶች ከጥቅማቸው ጉዳታቸው ያመዝናል። በመሆኑም የዕድገት ማነቆ ተደርገው ይቆጠራሉ።

የሴት ልጅ ግርዛት የሴትን ልጅ ብልት የተለያዩ ክፍሎች የመቁረጥ ልማዳዊ ድርጊት ነው። ድርጊቱ እንደተፈጸመና ከተፈጸመ በኋላም የሚያስከትላቸው የጤና ጉዳቶች በርካታ ናቸው። በግርዛት ጊዜና ከግርዛት በኋላ የሚመጣ የሕመም ስቃይ አለ፣ ግርዛቱ ጥሎ የሚያልፈው የፍርሃትና የጭንቀት ስሜትም አለ። የሴት ልጅ ግርዛት ዓይነቱና አፈጻጸሙ ከቦታ ቦታ ይለያያል። ለምሳሌ በአንዳንድ አካባቢዎች ሕፃኗ በተወለደች በሰባተኛው ቀን ይፈጸማል። የዚህም ምክንያት ሰውነት ሲጠነክር የሚፈጸም ግርዛት ለስቃይ ይዳርጋል የሚል ነው። በሌላ አካባቢ ደግሞ ግርዛቱ ከ7-18 ዓመት ባለ ዕድሜ ይከናወናል። ይህም የሚሆነው በሕጻን ነት ግርዛት ከተደረገ እድገትን ያዘገያል ከሚል እምነት ነው።

ያለዕድሜ ጋብቻ ደግሞ በአካልና በአእምሮ ሳይበስሉ የሚፈጸም ጋብቻ ነው። ጋብቻው በወላጆች ፍላጎት ብቻ ይፈጸማል። አፈጻጸሙ ከቦታ ቦታ ቢለያይም በተለይ ሴት ልጅን ከአሥራ ስምንት ዓመት ዕድሜ በፊት በመዳር ይከናወናል። ያለዕድሜ ጋብቻ የሚፈጸምበት ዋናው ምክንያት ዝምድናን ፍለጋ ነው። የተጋቢዎቹ ወላጆች በጋብቻ መተሳሰራቸው የሚያስገኝላቸውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያስቀድማሉ። ነገርግን ያለዕድሜ ጋብቻ ሰለባ የሆነች ሴት አካሏ ሳይጠነክር ስለምታረግዝ በወሊድ ጊዜ ከባድ ችግር ያጋጥማታል። ሽንትንና ዓይነምድርን መቆጣጠር እንዳትችል ለሚያደርግ ፌስቱላ በሽታ ልትጋለጥ ትችላለች።

አቅምን ያላገናዘበ ድግስ ሌላኛው ጎጂ ልማድ ነው። ይህም ለክብርና ለዝና ሲባል ወይም ከማን አንሼ በሚል ስሜት የሚፈፀም ነው። ለክብርና ለዝና ሲሉ የሚደግሱት አቅሙ ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ከማን አንሼ በሚል ስሜት የተትረፈረፈ ድግስ የሚደግሱት ግን አቅም የሌላቸው ናቸው። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ድግሱን የሚደግሱት ተበድረው ሊሆን ይችላል። ይህም ለከፋ ችግር እንዲጋለጡ ያደርጋቸዋል።

ከላይ የተጠቀሱት ልማዶች ሰዎች ለረጅም ጊዜ ባህል አድርገዋቸው የቆዩ ናቸው። ይሁንእንጂ ከጠቀሜታቸው ይልቅ ጉዳታቸው ያመዝናል። ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች

የሚባሉትም በሰዎች ላይ ከሚያደርሷቸው አካላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነልቦናዊ ጉዳቶች የተነሳ ነው።

(የኢትዮጵያ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች አስወጋጅ ማኅበር። 2000። ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት በኢትዮጵያ። ከገጽ 15-18 መነሻነት የተጻፈ)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. አንድ ድርጊት ጎጂ ልማድ ነው የሚባለው ምን ሲሆን ነው?

ለ. ያለዕድሜ ጋብቻ የሚፈፀምበት ዋነኛ ምክንያት ምንድን ነው?


ሐ. ያለዕድሜ ጋብቻ ከሴቷና ከወንዱ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሰው በማን ላይ ነው? ለምን?

መ. አቅምን ያላገነዘበ ድግስ ይበልጥ የሚጎዳው ማንን ይመስላችኋል?

ሠ. በአንቀጽ 4 «የተጋቢዎች ወላጆች በጋብቻ መተሳሰራቸው የሚያስገኝላቸውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያስቀድማሉ» ሲል ምን ማለት ይመስላችኋል?

ተግባር 2

ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሴት ልጅ ግርዛት፣ ያለዕድሜ ጋብቻና አቅምን ያላገናዘበ ድግስ የሚያስከትሉትን ጉዳት ቀጥሎ በቀረቡት ክቦች ውስጥ ጻፉ።



8ኛ ቀን

ቃላት

ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት

ተግባር

በ«ሀ» ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከ«ለ» ረድፍ ካሉት በመምረጥ አዛምዱ።

ሀ	ለ
1. በጎ	ሀ. እውቅና
2. ዝና	ለ. እንቅፋት
3. ማነቆ	ሐ. ብልፅግና
4. ጋብቻ	መ. ትዳር
5. መገለጫ	ሠ. ጥሩ
6. ዕድገት	ረ. መታወቂያ
7. መተሳሰር	ሰ. መዛመድ

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በዋናና መዘርዝር ሀሳብ ስልት የተጻፈ አንቀጽ መከለስ

ተግባር 1

ቀጥሎ የቀረበውን አንቀጽ በሠንጠረዥ ውስጥ ባሉት መገምገሚያ መስፈርቶች መሠረት አስተካክሉ። ስህተቶቹን በሚመለከት በመምህራችሁ የሚቀርቡላችሁን ጥያቄዎች መልሱ።

እንስሳት ከአመጋገባቸው አንፃር ዕፅበል፣ ሥጋበልና ሁለበል ተብለው በሦስት ይከፈላሉ። ዕፅበል የሚባሉት ዕፅዋትን ብቻ የሚመገቡ እንስሳት ነው። እነዚህም እንደፍየል በግ በሬ ላም ሚዳቋ ዝሆን ወዘተ ያሉት ናቸው። ሥጋበል የምንላቸው ሥጋ ብቻ የሚመገቡትን እንስሳት ነው። በዚህ የእንስሳት ምድብ ውስጥ ይካተታሉ እንደ ውሻ አንበሳና ነብር ያሉት። በሶስተኛው ምድብ ውስጥ ደግሞ እንደሰውና አይጥ ያሉ ሥጋና ዕፅዋትን የሚመገቡ እንስሳት ይገኛሉ።

	የጽሑፍ መገምገሚያ መስፈርቶች	አዎ	አይደለም
	በጽሑፌ ውስጥ ዋና ሀሳብ አለ?		
	በጽሑፌ ውስጥ ዋናውን ሀሳብ የሚያብራሩ ዝርዝር ሀሳቦች አሉ?		
	ሥርዓተነጥቦች በአግባቡ ተካተዋል?		
	በጽሑፌ ውስጥ የሰዋስው ስህተት አለ?		

ተግባር 2

ባለፈው ሳምንት የጻፋችሁትን አንቀጽ በምሳሌው መሠረት አስተካክላችሁ ጻፉ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

ተግባር

ከዚህ በታች የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች የቃላት ቅደምተከተላቸውን እንደገና በማዋቀር አስተካክላችሁ ጻፉ።

ሀ. ጓደኛውን በአጋጣሚ ስላገኘው ተደነቀ ሸፈራው።

ለ. አፈረ ስለተደረሰበት ልጁ ሲሰርቅ።

ሐ. ተናደደች ልብሷን ጭቃ ስለነካው ለምለም።

መ. ቀረች ሆዷን ስላመማት ከትምህርትቤት ዘይነባ።

ሠ. ስለነከሰው ዘለለ ከማል ጉንዳን።

9ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች

ቅድመንባብ

ተግባር

ድምፅ ሳያሰሙ በማንበብ ጊዜ መደረግ ያለባቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?

ማንበብ

ተግባር

«ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ። መምህር ማንበባችሁን አቁሙ ሲሏችሁ አቁሙ። ከዚያም ያነበባችኋቸውን ቃላት ብዛት ቁጥራችሁ ለመምህራችሁ ንገሩ።

መናገር

ተግባር

ከሚከተሉት ጥያቄዎች አንዱን መርጣችሁ በቡድን ተወያዩ። ከዚያም ከቡድናችሁ አንድ/ዲት ተማሪ የቡድኑን ሀሳብ ያቅርብ/ታቅርብ።

ሀ. «የሴት ልጅ ግርዛት ጎጂ ልማድ ነው» ሲባል፣ «የወንድ ልጅ ግርዛት» ለምን ጎጂ ልማድ ነው አልተባለም?

ለ. «ልጅ በልጅነት ነው» የሚለው አባባል ካለዕድሜ ጋብቻ ጋር የሚቃረን ይመስላችኋል? ለምን?

ሰዋስው

ኢሳቢ ግስ

ተግባር

በ«ሀ» ሥር የተዘረዘሩትን ጅምር ዓረፍተነገሮች ከ«ለ» ሥር ከተዘረዘሩት ተስማሚ ግሶችን በመምረጥ አሟልታችሁ ጻፉ።

«ሀ»	«ለ»
1. እኔ _____።	ሀ. ወጣች
2. እኛ _____።	ለ. ተደሰተ
3. አንቺ _____።	ሐ. አለቀሱ
4. አንተ _____።	መ. ተነሳህ
5. እናንተ _____።	ሠ. ከሳሁ
6. እሱ _____።	ረ. ተቀመጣችሁ
7. እሷ _____።	ሰ. ገባን
8. እነሱ _____።	ሸ. ሳቅሽ



የትራፊክ ደህንነት

ምዕራፍ 4

የመንገድ ደህንነት

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ተግባር

የሚከተሉትን ቃላት በቡድን ሆናችሁ እየነጠላችሁና እያጣመራችሁ አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	ዜ-ብ-ራ	ዜብራ
ለ	የ-ትራፊክ	የትራፊክ
ሐ	ተሽከርካሪ-ዎች-ን	ተሽከርካሪዎችን
መ	መቆም-አችሁ-ን	መቆማችሁን
ሠ	አለ-መኖር-ኡ-ን	አለመኖሩን
ረ	ሕይወት-አችሁ-ን	ሕይወታችሁን

ማንበብ

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች ከመምህራችሁ ጋር በመወያየት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በአካባቢያችሁ የመንገድ ላይ አደጋ ደርሶ ያውቃል?

ለ. ከቤታችሁ ወደትምህርትቤታችሁ ስትሄዱ ወይም መንገድ ስታቋርጡ ምን ዓይነት ጥንቃቄዎች ታደርጋላችሁ?

ሐ. ሥዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ሀሳብ ተናገሩ።

የማንበብ ሂደት

ተግባር

«የመንገድ ላይ ጥንቃቄ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ የሚሰጧችሁን ተግባራት እያከናወናችሁ ድምፃችሁን ሳታሰሙ በግል አንብቡ።

የመንገድ ላይ ጥንቃቄ



በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች አሳሳቢ በሆነ ደረጃ የመንገድ ላይ አደጋዎች ይደርሳሉ። በዚህም በየዓመቱ ብዙ ሰዎች ህይወታቸውን ያጣሉ። አያሌ ሰዎች የአካል ጉዳተኛ ይሆናሉ። ከእነዚህ ሰዎች መካከል አብዛኛዎቹ እግረኞች ናቸው። እግረኞች የመኪና አደጋ የሚደርስባቸው ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው ነው። ይህንን አሳሳቢ አደጋ ለመቀነስ የመንገድ አጠቃቀም ሥርዓትን መከተል ያስፈልጋል። እግረኞች በመኪና መንገድ ላይ ሲሄዱ ወይም ሲያቋርጡ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል።

ተሽከርካሪዎች በሚበዙባቸው አካባቢዎች ለመጓዝ በእግረኞች የሚደረጉ ጥንቃቄዎች አሉ። በመጀመሪያ እግረኞች፣ ለእግረኛ ተብሎ የተዘጋጀ መንገድ ካለ በዚያ መጠቀም ይኖርባቸዋል። የእግረኛ መንገድ ከሌለ ግን ሁለተኛው አማራጭ የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዞ መጓዝ ነው። ይህም የሚመረጠው ከፊት ለፊት የሚመጣውን መኪና በትኩረት ለማየት ስለሚያስችል ነው። ይህ ዓይነቱ ጥንቃቄ የመኪኖችን አመጣጥ በንቃት ለመከታተል ያስችላል።

የመኪና መንገድ ለማቋረጥም እንዲሁ የሚወሰዱ ጥንቃቄዎች አሉ። በመጀመሪያ ለእግረኛ ማቋረጫ ተብሎ ነጭ ቀለም የተቀባ ቦታ (ዜብራ) ካለ ማየት ያስፈልጋል። በመቀጠልም ማቋረጫው መኖሩ ከተረጋጋጠ መኪኖች ለእግረኞች ቅድሚያ ሰጥተው መቆማቸውን ማረጋገጥ ይገባል። ከዚያም መንገዱን ማቋረጥ ይቻላል። የማቋረጫ ምልክቱ (ዜብራው) በሌለበት ቦታ መኪና መንገዱን ለማቋረጥ በቅድሚያ ግራና ቀኝ መመልከት ይገባል። ከዚያም በቅርብ ርቀት መኪና ከሌለ ፈጥኖ መንገዱን ማቋረጥ ይቻላል። የትራፊክ መብራት ባለበት ቦታ መብራቱ መኪኖችን ሲያስቆም ማቋረጥ ተገቢ ነው። የመኪና መንገድ ለማቋረጥ ሌላው አማራጭ በትራፊክ ፖሊስ በመታገዘ ማቋረጥ ነው።

በአጠቃላይ ውድ ሕይወትንና ክቡር አካልን ላለማጣት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም በእግረኛ መንገድ ወይም ግራ ጠርዝን ይዞ መጓዝ ይገባል። የመንገድን ግራና ቀኝ በመቃኘት በቅርብ መኪና አለመኖሩን አረጋግጦ ማቋረጥም ተገቢ ነው። ይህንን በማድረግ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን መቀነስ ይቻላል።

(ብሔራዊ የመንገድ ደህንነት አስተባባሪ ጽ/ቤት። 1996። ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ለማዳበር የተዘጋጀ መማሪያ(ማጣቀሻ አጋዥ መጽሐፍ) ካሪኩለም ጋይድ፣ ገጽ 28-30 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የመንገድ ላይ አደጋ በሰዎች ላይ ምን ጉዳት እያደረሰ ነው?

ለ. እግረኞች የመንገዱን ግራ ጠርዝ ይዘው እንዲጓዙ የሚመከረው ለምንድን ነው?


ሐ. በምንባቡ ውስጥ በተሽከርካሪዎች የሚደርሱ ጉዳቶች ሙሉበሙሉ ተጠቅሰዋል ማለት ይቻላል? እንዴት ይታወቃል?

መ. የመኪና መንገድን የቀኝ ጠርዝ ይዞ መጓዝ ምን ችግር አለው?

ሠ. የማቋረጫ ምልክቱ በሌለበት ቦታ እግረኞች ከመሻገራቸው በፊት ግራና ቀኝ ሳይመለከቱ ቢሻገሩ ምን የሚያጋጥማቸው ይመስላችኋል?

ተግባር 2

የሚከተለውን የቢጋር ሳጥን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ በምንባቡ አንቀጽ 3 መሠረት እግረኞች መንገድ ሲያቋርጡ የሚያከናውኗቸውን የጥንቃቄ ተግባራት ጻፉ።



2ኛ ቀን

ቃላት

ለቃላትና ለሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ለተሠመረባቸው ቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ምሳሌ፡- እግረኞች፣ ለእግረኛ ተብሎ የተዘጋጀ መንገድ ካለ በዚያ <u>መጠቀም</u> ይኖርባቸዋል።

መልስ፡- *መሄድ፣ ምክንያቱም «የተዘጋጀ መንገድ» የሚለው ሐረግ «መጠቀም» የሚለው ቃል ፍቺ «መሄድ» መሆኑን ይጠቁማል።*

ሀ. የእግረኞች መንገድ ከሌለ የመንገዱን ግራ <u>ጠርዝ</u> ይዞ መጓዝ ይገባል።

ለ. <u>ተሽከርካሪዎች</u> በሚመላለሱባቸው መንገዶች የሚጓዙ እግረኞች መጠንቀቅ አለባቸው።

ሐ. የመኪና መንገድ <u>ለማቋረጥ</u> የሚወሰዱ ጥንቃቄዎች አሉ።

መ. መኪኖች <u>ለእግረኞች</u> ቅድሚያ ሰጥተው መቆማቸውን ማረጋገጥ ይገባል።

ሠ. የመንገዱን ግራና ቀኝ <u>በመቃኘት</u> በቅርብ ርቀት መኪና አለመኖሩን አረጋግጦ ማቋረጥ ይገባል።

ተግባር 2

በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ፍቺ ሳትለውጡ በሚከተሉት ቃላት የራሳችሁን ዐረፍተነገር ሥሩ።

ሀ. ነጭ ሐ. መቆም ሠ. መቃኘት

ለ. ውድ መ. መከተል ረ. ትኩረት

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በቅደምተከተላዊ መረጃ ሰጪ ገላጭ ስልት የቢጋር ሠንጠረዥ ማዘጋጀት

ማስታወሻ፡-


ቅደምተከተላዊ መረጃ ሰጪ ገላጭ ጽሑፍ

ቅደምተከተላዊ መረጃ ሰጪ ገላጭ ጽሑፍ ድርጊቶችን በቅደምተከተል የያዘ ጽሑፍ ነው። ይህንን ለማመልከት መጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ፣ ከዚያ፣ ቀጥሎ፣ ሌላው፣ በመጨረሻና የመሳሰሉትን መሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋት መጠቀም ይገባል።

ተግባር

ከመኝታችሁ ተነስታችሁ ትምህርትቤት እስክምትደርሱ የፈፀማችኋቸውን ድርጊቶች በቢጋር ሠንጠረዥ ውስጥ ዘርዝሩ።

የቢጋር ሠንጠረዥ



የአጻጻፍ ሥርዓት

ዓረፍተነገሮችን በድርጊት ቅደምተከተል ማስተካከል

ተግባር

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ከመነሻ እስከመድረሻ በድርጊት ቅደምተከተል አደራጅታችሁ ጻፉ።

ሀ. አቡሽም በጣም አዘነ።

ለ. በፍጥነት ይሽከረከር በነበረ መኪና ተገጨ።

ሐ. ወደመኪና መንገዱ ሮጦ ገባ።

መ. ውሻው ድንገት ከአቡሽ አመለጠ።

ሠ. አቡሽ ከውሻው ጋር ይሄድ ነበር።

ረ. ሁለቱም የማቋረጫ መንገድ ላይ ሲደርሱ ቆም አሉ።

3ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

የመንገድ ላይ ጥንቃቄ

ቅድመንባብ

ተግባር

ተሽከርካሪዎች በሚበዙባቸው አካባቢዎች ለመጓዝ እግረኞች ምን ምን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ማንበብ

ተግባር

«የመንገድ ላይ ጥንቃቄ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ 2ኛውን አንቀጽ፣ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ማዳመጥ

አርአያነት ያለው ተግባር

ቅድመማዳመጥ

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በትምህርትቤታችሁ የትራፊክ ደህንነት ክበብ አለ? ካለ ምን ምን ተግባራት እያከናወነ ነው?

ለ. የመንገድ ሥርዓትን የማስተማር ኃላፊነት የማን ይመስላችኋል?

የማዳመጥ ሂደት

ተግባር

«አርአያነት ያለው ተግባር» በሚል ርዕስ መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ በንቃት አዳምጡ።

አዳምጠ መረዳት

ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የአምቦ ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ያከናወኑት ተግባር ምንድን ነው?

ለ. የአምቦ አካባቢ ኗሪዎች የመንገድ ሥርዓትን መከተል የቻሉት እንዴት ነው?

ሐ. «እናንተም ይህን መልካም ተግባር ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባችኋል» የተባሉት እነማን ናቸው?

መ. የራሳቸውን ደህንነት የሚጠብቁ ሰዎች የሌሎችን ደህንነት ሊጠብቁ ይችላሉ? እንዴት?

ሠ. ከአምቦ ትምህርትቤት ተማሪዎች የተማራችሁት ቁምነገር ምንድን ነው? እናንተስ ምን ለማድረግ ታስባላችሁ?

ሰዋስው

ሳቢ ግሶች

ተግባር 1

«ወሰደ» የሚለውን ግስ በምሳሌው መሠረት በተለያየ ቅርፅ አርቡ።

ምሳሌ፡- «ሰበረ»

ሰበርኩ	ሰበርን
ሰበርሽ	ሰበራችሁ
ሰበረች	ሰበሩ

ተግባር 2

በምሳሌው መሠረት ክፍት ቦታዎችን በተገቢው ሳቢ ግስ አሟልታችሁ ጻፉ

ምሳሌ፡- እሱ እንጀራ በላ።

ሀ. እሷ ውኃ _____።

ለ. አንተ ቆሎ _____።

ሐ. አንቺ ጋቢ _____።

መ. እነሱ ድራማ _____።

ሠ. እኔ ሙዚቃ _____።

ረ. እኛ ዘፈን _____።

ማንበብ

«...አስቀድሞ መጠንቀቅ»

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስና መገመት

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «... አስቀድሞ መጠንቀቅ» የሚለውን ምሳሌያዊ አባባል አሚለ።

ለ. ሥዕሉን በደንብ አስተውሉና የተረዳችሁትን ተናገሩ።

ሐ. በሥዕሉና በርዕሱ መካከል ምን ዓይነት ዝምድና ያለ ይመስላችኋል? እንዴት ይታወቃል?

የማንበብ ሂደት

ተግባር

«...አስቀድሞ መጠንቀቅ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ በአዕምሯችሁ ምሥል እየፈጠራችሁ አንብቡ።



ሶፊያ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን ከወላጆቿ ጋር ሆና ተማረች። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ደግሞ ራቅ ወደአለ ከተማ ሄዳ ቀጠለች። የምትኖረውም ከጓደኞቿ ጋር ቤት ተከራይታ ነው። በትምህርቷ ጎበዝ፣ በአናኗሪ ጠንቃቃ ናት። ሁልጊዜ አርብ አርብ ወደወላጆቿ ቤት በመሄድ የሳምንት ስንቋን ይዛ እሁድ ትመለሳለች።

ሶፊያ የከተማ ኑሮ እንደጀመረች ሁኔታው ግር አላት። የምታየው ነገር ሁሉ አዲስ ሆነባት። ብዛቱን አይታው የማታውቀው የጭነት መኪናዎች ወደከተማ ይገባሉ፣ ይወጣሉ። ጋሪዎችና ብስክሌቶችም በብዛት ይተራመሳሉ። መኪናዎች እግረኞችን ይገጫሉ። ጋሪ የሚጎትቱ ፈረሶችና በቅሎዎችም በመደንበር በመንገደኞች ላይ አደጋ ያደርሳሉ። ብስክሌት የሚነዱ ሕጻናትና ወጣቶች በፍጥነት ሲነዱ እግረኞች ይጎዳሉ። ሶፊያ በየቀኑ ከባድና ቀላል ድንገተኛ አደጋዎችን ታያለች፣ ይህም ያስደነግጣታል፣ ያስጨንቃታል። ስለሆነም ለችግሩ መፍትሔ መፈለግ እንዳለባት ተረዳች።

መኪኖች እግረኞችን ይገጫሉ ጋሪ የሚጎትቱት ፈረሶችና በቅሎዎችም በመደንበር በመንገደኞች ላይ አደጋ ያደርሳሉ

ሶፊያ ችግሩን ለመቀነስ በመጀመሪያ የማኅበረሰብ አገልግሎት ለመስጠት ወሰነች። በመቀጠልም «ችግሩ ሊቃለል የሚችለው ምን ቢደረግ ነው?» የሚል ጥያቄ አነሳች። ከዚያም መፍትሔ ይሆናሉ ያለቻቸውን ዝርዝር ሀሳቦች መዘገበች።

ባቀደችው መሠረትም ሥራዋን ቀጠለች። ቀዳሚ ያደረገችው ተግባር ጓደኞቿ ችግሩን እንዲገነዘቡት ማድረግ ነበር። ከዚያም የትምህርትቤቷ ተማሪዎች አደጋ እንዳይደርስባቸው ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አስተማረች። በመቀጠልም ፈቃደኛ የሆኑ ጓደኞቿን አስተባብራ ኗሪዎችን ስለመንገድ አጠቃቀም አስገነዘበች። በመጨረሻም ብስክሌትና ጋሪ የሚነዱትን ሕጻናትና ወጣቶች በመሰብሰብ ግንዛቤ አስጨበጠች።


ከዚህ ሁሉ ጥረት በኋላ ዓላማዋ ተሳክቶላት የአደጋው መጠን ቀነሰ። የከተማዋ ኗሪዎችና ጓደኞቿም ዕድሜ ለሶፊያ እያሉ አመሰገኗት። አደጋ እንዳይደርስ መፍትሔው አስቀድሞ መጠንቀቅ መሆኑን ተገነዘቡ።

(ብሔራዊ የመንገድ ደህንነት አስተባባሪ ጽ/ቤት። 1996። ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ለማዳበር የተዘጋጀ መማሪያ (ማጣቀሻ አጋዥ መጽሔት ካሪኩለም ጋይድ፣ ገጽ 38 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

ቀጥሎ የቀረበውን የቢጋር ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጁ። ከዚያም ስለሶፊያ ከምንባቡ ውስጥ ያገኛችኋቸውን መረጃዎች በአራቱ ሣጥኖች ውስጥ ሙሉ።



ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «ሶፊያ ችግሩን ለመቀነስ በመጀመሪያ የማኅበረሰብ አገልግሎት ለመስጠት ወሰነች» በሚለው ዓረፍተነገር፣ ችግሩ የተባለው ምንድን ነው?

ለ. ምንባቡ «ከዚህ ሁሉ ጥረት በኋላ ዓላማዋ ተሳካ» ይላል። ዓላማዋ ምን ነበር?

ሐ. ሶፊያ በምትኖርበት ከተማ የቄጠላ መኪናዎች ሲጠቀሱ ሌሎች የመኪና ዓይነቶች ያልተጠቀሱት ለምንድን ነው?

5ኛ ቀን

ቃላት

ለቃላትና ለሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት

ተግባር 1

ለሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምሳሌው መሠረት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ፈልጉ።

ምሳሌ

1. ግር አላት = ተደናገራት
2. ተቃለለ = ቀነሰ

ሀ. ስንቅ ሐ. መፍትሔ ሠ. በመደንበር ሰ. ይተራመሳሉ

ለ. ጠንቃቃ መ. ቀዳሚ ረ. አስገነዘበች

ተግባር 2

በተግባር 1 ከሀ-ሰ ከቀረቡት ቃላት እየመረጣችሁ የሚከተሉትን የተጓደሉ ዓረፍተነገሮች አሟሉ።

ሀ. ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ አፋጣኝ _____ መፈለግ ብልህነት ነው።

ለ. ጎበዟ ተማሪ ያነበበችውን ምንባብ ዋና ሀሳብ ለጓደኞቿ_____።

ሐ. ከብዙ ተማሪዎች ጋር ተወዳድሮ _____ ለመሆን ጥረት ማድረግ ይገባል።

መ. _____ ተማሪዎች መጽሐፎቻቸውን ሸፍነው ይይዛሉ።

ሠ. ለአንድ ሳምንት የሚበቃ _____ አዘጋጀች።

ረ. በመኪና መንገድ ላይ የሚጓዙ የጋማ ከብቶች _____ በሰዎች ላይ አደጋ ያስከትላሉ።

ሰ. በግቢው ውስጥ በርካታ ሰዎች _____።

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በድርጊት ቅደምተከተል ስልት አንቀጽ መጻፍ

ተግባር

ባለፈው ሳምንት ያዘጋጃችሁትን ቅደምተከተላዊ የቢጋር ሠንጠረዥ መነሻ በማድረግ አንቀጽ ጻፉ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

የዓረፍተነገሮችን ቅደምተከተል ማስተካከል

ተግባር

ከዚህ በታች የሀሳብ ቅደምተከተላቸው ተዛብቶ የቀረቡትን ዓረፍተነገሮች አስተካክላችሁ ጻፉ።

ሀ. ሁሉም ተማሪ ወደትምህርትቤት ከገባ በኋላ እሷም ገባች።

ለ. የትራፊክ ፖሊስ መለዮዋንም በክበቡ ቢሮ ውስጥ አስቀመጠች።

ሐ. ስለዚህ በጧት ተነስታ የደንብ ልብሷን ለበሰች።

መ. አሚና የተማሪ የትራፊክ ፖሊስ ናት።

ሠ. ከዚያም በትምህርትቤቱ አቅራቢያ ወደሚገኘው መስቀለኛ መንገድ ሄደች።

ረ. ቀጥላ ተማሪዎች በጥንቃቄ መንገዱን እንዲያቋርጡ ስትረዳ ቆየች።

ሰ. በመጨረሻም ወደመማሪያ ክፍሏ ገባች።

6ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

«...አስቀድሞ መጠንቀቅ»

ቅድመንባብ

ተግባር

«... አስቀድሞ መጠንቀቅ» በሚል ርዕስ ያነበባችሁትን ምንባብ ዋና ሀሳብ በአጭሩ በቃላችሁ ግለጹ።

ማንበብ

ተግባር

«...አስቀድሞ መጠንቀቅ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ 3ኛውን አንቀጽ በቡድን ሆናችሁ ድምፃችሁን እያሰማችሁ አንብቡ።

መናገር

የድርጊቶች ቅደምተከተልን ጠብቆ መናገር

ተግባር

ትናንትና ከትምህርትቤታችሁ ተነስታችሁ እቤታችሁ እስከምትደርሱ ድረስ ያከናወናችኋቸውን ተግባራት በቅደምተከተል አዋቅራችሁ ለቡድን አባሎቻችሁ ተናገሩ።

ሰዋስው

ሳቢ ግሶች

ተግባር

«ገዛ» የሚለውን ግስ በተለያየ ቅርፅ እያስተካከላችሁ የተጓደሉትን ዓረፍተነገሮች በምሳሌው መሠረት አሟሉ።

ምሳሌ፡- ሸጠ

1. እሷ ሁለት ኪሎ ሙዝ _____።

   እሷ ሁለት ኪሎ ሙዝ ሸጠች።

2. እሱ አምስት መጽሐፎች _____።

   እሱ አምስት መጽሐፎች ሸጠ።

   ሀ. እኔ አሮጌ መጽሐፍ _____።

   ለ. እኛ አዲስ ልብስ _____።

   ሐ. አንተ ባለ 50 ሉክ ደብተር _____።

   መ. እናንተ ብዙ እርሳስ _____።

   ሠ. እነሱ አረንጓዴ ቦርሳ _____።

   ረ. አንቺ ላጲስ _____።

የመጀመሪያ እርዳታና በድንገተኛ አደጋ ጊዜ የሚወሰዱ እርምጃዎች

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ተግባር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	ኑሮ-ኣችው-ን	ኑሯቸውን
ለ	ባለ-ሙ-ያ-ዎች	ባለሙያዎች
ሐ	መገላጠሚ-ያ-ዎች	መገላጠሚያዎች
መ	በሚጫወት-ኡ-ብ-ኧት	በሚጫወቱበት
ሠ	የሚ-ያ-ስፈልግ-ኧው	የሚያስፈልገው
ረ	በሚሯሯጥ-ኡ-ብ-ኧት	በሚሯሯጡበት
ሰ	ነ-ር-ቮ-ች	ነርቮች
ሸ	ሆ-ስ-ፒ-ታ-ል	ሆስፒታል

ማንበብ

በድንገተኛ አደጋ ጊዜ የሚወሰድ እርምጃ

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ድንገተኛ አደጋ ምንድን ነው?

ለ. እስከዛሬ የሰማችኋቸውን ወይም ያያችኋቸውን ድንገተኛ አደጋዎች ጥቀሱ።

የማንበብ ሂደት

ተግባር

«በድንገተኛ አደጋ ጊዜ የሚወሰድ እርምጃ» የሚለውን ምንባብ የድርጊቶችን ቅደምተከተል እያስተዋላችሁና ምሥል እየፈጠራችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

በድንገተኛ አደጋ ጊዜ የሚወሰድ እርምጃ

ሰዎች የዕለት ኑሯቸውን ለማሟላት በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች በርካታ አደጋዎች ያጋጥሟቸዋል። በመኪና ሲጓዙ ጉዳት ሊደርስባቸው ይችላል። የመኪና መንገድ ሲያቋርጡ በጥንቃቄ ጉድለት አደጋ የሚደርስባቸው በርካታ ናቸው። ከዛፍ ላይ ወድቀው የሚጎዱም አሉ። ከገደል ውስጥ ወድቀው ከፍተኛ ጉዳት የሚደርስባቸው አሉ። በተለይም ሕጻናት ለጨዋታ በሚሯሯጡበት ጊዜ በተደጋጋሚ የጉዳት ሰለባ ይሆናሉ። ከላይ በተጠቀሱትና በመሳሰሉት ሁኔታዎች በሚፈጠሩ አደጋዎች ከፍተኛ የደም መፍሰስ ይከሰታል። የአጥንት ስብራትና ውልቃት ይደርሳል። እነዚህን የመሳሰሉ ጉዳቶች በሚደርሱበት ጊዜ የመጀመሪያ ዕርዳታ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ቀጥለን የአከርካሪና የዳሌ አጥንት ስብራት እንዲሁም የአጥንት ውልቃትን የመጀመሪያ ዕርዳታ አሠጣጥ እንመለከታለን።

በድንገተኛ አደጋ ምክንያት ከሚፈጠሩት ጉዳቶች መካከል አንዱ የአከርካሪ አጥንት ስብራት ነው። አከርካሪ ከጭንቅላት የታችኛው ክፍል እስከ መቀመጫ የላይኛው ክፍል ያሉትን አጥንቶች ያካትታል። የሰውነትን አቋም አስተካክሎ ለመጠበቅና በውስጡ የሚያልፉትን ታላላቅ ነርቮች ከጉዳት ለመጠበቅ ያስችላል። የአከርካሪ አደጋ የደረሰባቸውን ሰዎች ከወደቁበት ለማንሳት ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ አለበት። የጉዳተኞቹን እጅና እግር ጎትቶ ማንሳት በጭራሽ የተከለከለ ነው። መጀመሪያ በጉዳተኞቹ ቁመት ልክ የሆነ ደረቅ ጣውላ ማቅረብ ይገባል። ቀጥሎ ጉዳተኞቹን በዝግታ ከብለል አድርጎ በጣውላው ላይ ማስተኛት ያስፈልጋል። ከዚያም ጉዳተኞቹን በማይንቀሳቀስ (በማያረገርግ) አልጋ ወይም ወንበር ላይ አድርጎ ወደሆስፒታል መውሰድ ተገቢ ነው።

ሌላው የመጀመሪያ ዕርዳታ የሚያስፈልገው ጉዳት የዳሌ አጥንት ስብራት ነው። የዳሌ አጥንት አከርካሪን ከእግር አጥንቶች ጋር የሚያገናኝ ዋንጫ መሰል አጥንት ነው። ፊኛን፣ ትልቅ አንጀትንና ማህፀንን አቅፎ ይይዛል። የዳሌ አጥንት ስብራትን ተከትሎ ከፍተኛ መጠን ያለው ደም መፍሰስ ሊከሰት ይችላል። ይህም በደም ማነስ ምክንያት ራስን ያስትና ለሞት ያደርሳል። በመሆኑም ፈጥኖ ዕርዳታ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህም በቅድሚያ የጉዳተኞችን ሁለት እግሮች ማሰር ነው። ከዚያ በኋላ በፈጣን ማጓጓዣ ወደሕክምና ቦታ መውሰድ ይገባል።

የአጥንት ውልቃት ጉዳት ሌላው የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ የሚያስፈልገው ነው። የአጥንት ውልቃት በሰውነታችን ውስጥ የሚገኙት መገጣጠሚያዎች አቋማቸው በሚዛባበት ወቅት ይፈጠራል። ችግሩ ያጋጠማቸውን ሰዎች በዘፈቀደ ማንቀሳቀስ አያስፈልግም። አስቀድሞ የመገጣጠሚያ አጥንቶችን ጠበቅ አድርገን

ማሰር ይኖርብናል። ይህንንም የምናደርገው ከላይና ከታች ከአንድ ወጥ እንጨት ጋር በማሰር ይሆናል። ከዚህ በኋላ ጉዳተኞቹን ወደሕክምና ቦታ መውሰድ ይኖርብናል።

ከላይ የተዘረዘሩት ጉዳቶች የደረሰባቸው ሰዎች የመጀመሪያ የሕክምና ዕርዳታ ማግኘት አለባቸው። የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ ከተደረገላቸው በኋላ ጉዳተኞቹን ወደሀኪምቤት መውሰድ ይገባል። ምክንያቱም የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ ዓላማ የበሽተኞቹን ጉዳትና ስቃይ መቀነስ እንጂ ዘላቂ ሕክምና አይደለም። ዘላቂ ሕክምናና መፍትሄ የሚገኘው በሀኪምቤትና በባለሙያዎች ብቻ ነው።

(ሜዲካል፣ 2ኛ ዓመት፣ ቁ. 27። ግንቦት 1999 ዓ.ም.። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

1. ከሚከተሉት አንዱ በአንቀጽ አንድ ውስጥ ከተጠቀሱት ጉዳቶች መካከል አይመደብም።

   ሀ. የደም መፍሰስ
   ሐ. የአጥንት ውልቃት
   ለ. የአጥንት ስብራት
   መ. የደም መርጋት

2. አንቀጽ ሁለት ውስጥ እንደተገለፀው የአከርካሪ አጥንት አገልግሎት ምንድን ነው?

   ሀ. የደም ዝውውርን መቆጣጣር
   ለ. ሥርዓተ ልመትን ማገዝ
   ሐ. የሰውነትን አቋም መጠበቅ
   መ. አከርካሪንና ዳሌን ማገናኘት

3. የአከርካሪ ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ስናነሳ መደረግ <u>የሌለበት</u> ምንድን ነው?

   ሀ. የጉዳተኞችን እጅና እግር ጎትቶ ማንሳት፣
   ለ. በጉዳተኞች ቁመት ልክ ደረቅ ጣውላ ማቅረብ፣
   ሐ. ጉዳተኛውን በዝግታ ከብለል አድርጎ ጣውላው ላይ ማስተኛት፣
   መ. ጉዳተኛውን በማያረገርግ አልጋ ላይ ማስተኛት፣

4. ዋንጫ መሰል በሆነው የዳሌ አጥንት ሥር የሚገኘው የሰውነት ክፍል የትኛው ነው?

   ሀ. ሳንባ
   ሐ. ትልቅ አንጀት
   ለ. ልብ
   መ. እንጥል

5. የአጥንት ውልቃት የሚፈጠረው እንዴት ነው?

ሀ. መገጣጠሚያዎች አቋማቸው ሲዛባ፣

ለ. ጅማቶች ሲቆረጡና ብዙ ደም ሲፈስ ፣

ሐ. አጥንት ሲሰበርና ማገገም ሲያቅተው፣

መ. ከፍተኛ ቁስለት ሲደርስ፣

ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የደም መፍሰስ ሲኖር ፈጥኖ የመጀመሪያ የሕክምና ዕርዳታ መደረግ ያለበት ለምንድን ነው?

ለ አንቀጽ አንድ ላይ ከተጠቀሱት ጉዳቶች ውጪ ሌሎች ጉዳቶች አሉን? አሉ ካላችሁ ዘርዝሯቸው።

ሐ.የአከርካሪ አጥንት ስብራት የደረሰበትን ሰው ወደሕክምና ቦታ ለመውሰድ ጣውላ እንጨት እንደሚያስፈልግ ተገልጿል፣ ጣውላ ባይገኝስ ምን ማድረግ አለብን?

መ.የዳሌ አጥንት ስብራት የደረሰባቸው ሰዎች ወደሕክምና ስፍራ ሲጓጓዙ ሁለት እግሮቻቸው መታሰር ያለባቸው ለምንድን ነው?

8ኛ ቀን

ቃላት

ለቃላትና ለሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት

ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ መሠረት ያላቸውን ዐውዳዊ ፍቺ በጽሑፍ ግለጹ።

ሀ. አቅፎ

ለ. መጠበቅ

ሐ. ማንሳት

መ. መውሰድ

ሠ. ሲያቋርጡ

ረ. በዘፈቀደ

ተግባር 2

ከላይ በቀረቡት ቃላት ከምንባቡ ውጪ ያላቸውን ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በቅደም ተከተል ስልት አንቀጽ መጻፍ

ተግባር

መምህራችሁ በሚሠጧችሁ መመሪያ መሠረት ደብተራችሁን ተቀያይራችሁ አስተያየት ተሰጣጡ። ከዚያም በተሰጣችሁ አስተያየት መሠረት አስተካክላችሁ ጻፉ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

ተግባር

ዓረፍተነገሮችን በድርጊት ቅደምተከተል ማስተካከል

የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች በድርጊት ቅደምተከተላቸው መሠረት አስተካክላችሁ ጻፉ።

ሀ. ሹፌሩም ልጁ እንደታመመበት በመግለፅ ይቅርታ እንድታደርግለት ተማፀናት።

ለ. ሹፌሩ የልጁ መታመም በስልክ ተነገረው።

ሐ. ወዲያው ትራፊክ ፖሊሷ በሞተር ሳይክል ተከታትላ አስቆመችው።

መ. በመጨረሻ መኪናውን ወደቤት አስፈተለካት።

ሠ. ፖሊሷ ግን የመንጃ ፈቃዱን መዝግባ በማግስቱ ፖሊስ ጽሕፈትቤት እንዲቀርብ ነገረችው።

ረ. በጣም ከመቸኮሉ የተነሳ ቀይ መብራት ጥሶ አለፈ።

ሰ. ወደልጁ እንዲሄድ ፈቀደችለት።

9ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

በድንገተኛ አደጋ ጊዜ የሚወሰድ እርምጃ

ቅደመንባብ

ተግባር

«በድንገተኛ አደጋ ጊዜ የሚወሰድ እርምጃ» በሚለው ምንባብ ውስጥ የተጠቀሱት ሦስቱ በድንገተኛ አደጋ ምክንያት የሚፈጠሩት ጉዳቶች ምን ምን ናቸው?

ማንበብ

ተግባር

ከ4-6 አባላት ያሉት ቡድን መሥርቱ ። «በድንገተኛ አደጋ ጊዜ የሚወሰድ እርምጃ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ 2ኛውን አንቀጽ በቡድን ድምፃችሁን እያሰማችሁ አንብቡ።

መናገር

ቅደምተከተልን ጠብቆ መናገር

ተግባር

የአከርካሪ አጥንት አደጋ፣ የዳሌ አጥንት ስብራትና የአጥንት ውልቃት ለደረሰባቸው ሰዎች በመጀመሪያ ዕርዳታ ወቅት መደረግ ያለባቸውን ጥንቃቄዎች ከምንባቡ ባገኛችሁት መረጃ መሠረት በቅደምተከተል እየተቀባበላችሁ ተናገሩ።

ሰዋስው

ሳቢ ግስ

ተግባር

በቅንፍ ውስጥ ያሉትን ግሶች በተስማሚ ቅርፅ በመቀየር ዓረፍተነገሮቹን አስተካክላችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

1. ልጂቱ ጋዜጣ (ቀደደ)።
   ልጂቱ ጋዜጣ ቀደደች።
   ሀ. እነአንሻ ቁርሳቸውን (በላ)።
   ለ. ተመስገን ቡና(ወቀጠች)።
   ሐ. ድመቷ ወተት (ጠጣ)።
   መ. እኛ እንጨት (ሰበረ)።
   ሠ. አንቺ ደብዳቤ (ጻፈ)።

2. እነ ከድር ልብሳቸውን (አጠበ)።
   እነ ከድር ልብሳቸውን አጠቡ።



ምዕራፍ 5

ጽዳትና ንጽህና

ጽዳት

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ተግባር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	መጠበቅ-አ_ያ	መጠበቂያ
ለ	እንደ-አይራቡ	እንዳይራቡ
ሐ	ንጽህና-ው-ን	ንጽህናውን
መ	በ-ተጨማሪ_ም	በተጨማሪም
ሠ	የ-ወደቀ-ው-ን	የወደቀውን
ረ	የሚ-ወጣ-ው-ን	የሚወጣውን
ሰ	የሚ_ያደርግ-አ-ኣቸው	የሚ_ያደርጓቸው

ማንበብ

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስና መገመት

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በአካባቢያችሁ ቆሻሻ እንዴት ይወገዳል?

ለ. ሁለቱን ሥዕሎች አስተውሉና ስለምን እንደሚገልፁ ተናገሩ።

ሐ. የምንባቡን ርዕስና ሥዕሎችን በማገናዘብ ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

የማንበብ ሂደት

ተግባር

ቀጥሎ « ...ማቃጠል ወይስ መቅበር...?» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ በግል አንብቡ።

...ማቃጠል ወይስ መቅበር ...?





ማንኛውም ሰው ደስ ብሎትና ጤነኛ ሆኖ መኖር ይፈልጋል። ለዚህም የግልንና የአካባቢን ንፅህና መጠበቅ ያስፈልጋል። የግልንና የአካባቢን ንፅህና ለመጠበቅ የተለያዩ ስልቶችን መጠቀም ይቻላል። ለምሳሌ ልብስን በማጠብ፣ ሰውነትን በመታጠብ፣ የመኖሪያ ግቢን በመጥረግ፣ ወዘተ. የግል ንጽህናን መጠበቅ ይቻላል። በሌላ በኩል ቆሻሻን በጋራ ሰብስቦ በመቅበር ወይም በማቃጠል የአካባቢን ጽዳት መጠበቅ ይቻላል።

ቆሻሻን ማቃጠልና መቅበር በግልና በጋራ ሊከናወን ይችላል። በግል ወይም በጋራ ከየቤቱ የሚወጣውንና በየቦታው የሚገኘውን ቆሻሻ በመሰብሰብ ማቃጠል ይቻላል። ቆሻሻ መቅበር ከየቤቱ የሚወጣውንና በየቦታው የወደቀውን ቆሻሻ ሰብስቦ በጉድጓድ ውስጥ በመጨመር አፈር ማልበስ ነው። በዚህ ዘዴ በመጠቀም አካባቢን ጽዱና ማራኪ ማድረግ ይቻላል። በሽታ አምጪ ህዋሳት እንዳይራቡ ማድረግ የሚቻለው አካባቢን በማጽዳት ነው። በዚህም የበሽታን ምንጭ ማድረቅ ስለሚቻልና በሽታ በቀላሉ ስለማይዛመት ሰዎች ጤነኛ ይሆናሉ።

ቆሻሻን ማቃጠል ሌላ ቆሻሻ ይፈጥራል?

ቆሻሻን ማቃጠልና መቅበር ልዩነት አላቸው። አንደኛ፣ ቆሻሻ ማቃጠል አየር ይበክላል። ጪሱ በአካባቢው ካለው አየር ጋር በመቀላቀል ንጽህናውን ያሳጣዋል። ቆሻሻ ሲቀበር ግን ጪስ ስለማይፈጠር አየር አይበከልም። ሁለተኛ፣ ቆሻሻን ማቃጠል ብዙ ጊዜና ከፍተኛ ጉልበት አይጠይቅም። በአጭር ጊዜ ውስጥ በአንድ ሰው ብቻ ይከናወናል። ቆሻሻን መቅበር ቆሻሻን ከማቃጠል ጋር ሲወዳደር የበለጠ ጊዜና ጉልበት ይጠይቃል። ሦስተኛ፣ ቆሻሻን በማቃጠል ሌላ ቆሻሻ ይፈጠራል። የማይበሰብሱና

አፈርን የሚበክሉ ቆሻሻዎችን ለይቶ መቅበር ግን ሌላ ቆሻሻ አይፈጥርም። እንዲያውም ሰውሠራሽ ማዳበሪያ ያስገኛል። በማቃጠል ሊወገዱ የማይችሉ ቆሻሻዎችን በመቅበር ማስወገድም ይቻላል።

በአጠቃላይ ቆሻሻን ለማጥፋት ሌላ ቆሻሻ ከመፍጠር ቆሻሻን በመቅበር መጠቀም ይበጃል። ስለዚህ ቆሻሻን ከማቃጠል ቆሻሻን መቅበር ይሻላል።

(ኮድ ኢትዮጵያ። 2004። *የአካባቢ እንክብካቤ አጠባበቅ*። መነሻነት የተጻፈ)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተሉትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የአካባቢና የግል ንጽህና በመጠበቅ ምን ይገኛል?

ለ. የግል ንጽህና ምን ምን ነገሮችን ያጠቃልላል?

ሐ. አካባቢን ለማጽዳት ቆሻሻን ምን ማድረግ ይጠበቃል?

መ. ቆሻሻን መቅበር ቆሻሻን ከማቃጠል በምን ይለያል?

ሠ. ቆሻሻን መቅበር ብዙ ጊዜና ጉልበት የሚጠይቀው በምን ምክንያት ነው?

ረ. ቆሻሻን ማቃጠል ምን ጉዳት አለው?

ሰ. በማቃጠል ሊወገዱ የማይችሉ የተባሉት ምን ምን ዓይነት ቆሻሻዎች ሊሆኑ ይችላሉ?

ሸ. ቆሻሻን በማቃጠል ሌላ ቆሻሻ የሚፈጠረው እንዴት ነው?

ቀ. በቀረበው ርዕሰጉዳይ ላይ የጸሐፊው/ዋ አመለካከት ምን ይመስላችኋል? በምን አወቃችሁ?

ተግባር 2

የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጁ። ከዚያም የምንባቡን የመከራከሪያ ሀሳብና ሀሳቡን ለማጠናከር የቀረቡትን ማስረጃዎች በሠንጠረዡ ውስጥ ዘርዝሩ። ቀጥሎ የመከራከሪያ ሀሳቦቹ ትክክል ወይም ስህተት መሆናቸውን ለይታችሁ አመልክቱ።

የመከራከሪያ ሀሳብ	ማስረጃ	እውነት፣ ሐሰት
ቆሻሻን መቅበር ይሻላል	ቆሻሻ ከተቀበረ አየር አይበክልም	እውነት

2ኛ ቀን

ቃላት

ለቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት

ተግባር 1

በ«ሀ» ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት በምንባቡ መሠረት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከ«ለ» ረድፍ በመምረጥ አዛምዳችሁ ጻፉ።

ሀ	ለ
1. አምጪ	ሀ. መደባለቅ
2. ማዳፈን	ለ. ማባዛት
3. ማራባት	ሐ. መቅበር
4. መዛመት	መ. አስተላላፊ
5. መቀላቀል	ሠ. መተላለፍ

ተግባር 2

በ«ሀ» ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት በምንባቡ መሠረት ተቃራኒያቸውን ከ«ለ» ረድፍ በመምረጥ አዛምዳችሁ ጻፉ።

ሀ	ለ
1. ፅዱ	ሀ. ተፈጥሯዊ
2. ግቢ	ለ. አስቀያሚ
3. ማራኪ	ሐ. ውጪ
4. ወደቀ	መ. ተነሳ
5. በጋራ	ሠ. በግል
6. ሰውሠራሽ	ረ. ቆሻሻ

ድርሰት መጻፍ


በማወዳደርና በማነፃፀር ስልት የቢጋር ሠንጠረዥ ማዘጋጀት

ማስታወሻ፡-

ማወዳደርና ማነፃፀር፡- ማወዳደር በሁለት የተለያዩ ነገሮች መካከል ያለውን ተመሳሳይነት ማሳየት ነው። ማነፃፀር ደግሞ በተመሳሳይ ነገሮች መካከል ያለውን ልዩነት በመግለጽ ላይ ያተኩራል። ቀጥሎ የቀረበው ተግባር ነገሮችን ለማወዳደርና ለማነፃፀር ጠቃሚ ነው።

ተግባር

በደብተራችሁ እንስሳትና ዕፅዋት የሚጋሯቸውንና የሚለያዩባቸውን ለማሳየት የሚያስችል የቢጋር ሠንጠረዥ አዘጋጁ። ከዚያም የእንስሳትንና የዕፅዋትን ተመሳሳይነት ሁለቱ ክቦች በሚጋሩት መካከለኛው ክፍል ውስጥ ዘርዝሩ። የእንስሳትን ልዩ ባህርያት በአንደኛው ክብ፣ የዕፅዋትን ደግሞ በሌላኛው ክብ ውስጥ ዘርዝሩ።



የአጻጻፍ ሥርዓት

የቃል ጽሕፈት

ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቃላት በትክክል እያዳመጣችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።

3ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

...ማቃጠል ወይስ መቅበር...?

ቅድመንባብ

ተግባር

ባለፈው ክፍለጊዜ ባነበባችሁት ምንባብ መሠረት ቆሻሻን ከማቃጠልና ከመቅበር የትኛው ይሻላል? ለምን? አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ማንበብ

ተግባር

«...ማቃጠል ወይስ መቅበር ...?» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የመጀመሪያዎቹን ሦስት አንቀጾች መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ተራበተራ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ማዳመጥ

የግልንና የአካባቢን ንጽህና መጠበቅ

ቅድመማዳመጥ

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ንጽህና ሲባል ምን ማለት ነው?

ለ. ንጽህናን አለመጠበቅ ምን ጉዳት ያለው ይመስላችኋል?

ሐ. የአካባቢያቸውንና የግል ንጽህናቸውን በሚጠብቁና በማይጠብቁ ሰዎች መካከል ምን ዓይነት ልዩነቶችን መጥቀስ ይቻላል?

የማዳመጥ ሂደት

ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን የማዳመጥ ምንባብ ተመሳስሎዎችና ልዩነቶችን እያስተዋላችሁ አዳምጡ።

አዳምጠ መረዳት

ተግባር 1

በአዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ንጽህናን የመጠበቂያ መንገዶች የተባሉት ምንና ምን ናቸው?

ለ. በሽታ እንዳይዛመት እንደመከላከያ የተወሰደው ዘዴ ምንድን ነው?

ሐ. የግልና የአካባቢን ንጽህና ተመሳሳይነትና ልዩነት አብራሩ።

መ. የሚቀበሩ ቆሻሻዎች አካባቢን የመበከል አቅም አላቸውን? ለምን?

ሠ. የሰዎች እንቅስቃሴና የአካባቢ መቆሸሽ ምን ግንኙነት አላቸው?

ተግባር 2

ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት እየመረጣችሁ ባዶ ቦታዎችን በትክክል አሟሉ።

ማስወገድ	ማስረጊያ	መላጨት
መቁረጥ	ማፍሰሻ	መዛመት

ሀ. በግቢያችን ውስጥ የፍሳሽ ቆሻሻ _____ ጉድጓድ አዘጋጀን።

ለ. ቆሻሻን በአግባቡ _____ አካባቢን ጽዱና ውብ ያደርጋል።

ሐ. በቆሻሻ ስፍራ የሚራቡ ዝንቦች ለበሽታ _____ አመቺ ሁኔታ ይፈጥራሉ።

መ. የፀጉርን ንጽህና ለመጠበቅ በምላጭ _____ አንዱ ዘዴ ነው።

ሠ. የፀጉርን ንጽህና ለመጠበቅ በመቀስ _____ ይቻላል።

ረ. በግቢዬ ውስጥ የቆሻሻ _____ ቦይ ቆፈርኩ።

ሰዋስው

ቅጽል

ተግባር

ከዓረፍተነገሮቹ ስር የቀረበውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጁ።ከዚያም ቅጽሎችን ከዐረፍተነገሮች ውስጥ እየለያችሁ በሠንጠረዡ ውስጥ ጻፉ። ቀጥሎም የሚገልጹትን ነገር የ«✓» ምልክት በማድረግ አመልክቱ።

ሀ. በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀመጥን።

ለ. ሱዳናዊ አርሶአደር ተዋወቅሁ።

ሐ. አረንጓዴ ቀሚስ ገዛሁ።

መ. አያሌ ሰዎች ተሰበሰቡ።

ሠ. ጠፍጣፋ ድንጋይ ለመቀመጫ አዘጋጀሁ።

ረ. ደግ ሴት የተቸገረ ሰው ትረዳለች።

ሰ. ሀቀኛ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን ይወዳሉ።

ሸ. ወፍራሙ ነጋዴ ሱቅ ውስጥ ቁጭ ብሏል።

ቅጽሉ	የሚገልፀው ነገር				
	ቀለም/መልክ	መጠን	ባህርይ	ቅርፅ	ወገን
ክብ				✓	
ሱዳናዊ					✓

ማንበብ

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስና መገመት

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሰዎች ምሥጋና የሚያቀርቡት ምን ሲደረግላቸው ወይም ምን ሲያገኙ ነው?

ለ. ሥዕሉን ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን ተናገሩ።

ሐ. «ምሥጋና ለጓደኛዬ» በሚለው ርዕስና በሥዕሉ መካከል ያለው ዝምድና ምን ይመስላችኋል?

የማንበብ ሂደት

ተግባር

«ምሥጋና ለጓደኛዬ» የሚለው ምንባብ በማወዳደርና በማነፃፀር የቀረበ ነው። ስለዚህ በታሪኩ ውስጥ ያሉትን ገፀባህርያት ተመሳሳይነትና ልዩነት እያስተዋላችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ።

ምሥጋና ለጓደኛዬ









በአንድ ሠፈር ውስጥ አንዲት ሴትና አንድ ወንድ ልጅ ከቤተሰባቸው ጋር ይኖራሉ። ሁለቱም በተቀራራቢ የዕድሜ ክልል ውስጥ ናቸው። ወደትምህርትቤት ሲሄዱም ሆነ ሲመለሱ አይለያዩም። ሁለቱ ልጆች በብዙ ነገሮች ይግባባሉ። በግል ንጽህና አጠባበቃቸውና በትምህርት አቀባበላቸው ግን ልዩነት አላቸው።

ሴቷ ልጅ በትምህርቷ ጉብዝናና በግል ንጽህና አጠባበቋ ትታወቃለች። «አዘውትሬ የግል ንጽህናዬን ከጠበቅሁ ጤነኛ እሆናለሁ፤ በትምህርቴም ጎበዝ እሆናለሁ» ትላለች። በእውነትም ለግል ንጽህናዋ ከፍተኛ ትኩረት ትሰጣለች። ዘወትር በጧት ከመኝታዋ ተነስታ ወደመፀዳጃ ቤት ትሄዳለች። ከመፀዳጃቤት ደርሳ ስትመለስም እጇን በሳሙና ትታጠባለች። ምግብ ከመመገቧ በፊትና ከተመገበች በኋላ እጇን በሳሙናና በውኃ ትታጠባለች። ወደትምህርትቤት ከመሄዷ በፊት በየቀኑ ፀጉሯን አበጥራ ትጎንጉናለች። ሁልጊዜ በየሦስት ቀኑ ፀጉሯን ትታጠባለች። በየሳምንቱ ቅዳሜ ልብሷን አጥባ ትተኩሳለች፤ ሰውነቷንም ትታጠባለች። የእጅና እግር ጥፍሯን ትቆርጣለች። በየቀኑ የመኝታ ክፍሏን ታፀዳለች። አንሶላዋንና ብርድልብሷን አራግፋ አልጋዋን ታነጥፋለች። በዚህ ሁኔታዋም ወላጆቿና ጎረቤቶቿ ያደንቋታል። የክፍልና የሠፈር ጓደኞቿም ይቀኑባታል። እሷም ጤነኛና ደስተኛ ናት።

የግል ንጽህናዬን ከጠበቅሁ ጤነኛ እሆናለሁ።

ወንዱ ልጅ ግን ለትምህርቱና ለግል ንጽህናው አጠባበቅ የሴቷን ያህል ትኩረት አይሰጥም። ፊቱን አዘውትሮ ስለማይታጠብ ዝንቦች ይወሩታል። በዚህም ምክንያት ዘወትር ዓይኑን ያመዋል። ፀጉሩን በየጊዜው አይታጠብም፤ አያበጥርምም። በዚህም የተነሳ በፀጉሩ ውስጥ ተባይ አይጠፋም። ከመፀዳጃቤት ገብቶ ሲወጣም ሆነ ምግብ ከመብላቱ በፊትና ከበላ በኋላ እጁን አይታጠብም። ይህም ለከፍተኛ ሆድ ሕመም

ዳርንታል። ሰውነቱና ልብሱ ሳይታጠብ ስለሚቆይ ጠረኑ ጥሩ አይደለም። በዚህም ምክንያት ሰውነቱን በተደጋጋሚ ያሳክከዋል።

ልጁ የግል ንጽህናውን አለመጠበቁ ልጅቷን ሁልጊዜ ያሳስባት ነበር። በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ የከፋ ችግር እንዳያጋጥመው ሰጋች። ስለዚህ መፍትሔ መፈለግና ማገዝ ግዴታዋ መሆኑን በመገንዘብ ለመርዳት ወሰነች። አንድ ቀን ጠራችውና የግል ንጽህናውን እንዴት መጠበቅ እንዳለበት አስረዳችው። የግል ንጽህናውን ከጠበቀ ጤነኛ እንደሚሆን ገለጸችለት። ንጹህ ከሆነ ጓደኞቹ እንደሚወዱት አግባባችው። በተለይም ፊቱን፣ እጁን፣ እግሩንና ሰውነቱን አዘውትሮ እንዲታጠብ፣ ጥፍሩንም እንዲቆረጥ፣ ፀጉሩንም እንዲስተካከል አጥብቃ መከረችው። ልብስ ማጠብ እንደምታለማምደውና ትምህርቱን እንደምታስረዳው ቃል ገባችለት።

የግል ንጽህናውን እንዴት መጠበቅ እንዳለበት አስረዳችው።

ልጁም ልጅቷ የሰጠችውን ምክር ተቀብሎ ተግባራዊ አደረገ። የግል ንጽህናውን በመጠበቁም ጤነኛ ሆነ። የሰውነቱና የልብሱ ጠረንም ተስተካከለ። ያገሉት የነበሩ ጓደኞቹም አቀረቡት። ደስተኛ ሆኖም ትምህርቱን በሰላም ይከታተል ጀመር።

(ኢትዮጵያ ቄክ አኖ ኔት ሰኞ፣ 05/20/2013። መነሻነት የተጻፈ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በቃላችሁ መልሱ።

1. ስለሁለቱ ባለታሪኮች ትክክል የሆነው ነጥብ የትኛው ነው?
   ሀ. ሁለቱም ጎበዝ ተማሪዎች ናቸው።
   ለ. ሁለቱም በጓደኞቻቸው ዘንድ ተወዳጅ ናቸው።
   ሐ. ወደትምህርትቤት አብረው ይመላለሳሉ።
   መ. ሁለቱም ንፅህናቸውን ይጠብቃሉ።
2. ከሚከተሉት የሴቷ ልጅ ባህርይ የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. የግል ንፅህናዋን አለመጠበቋ
   ሐ. ለረጅም ሰዓታት መዝናናቷ
   ለ. ለትምህርቷ ትኩረት አለመስጠቷ
   መ. በየቀኑ ፀጉሯን መሠራቷ
3. ወንዱን ልጅ በተመለከተ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ፊቱን አዘውትሮ አይታጠብም።
   ለ. ከምግብ በፊትና በኋላ እጁን አይታጠብም።

ሐ. ልብሱን ቶሎ ቶሎ አያጥብም።

መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

4. ልጁ «ጠረኑ ጥሩ አይደለም» የተባለው ለምን ይመስላችኋል?

ሀ. ሰውነቱን ስለሚያክ

ለ. መልኩ ስለሚያስጠላ

ሐ. ሰውነቱና ልብሱ ለረጅም ጊዜ ስለማይታጠብ

መ. ፀጉሩን ስለማይላጭ

5. በ4ኛው አንቀጽ ላይ «በዚህ ሁኔታ» በሚል የተገለፀው ምንድን ነው?

ሀ. የልጅቷን መከፋት

ሐ. ልጁ በትምህርቱ አለመሻሻሉን

ለ. የልጁን የንፅህና ጉድለት

መ. የልጁ አስተሳሰብ መለወጡን

6. በ2ኛው አንቀጽ፣ የክፍልና የሠፈር ጓደኞቿ «ይቀኑባታል» ሲል ምን ማለት ነው?

ሀ. እርሷን ይቀናቀኗታል።

ሐ. እንደርሷ መሆን ይመኛሉ።

ለ. እርሷን ይጠሏታል።

መ. እንደርሷ መሆን ይጠላሉ።

7. ልጅቷ ልጁን ለመርዳት ቃል የገባችለት ጉዳይ የትኛው ነበር?

ሀ. ልብሱን ልታጥብለት

ሐ. ሰውነቱን ለማጠብ

ለ. ትምህርቱን ለማስጠናት

መ. ጥፍሩን ለመቁረጥ

ተግባር 2

ምንባቡን መሠረት በማድረግ ሴቷና ወንዱ ልጅ የሚመሳሰሉባቸውንና የሚለያዩባቸውን ባህርያት የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ በማዘጋጀት ዘርዝሩ።(ከአንድ በላይ መልስ መስጠት ይጠበቅባችኋል)

ተመሳስሏቸው	ገፀባህርያቱ	ልዩነታቸው
	ሴቷ ልጅ	
	ወንዱ ልጅ	

5ኛ ቀን

ቃላት

የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ

ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሠመረባቸው ቃላት በምንባቡ መሠረትና ከምንባቡ ውጪ ያላቸውን ፍቺ በደብተራችሁ ሠንጠረዥ አዘጋጅታችሁ ጻፉ።

ሀ. ፀጉሯን አበጥራ ትጎነጉናለች።

ለ. ዝንቦች ይወሩታል።

ሐ. አልጋዋን አራግፋ ታነጥፋለች።

መ. ልብሷን አጥባ ትተኩሳለች።

ሠ. ዘወትር በጧት ከመኝታዋ ተነስታ ወደመፀዳጃቤት ትሄዳለች።

ረ. ትምህርቱን በሰላም ይከታተል ጀመር።

ቃሉ	በምንባቡ ውስጥ ያለው ፍቺ	ከምንባቡ ውጪ ያለው ፍቺ
ትጎነጉናለች	ፀጉሯን ትሠራለች	ታሴራለች

ተግባር 2

ከላይ በተግባር 1 የተሠመረባቸውን ቃላት ከምንባቡ ውጪ ያላቸውን ፍቺ እንዲያሳዩ አድርጋችሁ ዓረፍተነገር ሥሩባቸው።

ምሳሌ፡- ትጎነጉናለች

ልጅቷ ከጓደኛዋ ጋር ሆና በእኔ ላይ ነገር ትጎነጉናለች።

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በማወዳደርና በማነፃፀር ስልት አንቀጽ መጻፍ።

ተግባር

ባለፈው ሳምንት ያዘጋጃችሁትን የቢጋር ሠንጠረዥ መነሻ በማድረግ በማወዳደርና በማነፃፀር ስልት አንድ አንቀጽ ጻፉ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

የቃል ጽሕፈት

ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ዓረፍተነገሮች በደብተራችሁ ጻፉ።

6ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

ቅድመንባብ

ተግባር

«ምሥጋና ለጓደኛዬ» በሚለው ምንባብ ሴቷና ወንዱ ልጅ የሚለያዩባቸውን ባህርያት ግለጹ።

ማንበብ

ተግባር

«ምሥጋና ለጓደኛዬ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የመጀመሪያዎቹን ሦስት አንቀጾች ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተራበተራ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

መናገር

ተግባር


የግልና የአካባቢ ንፅህና አጠባበቅን በተመለከተ በቡድን ተወያዩ። በውይይት ጊዜ ሀሳብ ስታቀርቡ (ስትናገሩ) ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት ተጠቀሙ። ቃላቱም፡-

ማስወገድ፣ መስተካከል፣ መፀዳጃቤት፣ መቆጣጠር፣ ግዴለሽነት፣ መዛመት፣ መላጨት፣ ማፍሰሻ፣ ማስረጊያ፣ ትኩረት፣...ናቸው።

በተጨማሪም፡-

- ሀሳባችሁን ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ አቅርቡ፤
- አያያዥ ቃላትንም ተጠቀሙ።

ሀሳባችሁን ከማቅረባችሁ በፊት በሚቀጥለው ስዕላዊ ቢጋር ላይ አደራጁ።



ሰዋስው

ቅጽል

ተግባር 1

በቀረበው ምሳሌ መሠረት ሠንጠረዡን አሟሉ።

ተ.ቁ	ቅጽል	ብዙ ቁጥር	አንስታይ ጾታ
ሀ	ጥቁር	ጥቁሮች	ጥቁሪቱ (ጥቁሯ)
ለ	ረጅም		
ሐ	ቀጭን		
መ	ደግ		
ሠ	ብልጥ		
ረ	ነጭ		

ተግባር 2

ቀጥሎ በቀረበው ምሳሌ መሠረት፣ ቅጽሎቹን ወደብዙ ቁጥር ለውጡ።

ምሳሌ፡-

1. ቀይ ⟶ ቀያይ
2. ረጅም ⟶ ረጃጅም

ሀ. ነጭ

ለ. ጥቁር

ሐ. አጭር

መ. ቀጭን

ሠ. ደግ

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ተግባር

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	ኘላስቲክ-ኦች	ኘላስቲኮች
ለ	እየ-ተጓጓዘ	እየተጓጓዘ
ሐ	ያለ-መፀየፍ	ያለመፀየፍ
መ	መሰረተ-ልማት-ኦች	መሰረተልማቶች

ማንበብ

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስና መገመት

ተግባር


የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ከዚህ በፊት የምታውቁትን የቆሻሻ መጣያ/ማከማቻ አስታውሳችሁ ግለጹ።

ለ. ሥዕሉን በትኩረት አስተውላችሁ የተረዳችሁትን ግለጹ፣

ሐ. በርዕሱና በሥዕሉ መካከል ያለውን ዝምድና ግለጹ።

ቆሼና አዲሱ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ



ቆሼና አዲሱ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የሚመሳሰሉባቸውና የሚለያዩባቸው ባህርያት አሉ። የአዲስአበባ ከተማ ቆሻሻ መድፊያ ቦታ መሆናቸው ሁለቱን ያመሳስላቸዋል። ሁለቱም ከከተማው ከአራቱም ማዕዘናት የተሰበሰበ ቆሻሻ እየተጓጓዘ የሚደፋባቸው ቦታዎች ናቸው።

ቆሼንና አዲሱን የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የሚለዩዋቸው ባህርያት አሉ። ቆሼ በአብዛኛው በማይበሰብሱ ኘላስቲኮች፣ ጨርቆችና ጣሳዎች የተሞላ ነው። በውስጡ ከያዘው ርጥብ ቆሻሻ የተነሳ አካባቢው በፍሳሽ የረጠበና ረግረግ ነው። ይህንን ቆሻሻ የቆሼ አካባቢ ልጆች በክስክስ ጫማቸው ያለመፀየፍ ይረግጡታል። አንዳንድ ጊዜ ከእጃቸው አምልጦ የወደቀን ዕቃ ለማንሳት በእጃቸው ይገቡበታል። ይህ የቆሻሻ መጣያ ስፍራ 14 ሄክታር ስፋት አለው። ለአዲስ አበባ ከተማ ብቸኛ የቆሻሻ መጣያ ስፍራ በመሆን ከ60 ዓመታት በላይ አገልግሏል።

አሁን ግን የቆሼ ህልውና ሊያበቃ የግድ ሆኗል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት መካኒሳ፣ ዘነበወርቅና ለቡ አካባቢ መሠረተልማቶች ተስፋፍተዋል። መንገዶች፣ መኖሪያቤቶችና ድርጅቶች ተገንብተዋል። የኗሪዎች ቁጥርም በእጅጉ ጨምሯል።

በዚህም ምክንያት የቆሼ ህልውና ማብቃት እውነት ሆኗል። አዲስ ተለዋጭ የቆሻሻ መጣያ ሊገነባ ደፋቀና ማለት ተጀምሯል።

ቆሻሻን በማከም በድጋሚ ለአገልግሎት ማዋል ይቻላል።

ተለዋጭ የቆሻሻ መጣያ ስፍራ ግንባታው በሰንዳፋ አካባቢ የሚከናወን ይሆናል። በ32 ሄክታር መሬት ላይ በዘመናዊ መልኩ የግንባታ ሥራው ተጀምሯል። አዲሱ የቆሻሻ መጣያ ስፍራ ኤ.ኤስ.ዲ. በተሰኘ የፈረንሳይ ኩባንያ ድጋፍ ይገነባል። ልክ እንደቆሼ ሁሉ ቆሻሻ የሚጣልበትና የሚከመርበት አይደለም። የአካባቢውን ኗሪ ጤናና ሰላም የሚነሳ አይደለም። ይህ ዘመናዊ ኩባንያ ደረቅና ብስባሽ ቆሻሻዎችን ይለያል። ቆሻሻን በማከም በድጋሚ ለአገልግሎት ያውላል። ለብዙ ሰዎችም የሥራ ዕድል ይፈጥራል። የቆሻሻን መጠን በመቀነስ ለአካባቢ ጽዳትና ለአረንጓዴ ልማትም የላቀ ድርሻ ያበረክታል።

(ኢትዮጵያን ሪፖርተር ጋዜጣ። ታህሣሥ 5 ቀን 2005 ዓ.ም.። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ቆሼና አዲሱን የቆሻሻ መጣያ ስፍራ የሚያመሳስላቸው ምንድን ነው?

ለ. የቆሼ አካባቢ በፍሳሽ የረጠበና ረግረግ የሆነው ለምንድን ነው?

ሐ. ቆሼ በቆሻሻ መጣያ ስፍራነት ለምን ያህል ዓመታት አገልግሏል?

መ. የቆሼ ህልውና እንዲያበቃ ያደረገው ምክንያት ምንድን ነው?

ሠ. አዲሱ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ከቆሼ የሚለየው በምንድን ነው?

ረ. የአዲሱ የቆሻሻ መጣያ ስፍራ ስፋት ከቆሼ ይበልጣል ወይስ ያንሳል? እንዴት ይታወቃል?

ሰ. የመሠረተልማቶች መስፋፋት ከቆሼ መነሳት ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነው?

ሸ. አዲሱ የቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራ ለበርካቶች የሥራ እድል የሚፈጥረው እንዴት ነው?

ቀ. ከምንባቡ የወደዳችሁት ነገር ምንድን ነው? ያልወደዳችሁትስ? ለምን?

8ኛ ቀን

ቃላት

ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት

ተግባር

ሀ. ቀጥሎ በሠንጠረዥ ውስጥ የቀረቡትን ቃላት ከምንባቡ ውስጥና ውጪ ያላቸውን ፍቺ ግለጹ።

ቃሉ	በምንባቡ ውስጥ ያለው ፍቺ	ከምንባቡ ውጪ ያለው ፍቺ
መድፊያ	መጣያ	ገበር ምጣድ (የድፎ ዳቦ መጋገሪያ)
ማዕዘን		
የሚነሳ		
ድርሻ		
ማከም		
ድጋፍ		

ለ. ከላይ በሠንጠረዡ ውስጥ በቀረቡት ቃላት ከምንባቡ ውጪ ያላቸውን ፍቺ እንዲያሳዩ አድርጋችሁ ዓረፍተነገሮች ሥሩ።

ምሳሌ፡- ለዳቦ መድፊያ የሚሆን ገበር ምጣድ ገዛሁ።

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በማወዳደርና በማነፃፀር ስልት አንቀጽ መጻፍ

ተግባር

ባለፈው ክፍለጊዜ የእንስሳትና የዕፅዋትን ተመሳሳይነትና ልዩነት በተመለከተ አንድ አንቀጽ ጽፋችኋል። ቀጥሎ የቀረበውን የጽሑፍ መገምገሚያ ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ ጽሑፋችሁን ገምግሙ። ቀጥሎ ስህተታችሁን አስተካክላችሁ አንቀጹን እንደገና ጻፉ። ከዚያም ደብተራችሁን ተቀያየሩና የጓደኛችሁን ጽሑፍ በቀረቡት የመገምገሚያ መስፈርቶች መሠረት እየገመገማችሁ ስህተቶችን በሠንጠረዥ ውስጥ መዝግቡ።

	ጽሑፍን የመገምገሚያ መስፈርቶች	አዎ	አይደለም
ሀ	በጽሑፉ ውስጥ የፊደላት ስህተት አለ?		
ለ	ሥርዓተነጥቦች በአግባቡ አገልግሎት ላይ ውለዋል?		
ሐ	በጽሑፉ ውስጥ የሰዋስው ችግር አለ?		
መ	ጽሑፉ የማወዳደርና የማነፃፀር ስልትን የተከተለ ነው?		
ሠ	ጽሑፉ በርዕሰጉዳዩ ላይ ያተኩራል?		

የአጻጻፍ ሥርዓት

የቃል ጽሕፈት

ተግባር

እያንዳንዱን ፊደል በጥንቃቄ በመጻፍ መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን አንቀጽ በደብተራችሁ ላይ ጻፉ። ከዚያም ደብተራችሁን ከጓደኛችሁ ጋር ተቀያየሩና አርሙ።

9ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

ቆሼና አዲሱ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ

ተግባር

«ቆሼና አዲሱ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ሁለተኛውን አንቀጽ ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ ተራበተራ አንብቡ። አንዳችሁ ስታነቡ አንዳችሁ በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ ስህተት በተፈፀመ ቁጥር የእዝባር (/) ምልክት አድርጉ። ለሁለተኛ ጊዜ ስታነቡ በጓደኞቻችሁ የተሠጣችሁን አስተያየት በመቀበል ከመጀመሪያው አሻሽላችሁ ለማንበብ ሞክሩ።

መስፈርቶች		የመጀመሪያ ንባብ	ሁለተኛ ንባብ
		(/)	(/)
ሀ	በትክክል ያልተነበቡ ፊደላት ብዛት		
ለ	እየተቆጠሩ (ተቆራርጠው) የተነበቡ ቃላት ብዛት		

ሐ	በትክክል ያልተነበቡ ሥርዓተነጥቦች ብዛት		
መ	በ1 ደቂቃ ውስጥ የተነበቡ ቃላት ብዛት		


መናገር

ተግባር

ሀ. በሚበሰብሱ ቆሻሻዎችና በማይበሰብሱ ቆሻሻዎች መካከል ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት በተመለከተ ንግግር አዘጋጅታችሁ በክፍል ውስጥ ተናገሩ። በምትናገሩበት ጊዜ፡-

- ቆሻሻ፣ አረንጓዴ ልማት፣ ብስባሽ ቆሻሻ፣ ጣሳዎች፣ ማከም፣ ደረቅ ቆሻሻ፣ ፕላስቲኮች፣ ወዘተ. የሚሉ ቃላትን ተጠቀሙ።
- ሀሳባችሁን በተጠየቃዊ መንገድ መግለፅ ይጠበቅባችኋል፤
- ተገቢ የሆኑ አያያዥ ቃላትን መጠቀማችሁንም አትርሱ።

ለ. የሚከተለውን ስዕላዊ ቢጋር በደብተራችሁ ሣሉ። መረጃዎቻችሁንም ባዘጋጃችሁት የስዕል ቢጋር ውስጥ አስፍሩ።



ሰዋስው

ቅጽል

ተግባር 1

ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት ቅጽል የሆኑትን መርጣችሁ ዐረፍተነገሮቹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ቆረጥኩ	ጎበዝ	ረጅም	ጥቁር
ለበሰ	ሰፊ	ሰነፍ	ህዝብ

ሀ. እኔ _____ ገመድ ገዛሁ።

ለ. _____ ተማሪ ሁልጊዜ ያጠናል።

ሐ. _____ ሰው ሥራ አይወድም።

መ. _____ አዳራሽ ለስብሰባ ተከራየን።

ሠ. _____ ልብስ የፀሀይ ሙቀት ይስባል።

ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላት በየምድባቸው ጻፉ።

ቀዪቱ	ረጅም	ቀጫጭን	ነጮች	ደጊቱ	ጎበዝ
ክፉዎች	ብልጠቱ	ወፍራሞች	አጭር	ጥቂቁር	

ነጠላ ቁጥር	ብዙ ቁጥር	አንስታይ ጾታ
ጎበዝ	ወፍራሞች	ቀዪቱ



ምዕራፍ 6 ምግብ

የምግብ ዓይነቶች

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ተግባር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	ተዋጽኦ-ዎች-ን	ተዋጽኦዎችን
ለ	ኢትዮጵያ-ው-ያን	ኢትዮጵያውያን
ሐ	ቅመማ-ቅመም-ኦች	ቅመማቅመሞች
መ	ከሚያስፈልግ-ኡ-ኣቸው	ከሚያስፈልጓቸው
ሠ	የምንጠቀም-ብ-ኣቸው	የምንጠቀምባቸው
ረ	የሚያገኝ-ኡ-ኣቸው-ን	የሚያገኟቸውን
ሰ	ምግብ-ኦች-ኣቸው-ን-ም	ምግቦቻቸውንም

ማንበብ

ምግቦቻችን

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ ከእንስሳትና ከዕፅዋት የሚገኙ ምግቦችን ዘርዝሩ።

ከእንስሳት የሚገኙ ምግቦች	ከዕፅዋት የሚገኙ ምግቦች

የማንበብ ሂደት

ተግባር

ቀጥሎ «ምግቦቻችን» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አንብቡ።

ምግቦቻችን



ሰዎች ለመኖር ከሚያስፈልጓቸው መሠረታዊ ነገሮች መካከል ዋናው ምግብ ነው። ምግብ ከዕፅዋትና ከእንስሳት ይገኛል። ከዕፅዋት የሚገኙት ምግቦች የእህል፣ የአትክልትና የፍራፍሬ ምግቦች ናቸው። ከእንስሳት የሚገኙት ምግቦች ደግሞ ሥጋን፣ እንቁላልን፣ ወተትንና የወተት ተዋጽዖዎችን ያካትታሉ። እነዚህ ምግቦች በተመጣጠነ ደረጃ ተዘጋጅተው ከቀረቡ ለሰውነት የሚሰጡት ጥቅም ከፍተኛ ነው።

ከዕፅዋትም ሆነ ከእንስሳት የሚገኙት የምግብ ዓይነቶች አዘገጃጀትና ምርጫ እንደየአካባቢው ይለያያል። ልዩነቱም ከተመጋቢዎች ባህልና እምነት ይመነጫል። በተጨማሪም የአካባቢው የአየር ፀባይ፣ የሚያመርቱት የአዝርዕት ዓይነትና የሚያረቡት የእንስሳ ዓይነት አመጋገባቸውን ይወስናል።







ከዕፅዋት የምግብ ዓይነት አትክልትና ፍራፍሬን የመመገብ ባህል በሀገራችን እየተለመደ መጥቷል። ጎመን፣ ሰላጣ፣ ቆስጣ፣ ቃሪያ፣ ቲማቲም፣ ድንች፣ ካሮት፣ ወዘተ. የአትክልት ምግቦች ይባላሉ። የተወሰኑት ተቀቅለው፣ የተወሰኑት ደግሞ

በጥሬው ሊበሉ ይችላሉ። በፍራፍሬ ምግብነት ከሚታወቁት መካከል ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ኮክ፣ ዶቅማ፣ ማንጎ፣ አቦካዶ፣ ሙዝ፣ እንጆሪ ተጠቃሾች ናቸው።

ከእንስሳት ከሚገኙ የምግብ ዓይነቶች አንዱ ሥጋ ነው። ሥጋ ከከብት፣ ከዶሮ፣ ከዓሳና ከሌሎችም እንስሳት ይገኛል። ሥጋ በቁርጥ፣ በክትፎ፣ በጥብስና በወጥ መልክ ተዘጋጅቶ ለምግብነት ይውላል። ሌላው የወተት ተዋጽዖ ነው። የወተት ተዋጽዖ የሚባሉት ቅቤ፣ እርጎ፣ አይብ፣ አሬራ፣ አጓት፣ ወዘተ. ናቸው። እነዚህ ከሌላ ምግብ ጋር ተቀላቅለው ወይም ብቻቸውን ሊበሉና ሊጠጡ ይችላሉ።






በጥቅሉ ሲታይ ግን ሁሉም ኢትዮጵያውያን በአብዛኛው የሚመገቧቸው ምግቦች አሉ። የጤፍ፣ የስንዴ፣ የገብስ፣ የዳጉሳ፣ የበቆሎ፣ የማሽላ፣ ወዘተ እንጀራ ከወጥ ጋር ይመገባሉ። ወጡ ከምስር፣ ከድንችና፣ ከሥጋ፣ ወዘተ. ሊዘጋጅ ይችላል።



ቂጣ፣ አምባሻ፣ ጨጨብሳ፣ ቆጮ፣ ጭኮ፣ በሶ፣ ዳቦ፣ ገንፎ፣ ጥሀሎና ቅንጬ የተለመዱ ምግቦች ናቸው። እነዚህን የምግብ ዓይነቶች ለማጣፈጥ የምንጠቀምባቸው ቅመማቅመሞችም አሉ። አብሽ፣ አዝሙድ፣ በሶብላ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ቀይ ሽንኩርት፣ በርበሬ፣ ዝንጅብል፣ ቅርንፉድ፣ ወዘተ. የቅመም ዓይነቶች ናቸው። ከጥራጥሬም አሸቅ፣ ቆሎ፣ በቆልት፣ ንፍሮ፣ ወዘተ. ተወዳጅ ምግቦች ናቸው።

በአጠቃላይ ሰዎች ጤነኛና ጠንካራ ሆነው መኖር እንዲችሉ የተመጣጠነ ምግብ ማግኘት ይኖርባቸዋል። ከዕፅዋትና ከእንስሳት የሚያገኟቸውን ምግቦች በመቀላቀል ከተመገቡ ተመጣጣኝ የሆነ ንጥረምግብ ያገኛሉ። ጠንካራና ጤነኛ ሆነውም መኖር ይችላሉ።

(ሌስላው። 2001። የአማርኛ ንባብ እና ጽሄ ዑቅባሚካኤል። 1991። *የእናት ጓዳ ባህላዊና ዘመናዊ ምግቦች አዘገጃጀት*። ከገጽ 26 ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ተስማሚ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በጽሑፍ መልሱ።

1. ገብስ፣ ዳጉሳ፣ በቆሎና ማሽላ ምን ዓይነት ምግብ ይዘጋጅባቸዋል?
   ሀ. አሸቅ ሐ. ክትፎ
   ለ. ሽሮ ወጥ መ. እንጀራ
2. «አሸቅ» ከየትኛው የእህል ዓይነት ይዘጋጃል?
   ሀ. ከምስር ሐ. ከበቆሎ
   ለ. ከባቄላ መ. ከስንዴ
3. ከሚከተሉት አንዱ ለአመጋገብ ልዩነት መንስኤ **አይደለም**።
   ሀ. ዶታ ሐ. የአዝርዕት ዓይነት
   ለ. ባህል መ. የአየር ፀባይ
4. አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያዘወትረው የምግብ ዓይነት ምንድን ነው?
   ሀ. ጨጨብሳ ሐ. ቆጮ
   ለ. እንጀራ መ. ቅንጬ
5. ከፍራፍሬ ምግቦች **የማይመደበው** የትኛው ነው?
   ሀ. ብርቱካን ሐ. ኮክ
   ለ. እንጆሪ መ. ቲማቲም
6. ከአትክልት ምግቦች **የሚካተተው** የትኛው ነው?
   ሀ. ሎሚ ለ. ትርንጎ

ሐ. ካሮት　　መ. መንደሪን

7. የወተት ተዋጽኦ **ያልሆነው** የትኛው ነው?

ሀ. ሥጋ　　ሐ. አሬራ

ለ. ቅቤ　　መ. አጓት

ተግባር 2

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን መደምደሚያ ተናገሩ።

ሀ. ቅመማቅመሞች አገልግሎታቸው ምንድን ነው?

ለ. የአካባቢ አየር ፀባይ በአመጋገብ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርሰው እንዴት ነው?

ሐ. አንድን የምግብ ዓይነት ብቻ አዘውትሮ መመገብ ለጤንነት ጠቃሚ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

2ኛ ቀን

ቃላት

ተግባር 1

ቀጥሎ የቀረቡትን ዝርዝር ቃላት በሠንጠረዡ ውስጥ በቀረቡት ጥቅል መጠሪያቸው ሥር መድቡ።

ቅርንፉድ	ሰላጣ	አይብ	በሶብላ
አጓት	ዶቅማ	ቆስጣ	እንጆሪ

አትክልት	ፍራፍሬ	የወተት ተዋፅኦ	ቅመማቅመም

ተግባር 2

በተሠመረባቸው ቃላትና ሐረጋት የዓረፍተነገሩን ሀሳብ የማይለውጥ ሌላ ዓረፍተነገር መሥርቱ።

ምሳሌ፡- የከተማ ሰዎች የተለያዩ <u>የአዝዕርት</u> ዓይነቶችን ከገበያ ይሸምታሉ።

መልስ፡- የከተማ ኗሪዎች ልዩልዩ አዝዕርትን ከገበያ ይገዛሉ።

ሀ. ቅመም ለምግብ ማጣፈጫነት ይውላል።

ለ. የምግብ ጥቅም በርካታ ነው።

ሐ. የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ለጤንነት አስፈላጊ ነው።

መ. የምግብ አዘገጃጀት ልምድ ይጠይቃል።

ሠ. የአካባቢያችን የአየር ፀባይ እየተቀያየረ ነው።

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በዋናና መዘርዝር ሀሳቦች ስልት የቢጋር ሠንጠረዥ ማዘጋጀት

ተግባር

ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን በተመለከተ መጻሕፍት በማንበብ፣ የጤና ባለሙያዎችን ወይም የሳይንስ መምህራንን በመጠየቅ በሽታዎችን በተለያዩ ምድቦች ከፋፍላችሁ በቢጋር ሠንጠረዥ አደራጁ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

የአንድ ነጥብ(.) አጠቃቀም

ማስታወሻ

አንድ ነጥብ (.) በርካታ አገልግሎቶች አሉት። ከአገልግሎቶቹ መካከልም አንዱ፣ አንድን ቃል ወይም ከአንድ ቃል በላይ ያላቸውን ስሞች (መጠሪያዎች) አሳጥሮ መጻፍ ነው። ቀጥሎ አንድን ቃል እንዴት አሳጥሮ እንደሚጻፍ እንመለከታለን። አንድን ቃል በሁለት የተለያዩ መንገዶች አሣጥሮ መጻፍ ይቻላል።

- አንደኛው መንገድ የቃሉን የመጀመሪያ ሁለት ፊደሎች በመጠቀም አሳጥሮ መጻፍ ነው። «መስተዳድር» የሚለውን ቃል «መስ.» ብሎ ማሳጠር ይቻላል።
- ሁለተኛው መንገድ ደግሞ የቃሉን የመጀመሪያና የመጨረሻ ሆሄያት በመጠቀም አሳጥሮ መጻፍ ነው። ለምሳሌ «ወይዘሮ» የሚለውን ቃል «ወሮ.» ብሎ ማሳጠር ይቻላል።

ተግባር

1. የሚከተሉትን ቃላት የመጀመሪያዎቹን ሁለት ፊደሎች በመጠቀም አሳጥራችሁ ጻፉ።

ሀ. ማቴዎስ ለ. ትምህርት ሐ. አስተዳደር

2. የሚከተሉትን ቃላት የመጀመሪያና የመጨረሻ ፊደሎች በመጠቀም አሳጥራችሁ ጻፉ።

ሀ. ወታደር
ለ. መምህር
ሐ. ሚኒስትር
መ. ኢንስፔክተር

3ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

ምግቦቻችን

ቅድመንባብ

ተግባር

«ምግቦቻችን» በሚለው ምንባብ መሠረት ምግቦች ከምን ከምን እንደሚገኙ ዘርዝሩ።

ማንበብ

«ምግቦቻችን» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ሶስተኛውንና አራተኛውን አንቀጾች በቡድን ሆናችሁ ድምፅ እያሰማችሁ በጋራ አንብቡ።

ማዳመጥ

በሽታ ተከላካይ ምግቦች

ቅድመማዳመጥ

ተግባር

የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ የምታውቋቸውን በሽታ ተከላካይ ምግቦችና የሚከላከሏቸውን የበሽታ ዓይነቶች ዘርዝሩ።

የማውቃቸው በሽታ ተከላካይ ምግቦች	የሚከላከሏቸው የበሽታ ዓይነቶች

የማዳመጥ ሂደት

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን እየለያችሁ በትኩረት አዳምጡ።

አዳምጠ መረዳት

ተግባር 1

ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ቀደም ሲል ከዘረዘራችኋቸው የተለዩ በሽታ ተከላካይ ምግቦችንና የሚከላከሏቸውን የበሽታ ዓይነቶች ቀጥሎ በቀረበው ሠንጠረዥ ዘርዝሩ።

በሽታ ተከላካይ ምግቦች	የሚከላከሏቸው የበሽታ ዓይነቶች

ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሙዝ የደም ግፊትን የሚቀንሰው በምን ምክንያት ነው?

ለ. ለደም ዝውውር አስፈላጊ የሆነው ንጥረነገር የሚገኘው ከየትኛው የምግብ ዓይነት ነው?

ሐ. ነጭ ሽንኩርትንና ሎሚን የሚያመሳስላቸው ምንድን ነው?

መ. የበሰለ ሙዝ በደም ውስጥ የቅባት መጠንን ለመቀነስ ይችላል? እንዴት?

ሠ. ነጭ ሽንኩርት ጥሬውን መብላት የሚመረጠው ለምንድን ነው?

ሰዋስው

የተጸውዖ ስም፣ የወል ስምና ግስ

ተግባር 1

የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ፣ የተሠመረባቸውን ቃላት የተጸውዖ ስም፣ የወል ስም ወይም ግስ መሆናቸውን የ«✓» ምልክት በማድረግ ለዩ።

	ዓረፍተነገር	የተጸውዖ ስም	የወል ስም	ግስ
ሀ	አስቴር መጽሐፍ ገዛች።			
ለ	ፈረሱ ሣር ይግጣል።			
ሐ	መስከረም መጽሐፍ አነበበች።			
መ	ድመቷ ዛፍ ላይ ወጣች።			
ሠ	ውሻው አጥንት ቆረጠመ።			
ረ	ሰኞ ከሳምንቱ የሥራ ቀናት የመጀመሪያው ነው።			
ሰ	ሀሰንና ጣይቱ ቡና ጠጡ።			
ሸ	ዓሣ በባህር ውስጥ ይኖራል።			

ተግባር 2

«ምግቦቻችን» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የተጸውዖና የወል ስሞችን እንዲሁም ግሶችን ለይታችሁ በማውጣት በደብተራችሁ ጻፉ።

ማንበብ

ዳቦ ከምን ከምን ይዘጋጃል?

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር

ዳቦ ለመጋገር ምን ምን ነገሮች የሚያስፈልጉ ይመስላችኋል?

የማንበብ ሂደት

ተግባር

የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጁ። ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ዋናና መዘርዝር ሀሳቦችን እያስተዋላችሁ አንብቡ። ምንባቡን በምታነቡበት ጊዜ፣ በአዕምሯችሁ የሚመላለሱትን ጥያቄዎች በሠንጠረዡ ውስጥ ጻፉ። አንብባችሁ ስትጨርሱ ጥያቄዎቻችሁን መልሱ።

ጥያቄዎች	መልሶች
•ይህን ጽሑፍ የማነበው ለምንድነው?	
•ያልገባኝ ነገር ምንድን ነው?	
•ምን ጥያቄዎች አሉኝ?	

ዳቦ ከምን ከምን ይዘጋጃል?

ዳቦ ለመጋገር መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ ግብዓቶች አሉ። የስንዴ ዱቄት፣ ጨው፣ ውኃና እርሾ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። እነዚህን ግብዓቶች በተፈለገው መጠን ቀላቅሎ በማቡካት ለዳቦ የሚሆን ሊጥ ማዘጋጀት ይቻላል።

ለዳቦ የሚሆነው ዱቄት ከንጹህ ስንዴ የተዘጋጀና ጥራት ያለው ሊሆን ይገባል። በመጀመሪያ ስንዴው ንጹህ እንዲሆን በውስጡ ያሉት እንደአፈር፣ እንክርዳድ፣ ጠጠርና የመሳሰሉት ደባል ነገሮች መለቀም አለባቸው። ከዚያም በደንብ ታጥቦ ከደረቀ በኋላ መፈጨት ይኖርበታል። ዱቄቱም ንጹህ እንዲሆን መነፋት አለበት። የስንዴው ሊጥ የመለጠጥ መጠንም ከፍ ያለ እንዲሆን ይፈለጋል። በተጨማሪም የዳቦ ዱቄት መልኩን ያልቀየረ፣ መጥፎ ሽታ የሌለው፣ ብዙ ያልቆየና ለሰውነት ጠቃሚ ንጥረነገሮች በብቃት ሊይዝ ይገባል።

ሌላው ለዳቦ አስፈላጊ የሆነ ግብዓት ጨው ነው። ጨው ለዳቦ ጣዕም ይሰጣል። ለዳቦ የምንጨምረው የጨው መጠን በአማካይ የዱቄቱን መጠን 2% ቢሆን ይመረጣል። ጨው በዳቦ ሊጥ ውስጥ መጨመር ሦስት ጥቅሞችን ያስገኛል። አንደኛ የዳቦውን ጣዕም ያሻሽላል። ሁለተኛ፣ የእርሾውን የማቡካት ፍጥነት በማዘግየት ሊጡ ወጥ በሆነ መልኩ ኩፍ እንዲል ያደርጋል። ሦስተኛ፣ የስንዴው ሊጥ የመለጠጥ መጠን ከፍ እንዲል ወይም እንዲጠነክር ያግዛል።

ዳቦ ለመጋገር ሌላው አስፈላጊ ግብዓት እርሾ ነው፣ ከሊጡ ውስጥ የተቃጠለ አየርንና አልኮልን በማስወጣት ሊጡ እንዲነፋ ያደርጋል። ለዳቦውም ጥሩ መአዛ ይሰጣል። የእርሾው መጠን በአማካይ የዱቄቱን መጠን ከ0.3% እስከ1% ቢሆን የተሻለ ነው። ነገርግን እርሾ በቀላሉ ሊበላሽ ስለሚችል ከመጠቀማችን በፊት ከማንኛውም ብልሽት ነፃ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል።

ሌላው ለዳቦ አስፈላጊ ግብዓት ውኃ ነው። ውኃን ከዱቄት ጋር በመቀላቀልና በማቡካት የዳቦ ሊጥ ማዘጋጀት ይቻላል። የሚጨመረው የውኃ መጠን እንደዱቄቱ መጠን ሊለያይ ይችላል። የሚመረጠው ግን የዱቄቱን መጠን ግማሽ ቢሆን ነው። ለዳቦ ሊጥ ማዘጋጃነት የምንጠቀምበት ውኃ ለብ ያለ ቢሆን ይመረጣል። ይህ ከሆነ የእርሾውን ተግባር ማፋጠን ይችላል።

በአጠቃላይ ጥራት ያለው ዳቦ ለማዘጋጀት ከላይ የተዘረዘሩትን ግብዓቶች በተገቢው መጠን ማቅረብ ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ ከስንዴ መረጣ ጀምሮ ዳቦው እስከሚጋገር ያለውን ሂደት በጥንቃቄ ማከናወን ይገባል። ይህን ካደረግን ጥሩ ቃና ያለው፣ ሲያዩት የሚያስጎመጅ ዳቦ መጋገር ይቻላል።

(የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ መንግሥት ንግድና ኢንዲስትሪ ቢሮ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ፕሮግራም። 1999። *የዳቦ፣ የአንባሻና የኩሲስ አዘገጃጀት ማሠልጠኛ ማንዋል*። ከገጽ 11-13፣ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

በሠንጠረዡ የተዘረዘሩትን ጠቀሜታዎች በማንበብ በግብዓቶች ሥር የ«✓» ምልክት አድርጉ።

ጠቀሜታዎች	ግብዓቶች			
	ዱቄት	ጨው	እርሾ	ውኃ
የዳቦውን ጣዕም ያሻሽላል				
የተቃጠለ አየርንና አልኮልን በማስወጣት ሊጡ እንዲነፋ ያደርጋል።				
የዱቄቱን መጠን ½ ቢሆን ይመረጣል።				

ለሰውነት ጠቃሚ ንጥረነገሮች በብቃት ሊይዝ ይገባል።				
ሊጡ ወጥ በሆነ መልኩ ኩፍ እንዲል ያደርጋል።				
በስንዴ ውስጥ ያለው የመለጠጥ ባህርይ እንዲጠነክር ያግዛል				

ተግባር 2

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የእርሾ መጠን ቢያንስ ወይም ቢበዛ ምን ችግር ያለው ይመስላችኋል?

ለ. የጨው መጠን ቢያንስ ወይም ቢበዛ ምን ችግር የሚኖረው ይመስላችኋል?

ሐ. ዱቄቱ ብዙ የቆየ መሆን የለበትም የተባለው ለምንድን ነው?

መ. ዳቦ ሊጋገር የሚችለው ከስንዴ ብቻ ነውን? ካልሆነ፣ ዳቦ ከምን ከምን ሊዘጋጅ እንደሚችል ዘርዝሩ።

5ኛ ቀን

ቃላት

የቃላት ተመሳሳይና ዐውዳዊ ፍቺ

ተግባር 1

በ«ሀ» ረድፍ የቀረቡትን ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከ«ለ» ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

ሀ	ለ
1 ግብዓት	ሀ. ጣዕም
2 ለብ ያለ	ለ. አስፈላጊ ነገር
3 በብቃት	ሐ. የሚያጓጓ
4 መአዛ	መ. የሞቀ
5 ቃና	ሠ. ጥሩ ሽታ
6 የሚያስጎመጅ	ረ. በተሟላ

ተግባር 2

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ዐውዳዊ ፍቺ በጽሑፍ ግለጹ።

ሀ. ደባል ነገሮች (አንቀጽ 2)

ለ. መልኩን ያልቀየረ (አንቀጽ 2)

ሐ. መነፋት (አንቀጽ 2)
ሠ. እንዲነፋ (አንቀጽ 4)
መ. እንዲጠነክር (አንቀጽ 3)

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

ዋናና መዘርዝር ሀሳቦችን በመጠቀም አንቀጽ መጻፍ

ተግባር

ባለፈው ሳምንት ባዘጋጃችሁት የቢጋር ሠንጠረዥ ላይ በመመሥረት ተላላፊ ስለሆኑና ተላላፊ ስላልሆኑ በሽታዎች በዋናና መዘርዝር ሀሳቦች ስልት አንድ አንቀጽ ጻፉ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

የይዘት/የአንድ ነጥብ (.) አገልግሎት

ማስታወሻ

አንድ ነጥብ ጥምር ቃላትና ከአንድ ቃል በላይ ያላቸውን ስሞች ለማሳጠርም ይጠቅማል።

- ጥምር ቃልን ለማሳጠር ቃሉን ከገነቡት ሁለት ቃላት የመጀመሪያ ፊደል በመውሰድ ከእያንዳንዱ ፊደል ቀጥሎ አንድ ነጥብን ተጠቅሞ አሳጥሮ መጻፍ ነው። ለምሳሌ «ዓመተምህረት» የሚለውን ቃል «ዓ.ም.» ብሎ ማሳጠር ይቻላል።
- ከአንድ ቃል በላይ ያለውን ስም ለማሳጠር፣ በስሙ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት የመጀመሪያውን ፊደል በመውሰድ በመካከላቸው አንድ ነጥብን በመጠቀም ማሳጠር ይቻላል። ለምሳሌ «የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት» የሚለውን ስም «አ.ብ.ክ.መ.» ብሎ ማሳጠር ይቻላል።

ተግባር

1. የሚከተሉትን ስያሜዎች አሳጥራችሁ ጻፉ።
   ሀ. ትምህርትቤት
   ሐ. አዲስ አበባ
   ለ. ፍርድቤት
   መ. ተራ ቁጥር
2. የሚከተሉትን ከአንድ ቃል በላይ ያላቸውን ስያሜዎች አሳጥራችሁ ጻፉ።
   ሀ. አፍሪካ ሕብረት
   መ. የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር
   ለ. ደራሲያን ማህበር
   ሠ. ወላጅ መምህር ህብረት
   ሐ. የኢትዮጵያ ሠራተኞች ማህበር

6ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

ዳቦ ከምን ከምን ይዘጋጃል?

ቅድመንባብ

ተግባር

«ዳቦ ከምን ከምን ይዘጋጃል?» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የምታስታውሱትን ተናገሩ።

ማንበብ

ተግባር


«ዳቦ ከምን ይዘጋጃል?» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ከ1-3 ያሉትን አንቀጾች በቡድን ሆናችሁ ድምፅ በማሰማት በጋራ አንብቡ።

መናገር

በዋናና መዘርዝር ሀሳቦች ስልት ውይይት ማድረግ

ተግባር

የዶሮ ወጥ አሠራርን በተመለከተ በቡድን ተወያዩና ቀጥሎ የቀረበውን የቢጋር ሳጥን አሟሉ።



ሰዋስው

የተጸውዖ ስም፣ የወል ስሞችንና ግሶችን መለየት

ተግባር

ቀጥሎ የተጸውዖ ስም፣ የወል ስሞችና ግሶች ተቀላቅለው ቀርበዋል። እየለያችሁ በደብተራችሁ ዘርዝሩ።

እንጦጦ	ተራራ	አገዘ	ሀረገወይን	ሜዳ
ፈለገ	ዘቢባ	ወንዝ	አገኘ	ደመላሽ
ዝቋላ	ሐይቅ	አደረገ	መቅደላ	ዘመረ
ከተማ	አሞ	ሐሙስ	ጨፈረ	



የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ተግባር

ሀ. የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	ካ-ሎ-ሪ	ካሎሪ
ለ	ኘ-ሮ-ቲ-ን	ኘሮቲን
ሐ	ቫ-ይ-ታ-ሚ-ን	ቫይታሚን
መ	ካ-ል-ሲ-የ-ም	ካልሲየም
ሠ	ካ-ር-ቦ-ሃ-ይ-ድ-ሬ-ት	ካርቦሃይድሬት

ለ. የሚከተሉትን ቃላት/ሐረግ በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	የተ-ዘረዘሩ-ትን	የተዘረዘሩትን
ለ	ንጥረ-ነገር-አች	ንጥረነገሮች
ሐ	ንጥረ-ምግብ-አች-ን	ንጥረምግቦችን

ማንበብ


የተመጣጠነ ምግብ ጥቅም

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር

የሚከተለውን የቢጋራ ክብ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ በተገቢ ቃላት አሟሉ።



የማንበብ ሂደት

ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጁ። ከዚያም «የተመጣጠነ ምግብ ጥቅም» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ እያነበባችሁ ሠንጠረዡን አሟሉ።

ጥያቄዎች	መልሶች
ያልገባኝ ነገር ምንድን ነው?	
የማነበው ምንባብ ትርጉም ሰጥቶኛል?	
ትርጉም ያልሰጠኝ ለምንድን ነው?	
የማንበብ ፍጥነቴን መቀነስ ወይም መጨመር ይኖርብኝ ይሆን?	

የተመጣጠነ ምግብ ጥቅም

የተመጣጠነ ምግብ ለሰውነት አስፈላጊ የሆኑ ንጥረምግቦችን የያዘ ምግብ ነው። ሰውነት ያለችግር የዕለትተዕለት ተግባሩን እንዲያከናውን ያግዛል። የተመጣጠነ ምግብ ፕሮቲን፣ ካርቦሃይድሬት፣ ቅባት፣ ማዕድን፣ ቫይታሚንና ውኃ በውስጡ እንዲኖሩ ተደርጎ ይዘጋጃል።

እያንዳንዱ የሰውነት ክፍል ጥንካሬና ጤንነት እንዲያገኝ ተመጣጣኝ ምግብ ያስፈልገዋል። የተመጣጠነ ምግብ ያላገኘ የሰውነት አካል ለልዩ ልዩ የጤና ችግሮች ይጋለጣል። ለምሳሌ ተገቢውን ንጥረምግብ አለማግኘት የአካል ዕድገትን ያጓትታል፣

አካልን ያቀጭጫል፣ ጥንካሬን ያሳጣል። ቆዳ የማያስደስት ቀለም እንዲኖረውና እንዲጠወልግ፣ ከንፈር እንዲደርቅና እንዲሰነጣጠቅ ያደርጋል። የአጥንት መጉበጥ፣ የድድ መድማት፣ የጥርስ መውለቅና የዓይን መፍዘዝ ያስከትላል። የሰውነት አካላት እንደፈለጉ እንዳይታዘዙ ያደርጋል፤ ለአቅም ማጣትና ለድካም ይዳርጋል።

የተመጣጠነ ምግብ አለመመገብ በአዕምሮ ዕድገት ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ አለው። በሕጻንነታቸው የተመጣጠነ ምግብ ያላገኙ ልጆች የአዕምሮ ብስለታቸው ከዕድሜያቸው ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ይሆናል። የትምህርት አቀባበላቸው፣ አካባቢያቸውን ፈጥኖ የመረዳት አቅማቸውና የማኅበራዊ ግንኙነት ችሎታቸውም ደካማ ይሆናል።


ስለዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን የጤና ችግሮች ለመከላከል የተመጣጠኑ ምግቦችን መመገብ ይገባል። የተመጣጠኑ ምግቦች ገንቢ፣ ኃይልና ሙቀት ሰጪ እንዲሁም በሽታ ተከላካይ ተብለው በሦስት ይከፈላሉ።



ገንቢ ምግቦች የሚባሉት በፕሮቲን የበለፀጉ ምግቦች ናቸው። ለሰውነታችን ዕድገት፣ ለጡንቻችን መዳበር፣ ለአጥንቶቻችንና ለጥርሶቻችን ጥንካሬ ያግዛሉ። ገንቢ ምግቦች ከሥጋ፣ ከወተት፣ ከእንቁላል፣ ከምስር፣ ከአተር፣ ከባቄላ፣ ወዘተ. ይገኛሉ።



ኃይልና ሙቀት ሰጪ ምግቦች በቅባትና በካርቦሃይድሬት የበለፀጉ ናቸው። ሰውነታችን በቂ ኃይልና ሙቀት እንዲያገኝ ያደርጋሉ። ኃይልና ሙቀት ሰጪ ምግቦችን ከድንች፣ ከሙዝ፣ ከበቆሎ እሸት፣ ከማር፣ ከዘይት፣ ከጤፍ፣ ከአጃ፣ ወዘተ. ማግኘት ይቻላል።



በሽታ ተከላካይ ምግቦች በቫይታሚንና በማዕድን የበለፀጉ ናቸው። ሰውነታችን በተለያዩ በሽታዎች እንዳይጠቃ ይከላከላሉ። ከቆስጣ፣ ከሎሚ፣ ከካሮት፣ ከፓፓያ፣ ከዱባ፣ ከብርቱካን፣ ከቃሪያ፣ ከሽንኩርት፣ ከጎመን፣ ወዘተ. ይገኛሉ።

የተመጣጠነ ምግብ በመመገብ ሰውነታችን የሚያገኛቸውን የንጥረምግቦች መጠን ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ በመመልከት መረዳት ይቻላል።

በተለያዩ ምግቦች ውስጥ የሚገኝ ንጥረምግብ መጠንን የሚያሳይ ሠንጠረዥ (በመቶ ግራም/ሚሊ ግራም)						
የምግብ ዓይነት	ካሎሪ	ፕሮቲን (በግራም)	ቅባት (በግራም)	ካርቦሃይድሬት (በግራም)	ካልሲየም (በሚ.ግ)	ብረት (በሚ.ግ)
ገብስ	334	9.3	1.9	75.4	47	10.2
በቆሎ	356	8.3	4.6	73.4	6	4.2
ስንዴ	339	10.3	1.9	71.9	49	7.5
ድንች	87	1.3	0.1	20.4	14	2.3
ብርቱካን	38	0.7	1.1	9.8	50	0.8
ነጭ ሽንኩርት	118	4.1	0.3	29.5	36	2.1
ነጭ ጤፍ	339	11.1	2.4	73.6	156	18.9

(የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ ንግድና ኢንደስትሪ ቢሮ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተር ፕራይዞች ልማት ፕሮግራም። 1999። የዳቦ፣ የአንባሻና የኩሪስ አዘገጃጀት ማሠልጠኛ ማንዋል። ገፅ2-3 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

በ«ሀ» ረድፍ የተዘረዘሩትን አንቀጾች፣ በ«ለ» ረድፍ ከተዘረዘሩት የአንቀጾቹ ዋና ሀሳብ ጋር አዛምዱ።

ሀ	ለ
1. አንቀጽ 1	ሀ. ገንቢ ምግቦች ለሰውነት እድገት ጠቃሚ የሆኑ ንጥረምግቦችን የያዙ ናቸው።
2. አንቀጽ 2	ለ. የተመጣጠነ ምግብ ለሰውነት አስፈላጊ የሆኑ ንጥረምግቦችን የያዘ ነው።
3. አንቀጽ 3	ሐ. በሽታ ተከላካይ ምግቦች ሰውነት በበሽታ እንዳይጠቃ በሚከላከሉ ንጥረምግቦች የበለፀጉ ናቸው።
4. አንቀጽ 4	መ. በሕጻንነታቸው የተመጣጠነ ምግብ ያላገኙ ልጆች የአዕምሮ ብስለታቸው ከዕድሜያቸው ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ይሆናል።
5. አንቀጽ 5	ሠ. የተመጣጠኑ ምግቦች በሦስት ይከፈላሉ።
6. አንቀጽ 6	ረ. ኃይልና ሙቀት ሰጪ ምግቦች በቅባትና በካርቦሃይድሬት የበለፀጉ ናቸው።
7. አንቀጽ 7	ሰ. ገንቢ ምግቦች ከሥጋ፣ ከወተት፣ ከእንቁላል፣ ከምስር፣ ከባቄላ፣ ወዘተ. ይገኛሉ።
	ሸ. የተመጣጠነ ምግብ እጥረት በአካል ላይ የጤና ችግር ያስከትላል።
	ቀ. በሽታ ተከላካይ ምግቦች ከቆስጣ፣ ከሎሚ፣ ከካሮት፣ ከፓፓዬ፣ ከብርቱካን፣ ወዘተ. ይገኛሉ።
	በ. የተመጣጠነ ምግብ እጥረት በአዕምሮ እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያደርሳል።

ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ ውስጥ የሚገኘውን ሠንጠረዥ መሠረት በማድረግ በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ከፍተኛ የካርቦሃይድሬት መጠን ያለው የምግብ እህል ዓይነት የትኛው ነው?

ለ. በካሎሪ መጠን ተመጣጣኝ የሆኑት የምግብ ዓይነቶች ምንና ምን ናቸው?

ሐ. ዝቅተኛ የካልሲየም መጠን ያለው የምግብ ዓይነት የትኛው ነው?


መ. በፕሮቲን መጠን ከገብስና ከስንዴ የትኛው ይበልጣል?

ሠ. በኃይል ሰጪነቱ ዝቅተኛ የሆነው የምግብ ዓይነት የትኛው ነው?

ረ. በገንቢነቱ ከፍተኛ የሆነው የምግብ ዓይነት የትኛው ነው?

ተግባር 3

ከምንባቡ ውስጥ ያለውን ሠንጠረዥና ቀጥሎ የቀረበውን የግራፍ መረጃ በማገናዘብ፣ በግራፉ የሚገኙት ቋሚዎች የሚወክሉትን ምግቦች በምሳሌው መሠረት በደብተራችሁ ጻፉ።



ሀ. ነጭ ጤፍ

ለ. _____

ሐ. _____

መ. _____

ሠ. _____

ረ. _____

ሰ. _____

8ኛ ቀን

ቃላት

ቃላትንና ሐረጋትን በዓረፍተነገር ውስጥ መጠቀም

ተግባር

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላትና ሐረጋት በተጓደሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ በማስገባት አሟሉ።

እንዳይጠቃ	የበለፀጉ	የዕለትተዕለት
ለማዳበር	አሚልቶ	ጥንካሬ

ሀ. _____ ተግባርን ለማከናወን ጤነኛ መሆን ያስፈልጋል።

ለ. በማዕድን _____ ምግቦች ጤናማና ጠንካራ ያደርጋሉ።

ሐ. ወተት ሦስቱን የምግብ ዓይነቶች _____ የያዘ ምግብ ነው።

መ. ሰውነታችን በበሽታ _____ ተመጣጣኝ ምግብ መመገብ ያስፈልጋል።

ሠ. ካልሲየም ያላቸው ምግቦች መመገብ አጥንት _____ እንዲኖረው ያደርጋሉ።

ረ. ዘወትር የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ሰውነትን _____ ይጠቅማል።

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በዋናና መዘርዝር ሀሳቦች አጻጻፍ ስልት የተጻፈ አንቀጽ መከለስ

ተግባር

የሚከተሉትን መስፈርቶች በመጠቀም ባለፈው ሳምንት የጻፍኸውን አንቀጽ አስተካክላችሁ ጻፉ።

	የጽሑፍ መገምገሚያ መስፈርቶች	አዎ	የለም
ሀ	በጹሑፉ ውስጥ የፊደላት ስህተቶች አሉ?		
ለ	በጽሑፉ ውስጥ የሰዋስው ስህተት አለ?		
ሐ	ጽሑፉ በርዕሰጉዳዩ ላይ ያተኩራል?		
መ	በጽሑፉ ውስጥ በግልፅ የሚታይ ዋና ሀሳብ አለ?		
ሠ	ዋናውን ሀሳብ የሚያብራሩ መዘርዝር ሀሳቦች አሉ?		
ረ	በጽሑፉ ውስጥ መቀነስ ያለበት (አላስፈላጊ) ሀሳብ አለ?		
ሰ	የጎደለ (መጨመር ያለበት) ሀሳብ አለ?		

የአጻጻፍ ሥርዓት

የይዘት (አንድ ነጥብ) (.) አጠቃቀም

ተግባር

1. ቀጥሎ በሠንጠረዥ ውስጥ የቀረቡትን አጥረው የተጻፉ ቃላትና ሐረጋት አሟልታችሁ ጻፉ።

ያጠረው ቃል/ሐረግ	ሙሉ ቃሉ/ሐረጉ
ተ.መ.ድ.	
ተ.ቁ.	
ፀ.ሙ.ኪ.	
አስ.	
ኢ.መ.ማ.	

ወሮ.	
ምዕ.	
አ.ሕ.	

2. የሚከተሉትን መጠሪያዎች አሳጥራችሁ ጻፉ።

ሀ. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

ለ. ጎንደር ዩኒቨርሲቲ

ሐ. መምህር ርዕሰመምህር ሱፐርቫይዘር

መ. ወላጅ ተማሪ መምህር ሕብረት

ሠ. የቀበሌ ትምህርትና ስልጠና ቦርድ

9ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

የተመጣጠነ ምግብ ጥቅም

ቅድመንባብ

ተግባር

የተመጣጠነ ምግብ አለመመገብ ምን ጉዳት ያለው ይመስላችኋል?

ማንበብ

ተግባር


«የተመጣጠነ ምግብ ጥቅም» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የመጀመሪያዎቹን አምስት አንቀጾች በቡድን ሆናችሁ በጋራ አንብቡ።

መናገር

ሀሳብን በቢጋር ሳጥን አደራጅቶ መናገር

ተግባር

የሚከተለውን የቢጋር ሳጥን በደብተራችሁ አዘጋጁ። ከዚያም በአካባቢያችሁ የሚመረቱ የምግብ ዓይነቶችን መሠረት አድርጋችሁ በሠንጠረዡ ውስጥ በመሙላት ንግግር አድርጉ።



ማሳሰቢያ፡-በሚከተለው መልኩ ሀሳባችሁን አደራጅታችሁ መናገር ትችላላችሁ።

እነዚህ የምግብ ዓይነቶች በአካባቢዬ ስለሚመረቱ፣

ቁርሴን፡- _____፣ _____፣ _____ ምግቦችን

ምሳዬን፡- _____፣ _____፣ _____ ምግቦችን

ራቴን፡- _____፣ _____፣ _____ ምግቦችን

በማዘጋጀት የተመጣጠነ ምግብ መመገብ እችላለሁ።

ሰዋስው

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የወል ስሞች፣ የተጸውዖ ስሞችና ግሶች በተገቢ ቦታቸው በማስገባት ዓረፍተነገሮቹን አሟሉ።

ተመረቀች	ነሐሴ	ሄደ
ጀሚላ	ተመለሰች	ትመረምራለች
ዶክተር	ቅዳሜ	ይዘንባል

ሀ. በ_____ ወር ዝናብ _____።

ለ. _____ ትናትና ከጎንደር _____።

ሐ. ናሥር በሩጫ ወደቤቱ _____።

መ. የወይዘሮ አልጋነሽ ልጅ _____ ዕለት _____።

ሠ. _____ ነቢያት በሽተኞቿን በጥንቃቄ _____።



ምዕራፍ 7 የዱር እንስሳት በኢትዮጵያ

የዱር እንስሳት

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

የቃላት ጥናት

ተግባር

1. የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	ው-ድ-ን-ቢ	ውድንቢ
ለ	አ-ም-ባ-ራ-ይ-ሌ	አምባራይሌ
ሐ	ይ-ሸ-ለ-ከ-ለ-ካ-ለ	ይሸለከለካለ
መ	ታ-ን-ዛ-ን-ያ	ታንዛንያ

2. የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	የሚ-ታወቁ-ብ-ኣቸው	የሚታወቁባቸው
ለ	እንደ-መመሳሰል-ኣቸው	እንደመመሳሰላቸው
ሐ	ቅጠል-ኣ-ቅጠል	ቅጠላቅጠል
መ	ከ-ጠላት-ኦች-ኣቸው	ከጠላቶቻቸው
ሠ	በ-ቅልጥም-ኦች-ኣቸው	በቅልጥሞቻቸው

ማንበብ

የአጋዘን አስተኔ

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር

የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጁ። ከዚያም ስለአጋዘን የምታውቁትንና ማወቅ የምትፈልጉትን በሠንጠረዡ ውስጥ ዘርዝሩ።

የማውቀው	ማወቅ የምፈልገው	ከምንባቡ የተማርኩት
•	•	•
•	•	•
•	•	•

የማንበብ ሂደት

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ። በቅድመንባብ ላይ «ማወቅ የምፈልገው» ብላችሁ የዘረዘራችኋቸው ነገሮች በምንባቡ ውስጥ መኖራቸውን ወይም አለመኖራቸውን እያስተዋላችሁ አንብቡ።


የአጋዘን አስተኔ

ሴት ውድንቢዎች ቀንድ አላቸው።

የአጋዘን አስተኔ ስምንት ዓይነት ዝርያዎች አሉት። ሁሉም ዝርያዎች በአፍሪካ ብቻ ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል አንዱ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኘው የደጋ አጋዘን ነው። በብዙ የአፍሪካ አገሮች የሚገኙት አጋዘን፣ አምባራይሌ፣ ድኩላና ውድንቢ የዚህ ቡድን አባሎች ናቸው። የአጋዘን አስተኔዎች ከሌሎች የዱር እንስሳት ተለይተው የሚታወቁባቸው የጋራ ባህርያት አሏቸው። ሁሉም ወንዶች ጥምዝ ቀንዶች አሏቸው። ከውድንቢ ሴቶች በስተቀር የሌሎቹ ሴት ዝርያዎች ቀንድ የላቸውም። በተጨማሪም የአጋዘን አስተኔዎች በሆዳቸውና በደረታቸው የሚወርዱ ነጫጭ መስመሮች አሏቸው። ቅጠላቅጠልም ይበላሉ።


የአጋዘን አስተኔዎች እንደተመሳሰሏቸው ሁሉ ልዩነትም አላቸው። ይህንንም የደጋ አጋዘንን፣ ድኩላንና ውድንቢን በመመልከት መረዳት ይቻላል።

የደጋ አጋዘን



የደጋ አጋዘኖች በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የአጋዘን አስተኔ ዝርያዎች ናቸው። ወንዶቹ ጥምዝ ቀንድ ሲኖራቸው ደረታቸውም አበጥ ያለ ሆኖ ባለሻኛ ናቸው። ሴቶቹ ግን ቀንድ የላቸውም። የወንዶቹ የሰውነት መጠን ከሴቶቹ ይበልጣል። ክብደታቸውም እጥፍ ይሆናል። የሁሉም የፀጉር ቀለም መደቡ የገረጣ ጉበት የመሰለ ቡናማ ቢጤ ነው። የተበታተኑ ነጫጭ ነጠብጣቦችና ከጀርባቸው ወደሆዳቸውና ወደደረታቸው የሚወርዱ ነጫጭ መስመሮች አላቸው። ከአርሲ ተራራዎች ጀምሮ በባሌ ተራራዎች አልፎ እስከሐረርጌ የጨርጨር ተራራዎች ድረስ ይገኛሉ።

የደጋ አጋዘኖች በአብዛኛው ቅጠላቅጠል ቢበሉም አንዳንዴ ሣር ሲበሉ ይታያሉ። በተጨማሪም የቲማቲም ዝርያዎችንና በበጋ ወራት ደግሞ የረገፉ የኮሶ ቅጠሎችን ይበላሉ።



ድኩላ

ድኩላዎች መካከለኛ የሰውነት መጠን ያላቸው፣ ከሰሃራ በስተደቡብ በብዙ ሥፍራዎች የሚገኙ እንስሳት ናቸው። ወንዶቹ ከ40-80 ኪ.ግ.፣ ሴቶቹ ደግሞ ከ25-60 ኪ.ግ. ይመዝናሉ። ወንዶቹ ባለአንድ ጥምዝ ቀንድ ሲኖራቸው ሴቶቹ ግን ቀንድ የላቸውም።

ድኩላዎች መንጋ ሠርተው አይገኙም።


ድኩላዎች ደኖች በሚበዙበት አካባቢ ይኖራሉ። ብቸኝነትን ስለሚመርጡ መንጋ ሠርተው አይገኙም። አብረው የሚኖሩት እናትና የመጨረሻ ልጇ ብቻ ናቸው። ራሳቸውን ከጠላቶቻቸው የሚከላከሉት በጫካ ውስጥ በመደበቅ ነው። የፀጉራቸው ቀለምም ከእይታ ለመከላከል ያመቻቸዋል።

ድኩላዎች በአብዛኛው ቅጠላቅጠል የሚመገቡ ቢሆኑም ጨሌ ሣርም ይግጣሉ። ቀን ቀን ቅጠላቅጠል ሲበሉ፣ ሌሊት ሌሊት ደግሞ ሣር ይግጣሉ። አብዛኛውን ጊዜ ከውኃ ርቀው መኖር አይመርጡም።

በኢትዮጵያ ሁለት ዓይነት ድኩላዎች ይገኛሉ። አንደኛው በባሌ ተራራዎችና በሌሎች ከፍተኛ ሥፍራዎች የሚገኘው የምኒሊክ ድኩላ የሚባለው ነው። ይህም

በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ የአጋዘን አስተኔ ቡድን አባል ነው። ሁለተኛው የድኩላ ዓይነት ግን ከኢትዮጵያ ውጭ በሌሎች አገሮች ይገኛል።

ውድንቢ



ከአጋዘን አስተኔዎች ሁሉ ግዙፉ ውድንቢ ነው። ወንዱ በአማካይ ከ500-600 ኪ.ግ.፣ ሴቷ ከ340-445 ኪ.ግ. ይመዝናሉ። ሁለቱም ፆታዎች አጫጭር ጥምዝ ቀንዶች አሏቸው። የወንዶቹ ቀንዶች ርዝመት 54 ሳ.ሜ. ነው። የሴቶቹ ደግሞ 60.5 ሳ.ሜ. ይሆናል። የሁለቱም ፆታዎች ጭራ እንደከብት ጅራት ረዘም ብሎ ከጫፉ ላይ ጎፈር አለው። የፀጉራቸው ቀለም ፈዛዛ ቡኒ ሆኖ ከዕድሜ መጨመር ጋር እየጠቆረ የሚሄድ ነው። ከ10-16 የሚሆኑ ነጫጭ መስመሮች ከጀርባቸው ይወርዳሉ። እንዲሁም ጠቆር ያለ ሻኛና በቅልጥሞቻቸው ላይ ነጫጭ ምልክቶች አሏቸው። ወንዶቹ ግን በግንባራቸውና በአፍንጫቸው ላይ ጥቂቁር ጎፈሬ አላቸው። በተጨማሪ አንገታቸው ግዙፍ ሆኖ ከርዳዳ ጋማ አለበት።

ውድንቢዎች በኢትዮጵያ በኦሞ ፓርክ፣ ከኢትዮጵያ ውጪ ደግሞ በደቡብ ሱዳን፣ በደቡብ ሱማሌ፣ በኬንያና በታንዛንያ ይገኛሉ። በየትኛውም የአየር ንብረት ውስጥ መኖር ይችላሉ። የተለያዩ ዕፅዋትን ይመገባሉ፤ ላልተወሰነ ጊዜ ያለውኃ መኖር ይችላሉ። ሌሊትም፣ ቀንም ይመገባሉ። ኑሯቸው ማኅበራዊ ሲሆን እስከ100 አባላት ያሉት መንጋ በብዙ ቦታዎች ማየት የተለመደ ነው።

(ሰለሞን ይርጋ። 2000። *አጥቢዎች*። ከገፅ 8-24 ለውጥ ተደርጎበት የቀረበ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የአጋዘን አስተኔ ዝርያዎች መለያዎች በሠንጠረዡ ውስጥ ጻፉ።

የእንስሳቱ መለያዎች	የእንስሳቱ ዝርያዎች		
	የደጋ አጋዘን	ድኩላ	ውድንቢ
ቀንድ	• ወንዶቹ ብቻ ጥምዝ ቀንድ አላቸው።		• ሁለቱም ፆታዎች ጥምዝና አጭር ቀንድ አላቸው
አመጋገብ			
አኗኗር			
የሰውነት መጠን			

ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ከአጋዘን አስተኔዎች በቡድን የማይታዩት የትኞቹ ናቸው?

ለ. ከአጋዘን አስተኔዎች በመንጋቸው ውስጥ ብዛት ያላቸው የትኞቹ ናቸው?

ሐ. «ከእይታ ለመከላከል ያመቻል» ማለት ምን ማለት ነው?

መ. ውድንቢዎች ላልተወሰነ ጊዜ ያለውኃ እንዴት መኖር የሚችሉ ይመስላችኋል?

ሠ. ሴት ውድንቢዎች ከድኩላና ከደጋ አጋዘን ዝርያዎች በምን ይለያሉ?

2ኛ ቀን

ቃላት

ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት

ተግባር 1

በ«ሀ» ረድፍ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ«ለ» ረድፍ በመምረጥ አዛምዳችሁ ጻፉ።

ሀ	ለ
1.ደን	ሀ. ጫካ
2.ጨሌ	ለ. ለምለም ሣር
3.እጥፍ	ሐ. ድርብ
4.ገረጣ	መ. ትልቅ
5.ግዙፍ	ሠ. አመዳማ ሆነ

ተግባር 2

«አጋዘን አስተኔ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ውስጥ ቀለምን የሚገልጹ ቃላትን ለይታችሁ በምሳሌው መሠረት በደብተራችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡- ነጭ = በረዶ፣ ጥጥ...


መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በማወዳደርና በማነፃፀር ስልት የቢጋር ምስል ማዘጋጀት

ተግባር

የሚከተለውን የቢጋር ምስል በደብተራችሁ አዘጋጁ። ከዚያም «የበግንና የፍየልን ተመሳስሎዎችና ልዩነቶች» በቢጋር ሠንጠረዡ ዘርዝሩ።



የአጻጻፍ ሥርዓት

ተግባር 1

በፊደል የተጻፉትን ብርና ሳንቲሞች አንድ ነጥብን በመጠቀም በቁጥር ጻፉ።

ሀ. አንድ ብር ከሀያ አምስት ሳንቲም

ለ. ስድስት ብር ከሰላሳ ሳንቲም

ሐ. አሥራሰባት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም

መ. ሀያ አምስት ብር ከአምስት ሳንቲም

ተግባር 2

የሚከተሉትን ሙሉና ሸርፍራፊ ቍጥሮች በፊደል ጻፉ።

ሀ. 3.5 ለ. 7.25 ሐ. 2.75

ተግባር 3

የምትወዷቸውን የአምስት እንስሳት ስም በተራቁጥር ወደጎን ዘርዝራችሁ ጻፉ።

3ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

የአጋዘን አስተኔ

ቅድመንባብ

ተግባር

«የአጋዘን አስተኔ» በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ የተጠቀሱት የዱር እንስሳት ምን ምን ናቸው? በምን ይመሳሰላሉ? በምንስ ይለያያሉ?

ማንበብ

ተግባር

«የአጋዘን አስተኔ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የመጀመሪያዎቹን ሦስት አንቀጾች ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ ተራበተራ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ማዳመጥ

የዝንጀሮዎች አኗኗር







ቅድመማዳመጥ

ተግባር

«የዝንጀሮዎች አኗኗር» የሚለውን ርዕስና ሥዕሉን መሠረት አድርጋችሁ የመጀመሪያዎቹን ሁለት የሠንጠረዥ ክፍሎች አሟሉ።

ስለዝንጀሮዎች የማውቀው	ስለዝንጀሮዎች ማወቅ የምፈልገው	ስለዝንጀሮዎች የተማርኩት
•	•	•
•	•	•
•	•	•
•	•	•

የማዳመጥ ሂደት

ተግባር

«የዝንጀሮዎች አኗኗር» በሚል ርዕስ መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ ማስታወሻ እየያዛችሁ በጥሞና አዳምጡ፤ የሚጠይቋችሁንም ጥያቄዎች መልሱ።

አዳምጠ መረዳት

ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በቅድመማዳመጥ የጀመራችሁትን ሠንጠረዥ 3ኛ ረድፍ አሟሉ።

ለ. ዝንጀሮዎች በምን በምን ይመሳሰላሉ?

ሐ. ዝንጀሮዎች በምን በምን ይለያያሉ?

መ. ከዝንጀሮዎች አኗኗር የትኛውን ወደዳችሁት? ለምን?

ሠ. ከዝንጀሮዎች አኗኗር ያልወደዳችሁት አለ? ለምን?

ረ. ጭላዳ ዝንጀሮዎች የመኝታ ስፍራቸውን በየቀኑ የሚለዋውጡት ለምን ይመስላችኋል?

ሰዋስው

ስም እንደባለቤት

ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ባለቤቶች በምሳሌው መሠረት ለዩ።

ምሳሌ፡- ሀቢባ ጠረጴዛ ጠገነች።

ጥያቄ፡- ጠረጴዛ የጠገነችው ማን ናት?

ባለቤት ⟶ ሀቢባ

ሀ. ፅንፍነሽ ቀሚስ ለበሰች።

ለ. ውሻው አጥንት በላ።

ሐ. መስከረም መጽሐፍ ታነባለች።

መ. ድመቷ ዛፍ ላይ ወጣች።

ሠ. ዳንኤል የአፍሪካን ካርታ ሣለ።

ረ. ዳዊትና ዘሀራ ወደገበያ ሄዱ።

ተግባር 2

«የአጋዘን አስተኔ» ከሚለው ምንባብ የዓረፍተነገር ባለቤት የሆኑ ስሞችን በደብተራችሁ ጻፉ።

ማንበብ

ዋልያና ቀይ ቀበሮ

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የምታውቋቸውን የዱር እንስሳት ዘርዝሩ።

ለ. ሥዕሉን በመመልከት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

የማንበብ ሂደት


ተግባር

ማንበብ ከመጀመራችሁ በፊት የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጁ። ከዚያም በምታነቡበት ጊዜ እየጠየቃችሁና ለጥያቄዎቻችሁ መልስ እየሰጣችሁ አንብቡ።


ጥያቄዎች	መልሶች
• ስለዋልያና ቀይ ቀበሮ ምን አውቃለሁ? • የማነበው ነገር ገብቶኛል? ካልገባኝ ምክንያቱ ምንድን ነው? • ስለጽሑፉ ምን ተሰማኝ?	

ዋልያና ቀይ ቀበሮ

ዋልያና ቀይ ቀበሮ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ የዱር እንስሳት ናቸው። እነዚህ ብርቅዬ የዱር እንስሳት፣ የሚመሳሰሉባቸውና የሚለያዩባቸው ባህርያት አሏቸው። እነዚህም ባህርያት እንደሚከተለው ቀርበዋል።



ዋልያ



ቀይ ቀበሮ

ዋልያና ቀይ ቀበሮ ተመሳሳይ ባህርይ ያላቸው የዱር እንስሳት ናቸው። ሁለቱም አጥቢ፣ ሰውንና ሌሎችን ለማዳ እንስሳት የማይተናኮሉ ገር የዱር እንስሳት ናቸው። ለመኖሪያነትም ከፍተኛ ተራራዎችን ይመርጣሉ። እነዚህን የዱር እንስሳት ለመጎብኘት ከሚመጡ የውጭና የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች በርካታ ገቢ ይገኛል። ዋልያና ቀይ ቀበሮ በፓርኮች ውስጥ ጥበቃና እንክብካቤ እየተደረገላቸው ይኖራሉ። በዚህም ምክንያት ለህገወጥ አደን አይጋለጡም። ስለሆነም ዝርያቸውም እንዳይጠፋና እንዲቀጥል ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥሮላቸዋል።

የዋልያ ምድብ ከፍየል ሲሆን የቀይ ቀበሮ ደግሞ ከውሻ ነው።

ዋልያና ቀይ ቀበሮ እንደሚመሳሰሉ ሁሉ ልዩነትም አላቸው። የዋልያ ቁመት እስከአንድ ሜትር ሲደርስ የቀይ ቀበሮ ቁመት ደግሞ 60 ሳንቲ ሜትር ነው። የዋልያ ምድብ ከፍየል ሲሆን የቀይ ቀበሮ ደግሞ ከውሻ ነው። ዋልያ ሳርና ቅጠላቅጠል ሲመገብ፤ ቀይ ቀበሮ ግን ሥጋ ይበላል። ዋልያ የሚመገበውን ምግብ ያመሰኳል (ያመነቧርካል)፣ ቀይ ቀበሮ ግን አያመሰኳም።

ዋልያዎች ቀንድ አላቸው። ትላልቆች ወንዶች፣ ወፍራምና ከባድ ክርክር ያለባቸው እንደደጋን ወደኋላ የተቀለበሱ ቀንዶች አሏቸው። አንዳንድ ጊዜ የቀንዶቹ ርዝመት ከአንድ ሜትር ሊበልጥ ይችላል። የቀንዳቸው ክብደትም ከ13 ኪሎ ግራም በላይ ይሆናል። ሴቶቹ ዋልያዎች ደግሞ አጠር ቀጠን ብለው ጥልቅ ክርክር የሌለባቸው ቀንዶች አሏቸው። ቀይ ቀበሮ ግን ቀንድ የለውም።

የዋልያ ሥጋ እንደፍየል ሥጋ ስለሚጥም ሰዎች ለምግብነት ያድኑታል። ቀይ ቀበሮ ግን ሥጋው ስለማይበላ ሰዎች አያድኑትም። የዋልያ ጅራት ልክ እንደፍየል ጅራት አጭር ነው። የጭራው ፀጉርም አጭር ሆኖ እንደቡርሽ ከርዳዳ ነው። የቀይ ቀበሮ ጅራት ረጅም ከመሆኑም በላይ ብዙ ፀጉር አለው።

በአጠቃላይ ዋልያና ቀይ ቀበሮ የሚመሳሰሉባቸውና የሚለያዩባቸው ባህርያት አሏቸው። ከሚያመሳስሏቸው ባህርያት አንዱ ሁለቱም በኢትዮጵያ ብቻ መገኘታቸው ነው። ሁለተኛው በከፍተኛ ተራራዎች መኖርን መምረጣቸው ነው። ሶስተኛው በፓርኮች ውስጥ ጥበቃና እንክብካቤ እየተደረገላቸው መኖራቸው ነው። አራተኛው አጥቢ እንስሳት መሆናቸው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ዋልያና ቀይ ቀበሮ በዝርያቸው፣ በአመጋገባቸውና በቁመታቸው ይለያያሉ።

(ፍሰሐ ሃይለመስቀል። 1966። *የኢትዮጵያ ታላላቅ አራዊት*። ከገፅ 61-72 ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ከዋልያና ከቀይ ቀበሮ በተጨማሪ በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱት በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የዱር እንስሳት ምን ምን ናቸው?

ለ. ዋልያና ቀይ ቀበሮ የሚኖሩት የት ነው?

ሐ. ዋልያና ቀይ ቀበሮ ለሕገወጥ አደን ያልተጋለጡት በምን ምክንያት ይመስላችኋል?

መ. ዋልያ የሚመገበው ምንድን ነው? ቀይ ቀበሮስ?

ሠ. በወንድና በሴት ዋልያዎች ቀንድ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ረ. ዋልያና ቀይ ቀበሮ የሚመሳሰሉባቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?

ሰ. ዋልያና ቀይ ቀበሮ ብርቅዬ የዱር እንስሳት የተባሉት ለምንድን ነው?

ሸ. ብርቅዬ የዱር እንስሳትን መጠበቅና መንከባከብ ለሀገራችንና ለዓለም ምን ጠቀሜታ አለው?

ቀ. «ቀይ ቀበሮ ሥጋው አይበላም» የተባለው ለምን ይመስላችኋል?

በ. ከዋልያ ሌላ የሚያመሰኩ (የሚያመነዥኩ) እንስሳትን ጥቀሱ።

ተ. የዋልያ ሥጋ የሚጥም ከሆነ እንደበግና ፍየል ሥጋ ለምግብነት የማይውለው ለምን ይመስላችኋል?

ተግባር 2

በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኙ የዱር እንስሳት የተለያዩ ጽሑፎችን አንብባችሁ በአጭሩ ጽፋችሁ አቅርቡ።

5ኛ ቀን

ቃላት

በአንቀጽ ውስጥ የተጓደሉ ቃላትን ማሟላት

ተግባር

የሚከተሉትን ቃላት በተገቢ ቦታቸው በማስገባት የተጓደለውን አንቀጽ አሟልታችሁ ጻፉ።

ምድባቸው	ያመነሸኮሳሉ	ይጥማል	ለአዳኞች
አደን	የማይተናኮሉ	ብርቅዬ	

በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ _____ የዱር እንስሳት በፓርክ ውስጥ ይኖራሉ። በመሆኑም ከሕገወጥ _____ ና ከሚተናኮላቸው ተባራሪ እንስሳትም ሆነ ሰው ነፃ ናቸው። ከነዚህ በፓርክ ውስጥ እንክብካቤ ከሚደረግላቸው እንስሳት መካከል ዋልያዎች ይገኙበታል። ዋልያዎች ሰው _____ ገር እንስሳት ናቸው። የሚኖሩት በሰሜን ተራራ በመሆኑ ምግባቸው ሳርና ቅጠላቅጠል ነው። በመኝታ ጊዜም _____። ዋልያዎች _____ ክፍየል በመሆኑ ሥጋቸው _____። በዚህ የተነሳ _____ እንዳይጋለጡ ጥበቃ ይደረግላቸዋል።

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በማወዳደርና በማነፃፀር ስልት አንቀጽ መጻፍ

ተግባር

ባለፈው ሳምንት ያዘጋጃችሁትን የቢጋር ሠንጠረዥ መነሻ በማድረግ በማወዳደርና በማነፃፀር ስልት ሁለት አንቀጽ ጻፉ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

የይዘት (የአንድ ነጥብ) አገላለጽ

ተግባር

1. በፊደል የተጻፉትን ብርና ሳንቲሞች አንድ ነጥብን በመጠቀም በቁጥር ጻፉ።
   ሀ. አሥራሦስት ብር ከሰማኒያ ሳንቲም
   ለ. ሀያ አራት ብር ከሰላሣ አምስት ሳንቲም

ሐ. ሀምሳ አንድ ብር ከሃምሳ አምስት ሳንቲም

መ. ዘጠና ዘጠኝ ብር ከአሥራ አምስት ሳንቲም

2. በፊደል የተጻፉትን ሙሉና ሽርፍራፊ ቁጥሮች አንድ ነጥብን በመጠቀም በቁጥር ጻፉ።

ሀ. ሦስት ነጥብ አምስት

ለ. አሥር ነጥብ አንድ

ሐ. ሀያ አምስት ነጥብ ዜሮ ሁለት

መ. ሰላሳ ዘጠኝ ነጥብ ሰባት አንድ

3. የአጋዘን አስተኔ ዝርያዎችን በተራ ቁጥር ከላይ ወደታች ዘርዝሩ።

6ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

ዋልያና ቀይ ቀበሮ

ቅድመንባብ

ተግባር

ዋልያና ቀይ ቀበሮ የሚመሳሰሉባቸውንና የሚለያዩባቸውን ባህርያት ዘርዝሩ።

ማንበብ

ተግባር

«ዋልያና ቀይ ቀበሮ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የመጀመሪያዎቹን ሦስት አንቀጾች በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ተራበተራ ድምፅ እያሰማችሁ አንብቡ።

መናገር

በማወዳደርና በማነፃፀር መናገር

ተግባር

ሀ. የድመቶችንና የውሾችን ተመሳስሎና ልዩነት ተናገሩ።

ለ. ከሁለቱ ይበልጥ ጠቃሚ የሆኑትስ የትኞቹ ይመስሏችኋል?

ሰዋስው

የወልና የተጸውዖ ስሞች እንደባለቤት

ስም እንደባለቤት

ተግባር 1

ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ባለቤቶች ለዩ። ከዚያም ባለቤቶቹ የተጸውዖ ወይም የወል ስሞች መሆናቸውን ለይታችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡- ልጆቹ ምግብ ያዘጋጃሉ።

ባለቤት ⟶ ልጆቹ

የስሙ ዓይነት ⟶ የወል ስም

ሀ. ዓሣ በባህር ውስጥ ይኖራል።

ለ. አባቴና እናቴ የመንግሥት ሠራተኞች ናቸው።

ሐ. በሸርና ወይንሸት የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር ዘመሩ።

መ. ፍየሎች ቅጠላቅጠል ይበላሉ።

ሠ. ያለምወርቅና ራህመት ወደቤታቸው ሄዱ።

ረ. ብዙ ቤቶች በአውሎንፋስ ፈረሱ።

ሰ. መሐመድ አዘውትሮ ያጠናል።

ተግባር 2

«ዋልያና ቀይ ቀበሮ» በሚለው ምንባብ ውስጥ የዓረፍተነገር ባለቤት የሆኑ የተጸውዖና የወል ስሞችን በደብተራችሁ ዘርዝሩ።

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ተግባር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	ፓርክ-አች	ፓርኮች
ለ	ሥነ-ምህዳር	ሥነምህዳር
ሐ	የሚ-ለያይ-አ-ብ-ላቸው	የሚለያዩባቸው
መ	የሚመሳሰል-አ-ብ-ላቸው	የሚመሳሰሉባቸው
ሠ	አዛውንት-አች-ም	አዛውንቶችም
ረ	የ-ተቋቋመ-ው	የተቋቋመው
ሰ	እየ-ተደረገ-ል-ላቸው	እየተደረገላቸው

ማንበብ

በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ይዞታ

ቅድመንባብ

ከካርታ መረጃ ማግኘት

ተግባር


በካርታው ላይ የተጠቀሱት ብሔራዊ ፓርኮች ማን ማን ናቸው? በየትኞቹ ክልልስ ይገኛሉ?

የማንበብ ሂደት

ቀጥሎ በማወዳደርና በማነፃፀር የቀረበውን ምንባብ አንብቡ። ስታነቡ በሠንጠረዡ ያሉትን ጥያቄዎች በአዕምሯችሁ እያሰላሰላችሁ መልሶቻችሁን ከጐን አስፍሩ።

ጥያቄዎች	መልሶች
በኢትዮጵያ ስለሚገኙ የዱር እንስሳትና ፓርኮች ምን አውቃለሁ? የማነበው ነገር እየገባኝ ነው? ያልገባኝ ለምንድን ነው? ምን ተሰማኝ?	

በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ይዞታ



ብሔራዊ ፓርኮች የሚገኙበትን አካባቢ የሚያሳይ ካርታ

በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ቁጥር እየተመናመነ የመጣው በአደንና በደን ጭፍጨፋ ምክንያት ነው።

ከጥቂት ዓመታት በፊት በኢትዮጵያ በርካታ የዱር እንስሳት ዓይነቶች ይገኙ ነበር። በአዋሽና በሌሎችም አካባቢዎች ቀጭኔዎችና ዝሆኖች ይገኙ ነበር። በቢሾፍቱና በአዳማ መካከል በርከት ያሉ ልዩ ልዩ የዱር እንስሳት ይኖሩ እንደነበር በሕይወት ያሉ አዛውንቶች ይናገራሉ። ለምሳሌ ከ100ሺህ ከሚያንሱ ዝሆኖች በአሁኑ ጊዜ የቀሩት ወደ3ሺህ የሚገመቱ መሆናቸውን አንዳንድ የተፈጥሮ ሀብት ሊቃውንት ይገልጻሉ። እንዲሁም የዛሬ 70 ዓመት በኡጋዴን የቆርኪ መንጋ በቀላሉ ይታይ ነበር፤ አሁን ግን በዚያ አካባቢ ለምልክት እንኳን አንድም አይገኝም። ሌሎችም የዱር እንስሳት ዓይነታቸው ከናካቴው ባይጠፋም ቁጥራቸው እየተመናመነ በመሄድ ላይ ነው።

በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ቁጥር እየተመናመነ የመጣው በሁለት ምክንያቶች ነው። አንደኛው አደን ነው። በጥንት ጊዜ ጀግንነት ይመዘን የነበረው በገደሉት የዱር እንስሳት ቁጥር ልክ ነበር። ገንዘብ ሳያወጡ ወይም ሳያረቡ ሥጋ መብላት የሚቻለው የዱር እንስሳትን በማደን ነበር። በተጨማሪም አንዳንድ የዱር እንስሳት ለጥርሳቸውና ለቆዳቸው ሲባል ይታደኑ ነበር። የእርሻ መስፋፋት ደግሞ ሁለተኛው ምክንያት ነው። ለእርሻ ሲባል የዱር እንስሳት የሚኖሩባቸው ጫካዎች ሲቃጠሉና ሲመነጠሩ አካባቢውን ለቀው ይሰደዳሉ። በሜዳ ላይ የሚገኙትም ለአዳኞች ይጋለጣሉ። በዚህም ሁኔታ የዱር እንስሳቱ ቁጥር ቀንሷል።

ፓርኮች ለዱር እንስሳት የሚሰጡት ጥቅም

አሁን ያሉት የዱር እንስሳት በዓይነትም ሆነ በብዛት እየቀነሱ ሄደው ዘራቸው እንዳይጠፋ ለመንከባከብና ለመጠበቅ ፓርኮች ተቋቁመዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ ከተቋቋሙት ፓርኮች መካከል የአዋሽ፣ የሰሜንና የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርኮች ተጠቃሾች ናቸው። ፓርኮቹ የሚመሳሰሉባቸውና የሚለያዩባቸው ባህርያት አሏቸው።

የአዋሽ፣ የሰሜንና የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርኮች ለተለያዩ የዱር እንስሳት መጠለያ በመሆን ያገለግላሉ። የዱር እንስሳቱ በህገወጥ አደን እንዳይገደሉ ዋስትና ይሆናሉ። የገቢ ምንጭ በመሆንም ያገለግላሉ። የዱር እንስሳቱን ለመጎብኘት ወደፓርኮቹ የሚመጡ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ዜጎች የሚከፍሉት ገንዘብ ለልዩ ልዩ ልማት እገዛ ያደርጋል። ፓርኮቹ ጥበቃ ስለሚደረግላቸው ደኖች አይመነጠሩም። ይህም አካባቢዎች ለምለምና አረንጓዴ እንዲሆኑና ዕፅበል የዱር እንስሳትም ምግባቸውን በቀላሉ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል።

የአዋሽ፣ የሰሜንና የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርኮች ልዩነት

የአዋሽ፣ የሰሜንና የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርኮች የሚለያዩባቸውም ባህርያት አሏቸው። ፓርኮቹ በኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ይገኛሉ። የአዋሽ ፓርክ በኦሮምያና በአፋር ክልሎች ሲገኝ የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ደግሞ በኦሮምያ ክልል ይገኛል። የአዋሽ ብሔራዊ ፓርክ መገኛ አዋሽ አካባቢ ሲሆን የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ደግሞ በባሌ ተራራዎች ነው። የሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ የሚገኘው በአማራ ክልል፣ በሰሜን ጎንደር ዞን በራስዳሸን ተራራዎች ውስጥ ነው። የሦስቱም ፓርኮች ክልል የተለያየ ስፋት አለው። አዋሽ ብሔራዊ ፓርክ 756፣ ሰሜን ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ 220፣ ባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ ደግሞ 2220 ስኩዬር ኪሎሜትር የመሬት ስፋት አላቸው።

የትኛው ፓርክ በየትኞቹ እንስሳት ላይ ያተኩራል?

የአዋሽ፣ የሰሜንና የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርኮች የተቋቋሙት የዱር እንስሳትን ደህንነት ለመጠበቅ ሲሆን የተለያየ ትኩረት አላቸው። የአዋሽ ፓርክ የተቋቋመው ሳላ፣ የሜዳ ፍየል፣ አምባራይሌ፣ ክርክሮ፣ ዝንጀሮ፣ ደፈርሳ፣ ሰስ፣ ብሆር፣ ድኩላ፣ አቦሸማኔ፣

የሚዳ አህያ፣ ኤንሸ፣ ተኩላና አንበሳ የተባሉትን እንስሳት ደህንነት ለመጠበቅና ለመንከባከብ ነው።

የሰሜን ተራራዎች ፓርክ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኘውን ዋልያ ለመንከባከብና ዝርያው እንዳይጠፋ ዋስትና ለመስጠት የተቋቋመ ነው። በተጨማሪም ጭላዳ ዝንጀሮና ቀይ ቀበሮ የሚባሉ የኢትዮጵያ ብርቅዬ የዱር እንስሳት ይገኙበታል። ሰስ፣ ድኩላና ጉሬዛም በፓርኩ ውስጥ ይኖራሉ። የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ የደጋ አጋዘን የተባለውን የኢትዮጵያ ብቻ የሆነ የዱር እንስሳ ከጥፋት ለመታደግ ሲባል ነው የተቋቋመው። ዝርያቸው ከኢትዮጵያ ውጭ የማይገኙ የምኒሊክ ድኩላና ቀይ ቀበሮም ይገኙበታል። ብሆር፣ ሚዳቋና አነር የተባሉ የዱር እንስሳትም በዚህ ፓርክ ውስጥ ይገኛሉ።

በሀገራችን የሚገኙት የዱር እንስሳት እንዳይጠፉ መጠበቅ ይኖርባቸዋል። የአዋሽ፣ የሰሜንና የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርኮችም የተቋቋሙት ለዚሁ ተግባር ተብሎ ነው። በእነዚህ ፓርኮች ውስጥ በርካታ የዱር እንስሳት ጥበቃ እየተደረገላቸው ይገኛሉ። ዋልያ፣ የምኒልክ ዱኩላ፣ ቀይ ቀበሮና ጭላዳ ዝንጀሮ የተባሉ ብርቅዬ እንስሳትም ይገኙባቸዋል። ስለሆነም አሁን ያሉት ፓርኮች የበለጠ መጠናከር ይኖርባቸዋል። በሌሎችም አካባቢዎች አዳዲስ ፓርኮች ቢቋቋሙ በአደጋ ላይ የሚገኙ የዱር እንስሳትን መታደግ ይቻላል።

ዊኪፒዲያ። እና (ፍሰሐ ሃይለመስቀል። 1966። *የኢትዮጵያ ታላላቅ አራዊት*። ከገጽ 111-113 ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

በምንባቡ መሠረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በቃላችሁ መልሱ።

1. የዛሬ 70 ዓመት በአጋዴን አካባቢ ይገኝ የነበረው የዱር እንስሳ ምን ነበር?

   ሀ. ዝሆን ሐ. የሚዳ አህያ

   ለ. ቀጭኔ መ. ቆርኪ

2. ፓርኮች በምን ይመሳሰላሉ?

   ሀ. በገቢ ምንጭነት ሐ. በቦታ ስፋት

   ለ. በመገኛ አካባቢ መ. በእንስሳት ብዛት

3. በምንባቡ ከተጠቀሱት ፓርኮች መካከል ሰፊው የትኛው ነው?

   ሀ. የባሌ ተራራዎች ሐ. የሰሜን ተራሮች

   ለ. አዋሽ መ. እኩል ናቸው።

4. ብሔራዊ ፓርኮቹ በስፋታቸው ቅደምተከተል ሲቀመጡ ትክክለኛው የትኛው ነው?

ሀ. አዋሽ፣ ሰሜን ተራሮች፣ ባሌ ተራሮች

ለ. ሰሜን ተራሮች፣ ባሌ ተራሮች፣ አዋሽ

ሐ. ባሌ ተራሮች፣ አዋሽ፣ ሰሜን ተራሮች

መ. ባሌ ተራሮች፣ ሰሜን ተራሮች፣ አዋሽ

5. በሰሜን ብሔራዊ ፓርክ ብቻ የሚገኘው የዱር እንስሳ የትኛው ነው?

ሀ. የደጋ አጋዘን

ሐ. አቦሸማኔ

ለ. ዋልያ

መ. ብሆር

6. የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክን በስተሰሜን የሚያዋስነው የትኛው ክልል ነው?

ሀ. አፋር

ሐ. አሮምያ

ለ. ትግራይ

መ. ቤንሻንጉልጉምዝ

7. በኦሮሚያ ክልልና በአፋር ክልል የሚገኘው የትኛው ነው?

ሀ. ያንጉዴ ብሔራዊ ፓርክ

ሐ. ኦሞ ብሔራዊ ፓርክ

ለ. ባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ

መ. አዋሽ ብሔራዊ ፓርክ

ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ቁጥር እየተመናመነ የመጣው በምን ምክንያት ይመስላችኋል?

ለ. የሰሜንና የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርኮች የሚጋሯቸው እንስሳት ምን ምን ናቸው?


ሐ. የዱር እንስሳት የገቢ ምንጭ የሚሆኑት እንዴት ነው?

መ. ፓርኮች ባይኖሩ በዱር እንስሳት ላይ ምን የሚከሰት ይመስላችኋል?

ሠ. የዱር እንስሳት በፓርኮች መጠበቅ ለደኖችና በአጠቃላይ ለሥነምህዳር ምን ጥቅም የሚሰጥ ይመስላችኋል?

ተግባር 3

በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱትን ፓርኮች ተመሳስሎዎችና ልዩነቶች በሚከተለው የቢጋር ሠንጠረዥ ዘርዝሩ።



8ኛ ቀን

ቃላት

ለቃላትና ለሐረጋት ተመሳሳይ ፍቺ በመስጠት ዓረፍተነገር መሥራት

ተግባር

ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሐረጋት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከሠጣችሁ በኋላ ዓረፍተነገር መሥርቱባቸው።

ምሳሌ፡- መታደግ

ተመሳሳይ ፍቺ = መጠበቅ፣ መከላከል፣ ማዳን

ዓረፍተነገር= ፓርኮች በመቋቋማቸው በርካታ የዱር እንስሳትን ከመጥፋት መታደግ ተችሏል።

ሀ. አዛውንት	መ. ተቋቋሙ	ሰ. መጠለያ
ለ. ሊቃውንት	ሠ. ምንጭ	ሸ. የተፈጥሮ ሀብት
ሐ. መንጋ	ረ. ዋስትና	ቀ. ሕገወጥ አደን

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በማወዳደርና በማነፃፀር ስልት ድርሰት መጻፍ

ተግባር

ባለፈው ሳምንት በማወዳደርና በማነፃፀር የጻፋችሁትን ድርሰት በሠንጠረዡ ውስጥ በቀረቡት የመገምገሚያ መስፈርቶች መሠረት አስተካክላችሁ እንደገና ጻፉና አንብቡ።

	የጽሑፍ መገምገሚያ መስፈርቶች	አዎ	አይደለም
ሀ	በጽሑፉ ውስጥ የፊደላት ስህተት አለ?		
ለ	ጽሑፉ በርዕሰጉዳዩ ላይ ያተኩራል?		
ሐ	ጽሑፉ ተመሳስሎዎችንና ልዩነቶችን የሚያሳይ ነው?		
መ	በጽሑፉ ውስጥ መቀነስ ያለበት (አላስፈላጊ ሀሳብ አለ)?		
ሠ	የጎደለ (መጨመር ያለበት) ሀሳብ አለ?		

የአጻጻፍ ሥርዓት

ይዘትን (አንድ ነጥብን) በጽሑፍ ውስጥ መጠቀም

ተግባር

1. የሚከተሉትን በፊደል የተጻፉ ብርና ሳንቲሞች አንድ ነጥብን በመጠቀም በቁጥር ጻፉ።

   ሀ. አሥራሁለት ብር ከሃያ ሳንቲም

   ለ. ሀያ ሰባት ብር ከስድሳ አምስት ሳንቲም

   ሐ. አርባ ሦስት ብር ከሰማንያ አምስት ሳንቲም

   መ. ሀምሳ ብር ከሀምሳ ሳንቲም

2. በፊደል የተጻፉትን ሙሉና ሸርፍራፊ ቁጥሮች አንድ ነጥብን በመጠቀም በቁጥር ጻፉ።

   ሀ. አሥራሦስት ነጥብ አምስት

   ለ. አሥር ነጥብ ዜሮ ሰባት

   ሐ. ዘጠና ሰባት ነጥብ ስምንት ሁለት

   መ. አራት መቶ አንድ ነጥብ ስድስት አምስት

3. የምታውቋቸውን የዱር እንስሳት በተራቁጥር ወደጎን ዘርዝሩ።

አቀላጥፎ ማንበብ

በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ይዞታ

ቅድመንባብ

ተግባር

«በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ይዞታ» በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ የተጠቀሱት ፓርኮች ማን ማን ናቸው? እነዚህ ፓርኮች የተቋቋሙበት ትኩረት ምንድን ነው?

ማንበብ

ተግባር

«በኢትዮጵያ የዱር እንስሳት ይዞታ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የመጀመሪያዎቹን አራት አንቀጾች በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ድምፅ እያሰማችሁ አንብቡ።

መናገር

በማወዳደርና በማነፃፀር ስልት ሀሳብን አደራጅቶ መከራከር

ተግባር

ፓርኮች የያዙት መሬት ለዱር እንስሳት መኖሪያነት ከሚውልና ለእርሻ ከሚውል የትኛው የበለጠ ጥቅም ይሠጣል? ከመናገራችሁ በፊት የሚከተለውን የቢጋር ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ ሀሳባችሁን አደራጁ።

መሬቱ ለዱር እንስሳት መኖሪያነት ቢውል ምን ጥቅም ይገኛል?	መሬቱ ለእርሻ ቢውል ምን ጥቅም ይገኛል?

መሬቱ ለዱር እንስሳት መኖሪያነት ቢውል ምን አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል?	መሬቱ ለእርሻ ቢውል ምን አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል?

ሰዋስው

የወልና የተጸውዖ ስሞች እንደባለቤት

ተግባር 1

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች የሚገኙትን ሰዋስዋዊ ባለቤቶች ከለያችሁ በኋላ የተጸውዖ ወይም የወል ስም መሆናቸውን ግለጹ።

ሀ. መጻሕፍት የዕውቀት ምንጭ ናቸው።

ለ. ተክዜ ወደሱዳን ይፈሳል።

ሐ. አበቦች አካባቢን ያሳምራሉ።

መ. ዑመር በሬዎቹን በጥሩ ዋጋ ሸጠ።

ሠ. ዝሆን ግዙፍ እንስሳ ነው።

ረ. አረጋሽና ሰይፉ ቤት አፀዱ።

ሰ. አርሶአደሩ ባቄላና ስንዴ ዘራ።

ሸ. ወንበር ከእንጨት ወይም ከብረት ይሠራል።

ቀ. ሩስያ የዓለማችን ሰፊዋ ሀገር ናት።

ተግባር 2

አምስት የወልና አምስት የተጸውዖ ስሞች እንደባለቤት በመጠቀም ዓረፍተነገር ሥሩ።

ምሳሌ፡- አፍሪካ፣ ውሻ

ሀ. <u>ውሻ</u> ግቢን ይጠብቃል። (የወል ስም)

ለ. <u>አፍሪካ</u> በርካታ ሀገራትን ይዛለች። (የተጸውዖ ስም)



ምዕራፍ 8

ባህላዊ ጨዋታዎች

የዐውዳመት ባህላዊ ጨዋታዎች

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ተግባር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጣጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	ሩር-ዋ-ን	ሩሯን
ለ	ጥንግ-ዋ-ን	ጥንጓን
ሐ	ይለጉ-ዋ-ት-ኣል	ይለጓታል
መ	በ-መለማመጥ	በመለማመጥ
ሠ	መደባደብ-ኣችሁ-ን	መደባደባችሁን
ረ	እንፈነካከት-ኣል-ኧ-ን	እንፈነካከታለን
ሰ	የሚያስታውስ-ኡ-ኣቸው-ን	የሚያስታውሷቸውን

ማንበብ

የገና ጨዋታ ትውስታ

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የምታውቋቸውን የውድድር ባህላዊ ጨዋታዎች ተናገሩ።

ለ. ሥዕሉን በመመልከት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

የማንበብ ሂደት

ተግባር

«የገና ጨዋታ ትውስታ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ በደብተራችሁ ላይ ሠንጠረዥ አዘጋጅታችሁ እየጻፋችሁ አንብቡ።

ምሳሌ፡-

ቃል	ስልት	ፍቺ	ምክንያት
ምንዝር	ፍንጭ በመጠቀም (ዐውድ)	ታዛዥ፣ የበታች ሠራተኛ	ከጎን ያለው ቃል «የታዛዥ» ተቃራኒ ስለሆነ

የገና ጨዋታ ትውስታ



እሁድ ረፋዱ ላይ ነው። አቶ ጫኔ ከሌሊቱ የጥበቃ ሥራቸው ተመልሰው በመኖሪያ ቤታቸው በረንዳ ላይ ከባለቤታቸው ጋር ጋዜጣ ያነባሉ። ልጃቸው ተመስገን ወደግቢው በመግባት ላይ እያለ፣

አቶ ጫኔ፡- «የት አርፍደህ ነው ተሜ?» ብለው ጠየቁት፤ ብቸኛ ልጃቸውን ዓይን ዓይኑን እየተመለከቱ።

ተመስገን፡- «የባህል ስፖርት ውድድር ስመለከት» አለ በትህትና።

አቶ ጫኔ፡- «ምን ዓይነት የባህል ስፖርት አየህ?» አሉት።

ተመስገን፡- «የገና ጨዋታ አየሁ» አለ።

አቶ ጫኔ፡- «የገና ጨዋታ! ወይኔ...አምልጦሃል በለኛ!» አሉ በቁጭት።

ተመስገን፡- «እንዴ አባዬ! የገና ጨዋታ ትወዳለህ?» ብሎ ጠየቃቸው።

(7) አቶ ጫኔ፡- «እንዴታ! መውደድ ብቻ ሳይሆን አሳምሬ እጫወተው ነበር እንጂ! እኔ አባትህ ንበዝ ነበርኩ!» አሉ፣ ትክዝ ብለው።

ተመስገን፡- «አባዬ! እስኪ በእናንተ ጊዜ የገና ጨዋታን እንዴት ትጫወቱት እንደነበር ንገረኝ» አለ፣ ትህትና በተሞላበት ስሜት።

አቶ ጫኔ፡- «እሺ! ደስ ይለኛል። ከገና ጨዋታው በፊት ባሉት ቀናት ወደዱር ሄደን ከወደታች ቆልመም ያለ ዱላ በመቁረጥ የገና መጫዎቻ እናዘጋጃለን። ዱላው ቆልመም እንዲል የሚፈለገው ጥንጓን (ሩሯን) ለመለጋት እንዲያመች ነው። ጥንጓ ደግሞ ከእንጨት፣ ከሐረግ፣ ከጠፍር ደቡልቡል ሆና ትዘጋጃለች።» ሲሉ፣

ተመስገን፡- ቀበል አድርጎ፣ ጥንግ ምንድን ነው?» አለ።

አቶ ጫኔ፡- «ጥንግ ድቡልቡል ሆና በመጫወቻ ዱላው የምትለጋ እንደኳስ የምታገለግል ነገር ናት። ገና የምንጫወተው በገናና በጥምቀት በዓላት ሰሞን በሰፊ ሜዳ ላይ ነው።»

ተመስገን፡- «የጨዋታው ሁኔታ ምን ይመስላል?»

(13) አቶ ጫኔ፡- «በጨዋታው ዕለት የቡድን አባት የሚሆኑ ሁለት ሰዎች በስምምነት ይመረጣሉ። ከዚያም ሁለት ሁለት ሆነን እየተቧደን ሁለት ቡድን እንመሠርታለን። ከሁለቱ ቡድኖች ቀልጣፋ የሆኑት ተመርጠው ጥንጓን ተቆራቁሰው ይለጓታል። ሁሉም ጥንጓን ተከትሎ ይሮጥና ለመለጋት ይራኮታል። ይህንንም ተከትሎ ጠብ ይፈጠርና እንፈነካከታለን» ብለው፣ ግንባራቸው ላይ ያለችውን ጠባሳ በእጃቸው አሻሹ።

ተመስገን፡- ሳያስበው «እንዴ!?» ብሎ ጮኸ፤ በመቀጠልም «ዳኛ የለም እንዴ? ይኸማ ምኑን ጨዋታ ሆነ፣ ድብድብ እንጂ!» አለ።

አቶ ጫኔ፡- «ዳኛ የለም፣ ግልጽ የሆነ ደንብም አልነበረም። በገና ጨዋታ ጊዜ ድብድብ ሲነሳ መገላገል የለም። ሽማግሌዎችም በሁኔታው እየሳቁ አሸናፊውን ማየት እንጂ፣ ጣልቃ ገብተው አይገላግሉም። ማስፈራራት፣ ወይም እንቆራቆስ ብሎ እጅና እግርን በዱላ መምታት በገና ጨዋታ የተለመደ ነው። ጥንጓንም ኃይለኛ ለጊ ከለጋት ዓይን እስከማጥፋት ትደርሳለች። ብርታትና ጥንካሬም የሚፈተነው በዚህ ጊዜ ነው። በጨዋታው ጊዜ በሚደርስ አደጋ ማንም ተጫዋች አይጠየቅም።»

ተመስገን፡- «ይገርማል! በገና ጨዋታው አሸናፊው ቡድን የሚለየው እንዴት ነው?»

አቶ ጫኔ፡- «ሁለቱ ቡድኖች የየራሳቸው የሆነ ሚና አላቸው። አንዱ ቡድን ጥንጓን እየለጋ ወስዶ ከተቃራኒ ቡድን ሜዳ የመጨረሻ ክልል ካሳለፋት ነጥብ ይመዘገብለታል። በዚህ ሁኔታ እየቀጠለ የጨዋታው ፍጻሜ ሲሆን ብዙ ያስመዘገበው ቡድን አሸናፊ ይሆናል።»

ተመስገን፡- «የገና ጨዋታ የሚጫወቱት ወንዶች ብቻ ናቸው ወይስ ሴቶችም ይጫወታሉ?»

አቶ ጫኔ፡- «ወንዶች ናቸው የሚጫወቱት» አሉ።

ወይዘሮ ፈትለወርቅ፡- «ጫኔ፣ እስኪ አሁን ደግሞ ከጨዋታው በኋላ አሸናፊ ስትሆኑ ምን እያላችሁ ትጨፍሩ እንደነበር ለልጅህ ንገረው» አሉ፣ ባለቤታቸውን በፍቅር እየተመለከቱ።

(21) አቶ ጫኔ፡- ፈገግ ብለው፣ «አንቺ ደግሞ! አሁንማ ረስቼው የለ! ባይሆን የማስታውሰውን ግጥም ልንገረው» ብለው፣ የሚያስታውሷቸውን ስንኞች እንዲህ በማለት ነገሩት።

«ማታ ነው ድሌ ማታ ነው ድሌ፣

አያሆሆ ማታ ነው ድሌ!

ይሄ ነው አመሌ።

አሲና በል አሲና ገናዬ!

ግፋው ግፋው አለኝ እኔ እንደምን ልግፋው፣

የአንድ በሬ ጨንራ እንደቅል የነፋው።

ካሥር ጋን አተላ፣

አይተርፈው በአንኮላ።»

በመቀጠልም፣ «በገና ጨዋታ ጊዜ ትልቅ ትንሽ፣ አለቃ ምንዝር የሚባል ነገር የለም። ሁሉም እኩል ነው።

በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ!

በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ

በገና ጨዋታ የለም ሎሌ ጌታ'

የሚባለውም ለዚህ ነው» አሉ።

ተመስገን፡- «ጭፈራው ደስ ይላል። በፍቅር መጫወት እየተቻለ መደባደባችሁን ግን አልወደድሁትም። እኔ ያየሁት ግን ሥነሥርዓት ያለው ነው። ጠብም ሆነ ድብድብ የለበትም። የሚያጠፋ፣ የሚሳደብ ተጫዋች እንኳን ቢኖር ዳኛው ያስጠነቅቁታል፣ ያለበለዚያ በቀይ ካርድ ያባርሩታል» አለ።

አቶ ጫኔ፡- «አሁንማ ብዙ ለውጥ አለ፣ ጨዋታውም 'ሕግ ወጥቶለታል' ሲባል ሰምቻለሁ። ይህ ከሆነ ጠብና ረብሻን ምን ያመጣዋል?» አሉ።

(ብሥራት ገብሬ። ሐምሌ 17/2012። *ገናና የገና ጨዋታ*። ከገጽ 1-2 መነሻነት የተጻፈ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር

የመምህራችሁን መመሪያ ተከትላችሁ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በታሪኩ ውስጥ ያሉትን ገፀባህርያት ዘርዝሩ።

ለ. የገና መጫወቻ ዱላ ከወደታች ቆልመም ያለ እንዲሆን የሚፈለገው ለምንድን ነው?

ሐ. በገና ጨዋታ ነጥብ የሚቆጠረው ተጨዋቾቹ ምን ሲያደርጉ ነው?

መ. በገና ጨዋታ አሸናፊው የሚለየው እንዴት ነው?

ሠ. የአባትየው ዘመን የገና ጨዋታ የነበረበትን ችግር ዘርዝራችሁ ጨዋታውን ዘመናዊ ለማድረግ ምን መደረግ እንዳለበት አብራሩ።

ረ. «በገና ጨዋታ፣ አይቆጡም ጌታ» የሚለው ስንኝ ምን ያመለክታል?

ሰ. በአቶ ጫኔ ግንባር ላይ ያለችው ጠባሳ በምን ምክንያት የተፈጠረች ይመስላችኋል?

ሸ. በአሁኑ ጊዜ የሚደረገው የገና ጨዋታ ከዱሮው በምን ይለያል?

ቀ. ሴቶች የገና ጨዋታ ሊጫወቱ አይችሉም ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

2ኛ ቀን

ቃላት

አዳዲስ ቃላትንና ሐረጋትን ተጠቅሞ ጥያቄ መመለስ

ተግባር 1

የተሠመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት በመጠቀም ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ።

ምሳሌ፡-

ጥያቄ = ጠባሳ በምን ምክንያት ይፈጠራል?

መልስ = በአደጋ ምክንያት የሚከሰት ቁስለት ሲድን ጠባሳ ይፈጠራል።

ሀ. ከጨዋታ በፊት የሚያዷድኑት እነማን ናቸው?

ለ. አለቃን ማክበር ለምን ያስፈልጋል?

ሐ.. መደባደብ ተገቢ ያልሆነው ለምንድን ነው?

መ. ኳስ ስትጫወቱ ኳሷን የምትለጉት በምናችሁ ነው?

ሠ. አንድ ሰው ሲፈነክት ምን ሊደረግለት ይገባል?

ተግባር 2

ቀጥሎ የቀረቡትን የተጓደሉ ዓረፍተነገሮች በሣጥኑ ውስጥ ከተዘረዘሩት ቃላትና ሀረግ በመምረጥ አሟልታችሁ ጻፉ።

ዱላቸውን	ተቆራቁሰ	ሚና	ተቧደኑ	ስለመታኝ

ሀ. ግንባሬ ያበጠው የገና ሩር _____ ነው።

ለ. የሁለቱ ሠፈር ወጣቶች _____ ለይተው የገና ጨዋታ ተጫወቱ።

ሐ. ጨዋታው እንደተጀመረ የእኛ ቡድን መሪ ሩሯን _____ ወደእኛ አሻገራት።

መ. በእድሜ ተቀራራቢ የሆኑ ልጆች _____ ና የገና _____ ይዘው ጨዋታቸውን ጀመሩ።

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

እየተቀባበሉ መጻፍ

ተግባር

በቡድን ሆናችሁ ያልተጻፈበት አንድ ገጽ ወረቀት አዘጋጁ። ከዚያም የገና ጨዋታን ሂደት በተመለከተ ወረቀቱን ተራበተራ እየተቀባበላችሁ አንድ አንድ ዓረፍተነገር ጻፉ። መምህራችሁ አቁሙ እስከሚሏችሁ ወረቀቱን እየተቀባበላችሁ መጻፋችሁን ቀጥሉ። በመጨረሻም ዓረፍተነገሮቹን አደራጅታችሁ አንድ አንቀጽ ጻፉ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

የገና ጨዋታ ትውስታ

የሠላምታ ደብዳቤ ናሙና

የላኪ አድራሻ
- ከሶፍያ አብዱልቃድር
- ወረታ አጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርት መሰናዶ 2ኛ ደረጃ ትምህርትቤት
- የመ.ሣ.ቁ _____
- ወረታ
- ቀን _____

የተቀባይ አድራሻ
- ለዳኛቸው መላኩ
- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
- የመ.ሣ.ቁ. _____
- አዲስ አበባ

ሠላምታ
- ውድ ጓደኛዬ ዳኛ።

መግቢያ — ከተለያየንበት ጊዜ ጀምሮ ለጤናህ እንደምን አለህ? እኔ ደህና ነኝ።

ሐተታ — ትምህርቴን በጥሩ ሁኔታ እየተከታተልኩ ነው። በሚቀጥለው ዓመት ብሄራዊ የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና እፈተናለሁ። በመሆኑም ከጓደኞቼ ጋር በቡድን በማጥናት ለፈተናው እየተዘጋጀን ነው። ሁላችንም ጥሩ ውጤት እንደምናመጣም ተስፋ አለኝ። ለጥናት የሚረዳኝ አጋዥ መጽሐፍ ብትልክልኝ ደስ ይለኛል።

አንተስ ትምህርት እንዴት ይዞሃል? አገሩስ ተስማምቶሃል? የዩኒቨርስቲ ትምህርትህን ለመጨረስ የቀረህ አንድ ዓመት አይደለም? መቼም በጥሩ ውጤት ተመርቀህ እንደምታኮራኝ እርግጠኛ ነኝ። አይዞህ፤ በርታ!

መደምደሚያ — በል እንግዲህ ክረምት ደርሶ እስክምንገናኝ ድረስ ደህና ሁን።

ናፍቂህ

ፊርማ

ሶፍያ አብዱልቃድር

ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከላይ በቀረበው የሥላምታ ደብዳቤ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. በላኪ አድራሻ የተገለጹት ምን ምን ናቸው?

ለ. በተቀባይ አድራሻ የተገለጹት ምን ምን ናቸው?

ሐ. በደብዳቤው የመግቢያ ክፍል የተገለጸው ምንድን ነው?

መ. በደብዳቤው የሐተታ ክፍል የተገለጸው ምንድን ነው?

ሠ. በደብዳቤው የመደምደሚያ ክፍል የተገለጸው ምንድን ነው?

3ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

የገና ጨዋታ ትውስታ

ቅድመንባብ

ተግባር

«የገና ጨዋታ ትውስታ» በሚለው ምንባብ ውስጥ «የገና ጨዋታ! ወይኔ!... አምልጦሃል በለኛ!» የሚለው የአቶ ጫኔ ንግግር በምን ዓይነት ስሜት የተነገረ ነው? የገፀባህርይውን ስሜት በሚገልጽ ሁኔታ ዓረፍተነገሩን አንብቡ።

ማንበብ

ተግባር

ጥንድ ጥንድ በመሆን እንደአባትና እንደልጅ ሆናችሁ «የገና ጨዋታ ትውስታ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምልልስ እየተቀባበላችሁ አንብቡ።

ማዳመጥ

አሸንዳዬ



ቅድመማዳመጥ

ከሥዕል የምንባብን ሀሳብ መገመት

ተግባር

ሥዕሉን አስተውላችሁ የተረዳችሁትን ተናገሩ።

የማዳመጥ ሂደት

ተግባር

«አሸንድዬ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ እያዳመጣችሁ በሠንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ቃላት ፍቺ በደብተራችሁ ጻፉ።

ቃል	ፍቺ
አሸንድዬ	
አጥቢያ	
አውራጅ	
ወግ	
አወድሰው	

አዳምጠ መረዳት

ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በአሸንድዬ በዓል ልጃገረዶች ምን ዓይነት ልብስ ይለብሳሉ?

ለ. በክተሞች አካባቢ ለአሸንድዬ ተጫዋቾች ምን ይሰጣል?

ሐ. የአሸንድዬ በዓል በየት በየት አካባቢ ይከበራል?

መ. የአሸንድዬ ባህላዊ ጨዋታ የሚጀመረው መቼ ነው?

ሠ. ጸሐፊው/ዋ «ብሩህ ሰማይ ሊታይ፣ አበባው ሊፈነድቅ...» የሚለውን አገላለጽ ምን ለማሳየት የተጠቀሙበት ይመስላችኋል?

ረ. የአሸንድዬ ተጫዋቾች ቅድሚያ ከሹሞች ቤት የሚሄዱት ለምን ይመስላችኋል?

ሰ. የአሸንድዬ ባህላዊ ጨዋታ ምን ጠቀሜታ አለው?

ሰዋስው

ቅጽል፣ መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮች

ተግባር

ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮች እንዲሁም ቅጽሎችን ለይታችሁ በምሳሌው መሠረት በደብተራችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

1. ስድስት ነጫጭ በጎች አሉኝ።

   ስድስት = መጣኝ ቁጥር

   ነጫጭ = ቅጽል

2. አንደኛው ረጅም ልጅ ጓደኛዬ ነው።

   አንደኛው = ደረጃ አመልካች ቁጥር

   ረጅም = ቅጽል

ሀ. የከተማው ሰባተኛ ትልቅ ፎቅ ቀለም ተቀባ።

ለ. አንድ ትልቅ ገብስማ ዶሮ ገዛሁ።

ሐ. ሶስተኛው ትልቅ ቤት የእኛ ነው።

መ. አንድ ረጅም አረንጓዴ ቀሚስ ገዛሁ።

ሠ. አራተኛው ሰፊ ግቢ የእነበቀለ ነው።

ረ. አሥር ረጃጅም ዛፎች በግቢው ውስጥ አሉ።

ሰ. የክፍላችን ሁለተኛዋ ጎበዝ ተማሪ ዘሀራ ናት።

ሸ. አንደኛ ጨዋ ልጅ እሱ ነው።

ማንበብ

እቴ ሜቴ

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በአካባቢያችሁ የምትጫወቷቸውን የልጆች ጨዋታዎች ዘርዝሩ።

ለ. ሥዕሉን በመመልከት የተረዳችሁትን ተናገሩ።

የማንበብ ሂደት

ተግባር

«እቴ ሜቴ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በአዕምሯችሁ ምሥል እየፈጠራችሁ አንብቡ።

እቴ ሜቴ



ልጆች ከዕድሜ አቻዎቻቸው ጋር የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ። በቤታቸው፣ በሰፈራቸው፣ በትምህርትቤታቸው ወዘተ. በሚፈጥሯቸው አጋጣሚዎች እየተጠቀሙ የሚጫወቷቸው ልዩ ልዩ ጨዋታዎች አሏቸው።

ከነዚህ ጨዋታዎች ጥቂቶቹ ትግል፣ ድብብቆሽ፣ ልቅሞሽ፣ ቅልልቦሽ፣ እቴ ሜቴ፣ መሀረቤን ያያችሁ፣ እንቡሼ ገላ፣ ሰኞ ማክሰኞ ወዘተ. ናቸው። አብዛኞዎቹ ጨዋታዎች በዜማ ይታጀባሉ። እነዚህን ጨዋታዎች ልጆች አጋጣሚዎችን ተጠቅመው ይጫወቷቸዋል። ወላጆችና ጎረቤቶችም በሠፈራቸው ልጆች የሚጫወቱበትን ሁኔታ ያመቻቻሉ። መምህራንም በትምህርትቤት የልጆችን የጨዋታ ዓይነቶች፣ ጊዜና ሥፍራ አቅደው ይተገብራሉ።

ልጆች ምን ይጫወታሉ?

የልጆች ጨዋታዎች የየራሳቸው ደንብና ሥርዓት አላቸው። አንዳንዶቹ ጨዋታዎች ወንዶችና ሴቶች በጋራ የሚጫወቷቸው ናቸው። ሌሎቹን ጨዋታዎች ደግሞ ሴቶችና ወንዶች ለየብቻቸው ይጫወቷቸዋል። በጨዋታው ወቅት ተጨዋቾቹ ተራ የሚገቡበት፣ አሸናፊና ተሸናፊ የሚለይበት፣ ጨዋታውን የሚጀምሩበትና የሚጨርሱበት ሥርዓት አላቸው። ሥርዓቱን ያላከበሩ ተጫዋቾች ከጨዋታው ውጪ ይሆናሉ።

እቴ ሜቴ ምን ዓይነት ጨዋታ ነው?

ልጆች ከሚጫወቷቸው ጨዋታዎች መካከል አንዱ እቴ ሜቴ ነው። የራሱ የሆነ ደንብና ሥርዓት አለው። ሁለት ሁለት እየሆኑ ይጫወቱታል። ሁለቱ ልጆች ፊት ለፊት ቆመው በየግላቸው አንድ ጊዜ ያጨበጭባሉ። ቀጥለው እጆቻቸውን ፊትለፊት ያጋጫሉ። ከዚያም ፊጥነው አንዷ/ዱ በቀኝ እጇ/ጁ የሌላዋን/ውን ቀኝ እጅ ትነካለች/ይነካል። በዚህን ጊዜ ሌላው እጅ የራስን ደረት ይነካል፣ ቀጥሎ በሌላው እጃቸው ሲነካኩ ሌላው የየራሳቸውን ደረት ይነካል። በዚህ ሁኔታ እስኪደክማቸው ድረስ ይቀጥላሉ። ይህም የሚከወነው በዜማ ጭምር ነው። ዜማውም ዝግ ብሎ ይጀምርና ከሰባተኛው ስንኝ ጀምሮ ይፈጥናል። ዜማውን ሁለቱም በአንድ ጊዜ ያዜሙታል። የዜማውም ግጥም፡-

እቴ ሜቴ የሎሚ ሽታ፣

እቴ ሜቴ የሎሚ ሽታ፣
እናት አባትሽ ምን አሉሽ ማታ?
ምንም ምንም ምንም አላሉኝ፣
ትምህርትሽን ተማሪ አሉኝ።
ለማስተማር ቃልኪዳን ገብተው፣
ምለውልኛል ጋሻ ጦር ደፍተው።
ከቤቱ በላይ ቁራ ሰፍሮ፣

ቁራ ሰፍሮ፣
የለችም ቢሉት ሄደ በሮ፣
ሄደ በሮ።
እሬን ያብረኝ ያብረኝ፣
ያብረኝ፣
የዝሆን አሞት ያስጠጣኝ፣
ያስጠጣኝ።
የዝሆን ሀሞት መራራ ነው፣
መራራ ነው፣
የጎበዝ ልቡ ተራራ ነው፣
ተራራ ነው።
ተራራ ሄጀ ስመለስ፣
ስመለስ፣
አህያ ሞቶ ጅብ ሲያለቅስ፣
ጅብ ሲያለቅስ፣
ቁንጫ ቆሞ ሲቀድስ፣
ሲቀድስ፣
እባብ አንገቱን ሲነቀስ፣
ሲነቀስ፣
የታረደው ሀምሳ ዶሮ፣
የደረሰኝ አንድ ዶሮ፣
እሷን ይገፍ ጓሮ ለጓሮ።

የሚል ነው።

የልጆች ጨዋታ ክዋኔ እንደባህሉ፣ እንደጨዋታው ዓይነትና እንደልጆቹ ዕድሜ ይለያያል። በአብዛኛው በዜማና በአካል እንቅስቃሴ የታጀበ ነው። ሲጫወቱ ይዘላሉ፤ ይሮጣሉ፤ ይቀመጣሉ፤ ይነሳሉ፤ ርስበርስ ይነካካሉ። በጨዋታ ጊዜ የሚያዜሟቸው ዜማዎችም ከእነዚህ እንቅስቃሴዎች ጋር የተቀናጁ ናቸው።

(ዘሪሁን አስፋው። 1992። *የሥነጽሑፍ መሠረታውያን*። ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት «እውነት» ወይም «ሐሰት» በማለት ምክንያት እየሰጣችሁ በቃላችሁ መልሱ።

   ሀ. የልጆች ጨዋታዎች ደንብና ሥርዓት የላቸውም።

   ለ. ሴቶችና ወንዶች ልጆች አብረው አይጫወቱም።

   ሐ. የልጆች ጨዋታ ለመጫወት አጋጣሚውን የሚፈጥሩት ልጆች ብቻ አይደሉም።

   መ. ሁሉም የልጆች ጨዋታዎች በዜማ ይታጀባሉ።

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

   ሀ. «የጨዋታውን ሥርዓት ያላከበሩ ተጫዋቾች ከጨዋታ ውጪ ይሆናሉ» ሲል ምን ማለት ነው?

   ለ. የልጆች ጨዋታ እንደልጆች ዕድሜ እንዴት እንደሚለያይ ግለጹ።

   ሐ. «እቴ ሜቴ» የሚባለው ጨዋታ ከአሸንዱዬ በምን ይመሳሰላል? በምን ይለያያል?

   መ. ከመጀመሪያዎቹ 6 ስንኞች ምን ተማራችሁ?

ተግባር 2

ቀጥሎ እንደቀረበው ያሉ አገላለጾችን (ሐረጎችን) ከምንባቡ ውስጥ አውጡና ሐረጋቱ የሚገልጹትን ሐሳብ አብራሩ።

ምሳሌ፡- የጎበዝ ልቡ ተራራ ነው።

የሚገልጸው ሀሳብ = የጎበዝ ሀሳብ ትልቅ ነው።

ተግባር 3

በምንባቡ በተገለጸው መንገድ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ «እቴ ሜቴ» የተባለውን ጨዋታ ተጫወቱ።

5ኛ ቀን

ቃላት

ቃላትን ከፍቻቸው ጋር ማዛመድ

ተግባር 1

ቀጥሎ በሳጥን ውስጥ የቀረቡትን ቃላት በምሳሌው መሠረት ከ«ሀ»-«ሠ» ከቀረቡት ሀረጋት ፍቺ ጋር እያዛመዳችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።

ቃልኪዳን	ዜማ	ክዋኔ	ሥርዓት	ሀሞት	ደንብ

ምሳሌ፡- ከጉበት የሚመነጭ በሆድዕቃ ውስጥ ምግብን ለማላም የሚረዳ አረንጓዴ ቀለም ያለው መራራ ፈሳሽ = ሀሞት

ሀ. አንድን ሁኔታ/ተግባር በድርጊት መግለጽ = _____

ለ. የደስታ ወይም የሀዘን ስሜትን መግለጽ የሚያስችል ሙዚቃዊ ድምፅ = _____

ሐ. የአንድ ድርጊት አፈጻጸም ሕግ ወይም ድንጋጌ = _____

መ. አንድን ነገር ለማድረግ ወይም ለማከናወን የሚደረግ ስምምነት= _____

ሠ. አንድ ነገር የሚሠራበት/የሚከናወንበት አሠራር ወይም ወግ = _____

ተግባር 2

ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሠረት ተመሳሳይ ፍቻቸውን በደብተራችሁ ጻፉ።

ሀ. ጋሻ	መ. ለየብቻ	ሰ. የታጀበ
ለ. ቁራ	ሠ. አቅደው	ሸ. የተቀናጀ
ሐ. ሰፍሮ	ረ. አጋጣሚ	

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በድርጊት ቅደምተከተል ስልት ድርሰት መጻፍ

ተግባር

ባለፈው ሳምንት የመረጣችሁትን አንድ ባህላዊ ጨዋታ የአጨዋወት ሥርዓት በተመለከተ በድርጊት ቅደምተከተል ስልት ባለሁለት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

የሠላምታ ደብዳቤ

ተግባር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት የሠላምታ ደብዳቤ ጻፉ።

ከ_____

_____

የመ.ሣ.ቁ._____

_____

ቀን _____

ለ_____

_____

የመ.ሣ.ቁ._____

_____

ውድ አባቴ/እናቴ (አባዬ/እማዬ...)

_____

_____

እኔ_____

ከሦስት ሳምንት በኋላ_____

ስለዚህ _____

_____

_____

_____ እስከምንገናኝ ድረስ _____

_____ ለሁሉም ዘመድ _____

_____

ናፋቂ ልጅህ/ሽ

(ፊርማ)

ስም_____

6ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

እቴ ሜቴ

ቅድመንባብ

ተግባር

የ«እቴ ሜቴ» የጨዋታ ሂደትን በአጭሩ በቃላችሁ ግለጹ።

ማንበብ

ተግባር

«እቴ ሜቴ» በሚለው ምንባብ ውስጥ ያለውን ግጥም በቡድን ሆናችሁ በጋራ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

መናገር

የሚና ጨዋታ

ተግባር

የመረጣችሁትን የልጆች ጨዋታ በቡድን ሆናችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

ሰዋስው

ቅጽሎች፣ መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮች

ተግባር 1

ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ ያሉትን መጣኝ ቁጥሮች፣ ደረጃ አመልካች ቁጥሮችና ቅጽሎች በማቀናጀት የተጓደሉትን ዓረፍተነገሮች አሟልታችሁ በደብተራችሁ ጻፉ። (በአንድ ዓረፍተነገር ውስጥ ከአንድ ቅጽል በላይ መጠቀም ትችላላችሁ።)

ቁጥሮች	ቅጽሎች
አሥራአምስት	ባለጌ
ሦስተኛዋ	ጠባብ
ሁለቱ	ጎበዝ
አንድ	ወፍራም
አምስት	ሰፊ
ሁለተኛው	ጠንካራ
አስር	ጥሩ
አራተኛው	ትንሽ
አንደኛው	ክፉ

ምሳሌ፡- _____ ጠረጴዛዎች ብዙ ቢያገለግሉም አልተሰበሩም።

መልስ፡- ሁለቱ ጠንካራ ጠረጴዛዎች ብዙ ቢያገለግሉም አልተሰበሩም።

ሀ. የትምህርት ቤቱ _____ ተማሪ አስቻለው ነው።

ለ. የክፍላችን _____ ልጅ በትግል አሸነፈ።

ሐ. _____ ተማሪዎች ወደእርሻ ምርምር ጣቢያ ሄዱ።

መ. _____ ልጅ አለቀሰች።

ሠ. _____ ወታደሮች ተሸለሙ።

ረ. _____ መንገድ ላይ ደረስን።

ሰ. _____ መጻሕፍት አነበብኩ።

ሸ. _____ ድመት በየቦታው ይፀዳዳል።

ቀ. _____ ውሻ ተገደለ።

በ. የህንፃው _____ ክፍል ትናንትና ተከራየ።

ተግባር 2

ቅጽሎችን፣ መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን ተጠቅማችሁ 6 ዓረፍተነገሮች ጻፉ።

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ተግባር

ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላትና ሐረጋት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	ሽ-ር-ጥ	ሽርጥ
ለ	ግ-ላ-ስ	ግላስ
ሐ	የ-ተወዳዳሪ-ዎች	የተወዳዳሪዎች
መ	በ-ተዘጋጀ-ል-ኣቸው	በተዘጋጀላቸው
ሠ	የ-ፈረስ-ኦች-ኣቸው-ን	የፈረሶቻቸውን
ረ	ይ-መዘገብ-ል-ኣቸው-ኣል	ይመዘገብላቸዋል

ማንበብ

የፈረስ ሽርጥ (ሽምጥ) ውድድር ጨዋታ

ቅድመንባብ

ከአዳዲስ ቃላት ፍቺ ጋር መተዋወቅ

ተግባር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ቀጥሎ በቀረቡት ቃላት ፍቺ ላይ ተወያዩ። ቃላቱን ከሥዕሉ ጋር አዛምዱ።

ኮርቻ	ግላስ	ልባብ	መም

የማንበብ ሂደት

ንዑሳን ርዕሶችን በመጠቀም መገመት

ተግባር

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ከንዑሳን ርዕሶቹ በመነሳት ስለአንቀጾቹ እየገመታችሁ አንብቡ።





የፈረስ ሽርጥ እሽቅድምድም ታዋቂ ፈረስ ጋላቢዎች የሚሳተፉበት የውድድር ስፖርት ነው። ይህ የውድድር ስፖርት የራሱ የሆነ የመወዳደሪያ ሜዳና ለሽምጥ ግልቢያ የሠለጠኑ ፈረሶች ያስፈልጉታል። ጨዋታው እንደአብዛኛዎቹ የውድድር ዓይነቶች ሁሉ የራሱ የሆነ ሥርዓት አለው።

ለፈረስ ሽርጥ እሽቅድምድም የሚያስፈልጉ ነገሮች

የፈረስ ሽርጥ እሽቅድምድም ለማከናወን ምቹ የሆነ ሜዳ ያስፈልጋል። ሜዳው አራት ማዕዘን ሆኖ ርዝመቱ ቢያንስ 400 ሜትር ቢበዛ 600 ሜትር ነው።

ወርዱ ደግሞ ቢያንስ 48 ሜትር ቢበዛ 60 ሜትር ነው። ሜዳው ስድስት መሞች ይኖሩታል። አባጣ ጎርባጣ ሳይኖረው ለፈረስ ውድድር አመቺ ሆኖ ይዘጋጃል። የእያንዳንዱ መም ስፋት ቢያንስ 8 ሜትር ቢበዛ 10 ሜትር ይሆናል። በመሙ የውስጥ መስመሮች በ10 ሜትር ርቀት ባለአንድ ሜትር፣ በየ100 ሜትር ርቀት ደግሞ ሁለት ሜትር ቁመት ባላቸው እንጨቶች ባንዲራዎች ይተከላሉ። የውድድሩ መነሻ መስመር ይደረግበታል ወይም በልዩ ምልክት እንዲታይ ሆኖ ይመሠረታል። የእሽቅድምድሙ መድረሻ የሜዳው የመጨረሻ መስመር ነው።

ለፈረስ ሽርጥ ውድድር ሌላው አስፈላጊው ነገር ፈረስ ከነሙሉ ዕቃው ነው። የፈረሱ ዕቃዎችም ኮርቻ፣ ግላስ፣ ልባብ፣ አለንጋ፣ ቀሚስ የመሳሰሉት ናቸው። የቀሚሱ መጠን እስከፈረሱ ጉልበት ሊደርስ ይችላል። የአለንጋው መጠንም እስከሰባ ሳንቲ ሜትር የሚደርስ ከቆዳ የሚሠራ ነው።

የፈረስ ሽርጥ እሽቅድምድም ሕግና ሥርዓት

ዳኞቹ ሴቶችና ወንዶች ናቸው።

የፈረስ ሽርጥ እሽቅድምድም ሕግ አለው። አሥራሦስት ዳኞችም አሉት። እነዚህ ዳኞችም የየራሳቸው የሆነ ኃላፊነት አላቸው። ሦስቱ ነጥብ መዝጋቢ፣ አስነሽ፣ መነሻ መስመር ተቆጣጣሪ፣ አራቱ የመሀል (የ100 ሜትር ተቆጣጣሪ)፣ ስድስቱ የመግቢያ (ደረጃ ያዥ) ናቸው። በዳኝነቱም ሴቶችና ወንዶች ይሳተፉለ።

የተወዳዳሪዎች ዕድሜ ከ18-60 ዓመት መሆን አለበት። በዚህ ዕድሜ ክልል የሚገኙ ስድስት ተወዳዳሪዎች በአንድ ጊዜ ይሳተፋሉ። ውድድሩን ለመጀመር ተወዳዳሪዎች በተሰጣቸው መም መነሻ መስመር ላይ የፈረሶቻቸውን የፊት እግሮች ያቆማሉ። ዋናው ዳኛ በሚያሳዩት ምልክት ወይም በሚያሰሙት ድምፅ አማካይነት ግልቢያውን ይጀምራሉ። ተወዳዳሪዎች በተዘጋጀላቸው መም ውስጥ ብቻ ይጋልባሉ። በውድድሩ ተሳታፊ ቡድኖች ብዙ ከሆኑ ውድድሩ በሁለት ምድብ ተከፍሎ በጥሎ ማለፍ ይከናወናል። የተሳታፊ ቡድኖች ቁጥር አነስተኛ ከሆነ ግን በአንድ ዙር በጥሎ ማለፍ ይከናወናል። በውድድሩ ሂደት ፈረሱም ሆነ ጋላቢው በአጋጣሚ ቢወድቁ ከመወዳደሪያው መም ካልወጡ እንደገና በመነሳት ውድድሩን መቀጠል ይችላሉ።

የፈረስ ሽርጥ የውጤት አመዘጋገብ ሥርዓት አለው።

የፈረስ ሽርጥ እሽቅድምድም የራሱ የሆነ የውጤት አመዘጋገብ ሥርዓት አለው። ከ1ኛ-6ኛ የወጡ ተወዳዳሪዎች በቅደምተከተል ከ7-1 ውጤት ይመዘገብላቸዋል። ተወዳዳሪ ጋላቢዎች የማጣሪያ ውድድሮች አልፈው በፍጻሜው ውድድር የተመደበላቸውን የ400 ወይም የ600 ሜትር ርቀት ሲያጠናቅቁ የውድድሩ ፍጻሜ ይሆናል።

በአጠቃላይ የፈረስ ሽርጥ ውድድር ሜዳ ከ400-600 ሜትር ርዝመትና ከ48-60 ሜትር ወርድ አለው። በዚህ ሜዳ በሚገባ የተያዙና በኮርቻ ዕቃዎቻቸው ያሸበረቁ ፈረሶች በስድስት መም ተሰልፈው ይሽቀዳደማሉ። ጋላቢዎቹም አለንጋቸውን

እያወናጨፉና ፈረሶቻቸውን እየኰረኰሩ ሽምጥ ይጋልባሉ። በመጨረሻም በአሥራሦስቱ ዳኞች ይሁንታ በሚሰጠው ውጤት መሠረት ተሸላሚ ይሆናሉ።

(የኢትዮጵያ ባህል ስፖርት ፌደሬሽን። 2004። *የባህል ስፖርቶች ሕግና ደንብ*። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

በምንባቡ መሠረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል መርጣችሁ በቃላችሁ መልሱ።

1. በመሙ የውስጥ መስመሮች በየ100 ሜትር ርቀት የሚተከሉት የባንዲራ መስቀያ እንጨቶች ቁመት ምን ያህል ነው?

   ሀ. 8 ሜትር ለ. 10 ሜትር ሐ. 1 ሜትር መ. 2 ሜትር

2. ከሚከተሉት አንዱ ከፈረስ ዕቃዎች አይመደብም።

   ሀ. አለንጋ ለ. መም ሐ. ግላስ መ. ልባብ

3. የመግቢያ (ደረጃ ያዥ) ዳኞች ብዛት ምን ያህል ነው?

   ሀ. ሦስት ለ. አራት ሐ. ስድስት መ. አሥራሦስት

4. በፈረስ ሽርጥ እሽቅድምድም በአንድ ጊዜ የሚሰለፉ ተወዳዳሪዎች ብዛት ስንት ነው?

   ሀ. ስድስት ለ. አሥራሦስት ሐ. ስምንት መ. ሰባት

ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. የሜዳው ስፋት 600 ሜትር በ60 ሜትር ከሆነ የእያንዳንዱ መም ስፋት ምን ያህል ይሆናል?

ለ. ለፈረስ ሽርጥ እሽቅድምድም 13 ዳኞች መመደብ ተገቢ ይመስላችኋል? ለምን?

ሐ. ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ወይም ከ60 ዓመት በላይ የሆኑ በፈረስ ሽርጥ ውድድር እንዳይሳተፉ የተከለከለው ለምን ይመስላችኋል?

መ. ተወዳዳሪዎች ከተዘጋጀላቸው መም ቢወጡ ምን ይደረጋሉ?

ሠ. «ጥሎ ማለፍ» ምን ማለት ነው?

8ኛ ቀን

ቃላት

የቃላት ፍቺ፣ ምደባና ቃላትን በአንቀጽ ውስጥ መጠቀም

ተግባር 1

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት በምሳሌው መሠረት በየወገናቸው መድቡ።

ምሳሌ፡-

የፈረስ ዕቃ	የመወዳደሪያ ሜዳ	የውድድር ሂደትና ሥርዓት
ግላስ	አባጣጎርባጣ	ጥሎማለፍ

አለንጋ	ወርድ	ምድብ	ቀሚስ
መም	ዳኛ	አባጣጎርባጣ	እሽቅድምድም
ጥሎማለፍ	ግላስ	ልባብ	ግልቢያ
ኮርቻ	ርዝመት	ሽምጥ	

ተግባር 2

ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላትና ሐረጋት በክፍት ቦታዎቹ በማስገባት አንቀጹን አሟልታችሁ ጻፉ።

ለእሽቅድምድሙ	ግላስ	ልባቡን	ኮርቻውን	በአለንጋው	ሽምጥ

ጋላቢው ፈረሱ ጀርባ ላይ _____ ጭኖ ያማረውን _____ ለበስ አደረገው። ከዚያም _____ በፈረሱ ጭንቅላት ላይ አጠለቀው። ፈረሱን ከለጎመ በኋላ ርካቡን ረግጦ ኮርቻው ላይ ተቀመጠና _____ ተዘጋጀ። በመቀጠልም ፈረሱን _____ ሸጥ ሲያደርገው _____ መጋለብ ጀመረ።

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በድርጊት ቅደምተከተል ስልት የተጻፈን ድርሰት አስተካክሎ መጻፍ

ተግባር

ስለባህላዊ ጨዋታዎች የጻፋችሁትን ድርሰት መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት አሻሽላችሁ ጻፉ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

ተግባር

ለዘመዳችሁ ወይም ለጓደኛችሁ የሠላምታ ደብዳቤ ጻፉና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።

9ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

የፈረስ ሽርጥ (ሽምጥ) የውድድር ጨዋታ

ቅድመንባብ

ተግባር

የፈረስ ሽርጥ የውድድር ጨዋታን ሕግና ሥርዓት በአጭሩ በቃላችሁ ግለጹ።

ማንበብ

ተግባር

«የፈረስ ሽርጥ (ሽምጥ) የውድድር ጨዋታ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የመጀመሪያዎቹን አምስት አንቀጾች ድምፅ እያሰማችሁ አንብቡ።

መናገር

በተነበበ ጽሑፍ ላይ የግምገማ አስተያየት መስጠት

ተግባር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ጓደኞቻችሁ በሚያነቡላችሁ ጽሑፍ ላይ የግምገማ አስተያየት ስጡ።

ሰዋስው

ቅጽል፣ መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮች

«የፈረስ ሽርጥ (ሽምጥ) የውድድር ጨዋታ» ከሚለው ምንባብ ቅጽሎች፣ መጣኝና ደረጃ አመልካች ቁጥሮችን ለይታችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።



ምዕራፍ 9

ሥነቃል

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

እንቆቅልሽና ቃላዊ ግጥም

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ተግባር

የሚከተሉትን ሐረጋት በመነጣጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	በ-ዕልል-ታ-ም	በዕልልታም
ለ	በ-ቅብብል-አሽ	በቅብብሎሽ
ሐ	እንዲ-ያስችል-ኣቸው	እንዲያስችላቸው
መ	እንደ-አ-ይጫን-ኣቸው	እንዳይጫናቸው
ሠ	በ-አከዋወን-ኣቸው	በአከዋወናቸው

ማንበብ

ቃላዊ ግጥም

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በአካባቢያችሁ ሰዎች በሥራ፣ በሠርግ ወዘተ. ጊዜ የሚያዜሟቸውን ግጥሞች አስታውሳችሁ ተናገሩ።

ለ. ስዕሉን ተመልከቱና ምንባቡ ስለምን እንደሚገልፅ ገምቱ።

የማንበብ ሂደት

ተግባር

ቀጥሎ «ቃላዊ ግጥም» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከንዑስ ርዕሶቹ በመነሳት እየገመታችሁና ግምታችሁን እያረጋገጣችሁ አንብቡ።

ቃላዊ ግጥም

ቃላዊ ግጥም፣ በዘፈንና በእንጉርጉሮ መልክ ይቀርባል። በድርጊትም ይገለጻል። የቃላዊ ግጥም አቅራቢው የሰውነት እንቅስቃሴ፣ የፊት ገጽታና የድምጽ ውበት ቃላዊ ግጥሙን አሳዛኝ፣ አዝናኝ፣ ቀስቃሽ ወዘተ. ያደርገዋል። ቃላዊ ግጥም በጊዜና በቦታ የአቀራረብና የትርጉም ለውጦች ሊታይበት ይችላል። ይህም የሚሆነው ያልተጻፈና በቃል የሚተላለፍ በመሆኑ ነው። የሥራ፣ የፉከራ፣ የሠርግ፣ የለቅሶ፣ የልመና ግጥሞች በቃላዊ ግጥም ውስጥ ይካተታሉ። የተወሰኑትን ቀጥሎ እንመለከታለን።

የሥራ ዘፈን ግጥሞች

የሥራ ዘፈኖች ስልቹነትንና ድካምን ይቀንሳሉ

ሰዎች በጋራም ሆነ በተናጠል ይሠራሉ። ሥራውን ለማቀላጠፍ እንዲያስችላቸው ይዘፍናሉ፣ ይጨፍራሉ፣ ያንጎራጉራሉ። ለምሳሌ እንደደቦ ባሉ የቡድን ሥራዎች ቤት ሲሠሩ፣ አጥር ሲያጥሩ፣ ሰብል ወይም ሳር ሲያጭዱ ያዜማሉ። በተናጠልም ሲያርሱ፣ ሲፈጩ፣ ሲፈትሉ ያንጎራጉራሉ። የሥራ ዘፈኖች ሥራው አሰልቺ እንዳይሆንና ሠራተኞች ድካም እንዳይጫናቸው ያደርጋሉ። ከሥራ ዘፈኖች መካከል በእርሻ ጊዜ የሚዜም ግጥም ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

ሀ. የባህር ማሽላ በጤፍ ከመበደር፣
እርሻ ሲያርሱ ውሎ ሲያርሱ ነበር ማደር።

ለ. መጋል ጠንክር በል እንጠንክር አብረን፣
እኔም እርፍ ልያዝ አንተም ሞፈሩን።



በደቦ ሲያርሱ የዋሉ አርሶአደሮች ማታ ወደቤት ተመልሰው እየበሉና እየጠጡ ይዘፍናሉ፤ ይጫወታሉ፤ ይፎክራሉ። ለምሳሌ አንዱ ተነስቶ

ሐ. የወይኖ ጌታ የስመጥሩ፣
የጫሌ ጌታ የስመጥሩ፣
የጀንበር ጌታ የስመጥሩ፣
መብረቅ ያረሰው ይመስላል ፈሩ።

በማለት ሲፎክር ሌላው «ሥራህ ነው!» እያለ ያበረታታል፤ ያሞካሽዋል። ሌላውም በተራው ይቀጥላል።

የቀረርቶ ግጥም

ቀረርቶ የጀግንነት መገለጫ ነው። ጠላትን ለመተንኮስም ያገለግላል። ለአብነትም የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

ሀ. እስኪ ላሙን ንዳው አቧራው ይነሳ፣
ይከተል የለም ወይ ኮርማው እያገሳ።

ለ. አሙን አለ፣ አሙን አለ፣ ተዋቸው ይሙን፣
ቢፈሩን ነውና ቢጠረጥሩን።

ሐ. ነጭ አሞራ በሮ ይገባል ከዋሻ፣
ያገርህን ጠላት አሳጣው መድረሻ።

የሠርግ ዘፈኖች

የሠርግ ዘፈን የሠርግ ሥነሥርዓት በሚከናወንበት ጊዜ ሥነሥርዓቱን ለማድመቅ ይዘፈናል። ሙሽራዋንና ሙሽራውን ለማሞካሸት፣ ታዳሚዎችን ለማዝናናት ብሎም ለማስጨፈር ይዘፈናል። የሙሽራዋና የሙሽራው እናት፣ አባት፣ አሳዳጊና ዘመድ አዝማድ ይወደሱበታል።

ሀ. ሊወስዳት ነው እኮ፣ ሊወስዳት ነው እኮ፣
ባልቴት ሸማግሌ አማላጁን ልኮ።

ለ. መሄዷ ነው፤ መሰናበቷ ነው፣
ችላው ምንድን ነው?

ሐ. ወንድምየ ወንድም አበባ፣
ይዘህ በጊዜ ግባ።



እየተባለ ይዘፈናል። በዕልልታም ይደምቃል።
ከላይ ያየናቸው ግጥሞች በቃል የሚነገሩና ክዋኔ ያላቸው በመሆናቸው ይመሳሰላሉ። በአከዋወናቸውና በሚያስተላልፉት መልእክት ደግሞ ይለያያሉ። የሥራ ዘፈኖች ሥራን ለማቀላጠፍና የሥራ ፍላጎትን ለማነቃቃት ይዜማሉ። የፉከራና የቀረርቶ ግጥሞች ወኔን ለመቀስቀስና ለማደፋፈር በሽለላና በፉከራ ይቀርባሉ። የሠርግ ዘፈኖች ደግሞ የሠርግን ሥነሥርዓት ለማድመቅ በአቀንቃኝ ይቀነቀናሉ።

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት «እውነት» ወይም «ሐሰት» ካላችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ተናገሩ።

ሀ. ቃላዊ ግጥም በጊዜና በቦታ አንዳንድ የአቀራረብና የትርጉም ለውጥ እየተደረገበት ይተላለፋል።

ለ. የሥራ ዘፈኖች ሠራተኞች ድካም እንዳይጫናቸው ያደርጋሉ።

ሐ. የቀረርቶ ግጥሞች ዋና ዓላማ ማዝናናት ነው።

መ. ቃላዊ ግጥሞች እንደዓይነታቸው ሁሉ ዓላማቸውም ይለያያል።

ተግባር 2

የቃላዊ ግጥሞችን ተመሳስሎና ልዩነት በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ ዘርዝሩ።

ተመሳስሎ	የቃላዊ ግጥሙ ዓይነት	ልዩነት
	የሥራ	
	የቀረርቶ	
	የሠርግ ዘፈን	

ተግባር 3

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ቃላዊ ግጥሞች ለከዋኙ ማኅበረሰብ ምን ጠቀሜታ አላቸው?

ለ. «ነጭ አሞራ በሮ ይገባል ከዋሻ፣

ያገርህን ጠላት አሳጣው መድረሻ»

የሚለው ግጥም መልዕክት ምን ይመስላችኋል?

ሐ. ቃላዊ ግጥሞች ባይኖሩ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ምን የሚያጎድሉት ነገር የሚኖር ይመስላችኋል?

2ኛ ቀን

ቃላት

ተግባር

በምንባቡ ውስጥ የተሠመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት የምንባቡን ሀሳብ በማይቀይሩ ተመሳሳይ ቃላትና ሐረጋት ተክታችሁ አንብቡ።

ምሳሌ፡-

ሥራውን ለማቀላጠፍ እንዲያስችላቸው ይዘፍናሉ፤ ይጨፍራሉ፤ ያንጎራጉራሉ።

ሥራውን ለማፋጠን እንዲያስችላቸው ይዘፍናሉ፤ ይጨፍራሉ፤ ያንጎራጉራሉ።

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

ግጥምን አስተካክሎ መጻፍ

ተግባር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት የሚከተሉትን ቃላዊ ግጥሞች ቤት እንዲመቱ አድርጋችሁ በማስተካከል ጻፉ።

ሀ. ሥነዜጋ ሚባል የምናውቅበት፣
መጥቶልን ትምህርት መብትና ግዴታን።

ለ. መጥፎውን ትታችሁ ጥሩ ሥራ ሥሩ፣
አንድ ነገር አለኝ አደራ ምላችሁ፣
አንድ ይሁን ልባችሁ መለያየት ይቅር።

ሐ. እጅጉን ልቃችሁ የእድገት መሠረት፣
መጽሐፍ አንብባችሁ በዕውቀት በሥራ
ለውድ አገራችሁ አለሁልሽ በሏት።

መ. ዕድሜ ላይሆን መተማመን
ሣይመረመሩ ባዶ ተስፋ

የፖስታ ላይ አድራሻ አጻጻፍ

ተግባር

በቡድን ሆናችሁ በፖስታ ላይ በላኪና በተቀባይ አድራሻ የሚካተቱ ነጥቦችን ምሳሌ እየሰጣችሁ ዘርዝሩ።



3ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

ቃላዊ ግጥም

ቅድመንባብ

ተግባር

የቃል ግጥም ዓይነቶችን ከዘረዘራችሁ በኋላ ተመሳስሏቸውን ተናገሩ።

ማንበብ

ተግባር

«ቃላዊ ግጥም» በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ የሚገኙትን ግጥሞች ተራበተራ ድምፅ እያሰማችሁ በጥንድ በጥንድ አንብቡ።

ማዳመጥ

እንቆቅልሽ

ቅድመማዳመጥ

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሥዕሉን ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን ተናገሩ።

ለ. በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ እንቆቅልሽ ተጫወቱ።

የማዳመጥ ሂደት

ተግባር

«እንቆቅልሽ» በሚል ርዕስ መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ ዋናዋና ሀሳቦች ማስታወሻ እየያዛችሁና የእንቆቅልሹንም መልስ እየገመታችሁ አዳምጡ።



አዳምጠ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በእንቆቅልሽ ጨዋታ ተሸናፊ የሚለየው እንዴት ነው?

ለ. የእንቆቅልሽ ጨዋታ በአብዛኛው የሚከወነው መቼ ነው?

ሐ. በተከታተላችሁት የእንቆቅልሽ ጨዋታ አሸናፊ ማን ነበር?

መ. የእንቆቅልሽ ጨዋታን ሕግና ሥርዓት ተናገሩ?

ሠ. «ዋለብህ አደረብህ፣

ሰርዶ በቀለብህ፣

እንደእንጀራ ነፈሰብህ»

የሚለው አገላለፅ መልዕክቱ ምንድን ነው?

ረ. «እንቆቅልሽ የልጆችን አዕምሮ ያሰላል» ሲባል ምን ማለት ነው? እንዴትስ ያሰላዋል?

ሰ. «ዐይኗን ተኩላ ገበያ ትወጣ» የተባለችው ባቄላ ናት። ዐይን መኳል ከባቄላ ጋር እንዴት እንደተዛመደ ተናገሩ።

ተግባር 2

የሚከተሉትን የእንቆቅልሽ ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. አልቀረም ተቀጥቅጦ አስተኛው ፈልጦ ፈልጦ።

ለ. ላዩ ሰርዶ ውስጡ ብርንዶ።

ሐ. ሰው ሳይቀምስ የምትቀምስ።

መ. ወገበ ጎባጣ አገሩን ሁሉ ቆምጣ ቆምጣ።

ሠ. ከመሬት ወደቀ አንስቼ ብይዘው አለቀ።

ረ. ሕይወት የሌለው ሌት ተቀን የሚሄድ።

ሰዋስው

ግሳዊ ሐረግን መለየት

ተግባር

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ግሳዊ ሐረጎች ለይታችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

በለጡ ወደቤቷ ሮጠች

ግሳዊ ሐረግ = ወደቤቷ ሮጠች

ሀ. ማስተዋል የቤትሥራዋን ሠራች።

ለ. እድሪስ የጓሮ አትክልት ተከለ።

ሐ. ሐያትና ቤተልሔም አበቦቹን ውኃ አጠጡ።

መ. አለልኝና ሙስጠፋ እግርኳስ ተጫወቱ።

ሠ. ሁሉአገርሽ ብዙ ተማሪዎችን መዘገበች።

ረ. ፍየሏ መንታ ግልገሎች ወለደች።

ሰ. በሬው የታሠረበትን ገመድ በጠሰ።

ማንበብ

ዝሆንና አውራ ዶሮ

ቅድመንባብ


መገመት

ከርዕሱና ከሥዕሉ በመነሳት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልፅ ገምቱ።

የማንበብ ሂደት

«ዝሆንና አውራ ዶሮ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ራሳችሁን እየጠየቃችሁና ለጥያቄዎቻችሁ ምላሽ ለማግኘት እየሞከራችሁ አንብቡ።

ዝሆንና አውራ ዶሮ



ዝሆኑ ራሱን ከአውራ ዶሮው ጋር እያወዳደረ ያኩራራል

ከዝሆን ጋር የሚኖር አንድ አውራ ዶሮ ነበር። አውራ ዶሮው ትንሽና ደካማ ትንሽና ደካማ ሲሆን ዝሆኑ ደግሞ ትልቅና ጠንካራ ነው። ዝሆን ራሱን ከአውራ ዶሮው ጋር እያወዳደረ ይኩራራል። «ተመልከት! እኔ ግዙፍና ጠንካራ

ነኝ፣ አንተ ግን ከማነስ በላይ ደካማ ነህ። ካንተ ይልቅ እጅግ ተፈላጊው እኔ ነኝ» እያለ ዝሆን ሁልጊዜ ለዶሮው ይነግረዋል።

ዶሮው በዝሆኑ ጭቅጭቅና ጉራ ተሰላቸ። እንዲህም ሲል መልስ ሰጠው። «አንተ ከእኔ በተሻለ ሁኔታ ተፈላጊ ልትሆን አትችልም። ግዙፍነትህን ጠንቅቄ አውቃለሁ። ግን አካላዊ ግዝፈት ብቻውን ተፈላጊ አያደርግም። አንተ ገዘፍክ እንጂ ብልሀት ብሎ ነገር ጨርሶ አልፈጠረብህም። እኔ በብልሀት ከአንተ የተሻልኩ ስለሆንኩ ይህ ችሎታዬ በሌሎች ዘንድ ተፈላጊ ያደርገኛል» አለ።

... አካላዊ ግዝፈት ብቻውን ተፈላጊ አያደርግም...

«ስህተት ፍፁም ስህተት!» አለ ዝሆን የዶሮውን ሀሳብ በማጣጣል። ዶሮው በበኩሉ ሀሳቡ ተቀባይነት እንዲያገኝ ሽንጡን ገትሮ ተከራከረ። «በጉዳዩ ላይ ላንስማማ እንችላለን። ስለዚህ እውነቱ መረጋገጥ ያለበትም በውድድር ብቻ ነው» አለ።

«ምን አይነት ውድድር እባክህ?» ሲል ዝሆኑ ወደታች በንቀት እያየ በመጠጋት ጠየቀው። «ማንኛችን ብዙ ውሃ መጠጣት እንደምንችል እንወዳደር? አሁኑኑ ወደ ወንዝ እንውረድ!» አለ ዶሮው ወደኋላ እያፈገፈገ። በዶሮው ንግግር ዝሆኑ ከት ብሎ ሳቀ። «ከአንተ የበለጠ ውሃ ጠጥቼ ውድድሩን አሸንፋለሁ!» በማለት ዝሆኑ ተኩራራ።

«ማንኛችን ብዙ ውሃ መጠጣት እንደምንችል እንወዳደር።»

ዝሆኑና አውራ ዶሮውም ሁሉም እንስሳት ወደወንዙ መጥተውና ውድድሩን እንዲታዘቡና እንዲዳኙ ጠየቁ። ውድድሩ ተጀመረ። ዝሆኑ ኩምቢውን ዶሮው ደግሞ ምንቃሩን ወደውሃው ጨመሩ። ዝሆኑ ውሃውን በጉሮሮው ያንደቀድቃል። ዶሮው ግን አፉን እየከፈተ ይገጥማል እንጂ ውሃ ፈፅሞ አልጠጣም።

ውድድሩ ተጀመረ... ዝሆኑ ፈንድቶ ሞተ... ትልቅ ከመሆን ብልህ መሆን ይሻላል

ታዛቢዎቹ አስተያየት ከመስጠት ተቆጥበው የውድድሩን መጨረሻ በጉጉት ይጠባበቃሉ። ዶሮው አሁንም አሁንም ከአንገቱ ደፋ ቀና ይላል። ዝሆን መጠጣቱን ቀጠለ። ሆዱ ትልቅ እየሆነ መጣ። ይበልጥ በጠጣ ቁጥር ሆዱ ይበልጥ እያበጠ መጥቶ፣ በመጨረሻ ዝሆኑ ፈንድቶ ሞተ። «አያችሁ!» አለ አውራዶሮ «ትልቅ ከመሆን ብልህ መሆን ይሻላል» አላቸው።

ምንጭ ዝሆንና አውራዶሮ። ኤልሳቤት ሌርድ። 2003። ቅፅ 1 መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሠደ።

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተለውን የድርጊት ቅደምተከተል ማሳያ ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ አዘጋጁ። ከዚያም «ዝሆንና አውራ ዶሮ» በሚለው ምንባብ ውስጥ የተከናወኑትን ድርጊቶች በቅደምተከተል ጻፉ።

1.	ዝሆን ሁልጊዜ ጠንካራ ነኝ እያለ ለአውራ ዶሮ ይነግረዋል።
2.	
3.	
4.	

ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ዝሆን አውራ ዶሮውን የሚጨቀጭቅበት ምክንያት ምን ነበር? (አንቀፅ 1)

ለ. አውራ ዶሮ ዝሆንን «አንተ ገዘፍክ እንጂ...» ሲል ምን ማለቱ ነው? (አንቀፅ 2)

ሐ. ዝሆንና አውራ ዶሮ ለውድድር የሄዱት የት ነበር?

መ. ከሁለቱ ተወዳዳሪዎች ውድድሩን ያሸነፈው ማን ነው?

ሠ. «ምንቃር» ምንድን ነው?

ረ. ከምንባቡ ምን እንደተማራችሁ ተናገሩ።

5ኛ ቀን

ቃላት

ቃላትን በድርጊት መግለፅ፣ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት

ተግባር 1

የሚከተሉትን ቃላት በተመለከተ መምህራችሁ በሚሠጧችሁ መመሪያ መሠረት በተግባር ምላሽ ስጡ።

ወደታች	ወደፊት	መራመድ
ወደላይ	ወደጎን	ማፈግፈግ

ተግባር 2

በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሠመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት የሚተኩ ተመሳሳይ ቃላትና ሐረጋት ከቀረቡት አማራጮች መርጣችሁ ፃፉ።

1. እህቴ ከአቅሟ <u>በላይ</u> ትሰራለች።

   ሀ. የበለጠ ለ. ውጭ ሐ. በተቃራኒ መ. ትይዩ

2. ቤተሰቦቹ በሚያደርጉለት ተገቢ ያልሆነ ድጋፍ <u>ይኩራራል</u>።

   ሀ. ይፎክራል ሐ. ይሸለላል

   ለ. ይመካል መ. ይንጎራደዳል

3. ዝሆን አውራ ዶሮን <u>በማጣጣል</u> መናገሩ ትክክል አይደለም።

   ሀ. ትንሽ በማድረግ ሐ. ዝቅ በማድረግ

   ለ. በማራከስ መ. በመሳደብ

4. ተማሪው <u>ሽንጡን ገትሮ</u> ከመምህሩ ጋር ተከራከረ።

   ሀ. በትምክህት ሐ. በመጮህ

   ለ. ቀጥ ብሎ መ. በፅናት

5. እንስሳቱ ውድድሩን <u>እንዲታዘቡ</u> ተጋበዙ።

   ሀ. እንዲያዩ ሐ. እንዲመሩ

   ለ. እንዲቆጣጠሩ መ. እንዲያስጀምሩ

6. ዝሆኑ ውሃውን በጉሮሮው <u>ያንደቀድቃል</u>።

   ሀ. ይጠጣል ሐ. ያፈሳል

   ለ. ያንቆረቁራል መ. ይውጣል

7. እንስሳቱ ወደወንዙ ወርደው የውድድሩን መጨረሻ <u>በጉጉት</u> ተጠባበቁ።

   ሀ. በፍቅር ሐ. በፍጥነት

   ለ. በናፍቆት መ. በትኩረት

8. አውራዶሮው ዝሆንን ለመፋለም ወደወንዝ <u>እንውረድ</u> አለው።

   ሀ. እንጓዝ ለ. እንሩጥ ሐ. እንሂድ መ. እንግስግስ

9. ወፍራሙ ሰውዬ ጡንቻውን በመተማመን <u>ጉራ</u> ያበዛል።

   ሀ. ክርክር ለ. ወሬ ሐ. ስድብ መ. ድንፋታ

10. አውራ ዶሮ ዝሆንን ለማሸነፍ የሚያስችል <u>ብልሃት</u> ተጠቀመ።

   ሀ. ትምህርት ለ. ተግባር ሐ. ተንኮል መ. ዘዴ

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በተሰጠ ርዕስ ግጥም መጻፍ

ተግባር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት ቀጥሎ ከቀረቡት ርዕሶች አንዱን መርጣችሁ ግጥም ፃፉ።

ሀ. ትምህርት ቤት ለ. ሀገሬ

የአጻጻፍ ሥርዓት

ፓስታ ማዘጋጀትና አድራሻ መፃፍ

ተግባር

መምህራችሁ በሚያሳዩአችሁ መሠረት ፓስታ አዘጋጅታችሁ የላኪና የተቀባይ አድራሻ በመፃፍ ለጓደኞቻችሁ ስጡ።

6ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

ዝሆንና አውራ ዶሮ

ቅድመንባብ

ተግባር

ከዝሆንና ከአውራዶሮ አሸናፊውን ለመለየት ብዙ ውሃ የመጠጣት ውድድር እንዲደረግ ሐሳብ ያፈለቀው ማን ነበር?

ማንበብ

ተግባር

«ዝሆንና አውራዶሮ» ከሚለው ምንባብ የመጀመሪያዎቹን 3 አንቀጾች በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ተራበተራ ድምጽ በማሰማት አንብቡ።።

መናገር

እንቆቅልሽ መጫወት

ተግባር

መምህራችሁ የሚሰጧችሁን መመሪያ በመከተል እንቆቅልሽ ተጫወቱ።

ሰዋስው

ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ያሉትን ባለቤቶችና ግሳዊ ሐረጎች እዝባር (/) በማድረግ ለዩ።

ምሳሌ፡- አውራዶሮ ሀሳብ አቀረበ።

አውራዶሮ / ሀሳብ አቀረበ።

ሀ. አየለች አውራ ዶሮዋን ሸጠች።

ለ. ዶሮወቹ እንቁላል ጣሉ።

ሐ. ገበሬው ዶሮዎቹን ወደውጭ ለቀቃቸው።

መ. ዶሮዎቹ መሬቱን ጫሩት።

ሠ. ዝሆንና አውራዶሮ ውድድራቸውን አካሄዱ።

3ኛ ሳምንት 7ኛ ቀን

የባህል ተስተላልፎና የቃላዊ ልማዶች ጠቀሜታ

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ተግባር

የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ።

ነጣጥሎ ማንበብ		አጣምሮ ማንበብ
ሀ	ቅሬታ-ኣቸው-ን	ቅሬታቸውን
ለ	ይነቅፉ-ብ-ኣቸው-ኣል	ይነቅፉባቸዋል
ሐ	ያንፀባርቁ-ብ-ኣቸው-ኣል	ያንፀባርቁባቸዋል
መ	ይገልፁ-ብ-ኣቸው-ኣል	ይገልፁባቸዋል
ሠ	ያሳውቁ-ብ-ኣቸው-ኣል	ያሳውቁባቸዋል
ረ	ይኮንኑ-ብ-ኣቸው-ኣል	ይኮንኑባቸዋል

ማንበብ

የምሳሌያዊ ንግግሮች ፋይዳ

ቅድመንባብ

የቀደመ ዕውቀትን መቀስቀስ

ተግባር

የምታውቋቸውን ምሳሌያዊ ንግግሮች ተናገሩ።

የማንበብ ሂደት

«የምሳሌያዊ ንግግሮች ፋይዳ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ራሳችሁን እየጠየቃችሁና ለጥያቄያችሁ መልስ ለማግኘት እየጣራችሁ አንብቡ።

የምሳሌያዊ ንግግሮች ፋይዳ

ምሳሌያዊ ንግግሮች ሰዎች ስለማኅበራዊ፣ ስለኢኮኖሚያዊ፣ ስለፖለቲካዊ ጉዳዮች ሂስ ይሰጡባቸዋል።

ምሳሌያዊ ንግግሮች ከሥነቃል ዓይነቶች ይመደባሉ። በጥቂት ምርጥ ቃላት አማካይነት ሰፊ ሀሳብን ይገልጻሉ። ምሳሌያዊ ንግግሮች ለሀሳብ መቋጫ፣ ማጠናከሪያ፣ ማጉያና ግልጽ ማድረጊያ

ይሆናሉ። ሰዎች በንግግራቸውና በጽሑፋቸው መካከል ጣልቃ እያስገቡ ይገለገሉባቸዋል።

ምሳሌያዊ ንግግሮች በማኅበረሰቡ ዘንድ ጠቃሚና ተፈላጊ መግባቢያዎች ናቸው። ሰዎች ብሶታቸውን፣ ሀዘናቸውን፣ ደስታቸውን፣ አመለካከታቸውን ያንጸባርቁባቸዋል፤ እምነታቸውን ይገልጹባቸዋል። በተጨማሪም ቅሬታቸውን ያሳውቁባቸዋል፤ አስነዋሪ ተግባራቸውን ይነቅፉባቸዋል። ጎጂ ድርጊቶችን ያወግዙባቸዋል፤ ሠናዮቹንም ያወድሱባቸዋል። በአጠቃላይ በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ፣ በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሂስ ይሰጡባቸዋል። ከነዚህም መካከል ጥቂቶቹን በምሳሌ እንመለከታለን።

1. ምሳሌያዊ ንግግሮች የሥራ ክቡርነትና አስፈላጊነት ይገለጽባቸዋል። በአንጻሩ ደግሞ ስንፍና ይወገዝባቸዋል።

   ሀ. የሥራን ክቡርነት የሚገልጹ ምሳሌያዊ ንግግሮች

   - ሥራ ካልሠራችሁ፣ የት ይገኝ ምሳችሁ?
   - ከመቸገር ሠርቶ ማደር።

   ለ. ስንፍናን የሚያወግዙ ምሳሌያዊ ንግግሮች

   - ሰነፍ ሰንፎ ያሰንፋል።
   - ሰነፍ ይዘራል እንጂ፣ አያርምም።

2. ምሳሌያዊ ንግግሮች ሰናይ ልማዶች ተጠብቀው ከትውልድ ወደትውልድ እንዲተላለፉ፣ ከልማድ ማፈንገጥ እንዳይኖር በማድረግ ረገድ ፋይዳቸው የጎላ ነው፤ ጎጂ ልማዶች ደግሞ እንዲለወጡ ያስተምራሉ።

   ሀ. ሰናይ ልማዶችን የሚገልጹ ምሳሌያዊ ንግግሮች

   - ስም ከመቃብር በላይ ይውላል።
   - ሽማግሌ ይገላግላል፣ የተጠቃ አቤት ይላል።
   - እውነት የተናገረ በመርከብ የተሻገረ።

   ለ. ጎጂ ልማዶችን የሚያንፀባርቁ ምሳሌያዊ ንግግሮች

   - ለልጅ ፊት አይሰጡም።
   - ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል።

3. ምሳሌያዊ ንግግሮች ስስታምነት፣ ግለኝነትና ራስወዳድነት አሳፋሪ ምግባሮች መሆናቸውን ያስገነዝባሉ።

   - አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል።
   - «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል» አለች አህያ።

4. ምሳሌያዊ ንግግሮች ፍርሃትን በማንኳሰስ፣ ጉብዝናንና ድፍረትን ያሞግሳሉ።

   - «በጎደሎ ቀን የገዛሁት ጋሻ ሳያስገድለኝ አይቀርም» አለ፣ ፈሪ።

- ደፋርና ጨለ፣ መውጫ አያጣም።
- ፈሪ፣ የሚያባርረው ሰው ሳይኖር ይሸሻል።

5. ምሳሌያዊ ንግግሮች በግልጽ መወያየትን፣ መመካከርን፣ መደጋገፍን ያበረታታሉ።
   - በሽታውን የደበቀ መድኀኒት አይገኝለትም።
   - ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ።
6. ምሳሌያዊ ንግግሮች የህዝብን ቅሬታና የመተባበርን አስፈላጊነት ይገልጻለ።
   - አገር ቢያብር ለንጉሥ ያስቸግር።
   - ድር ቢያብር አንበሳ ያስር።
   - «በካብ ላይ ብሠራ እባቡ መከራ፣ በዛፍ ላይ ብሠራ አሞራው መከራ፣ የት ውየ የት አድር ብየ» አለች፣ ወፍ።

በአጠቃላይ ምሳሌያዊ ንግግሮች በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ ልማዳዊና ባህላዊ ዕሴቶች ይንጸባረቁባቸዋል። በዘመናት የተካበቱት ጠቃሚ ዕሴቶች ከትውልድ ወደትውልድ እንዲተላለፉ፣ ትውልዱም እንዲማርባቸው ያግዛለ። ተተኪ ትውልዶች ማንነታቸውን እንዲያውቁና በመልካም ሥነምግባር እንዲታነጹ ያደርጋለ።

(ኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ፣ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር። 1982። *የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች*። መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ምሳሌያዊ ንግግሮች ለምን ይጠቅማለ?

ለ. በምሳሌያዊ ንግግሮች ሰዎች ምን ምን ጉዳዮችን ይገልፁባቸዋል?

ሐ. «ምሳሌያዊ ንግግሮች ተተኪ ትውልዶች ማንነታቸውን እንዲያውቁና በመልካም ሥነምግባር እንዲታነፁ ያደርጋለ።» ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል? በቡድን ተወያዩና ለመምህራችሁ ተናገሩ።

ተግባር 2

ምሳሌያዊ ንግግሮቹን በተለመደው መንገድ የሚያሟሉ አባባሎችን መርጣችሁ ጻፉ። በመቀጠልም በምንባቡ መሠረት መድቧቸው።

1. ፈሪና ንፉግ _____።

ሀ. የያዙትን አይሰጡም

ለ. ከያዙ አይለቁም

ሐ. እያደር ይቆጫለ

መ. ፈጥነው ይሄዳለ

2. ያበረ ወገኑን _____።

ሀ. አስደፈረ
ሐ. አስቸገረ
ለ. አስከበረ
መ. አስደበደበ

3. ለተራበ ቂጣ፣ _____።

ሀ. ለተጠማ ዋንጫ
ሐ. ለተጠማ አረቄ
ለ. ለጠገበ ጡጫ
መ. ለበላ ቆሎ

4. የቆጡን አወርድ ብላ _____።

ሀ. ወደላይ ተንጠራራች
ሐ. ወድቃ ተሰበረች
ለ. ፈጥና ተነሳች
መ. የብብቷን ጣለች

5. ጋን በጠጠር _____።

ሀ. ይመረጋል
ለ. ይሠራል
ሐ. ይደገፋል
መ. ይሰበራል

6. ሰነፍ ተቀምጦ ተቀምጦ _____።

ሀ. ከብት ሲገባ ይሠራል
ሐ. በረሃብ ይሞታል
ለ. ሲያንቀላፋ ይውላል
መ. ገንዘብ ያበድራል

8ኛ ቀን

ቃላት

ለቃላት ዐውዳዊና ተቃራኒ ፍቺ መስጠት

ተግባር 1

ለሚከተሉት ቃላት ዐውዳዊ ፍቺ ስጡ።

ሀ. መቋጫ (አንቀጽ 1)
ለ. ማጉያ (አንቀጽ 1)
ሐ. ጣልቃ (አንቀጽ 1)
መ. አመለካከት (አንቀጽ 2)
ሠ. ሲሾም (አንቀጽ 2፣ ተራ ቁጥር 2፣ ለ)

ተግባር 2

በ«ሀ» ረድፍ ለተዘረዘሩት ቃላት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ«ለ» ረድፍ በመምረጥ አዛምዱ።

ሀ	ለ
1. ሠናይ	ሀ. መስማማት
2. ሲሻር	ለ. ሲሾም
3. ነቀፌታ	ሐ. ድጋፍ
4. ማፈንገጥ	መ. አኩሪ
5. አስነዋሪ	ሠ. መጥፎ

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

ግጥም አስተካክሎ መጻፍ

ተግባር

ባለፈው ክፍለጊዜ የጻፋችሁትን ግጥም በቡድን አስተካክላችሁ በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

የሠላምታ ደብዳቤ ጽፎ በፖስታ መላክ

ተግባር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት የሠላምታ ደብዳቤ ጽፋችሁ በፖስታ አሽጉ። በፖስታውም ላይ የላኪና የተቀባይ አድራሻ ጻፉ።

9ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

የምሳሌያዊ ንግግሮች ፋይዳ

ቅድመንባብ

ተግባር

የምሳሌያዊ ንግግሮችን ጠቀሜታ ዘርዝሩ።

ማንበብ

ተግባር

«የምሳሌያዊ ንግግሮች ፋይዳ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ በማሰማት በጋራ አንብቡ።

መናገር

ምሳሌያዊ ንግግሮች የሚነገሩባቸውን ዐውድ መናገር

ተግባር

ቀጥሎ የተዘረዘሩት ምሳሌያዊ ንግግሮች የሚነገሩባቸውን ዐውዶች/አጋጣሚዎች ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

ሀ. ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው።

ለ. ዶሮ ጭራ ጭራ አወጣች መታረጃዋን ካራ።

ሐ. ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ።


ሰዋስው

ግሳዊ ሐረግ

የሚከተሉትን ግሶች በመጠቀም ዓረፍተነገር መሥርቱና ግሳዊ ሐረጉን በእዝባር(/) አሳዩ።

ምሳሌ፡- በርካታ የዱር እንስሳት/ደኑ ስለተመነጠረባቸው ተሰደዱ።

ተሰደዱ	ቀባች	ተለቀቁ	ሠሩ
ጠገነ	አጠበ	ቆፈረች	አስተካከለች



ምዕራፍ 10 ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ፤ መድሎና መገለል

የመድሎና የመገለል ተፅዕኖዎች

1ኛ ሳምንት 1ኛ ቀን

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጣጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	የ-ተከታተሉ-ት	የተከታተሉት
ለ	በ-አኗኗር-ኡ-ም	በአኗኗሩም
ሐ	ያ-ተኩስ-ኧው-ኣል	ያተኩሰዋል
መ	እንዲደረግ-ል-ኧት	እንዲደረግለት
ሠ	አስ-መክራ-ው-ኣል-ኧች	አስመክራዋለች

ማንበብ

ወይኔ ሰውዬው!

ቅድመንባብ

መገመት

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «ወይኔ ሰውዬው!» የሚለው አገላለጽ ምንን ያመለክታል?

ለ. ሥዕሉን በመመልከትና ከርዕሱ ጋር በማዛመድ ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

የማንበብ ሂደት

ተግባር

ቀጥሎ «ወይኔ ሰውዬው!» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ እየገመታችሁና ግምታችሁን እያረጋገጣችሁ አንብቡ።

ወይኔ ሰውዬው!



ሰውዬው ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት ነው። ቤተሰቡ የሚተዳደረው እሱና ባለቤቱ የቀን ሥራ ሠርተው በሚያገኙት ገቢ ነው። ባለቤቱ በየቤቱ እየዞረች እንጀራ ትጋግራለች፤ አሻሮ ቆልታ ትፈጫለች፤ ልብስም ታጥባለች። እሱም እንጨት ይፈልጣል፤ ጭቃ አቡክቶ ቤት ይመርጋል። ቀን ሲሠራ ውሎ ማታ ጠላና አረቄ ጠጥቶ ሞቅ ብሎት ወደቤቱ ይገባል። ባለቤቱ ይህንን ልማድ እንዲተው በተደጋጋሚ ጠይቃዋለች። በዘመድና በሽማግሌ አስመክራዋለች። እሱ ግን ጆሮ አልሰጠም። ይባስ ብሎም በተደጋጋሚ ሰክሮ እየገባ መረበሽና ሲያሰኘውም ከቤቱ ውጪ ማደር ጀመረ።

የደም ናሙና ሰጥቶ ሲመረመርም ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንዳለበት ታወቀ።

ከጊዜ በኋላ ሰውዬው የጤና መታወክ አጋጠመው። ህመሙ እየበረታበት ስለመጣ የቀን ሥራውን እንደድሮው መሥራት አልቻለም። ለብዙ ሰዓት ያስለዋል፤ የማያቋርጥ ትኩሳት አለበት፤ የምግብ ፍላጎቱም ከወትሮው ቀንሷል። ሕመሙ እየተባባሰ

በመምጣቱ ወደሆስፒታል ተወሰደ። የሳንባ ቲቢ ሕመምተኛ መሆኑ ስለተረጋገጠ ተኝቶ ሕክምናውን እንዲከታተል ተደረገ። የጤንነቱን ሁኔታ የተከታተሉት ሐኪም የምክር አገልግሎት ከሰጡት በኋላ የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ምርመራ እንዲደረግለት ፈቃደኛነቱን ጠየቁት። ለተወሰኑ ቀናት ከራሱ ጋር ሲሟገት ከሰነበተ በኋላ ፈቃደኛ መሆኑን ገለጸላቸው። የደም ናሙና ሰጥቶ ሲመረመርም ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ እንዳለበት ታወቀ። ውጤቱ ሲነገረውም ከመጠን በላይ ደነገጠ። ሁሉም ነገር ድብልቅልቅ አለበት። የዓለም ፍጻሜ የሆነ መሰለው። ሁኔታውን የተመለከቱት ሐኪም መረጋጋት እንዳለበት አጥብቀው መከሩት። በሽታን የመከላከል አቅሙ ስለተዳከመ የፀረኤች..አይ.ቪ.. ሕክምና ተጠቃሚ መሆን እንዳለበትም አስረዱት።

ከአንድ ወር ተከታታይ ሕክምና በኋላ የሰውዬው ጤንነት እየተሻሻለ መጣ። ከጭንቀት ተላቆ የመኖር ተስፋው ለመለመ። ሐኪሙ በየጊዜው እየተከታተሉ ህይወቱን እንዴት መምራት እንዳለበት አስረዱት። የፀረኤች.አይ.ቪ.. መድኀኒት ሳያቋርጥ እንዲወስድና በአኗኗሩም እንዲጠነቀቅ መከሩት። አልኮል መጠጣት እንደሌለበትም አስጠነቀቁት። ይህንን ካደረገ እንደማንኛውም ሰው መኖር እንደሚችል ገለጹለት። ተጨማሪ ድጋፍና እንክብካቤ እንደሚደረግለት ቃል ከገቡለት በኋላ ከሆስፒታል ወጣ።

ከሁለት ወራት በኋላ ግን ሰውዬውና ቤተሰቡን ያልጠበቁት ችግር አጋጠማቸው። የቤት ለቤት ድጋፍና እንክብካቤ ሠራተኞች ከሰውዬው ቤት ወጣገባ ማለት ጀመሩ። ይህንን የተመለከቱት ጎረቤቶቻቸው ጥርጣሬ ስላደረባቸው ማጣራት ጀመሩ። የሰውዬው ተደጋጋሚ የጤና ችግር ከኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ጋር የተያያዘ መሆኑን አረጋገጡ። ሰውዬውንና ቤተሰቡን ፊት ነሷቸው። በቅርብ ይረዷቸው የነበሩት ዘመዶቻቸው ሳይቀሩ ራቋቸው። በአንድ ግቢ ውስጥ አብረው የሚኖሩት ጎረቤቶቻቸውም ልጆቻቸው ከሰውዬው ልጆች ጋር አብረው እንዳይጫወቱ ከለከሉ። የቤት አከራዩም ቤቱን ሊያድሱት እንደሚፈልጉ ገለጸውላቸው በአንድ ሳምንት ውስጥ እንዲለቁላቸው ነገሯቸው። ሰውዬውና ቤተሰቡም እየተፈጠረ ባለው ሁኔታ እጅግ ተደናገጡ። በከፍተኛ ሀዘን ላይም ወደቁ። የተስፋ መቁረጥ ስሜትም ተሰማቸው። የወደፊት ኑሯቸውም ድቅድቅ ጨለማ መስሎ ታያቸው።

> **በአንድ ግቢ ውስጥ አብረው የሚኖሩ ጎረቤቶቻቸውም ልጆቻቸው ከሰውዬው ልጆች ጋር አብረው እንዳይጫወቱ ከለከሉ።**


ሰውዬውም ቤተሰቡን ለችግር በመዳረጉ ራሱን ይዞ በህይወቱ የፈፀማቸውን መጥፎ ተግባራት በማስታወስ «ወይኔ ሰውዬው» በማለት ፀፀቱን ገለጸ።

(ፌደራል ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት። ግንቦት 2004። ማግለል፣ መድሎዎና አለመቀበልን ለመከላከል የተዘጋጀ የስልጠናና የአፈጻጸም መመሪያ ገጽ 37 ለውጥ ተደርጎ የተወሰደ።)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተለውን የቢጋር ሳጥን በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ የምንባቡን የመጀመሪያ፣ የመካከልና የመጨረሻ ድርጊቶች በቅደምተከተል ዘርዝሩ።



ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. ሰውዬው በዘመድና በሽማግሌ ከተመከረ በኋላ ያመጣው የባህርይ ለውጥ ምንድን ነው?

ለ. ሰውዬው ለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ የተጋለጠው በምን ምክንያት ነው?

ሐ. በሰውዬው ላይ በመጀመሪያ የታዩትን የሕመም ምልክቶች ዘርዝሩ።

መ. ሰውዬው ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ እንዳለበት ሲነገረው የተሰማውን ስሜት ተናገሩ።

ሠ. ሐኪሙ ለሰውዬው የሰጡት ምክር ምንድን ነው?

ረ. ሰውዬውና ቤተሰቡ የደረሰባቸው የመገለል ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

ሰ. የምንባቡ ዓላማ ምን ይመስላችኋል?

ሸ. የአካባቢው ሰዎች በሰውዬውና በቤተሰቡ ላይ ያደረጉት ነገር ትክክል ይመስላችኋል? ለምን?

ቀ. የቤት አከራዩን ብትሆኑ ኖሮ ተከራዩ በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መያዙን እንዳወቃችሁ ምን ታደርጉ ነበር?

2ኛ ቀን

ቃላት

የተለየ ፍቺ ያለውን ቃል መለየት፤ ለፊሊጣዊ አነጋገር ፍቺ መስጠት

ተግባር 1

ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ ካላቸው ፍቺ የተለየ ፍቺ የያዘውን አማራጭ ለይታችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።

1	ሲያሰኘው	ሀ. ሲሻው	ለ. ሲያስፈልገው	ሐ. ሲያምረው
2	መታወክ	ሀ. መበጥበጥ	ለ. መዛባት	ሐ. መቃወስ
3	አስጠነቀቁት	ሀ. አሳወቁት	ለ. ዛቱበት	ሐ. ነገሩት
4	እየበረታበት	ሀ. እየተጋነነበት	ለ. እየጠነከረበት	ሐ. እየባሰበት
5	ድጋፍ	ሀ. እገዛ	ለ. ማጠናከሪያ	ሐ. እርዳታ
6	ሊያድሱ	ሀ. ሊዝናኑ	ለ. ሊያሻሽሉ	ሐ. ሊጠግኑ
7	አስመክራዋለች	ሀ. አስጠንቅቃዋለች	ለ. አስለምናዋለች	ሐ. አስገስፃዋለች

ተግባር 2

ለሚከተሉት ፊሊጣዊ ንግግሮች ፍቻቸውን ስጡ።

ምሳሌ፡- ሞቅ ብሎት ⟹ ሰክሮ

ሀ. ጆሮ አልሠጠም

ለ. አመዱ ቡን አለ

ሐ. ፊት ነሷቸው

መ. ተስፋ መቁረጥ

ሠ. ተስፋው ለመለመ

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

የምንባቡን ሀሳብ በምክንያትና ውጤት መተንተን

«ወይኔ ሰውዬው!» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ሀሳቦች የምክንያትና ውጤት ግንኙነት በቢጋር ሠንጠረዥ አዘጋጅታችሁ ተንትኑ።

የአጻጻፍ ሥርዓት

የማመልከቻ ደብዳቤ አጻጻፍ

የማመልከቻ ደብዳቤ ናሙና

ማመልከቻ ደብዳቤ የራሱ የሆነ የአጻጻፍ ሥርዓት አለው። ይህንንም በሚከተለው የማመልከቻ ደብዳቤ ናሙና መመልከት ይቻላል።

ከተማሪ ናሆም ዘለቀ
ህብር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት
5ኛ«ሀ» ክፍል
ስልክ ቁጥር
አዲስ አበባ
ቀን፡- ሰኔ 25/2006 ዓ.ም.

ለህብር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለከተማ
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የመሸኛ ደብዳቤ እንዲሰጠኝ መጠየቅ

ቤተሰቦቼ ወደሰሜን ጎንደር መስተዳድር ዞን በመንግሥት ሥራ ምክንያት ተዛውረዋል። እኔም በ2007 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን በአዬ በካፋ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤት እንደምማር ወላጆቼ ስለነገሩኝ የመሸኛ ደብዳቤ እንዲሠጠኝ አመለክታለሁ።

ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም!

ፊርማ

ናሆም ዘለቀ (ተማሪ)

ተግባር

መምህራችሁ የሚጠይቋችሁን ጥያቄዎች ከላይ የቀረበውን ማመልከቻ መነሻ በማድረግ በጽሑፍ መልሱ።

3ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

ወይኔ ሰውዬው!

ቅድመንባብ

ተግባር

የሬድዮ ጋዜጠኞች በሬድዮ ሲያነቡ አዳምጣችሁ ታውቃላችሁ? እንዴት ያነባሉ?

ማንበብ

ተግባር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት «ወይኔ ሰውዬው!» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ድምፅ በማሰማት አንብቡ።

ማዳመጥ

የበቀል ጥንስስ

ቅድመማዳመጥ

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. «በቀል» ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. «ጥንስስ» የሚለው ቃል ፍቺስ ምን ይመስላችኋል?

ሐ. «የበቀል ጥንስስ» ከሚለው ርዕስ ተነስታችሁ ምንባቡ ስለምን እንደሚገልፅ ገምቱ።

የማዳመጥ ሂደት

ተግባር

መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ምንባብ ሀሳቦች የምክንያትና ውጤት ግንኙነት እያስተዋላችሁ አዳምጡ። ስታዳምጡ ዋናዋና ምክንያቶችንና ውጤቶችን በተመለከተ ማስታወሻ ያዙ።

አዳምጦ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. የልጅቷ ወንድ ጓደኛ ታሞ የሞተው በምን ምክንያት ነው?

ለ. የፀረኤች.አይ.ቪ. ሕክምና ተጠቃሚ ሆነች ሲባል ምን ማለት ይመስላችኋል?

ሐ. ያዳመጣችሁት ታሪክ ምን ስሜት ፈጠረባችሁ?


መ. የልጅቷ ቤተሰብ ብትሆኑ ኖሮ በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መያዟን ስትነግራችሁ ምን ታደርጉ ነበር?

ሠ. የደራሲው/ዋ ዓላማ ምን ይመስላችኋል?

ረ. ያዳመጣችሁት ምንባብ ታሪኩ ያለቀ አይመስልም፣ እስኪ በራሳችሁ መንገድ ጨርሱት።

ተግባር 2

ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተለውን የቢጋር ሳጥን አሟሉ።



ሰዋስው

ሐተታዊ ዓረፍተነገር

ተግባር 1

የሚከተሉት ዓረፍተነገሮች አወንታዊ ወይም አሉታዊ መሆናቸውን በመለየት በደብተራችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡-

1. ሴትዮዋ ክፉ ሰው አይወዱም። (አሉታዊ ዓረፍተነገር)
2. ወይንሸት የልብስ ሱቅ አላት። (አወንታዊ ዓረፍተነገር)

ሀ. መስታወት መኪና አልገዛችም።

ለ. ነኢማ ዳቦ ቤት አላት።

ሐ. አንበሳ ሣር አይበላም።

መ. አዳዲስ ቤቶች ተገነቡ።

ሠ. ሰላማዊት ዶሮ ወጥ ትወዳለች።

ረ. አወል ወፍራም ሸራብ ገዛ።

ሰ. ዛሬ ምንም ሥራ አልሠሩም።

ሸ. አፀደ ከትምህርትቤት አልተመለሰችም።

ቀ. ሃሊማ ትልቅ ቤት ሠራች።

በ. ልጆቹ ከመኝታቸው አልተነሱም።

ተግባር 2

«ወይኔ ሰውዬው!» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ውስጥ 5 አወንታዊ ሐተታ ዓረፍተነገሮችና ሁሉንም አሉታዊ ዓረፍተነገሮች ለይታችሁ በማውጣት በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ፤ መድሎና መገለልን የመከላከያ መንገዶች

ማንበብ

ሁሉም የድርሻውን ይወጣ!

ቅድመንባብ

መገመት

ተግባር

የሚከተሉትን የቅድመንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በሥዕሉ በምትታየው ተማሪ ደረት ላይ ያለው የምን ምልክት ነው?

ለ. ተማሪዋ ምን እያደረገች ይመስላችኋል?

ሐ. ርዕሱንና ሥዕሉን በመመልከት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

የማንበብ ሂደት

ሁሉም የድርሻውን ይወጣ!

ተግባር

«ሁሉም የድርሻውን ይወጣ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ራሳችሁን እየጠየቃችሁና፣ ለጥያቄያችሁ መልስ ለማግኘት እየጣራችሁ አንብቡ።



ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ስለሚተላለፍባቸውና ስለማይተላለፍባቸው መንገዶች መረጃ ማግኘት መድሎንና መገለልን ለመከላከል ሁነኛ ዘዴ ነው።

ሙሳና አስቴር የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ሁለቱም በትምህርታቸው ጎበዞች ናቸው። ከትምህርታቸው ጎንለጎን በትምህርትቤቱ ውስጥ በተቋቋመው የፀረኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ክበብ አባል ሆነው ያገለግላሉ። ለትምህርትቤቱ ማኅበረሰብ ፀረኤች.አይ.ቪ./ኤድስን በተመለከተ ልዩልዩ መረጃዎችን ሲያስተላልፉ ቆይተዋል። ዛሬም ከሠንደቅዓላማ ሥነሥርዓት በኋላ «የመድሎና መገለል መከላከያ መንገዶችን» ለማስተዋወቅ ቀጠሮ ተይዞላቸው በቦታው ተገኝተዋል።

በመጀመሪያ ሙሳ ገለጻውን እንደሚከተለው አቀረበ። «ኤች.አይ.ቪ. ስለሚተላለፍባቸውና ስለማይተላለፍባቸው መንገዶች መረጃ ማግኘት መድሎንና መገለልን ለመከላከል ሁነኛ ዘዴ ነው። ምክንያቱም መድሎና መገለል የሚመጡት ከዕውቀት ማነስ ነውና። ለማኅበረሰቡ ተገቢ መረጃዎችን ባለማስተላለፋችን ወገኖቻችንን እየጎዳን እንገኛለን። ስለዚህ ሁላችንም ተረባርበን ማስተማር ይገባናል። በተለይ ከሃይማኖት አባቶች፣ ከጎሳ መሪዎች፣ ከአገር ሽማግሌዎችና ከታዋቂ ሰዎች ጋር ሆነን ብንሠራ ውጤታማ እንሆናለን። ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች በማኅበረሰቡ ዘንድ ተደማጭነትና ተአማኒነት አላቸው። እነሱ የሚናገሩት ተቀባይነት አለው። ይህንን ካደረግን ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በደማቸው ውስጥ ካለባቸው ሰዎች ጋር ለመቀራረብና አብሮ ለመኖር ያለው ፍርሀት ይወገዳል» አለ።

ሙሳ ንግግሩን ገታ አድርጎ አድማጮቹን ከቃኘ በኋላ ንግግሩን ቀጠለ። «ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በደማቸው ውስጥ ካለባቸው ሰዎች ጋር አብሮ በመኖርም መድሎና መገለልን መከላከል ይቻላል። ይህም ማለት አብሮ በመብላትና በመጠጣት፣ ጊዜ ሰጥቶ አብሮ በመቆየት፣ በማገዝና ችግራቸውን አድማጭና መፍትሔ ሰጪ በመሆን መርዳት ማለት ነው። በተጨማሪም የፀረኤች.አይ.ቪ. አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማበረታታት መርዳት ይቻላል። ብዙ ሰዎች አብረዋቸው በሆኑ ቁጥር ሌሎች ሰዎችም እነሱን መቅረብ አደጋ የሌለው መሆኑን ያስተውላሉ። ስለዚህ ወገኖቻችንን ለመታደግ በቅድሚያ እኛ ራሳችንን አሳምነን ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል» ካለ በኋላ አመስግኖ ከመድረክ ወረደ፣ ተማሪዎችም ሞቅ ባለ ጭብጨባ አድናቆታቸውን ገለፁለት። በመቀጠልም «ማለባበስ ይቅር» የሚለው ታዋቂ ድምጻውያን በጋራ ያዜሙት ሙዚቃ መሰማት ጀመረ።

ከሙዚቃው በኋላም አስቴር ወደመድረክ ወጥታ ገለጻዋን ቀጠለች። «መድሎንና መገለልን ለመከላከል በደማቸው ኤች.አይ.ቪ. ያለባቸው ሰዎች አወንታዊ የአኗኗር ዘዴን እንዲከተሉ ማድረግ ይገባል። ይህም ጤንነታቸው ተጠብቆ እንዲቆይ ያግዛቸዋል። የተመጣጠኑ ምግቦችን በመመገብና የአልኮል መጠጦችን በመተው

ጤንነታቸውን ጠብቀው መቆየት ይችላሉ። እንዲሁም ሲጋራ ከማጨስና ጫት ከመቃም በመቆጠብ ጤንነታቸውን መጠበቅ ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም ከበሽታ አምጪ ተሃዋስያን ራሳቸውን በመጠበቅና ሕመም ሲያጋጥማቸው ፈጥነው በመታከም ጤንነታቸውን መጠበቅ ይገባቸዋል። በዚህ ሁኔታ ጤናማ ሆነው መኖር ከቻሉ ማኅበረሰቡ ስለበሽታው ያለው የተጋነነ ፍርሀት ይቀንሳል። ይህም መድሎና መገለል እንዲቀንስ ያደርጋል። ስለዚህ ከእኛ የሚጠበቀው እነዚህን ተግባራት ባለጉዳዮቹ እንዲያውቋቸውና እንዲተግብሯቸው ማስተማርና ማገዝ ነው» ካለች በኋላ ንግግሯን ለአፍታ ቆም አድርጋ፣ ታዳሚዎቿን በዐይኗ ቃኘች። ሁሉም ፀጥ ብለው ይከታተላሉ። ጉሮሮዋንም ጠራርጋ ንግግሯን ቀጠለች።

ሰዎች በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በመያዛቸው ምክንያት የመገለል ስሜት ሊፈጠርባቸው አይገባም።

«ከሰዎች ጋር ስንነጋገር የምንጠቀምባቸው ቃላት የመድሎና የመገለል ስሜትን የሚያንጸባርቁ መሆን የለባቸውም። ሰዎችም እንደነዚህ ያሉ ቃላትን እንዳይጠቀሙ መምከር አለብን። ምክንያቱም ቃላቱን በተጠቀምን ቁጥር ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ ያለባቸውን ሰዎች ስሜት በከፍተኛ ደረጃ ልንጎዳ እንችላለን።»

«በመጨረሻም እንድታውቁት የምፈልገው መሠረታዊ ጉዳይ አለ። መድሎና መገለልን መቀነስ የኤች.አይ.ቪ. ስርጭትን ለመግታት የሚደረገው ጥረት አካል መሆኑን ማወቅ ይኖርባችኋል። ሰዎች በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በመያዛቸው ምክንያት የመገለል ስሜት ሊፈጠርባቸው አይገባም። የመገለል ስሜት ከተፈጠረባቸው በይፋ መመርመርና ሕክምና መከታተል አይፈልጉም። ይህ ደግሞ ለቫይረሱ መስፋፋት መንገድ ይከፍታል። ስለዚህ ሁላችንም መድሎንና መገለልን መከላከል ይኖርብናል» ካለች በኋላ ጥያቄ እንዲያቀርቡ ጋበዘች። የተወሰኑ ተማሪዎችም ጥያቄዎቻቸውን አቅርበው መልስ ተሰጣቸው። አስቴርም አመስግና ከመድረክ ስትወርድ ጭብጨባ አስተጋባ። ተማሪዎችም ወደየመማሪያ ክፍላቸው ገቡ።

(ሔልዝ ኮሚውኒኬሽን ፓርትነርሺፕ። *ወጣቱና ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ፣ የመልዕክት መመሪያ፣ ጤናማ ተግባራት ለኢትዮጵያ ወጣቶች።* መጠነኛ ለውጥ ተደረጎበት የቀረበ። ዓ.ም. ያልተጻፈበት)

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

የሚከተሉት ዓረፍተነገሮች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ «እስማማለሁ» ትክክል ካልሆኑ ደግሞ «አልስማማም» ካላችሁ በኋላ ምክንያታችሁን በቃላችሁ ተናገሩ።

ሀ. ሙሳና አስቴር በትምህርትቤቱ ውስጥ የተመደቡ የጤና ባለሙያዎች ናቸው።

ለ. መድሎና መገለል የሚመጡት ከዕውቀት ማነስ ነው።

ሐ. ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ካለባቸው ሰዎች ጋር አብሮ በመኖር መድሎንና መገለልን መቀነስ አይቻልም።

መ. መድሎንና መገለልን መቀነስ የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ሥርጭትን ለመግታት የሚደረግ ጥረት አካል ነው።

ተግባር 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል መርጣችሁ ጻፉ።

1. ስለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በማኅበረሰቡ ዘንድ ግንዛቤ ለመፍጠር ከታዋቂ ሰዎች ጋር ሆነን ከሠራን ውጤታማ የምንሆነው ለምንድን ነው?

   ሀ. በማኅበረሰቡ ዘንድ ተደማጭነት ስለሌላቸው።

   ለ. በማኅበረሰቡ ዘንድ ተአማኒነት ስላላቸው።

   ሐ. የተናገሩት ነገር በማኅበረሰቡ ተቀባይነት ስለሌለው።

   መ. ኅብረተሰቡ ስለሚፈራቸው።

2. ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ያለባቸውን ሰዎች አወንታዊ የአኗኗር ዘዴ የሚጎዳ የትኛው ነው?

   ሀ. የተመጣጠነ ምግብ መመገብ

   ለ. የአልኮል መጠጦች አለመጠጣት

   ሐ. ሲጋራ ማጨስና ጫት መቃም

   መ. ሕመም ሲሰማቸው ፈጥነው መታከም

3. ሙሳና አስቴር ለትምህርትቤቱ ማኅበረሰብ ትምህርት የሰጡት ምን ጊዜ ነው?

   ሀ. በረፍት ጊዜ ሐ. ከሰዓት በኋላ

   ለ. በምሳ ሰዓት መ. ጧት

4. ሲጋራ ከማጨስና ጫት ከመቃም ድርጊት መቆጠብ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

   ሀ. ገንዘብ ስለሚያባክን ነው።

   ለ. ጎጂ ተግባራት ስለሆኑ ነው።

   ሐ. ለጤና ጠንቅ ስለሆኑ ነው።

   መ. በማኅበረሰቡ ዘንድ ስለማይደገፍ ነው።

5. ስለ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መረጃ ማግኘት የሚጠቅመው ማንን ነው?

   ሀ. ኅብረተሰቡን በጠቅላላ። መ. ሐኪሞችን ብቻ።

   ለ. ወጣቱን ትውልድ ብቻ።

   ሐ. የበሽታውን ተጠቂዎች ብቻ።

6. ሙሳና አስቴር ስለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ትምህርት የሚሰጡበት ምክንያት ምንድን ነው?

ሀ. መምህሮቻቸው ስላዘዟቸው።

ለ. የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ተጎጂ በመሆናቸው።

ሐ. የፀረኤች.አይ.ቪ./ኤድስ ክበብ አባል ስለሆኑ።

መ. ባስተማሩ ቁጥር ገንዘብ ስለሚከፈላቸው።

ተግባር 3

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በጽሑፍ መልሱ።

ሀ. ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ያለባቸው ሰዎች አወንታዊ የአኗኗር ዘዴን እንዲከተሉ ማድረጉ ለምን ይጠቅማል?

ለ. አድሎንና መገለልን ለመከላከል አስፈላጊ በመሆናቸው በምንባቡ የተጠቀሱት ነጥቦች ምን ምን ናቸው?

ሐ. «ማለባበስ ይቅር» የሚለው ሙዚቃ መልዕክቱ ምን ይመስላችኋል?

መ. በቀይ ሪባንና በነጭ ሪባን መካከል ያለው የመልዕክት ልዩነት ምን ይመስላችኋል?

5ኛ ቀን

ቃላት

በቃላትና ሐረጋት ዓረፍተነገር መመሥረት

የሚከተሉት ቃላትና ሐረጋት በምንባቡ ውስጥ ባላቸው ፍቺ ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ፍቻቸውን የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮች በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

ምሳሌ፡- መረባረብ

ፍቺ ⟹ መተባበር

ዓረፍተነገር ⟹ ድህነትን ከሀገራችን ለማጥፋት መረባረብ ያስፈልጋል።

ሀ. ቃኘች	መ. መግታት	ሰ. ተሣዋስያን
ለ. መቆጠብ	ሠ. ማለባበስ	ሸ. ሞቅ ባለ
ሐ. መገለል	ረ. ተአማኒነት	

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በምክንያትና ውጤት ስልት የተዋቀረ ድርሰት መጻፍ

ተግባር

ኤች.አይ.ቪ./ኤድስን በተመለከተ የመድሎና የመገለል መንስኤዎችንና የሚያስከትሏቸውን ጉዳቶች (ውጤቶች) በሚከተለው የቢጋር ሳጥን ሀሳባችሁን ካደራጃችሁ በኋላ ባለሦስት አንቀጽ ድርሰት ጻፉ።




የአጻጻፍ ሥርዓት

የማመልከቻ ደብዳቤ አጻጻፍ

ተግባር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት የሚከተለውን የማመልከቻ ደብዳቤ ቅፅ አሟልታችሁ ጻፉ።


ሀ
ለ
ሐ
መ
ሠ
ረ
ሰ

6ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

ሁሉም የድርሻውን ይወጣ

ቅድመንባብ

ተግባር

«ሁሉም የድርሻውን ይወጣ» በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ የመድሎና መገለል መከላከያ መንገዶች ተብለው የተዘረዘሩት ምን ምን ናቸው?

ማንበብ

ተግባር

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት «ሁሉም የድርሻውን ይወጣ» የሚለውን ምንባብ በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ድምፅ እያሰማችሁ ተራበተራ አንብቡ።

መናገር

ተግባር

የሚከተሉትን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ ሀሳባችሁን በምክንያትና ውጤት እያደራጃችሁ ተነጋገሩ። ስትናገሩ እንደመድሎ፣ መገለል፣ መከላከል፣ ማለባበስ፣ መቆጠብ፣ ተሃዋስያን...ያሉ የተማራችኋቸውን አዳዲስ ቃላት ተጠቀሙ።

ሀ. ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ያለባቸው ሰዎች አወንታዊ/ጤናማ የአኗኗር ዘዴን መከተላቸው መድሎንና መገለልን የሚከላከለው እንዴት ነው?

ለ. በደማቸው ውስጥ ኤች.አይ.ቪ. ካለባቸው ሰዎች ጋር ስንነጋገር የመገለል ስሜትን የሚያንፀባርቁ ቃላትን መጠቀም ምን ችግር ይፈጥራል?

ሐ. ኤች.አይ.ቪ. በደማቸው ውስጥ ያለባቸውን ሰዎች ማግለል የሚያስከትለው ችግር ምንድን ነው?

ሰዋስው

አወንታዊና አሉታዊ ሐተታ ዓረፍተነገር

ተግባር 1

የሚከተሉትን አሉታዊ ዓረፍተነገሮች ወደአወንታዊ ዓረፍተነገሮች ለውጡ።

ምሳሌ፡- ወደቤታችን ለመሄድ ታክሲ አያስፈልገንም።

መልስ፡- ወደቤታችን ለመሄድ ታክሲ ያስፈልገናል።

ሀ. አርሶአደሩ በዚህ ዓመት ብዙ አላመረተም።

ለ. መምህሯ ዛሬ አልመጡም።

ሐ. ልጆቹ ጎበዝ አይደሉም።

መ. ሰውዬው በሰማው ነገር አልተደሰተም።

ሠ. ዑመር ኳስ ጨዋታ አይወድም።

ተግባር 2

የሚከተሉትን አወንታዊ ዓረፍተነገሮች ወደአሉታዊ ዓረፍተነገሮች ለውጡ።

ምሳሌ፡- ዳዊት የገዛው መጽሐፍ በጣም ውድ ነው።

መልስ፡- ዳዊት የገዛው መጽሐፍ በጣም ውድ አይደለም።

ሀ. ፋጡማ ከሐረር መጣች።

ለ. የእነመህቡባ ግቢ በግንብ ታጥሯል።

ሐ. ብዙ ተማሪዎች ከክፍል ወጡ።

መ. ዳኛው የህዝቡን አቤቱታ ይሠማሉ።

ሠ. ሁለቱ ልጆች የካሣ ወንድሞች ናቸው።

ተግባር 3

ከምንባቡ ውስጥ 5 አወንታዊ ዓረፍተነገሮችን በማውጣት ወደአሉታዊ ዓረፍተነገሮች ቀይሩ።

የቃላት ጥናት

መነጠልና ማጣመር

ተግባር

የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት በመነጣጠልና በማጣመር አንብቡ።

	ነጣጥሎ ማንበብ	አጣምሮ ማንበብ
ሀ	እንደሚፈጠር-ብ-ኣት	እንደሚፈጠርባት
ለ	እንደማይነፍግ-ኡ-ኣት	እንደማይነፍጓት
ሐ	እየ-ተ-ቆራረጠ	እየተቆራረጠ
መ	እንደ-ኣያውቅ-ብኝ	እንዳያውቅብኝ
ሠ	እንደ-ተናገረ-ብኝ	እንደተናገረብኝ
ረ	እናገኝ-ል-ኣቸው-ኣል-ኧን	እናገኝላቸዋለን
ሰ	ኣጫው-ት-ኣቸው-ኣል-ኧች	ኣጫውታቸዋለች

ማንበብ

ፍቅርና እንክብካቤ

ቅድመንባብ

መገመት

ተግባር

ሀ. ፍቅርና እንክብካቤ የሚያስፈልገው ለእነማን ይመስላችኋል?

ለ. ከርዕሱና ከሥዕሉ በመነሳት ምንባቡ ስለምን እንደሚገልጽ ገምቱ።

የማንበብ ሂደት

ተግባር

የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ አዘጋጅታችሁ «ፍቅርና እንክብካቤ» በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ራሳችሁን እየጠየቃችሁና የጥያቄያችሁን መልስ እየጻፋችሁ አንብቡ።

ጥያቄ	መልስ
•	•
•	•
•	•

ፍቅርና እንክብካቤ ...



አቶ ጉልማ በአንድ የኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መሥሪያቤት ውስጥ የማኅበረሰብ አገልግሎት ከፍተኛ ባለሙያ ናቸው። ሰሞኑን አንዲት በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ የተያዘች ልጅ የነገረቻቸው ጉዳይ በጣም ሲያሳስባቸው ሰንብቷል። ልጅቷ በመሥሪያቤቷ፣ በጓደኞቿና በወላጆቿ መድሎና መገለል የደረሰባት ናት። በእንባ እየታጠበችና ድምጽዋ በሳግ እየተቆራረጠ ችግሯን አጫውታቸዋለች።

ልጅቷ፡- «ጋሼ ጉልማ፣ ከእንግዲህ እኔ ምን ተስፋ አለኝ? በዙሪያዬ ያሉት ሰዎች ሁሉ አገለሉኝ። በልጅነቴ በጣም ይወዱኝና ይሳሱልኝ የነበሩት እናቴ፣ አባቴ፣ ወንድሞቼና እህቶቼ ዓይንሽን ላፈር አሉኝ። ከመሥሪያቤቴም በየሦስት ወሩ ይሰጠኝ የነበረውን ፈቃድ ተከለከልሁ። እና...እኔ...ተስፋ ያልቆረጥሁ ማን ተስፋ ይቁረጥ?»

አቶ ጉልማ፡- «ተረጋጊ! ችግሮችሽ በቀላሉ ሊፈቱ የሚችሉ ናቸው። ከተመካከርን መፍትሔ እናገኝላቸዋለን። ለመሆኑ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ እንዳለብሽ ካወቅሽ በኋላ ማንን አማክረሻል?»

ልጅቷ፡- «እኔ ከሐኪሜ ውጪ ማንንም አላማከርኩም። እንዲያውም ማንም እንዳያውቅብኝ ደብቄ ነበር። ማን እንደተናገረብኝም አላውቅም።»

አቶ ጉልማ፡- «ለምን አላማከርሽም?»

ልጅቷ፡- «እንዴ! ጋሼ ጉልማ፣ ምን ማለትዎ ነው? እንዴት አድርጌ ነው ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ አለብኝ ብዬ የምናገረው? ሁሉም ዓይንሽን ላፊር ነበር የሚለኝ።»

አቶ ጉልማ፡- «ልክ ነሽ! ለማንኛውም ሰው መናገር የለብሽም። ሆኖም በማኅበረሰቡ ዘንድ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ እስከሚሠራ ድረስ ችግርሽን ለባለሙያ መንገር ነበረብሽ። እነዚህ ሰዎች ደግሞ ከሚመለከታቸው ሰዎች ጋር በመመካከር ችግርሽን ይፈቱልሽ ነበር።»

ልጅቷ፡- «እሱስ ትክክል ነዎት። ይህንን አለማድረጌ ጥፋቴ ነው። ታዲያ አሁን ምን ማድረግ አለብኝ?»

አቶ ጉልማ፡- «ይህንን ችግር አብረን እንፈታዋለን። በዚህ ሳምንት ውስጥ ከመሥሪያቤትሽ ኃላፊ፣ ከጓደኞችሽና ከቤተሰቦችሽ ጋር እንወያያለን። ከዚያም ከማኅበረሰቡ ጋር የጋራ ውይይት በማድረግ ተመሳሳይ ችግሮችን እንፈታለን። ለመሆኑ አንቺ ማድረግ የሚገባሽን ጥንቃቄ እያደረግሽ ነው?»

ልጅቷ፡- «ተስፋ ስለቆረጥሁ ሁሉንም ነገር ትቸዋለሁ።»

አቶ ጉልማ፡- «ምን ማለትሽ ነው? ታዲያ መማርሽ ለምን ሊጠቅምሽ ነው? መኖር ይቻላል። ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር የለም። ከዛሬ ጀምሮ መድኀኒትሽን በሰዓቱ ውሰጂ። የተጎዳ ሰውነትሽን ለመጠገን የተመጣጠነ ምግብ ተመገቢ። በየሦስት ወሩ የምታደርጊውን ምርመራም በሚቀርብሽ የሕክምና ተቋም ተከታተይ። ማኅበረሰቡንም በማስተማር የብዙ መሰል ወገኖችሽን ችግር ለመቅረፍ አርአያ ሁኚ።»

ልጅቷ፡- «'እሺ!' ባለማወቅ ራሴን ጎድቻለሁ። በሰጡኝ ምክር አማካይነትም ማኅበረሰቡን ለማስተማር ፈቃደኛ ነኝ» ብላ አመስግና ከቢሮ ወጣች።

ማኅበረሰቡን በማስተማር የብዙ መሰል ወገኖችሽን ችግር ለመቅረፍ አርአያ መሆን ይገባሻል ።

አቶ ጉልማም በሚቀጥለው ቀን ከሥራ ቦታዋ ድረስ ሄደው፣ ከኃላፊዋና ከሥራ ባልደረባዎቿ ጋር ውይይት አደረጉ። ቀጥሎም ወደወላጆቿ ቤት በመሄድ አብሮ በመኖር፣ በመብላትና በመጠጣት ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ እንደማይተላለፍ ገለጹላቸው። ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎችም አስረዷቸው። ልጃቸውንም ማግለል እንደሌለባቸውና ባገለሏት ቁጥር

ከፍተኛ የሆነ የመንፈስ ጭንቀት እንደሚፈጠርባት ነገሯቸው። ፍቅር ሊሰጧትና እንክብካቤ ሊያደርጉላት እንደሚገባ መከሯቸው። ወላጆቿም ምክሩን ተቀብለው በልጃቸው ላይ ባደረሱት በደል ተፀፀቱ። ልጃቸውንም የወላጅነት ፍቅራቸውንና እንክብካቤያቸውን እንደማይነፍጓት አረጋገጡላት።

ከቀናት በኋላም ልጅቷ በመሥሪያቤቷ፣ በጓደኞቿና በወላጆቿ እየተደረገላት ባለው ፍቅርና እንክብካቤ ተጽናናች። የመኖር ተስፋዋም የበለጠ ለመለመ። በአኗኗሯም ደስተኛ ሆነች። በቀሪ ህይወቷ ከራሷ ተሞክሮ በመነሳት ስለኤች.አይ.ቪ./ኤድስ በማኅበረሰቡ ዘንድ ግንዛቤ ለመፍጠር ወስና ሥራዋን ቀጠለች።

አንብቦ መረዳት

ተግባር 1

ከዚህ በታች የቀረቡት ዓረፍተነገሮች በምንባቡ መሠረት በያዙት ሀሳብ የምትስማሙ ከሆነ ሁለት ጊዜ አጨብጭቡ፤ የማትስማሙ ከሆነ ደግሞ እጃችሁን አውጡ፤ ከዚያም ምክንያታችሁን ተናገሩ።

ሀ. ልጅቷ አቶ ጉልማን ያነጋገረቻቸው በደስታ እየተፍለቀለቀችና ድምጽዋ በሲቃ እየተቆራረጠ ነበር።

ለ. ልጅቷ አቶ ጉልማን ከማማከሯ በፊት ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጋለች።

ሐ. ልጅቷ ከአቶ ጉልማ ጋር ያደረገችው ምክክር የተሳካ ነበር።

መ. የልጅቷ ወላጆች ከአቶ ጉልማ ጋር ከተመካከሩ በኋላ በልጃቸው ላይ ሲያደርሱ በነበሩት በደል ተፀፅተዋል።

ተግባር 2

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. አቶ ጉልማን በጣም ሲያሳስባቸው የሰነበተው ጉዳይ ምን ነበር?

ለ. ልጅቷን ተስፋ እንድትቆርጥ ያደረጋት ምንድን ነው?

ሐ. ልጅቷ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ እንዳለባት መናገር ያልፈለገችው ለምን ነበር?

መ. ልጅቷ ኤች.አይ.ቪ./ኤድስ እንዳለባት አለመናገሯ ትክክል ይመስላችኋል? ለምን?

ሠ. አቶ ጉልማ የልጅቷን ችግር ለመፍታት የወሰዷቸውን ርምጃዎች በቅደምተከተል ዘርዝሩ።

ረ. እናንተ በአቶ ጉልማ ቦታ ብትሆኑ ለልጅቷ ምን ዓይነት ምላሽ ትሠጡ ነበር?

8ኛ ቀን

ቃላት

በምንባቡ ውስጥ የተሠመረባቸውን ቃላትና ሐረጋት በተመሳሳይ ቃላትና ሐረጋት ተክታችሁ ዓረፍተነገሮቹን በደብተራችሁ ላይ ጻፉ።

መጻፍ

ድርሰት መጻፍ

በምክንያትና ውጤት ስልት የተዋቀረ ድርሰት መጻፍ

ተግባር

ባለፈው ክፍለጊዜ የጻፋችሁትን ድርሰት ቀጥሎ በቀረቡት መሥፈርቶች መሠረት ከገመገማችሁ በኋላ አስተካክላችሁ እንደገና ጻፉ።

	የድርሰት መገምገሚያ መሥፈርቶች	አዎ	አይደለም
1	ቃላቱ በትክክል ተጽፈዋል?		
2	ዓረፍተነገሮቹ የተሟሉ ናቸው?		
3	ሥርዓተነጥቦች በአግባቡ አገልግሎት ላይ ውለዋል?		
4	ጽሑፉ የሀሳብ ፍሰት/ቅደምተከተል አለው?		
5	ጽሑፉ በርዕሰጉዳዩ ላይ ብቻ ያተኩራል?		
6	ጽሑፉ በምክንያትና ውጤት የተዋቀረ ነው?		
7	ምክንያትና ውጤትን የሚጠቁሙ አያያገሮች አሉ?		

የአጻጻፍ ሥርዓት

ማመልከቻ መጻፍ

ተግባር

ከሚከተሉት ርዕሰጉዳዮች መካከል አንዱን በመምረጥ ለትምህርትቤታችሁ አስተዳደር ማመልከቻ ጻፉ።

- የትምህርትቤት መታወቂያ እንዲሰጣችሁ፣ ወይም
- የሦስት ቀናት ፈቃድ እንዲሠጣችሁ አመልክቱ።

9ኛ ቀን

አቀላጥፎ ማንበብ

ፍቅርና እንክብካቤ

ቅድመንባብ

ተግባር

«ፍቅርና እንክብካቤ» በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ የተማራችሁትን ቁምነገር አስታውሳችሁ ተናገሩ?

ማንበብ

ተግባር

«ፍቅርና እንክብካቤ» በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ የሚገኘውን ምልልስ የልጅቷንና የአቶ ጉልማን ንግግር በማስመሰል በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ተራበተራ ድምፅ እያሰማችሁ አንብቡ። አንዳችሁ ስታነቡ አንዳችሁ የጓደኛችሁን አነባበብ በሚከተሉት መሥፈርቶች ገምግሙ።

- በትክክል ያልተነበቡ ቃላት ብዛት ስንት ነው?
- በስህተት የተነበቡ ሥርዓተነጥቦች ብዛት ስንት ነው?
- አነባበቡ የገፀባህርያቱን ንግግር ምን ያህል ይወክላል?
- በተሠጠው ጊዜ ውስጥ የተነበቡ ቃላት ብዛት ስንት ነው?

መናገር

ተግባር

በ1ኛው ሳምንት ያነበባችሁትን «ወይኔ ሰውዬው» የሚለውን ምንባብ «ፍቅርና እንክብካቤ» ከሚለው ምንባብ ጋር እያወዳደራችሁ ተወያዩ። የምንባቦቹን ቅርፅና ይዘት፣ ታሪኮቹን፣ ገፀባህርያቱን ወዘተ. ለውይይታችሁ እንደመነሻ ነጥብ ልትጠቀሙባቸው ትችላላችሁ።

ሰዋስው

አወንታዊና አሉታዊ ሐተታ ዓረፍተነገሮች መመስረት

ተግባር

አምስት አምስት አወንታዊና አሉታዊ ሐተታ ዓረፍተነገሮች መሥርቱ።

ሙዳየቃላት

ሀሳብ ማጋራት (Think-aloud)፡- በአርዓያነት እያነበቡ እያሉ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ቆም እያሉ ስለአንድ ነገር/ጉዳይ እንዴት እያሰብን እንደሆነ ለሌላ ሰው ሀሳብን ማካፈል፣

መለየት/ማንበብ (Decoding)፡- የተጻፉ ቃላትን (ጽሑፍን) ወደንግግር ቋንቋ ለመቀየር የፊደል ድምፅ ግንኙነትንና የቃላት ዕውቀትን መጠቀም፣

መላልሶ ማንበብ (Repeated reading)፡- በትክክለኛና በፍጥነት የማንበብ ችሎታን ለማጎልበት በግብረመልስ እየታገዙ ደጋግሞ የማንበብ ሂደት

መልሶ ማንበብ (Reread)፡- በማንበብ ሂደት ግልጽ ያልሆነ ጉዳይ ሲያጋጥም ሀሳቡን መረዳት እስኪቻል ድረስ ወደኋላ እየተመለሱ ማንበብ፣ መልዕክት ሰጪ ንባብ (Prosody)፡- አንድ ጽሁፍ በትክክለኛው ወይም በተገቢው የድምፅ ቅላፄ ማንበብ፣

መምህር መር ንባብ (Guided Reading)፡- ለደረጃው የቀረበውን ጽሑፍ በትክክል ማንበብ እንዲቻል መምህራን አንብበው በማሳየት ንባቡን የሚያስቀጥሉበት ሂደት፣

መረዳት (Comprehension)፡- የንግግርን ወይም የጽሑፍን ቋንቋ የመረዳትና ትርጉም የማግኘት ሂደት፣

መነጠል (Segmenting)፡- አንድን ሙሉቃል ወይም ሐረግ በተናጠላዊ ፊደሎች ወይም በአነስተኛ የቃል ክፍልፋዮች የመነጣጠል ሂደት

መገመት (prediction)፡- ከማንበብ/ከማዳመጥ በፊት ወይም በማንበብ/በማዳመጥ ሂደት ቀጥሎ ምን ሊመጣ ወይም ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት፤ ስለገፀባህርያቱና ስለሴራው ድምዳሜ መስጠት፣

የማዳመጥ ቃላት (Listening vocabulary)፡- ሰዎች በንግግር ጊዜ አዳምጠው የሚረዷቸው ቃላት፣

ማጠቃለል/ማሳጠር (Summarizing)፡- የምንባብን አቢይ ሀሳብ ጨምቆ የማውጣት ሂደት፣

ማጣመር (blending)፡- በአነስተኛ ክፍልፋዮች ወይም ፊደሎች ተነጣጥሎ የቀረበን ቃል በአንድ ላይ አጣምሮ የመናገር፣ የማንበብ ወይም የመጻፍ ሂደት፣

ራስን የመከታተያ ስልት (Self-checking strategy)፡- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ መረዳታቸውን የሚያረጋግጡበት ብልሃት፣

ቃላት በደቂቃ (ቃበደ) (WPM)፡- በአንድ ደቂቃ በፍጥነት የተነበቡ ቃላት ብዛት፣ በአንድ ደቂቃ በትክክል የተነበቡ ቃላት ብዛት (WCPM ቃላት ትክክል በደቂቃ (ቃትበደ))፣ (የተማሪዎችን የማንበብ ብቃት ደረጃ ለመወሰን ያገለግላል።)

ቃላት ትንተና (Word analysis)፡- አንባቢዎች የተጻፉ ቃላትን በአነስተኛ ክፍልፋዮች ወይም ቅጥያዎች በመተንተን ለማንበብ የሚጠቀሙበት ስልት፣

ቅጥያ (Affix)፡- በቃል መጀመሪያ ወይም መጨረሻ የሚቀጠሉ ትርጉም አዘል ቅጥያዎች፣ (በቃል መጀመሪያ ሲቀጠሉ ቅድመአምድ ቅጥያ (Prefix)፣ በቃል መጨረሻ ሲቀጠሉ ድህረአምድ ቅጥያ (Suffix) ይባላሉ።)

ቅጽበታዊነት (Automaticity)፡- ፊደላትን፣ ድምጾችንና ቃላትን ያለችግር፣ ሳያመነቱ፣ ሳያወላውሉ፣ በቅጽበትና በትክክል የመለየትና የማንበብ ችሎታ፣

ቀጥተኛ ጥያቄ (Explicit question)፡- መልሱ በቀጥታ ከምንባብ ወይም ከንግግር የሚገኝ ጥያቄ ዓይነት፣

ቃላትን መረዳት/ማወቅ (Word Recognition)፡- አንባቢዎች የተጻፉ ቃላትን ለመለየት የሚጠቀሙበት ስልት

በማንበብ ሂደት መቆምና ማሰብ (Stop and think)፡- በማንበብ ሂደት ምን እየተነበበ እንደሆነ ቆምብሎ ማሰብ፣ ስለተነበበው ምንባብ ምንም ነገር ማስታወስ ካልተቻለ ወደፊት ከማንበብ ይልቅ ቆም ብሎ የተነበበውን ሀሳብ በአዕምሮ ለመረዳት መሞከር፣

በቢጤ መማማር (Peer tutoring)፡- ተማሪዎች ትምህርታዊ ክሂሎችን ርስበርስ የሚማማሩበት ሂደት

የቢጋር ሠንጠረዥ (Graphic organizer)፡- የሀሳብን ግንኙነት በሥዕል ወይም በግራፍ ወይም በሠንጠረዥ የማደራጃ ስልት፣

በትብብር መማር (Cooperative learning)፡- አንድን የትምህርት ይዘት በጋራ እየተረዳዱ የመማር ሂደት፣

ቤት መምታት (Rhyme)፡- በተመሣሣይ ፊደሎች/ድምጾች የሚጨርሱ ቃላት / የግጥም ቤት/

በጋራ ማንበብ (Choral reading)፡- በርከት ያሉ ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ በጋራ ሆነው ድምፅ በማሰማት የሚያነቡበት ስልት፣

ተራኪ ጽሑፍ (Narrative text)፡- ታሪክን በጊዜ ወይም በቦታ ወይም በድርጊት ቅደምተከተል የሚያሳይ የጽሑፍ መዋቅር

የታሪክ መዋቅር (Story structure)፡- እንደመቼት ፣ድርጊት፣ ሁነት፣ ችግርና መፍትሄ ያሉትን አላባውያን የሚያካትት የድርሰት መዋቅር

ትክክለኛነት (Accuracy)፡- አንድን ቃል ወይም ሐረግ ወይም ዓረፍተነገር ያለስህተትና ያለማወላወል የማንበብ ችሎታ፣

ንባብን ወደፊት መቀጠል (Read ahead)፡- አሻሚ ሀሳብ ሲያጋጥም ግልፅ እንዲሆን ወደፊት ያሉትን ዓረፍተነገሮች ማንበብ፤ የተወሰኑ ዓረፍተነገሮች ተነበው ሀሳቡ ግልፅ ካልሆነ ሌላ ስልት መፈለግ፣

አመራማሪ ጥያቄዎች (Implicit/inferential Questions)፡- ተማሪዎች በሚያነቡት/በሚያዳምጡት ጽሑፍ ውስጥ ያሉ መረጃዎችን ከቀደመ ዕውቀታቸው ጋር በማገናኘት መልስ የሚሰጡባቸው የአንብቦ/የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

አስረጂ ጽሑፍ (Expository text)፡- መረጃ ሰጪ የሆነ ጽሑፍ ሆኖ ስለአንድ ርዕሰጉዳይ ወይም እውነት ለማስተማር/ለማስረዳት የሚያገለግል ጽሑፍ፣

አቀላጥፎ ማንበብ (Fluency)፡- ፊደላትን፣ ቃላትንና ሐረጋትን በትክክል፣ በፍጥነትና መልዕክት ሰጭ በመሆነ መንገድ የማንበብ ችሎታ፣

አንብቦ መረዳት (Reading comprehension)፡- አንድ ጽሑፍ አንብቦ የመረዳትና ትርጉም የማግኘት ችሎታ፣

አዕምሯዊ ምሥል (Mental picture)፡- የገፀባህርያት፣ የቦታና የሁነቶች ገለፃን በተመለከተ በአዕምሮ ምሥል እየፈጠሩ ማንበብ፣

አዳምጦ መረዳት (Listening comprehension)፡- ንግግርን ወይም ጽሑፍን አዳምጦ መረዳትና ትርጉም የመስጠት ችሎታ፣

የአጋዘን አስተኔ

የአጻጻፍ ሥርዓት (Writing convention)፡- የፊደላትን ቅርጽ፣ አሰዳደር፣ የአጻጻፍ አቅጣጫና የሥርዓተነጥብን አጠቃቀም የሚያሳይ የአጻጻፍ ሥርዓት፣

ዋና ሀሳብ/ዐቢይ ሀሳብ (Main idea)፡- ከምንባብ ተጨምቆ የሚወጣ አቢይ ወይም ዋና ሀሳብ፣

ዐውድ (Context)፡- ለአንድ እንግዳ ቃል ፍቺ ፍንጭ የሚሰጡ ከቃሉ በፊት ወይም በኋላ የሚገኙ ቃላት፣ ሐረጋት ወይም ዓረፍተነገሮች፣

ዘውግ (Genre)፡- በልዩ መዋቅሩ ወይም ባህሪያቱ የሚታወቅ የጽሑፍ መዋቅር፤ ምሳሌ፡- ተውኔት፣ ገላጭ ድርሰት፣ ተራኪ ድርሰት፣

ዘዬ (dialect)፡- በንበት/በድምጽ፣ በቃል ወይም በሰዋስው የሚከሰት አካባቢያዊ የቋንቋ አጠቃቀም ልዩነት፣

የጥንድ ንባብ (partner reading)፡- በጥንድ ሆኖ ተራ በተራ የማንበብ ሂደት

ጥያቄ መጠየቅ (ask question)፡- ጥያቄ እየጠየቁ ማንበብ፣ ምንባቡን ለመረዳት ይጠቅማል። ለጥያቄዎች ምላሽ ማፈላለግ ያነበቡትን ለመረዳት ይረዳል፣

- ምንባቡ ስሜት ሰጥቶኛል?
- የማነበው ለምንድን ነው?
- ስለዚህ ምንባብ ምን የማውቀው ነገር አለኝ?
- ካነበብኩ በኋላ የምማረው ምንድን ነው?
- የዘለልኩት ነገር አለ?
- ምን ምን ጥያቄዎች አሉኝ?
- ስለምንባቡ ምን አስባለሁ? እስማማለሁ? ግራ ተጋብቻለሁ?
- ፍጥነቴን መቀነስ ነው ያለብኝ ወይስ መጨመር?

የጽሑፍ መዋቅር (text structure)፡- በጽሑፍ ውስጥ የይዘቶች አደረጃጀት

ዋቢዎች

ምዕራፍ 1

Baye Yimam.1997. «The pragmatics of greeting, felicitation and condolence expression infour Ethiopian Language». *In Africa Languages and cultures:10(2):103-128.*

ባየ ይማም። 2002። *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ጎሩይ ወልደሥላሴ (ብላቴን ጌታ)። 2000። *ወዳጀ ልቤና ሌሎችም።* አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕረስ።

ጌታሁን አማረ። 1989። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ።*አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ምዕራፍ 2

Chris Woodford. May 24/2014(Last updated). *Water Pollution: an Introduction.* (No place)

ባየ ይማም። 2002። *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ጌታሁን አማረ። 1989።*ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች

ምዕራፍ 3

በዓሉ ግርማ። 1984። *ኦሮማይ።* አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

ባየ ይማም። 2002። *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

አለባቸው ኬዕሚሶና ሳሙኤል ሀንዳሞ። 2002። *የሀዲያ ህዝብ ታሪክና ባህል።* አዲስ አበባ፤ ሰፊር አታሚ።

የአብክመ ትምህርት ቢሮ። 2002። *ሥነህዝብና የቤተሰብ ሕይወት ለሁለተኛ ደረጃ መምህራንና ወጣት ተማሪዎች የተዘጋጀ አጋዥ መጽሐፍ።* (ቦታ የሌለው)

የኢትዮጵያ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አስወጋጅ ማኅበር። 2000። *ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በኢትዮጵያ አዲስ አበባ።* (ማተሚያቤቱ ያልተጠቀሰ።)

ጌታሁን አማረ። 1989። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ።* አዲስ አበባ፤አልፋ አታሚዎች።

ምዕራፍ 4

ብሔራዊ የመንገድ ደህንነት አስተባባሪ ጽሕፈት ቤት። 1996። *ክ1ኛ-4ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ለማዳበር የተዘጋጀ መማሪያ (ማጣቀሻ አጋዥ መጽሐፍ) ካሪኩለም ጋይድ።* (ቦታና አሳታሚ የሌለው።)

ባየ ይማም። 2002። *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

አብርሃም ክብረት። 1999። *ሚዴካል ጋዜጣ።* 2ኛ ዓመት ቁ.2፤ ገጽ 11።

ጌታሁን አማረ።1989። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ምዕራፍ 5

ማረው አለሙ። 2005። *በሳል ድርሰት ማስተማሪያ።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ባየ ይማም። 2002። *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ኮድ ኢትዮጵያ። 2004። *የአካባቢ እንክብካቤና ጤና አጠባበቅ።* አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያቤት።

ጌታሁን አማረ። 1989። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ምዕራፍ 6

Lasau, W.and Kane, T.L. 2001. *Amharic Cultural Reader, Harrassowitz Verlag.Wiesbaden (No Place)*

ባየ ይማም። 2002። *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው።* አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

የደ.ብ.ብ.ሕ.ክ.መ.ን.ኢ.ቢሮ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ በጋራ የተዘጋጀ። 1999። *«የዳቦ፣ የአንባሻና የኩኪስ አዘጋጀጀት ማሰልጠኛ ማንዋል»* (ያልታተመ)።

ጌታሁን አማረ። 1989። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ*። አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ጽጌ ዑቁባሚካኤል። 1991። *የእናት ጓዳ፣ ባህላዊና ዘመናዊ ምግቦችናአዘገጃጀታቸው፣ (2ኛ መጽሐፍ)*። አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ምዕራፍ 7

ሰለሞን ይርጋ። 2000። *አጥቢዎች*። አዲስ አበባ፤ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ታሪክ ማህበር።

ባየ ይማም። 2002። *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው*። አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ጌታሁን አማረ። 1989። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ*። አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ፍሰሐ ሃ/መስቀል። 1966። *የኢትዮጵያ ታላላቅ አራዊት*። አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ምዕራፍ 8

በኢትዮጵያ ባህል ስፖርት ፌዴሬሽን። 2004። አዲስ አበባ፤ የባህል ስፖርቶች ህግና ደንብ (ያልታተመ)።

ባየ ይማም። 2002። *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው*። አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ብሥራት ገብሬ። ሐምሌ 17/2012። *ገናና የገና ጨዋታ*። (ቦታው ያልተጠቀሰ)

ዘሪሁን አስፋው። 1992። *የሥነጽሑፍ መሠረታውያን*። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ጌታሁን አማረ። 1989። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ*። አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ምዕራፍ 9

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ። 2001። *የአማራ ሕዝብ ባህልና ቋንቋ*። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

በአብክመ ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ፣ የባህል እሴቶችና ተቋማት ጥናት፣ ልማትና አጠቃቀም የሥራ ሂደት። 2005። *የግብርና ግጥማዊ ሰነቃል*። ባህር ዳር።

ባየ ይማም። 2002። *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው*። አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ዘሪሁን አስፋው። 1992። *የሥነጽሑፍ መሠረታውያን*። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ፣ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር። 1982። *የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች*።አዲስ አበባ።

ጌታሁን አማረ። 1989። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ*። አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ምዕራፍ 10

ሂልዝ ኮሚውኒኬሽን ፓርትነርሺፕ። *ወጣቱና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ የመልዕክትመመሪያ፣ ጤናማ ተግባራት ለኢትዮጵያ ወጣቶች*። (ቀንና ቦታ ያልተጠቀሰ)

ባየ ይማም። 2002። *አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው*። አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ጌታሁን አማረ። 1989። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ*። አዲስ አበባ፤ አልፋ አታሚዎች።

ፌደራል ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ጽ/ቤት። ግንቦት 2004። *ማግለል፣ መድሎዎና አለመቀበልን ለመከላከል የተዘጋጀ የስልጠናና አሰጻጸም መመሪያ*። አዲስ አበባ።